# መላእክት

በቢሊ ግራሃም

ትርጉም፦ ይግረም ረታ

እርማት፦ ግራማዊ ቡሽና

ዘነበ ገብረሐና

BIBLE BASED BOOKS

SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት

መላእክት፡- የእግዚአብሔር ምሥጢራዊ መልእክተኞች

የመጀመሪያ እትም - 1997 ዓ.ም (2005)

Copyright © 2002 by SIM, Addis Ababa, Ethiopia. Originally published in English under the title of ANGELS: God's Secret Agents by Billy Graham. Copyright © 1995 WPublishing, a division of Thomas Nelson Inc., Nashville, Tennessee 37214, USA. All rights reserved.

የአሳታሚው መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

መላእክት መለኮት ለእኛ ያዘጋጀውን በረከት የሚያከፋፍሉና የሚያስተዳድሩ ናቸው፤ ደህንነታችንን ይጠብቃሉ፣ ይከላከሉልናል፣ መንገዳችንን ይመሩናል፣ በተጨማሪም ምንም ክፉ እንዳያጠቃን ያለማቋረጥ ይጠብቁናል፡፡

ጆን ካልቪን

Institutes of the Christian Religion, I

# ስለ ደራሲው

ዶ/ር ቢሊ ግራሃም በታሪክ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል የምስራች ከማንም ሰው ይልቅ ብዛት ላለው ሕዝብ ያደረሱ ሰው ናቸው:: ያካሄዷቸው መንፈሳዊ ስብሰባዎቻቸው ሁሉንም አህጉራት እንዲያዳርሱ ያደረጋቸው ከመሆኑም ባሻገር፣ በዓለም ውስጥ ያሉ የመንግሥታት መሪዎችን የመተዋወቅ ዕድልም ገጥሟቸዋል:: በዶ/ር ግራሃም ከተጻፉት በከፍተኛ ደረጃ ከተሸጡ መጻሕፍት መካከል «Storm Warning» (የማዕበሉ ማስጠንቀቂያ)፣ «Hope for the Troubled Heart» (ተስፋ ለቆረጠ ልብ ተስፋ)፣ «How to Be Born Again» (እንዴት ዳግም መወለድ ይቻላል?)፣ *«Peace with God» (ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ)፣ *«The Holy Spirit» (መንፈስ ቅዱስ) እና *«The Sectret of Happiness» (የደስታ ምሥጢር) የተሰኙት ይገኙባቸዋል:: ዶ/ር ቢሊ ግራሃም በአሁኑ ጊዜ የሚኖሩት ከባለቤታቸው ከወ/ሮ ሩት ቤል ግራሃም ጋር በሰሜናዊው የካሮላይና ተራራማ ስፍራ ነው::

*እነዚህ መጻሕፍት በአማርኛ ቋንቋ ተተርጉመው ታትመዋል::

# ማውጫ


1. መላእክት የእግዚአብሔር ምሥጢራዊ
መልእክተኞች ናቸው? ......................................... 1
2. መላእክት በትክክል አሉ ......................................... 17
3. መላእክት - ይታያሉ ወይስ አይታዩም? .............. 26
4. መላእክት - ከሰው እንዴት እንደሚለዩ ................. 34
5. የመላእክት አደረጃጀት ......................................... 47
6. ሉሲፈርና የመላእክት ዓመፅ ................................. 57
7. መላእክት እንደ እግዚአብሔር መልእክተኞች ....... 70
8. መላእክት ይጠብቁናል፣ ነፃ ያወጡናልም .............. 82
9. መላእክት - በፍርድ የእግዚአብሔር ወኪሎች ...... 93
10. መላእክትና ወንጌሉ ......................................... 104
11. በኢየሱስ ሕይወት የመላእክት አገልግሎት ......... 117
12. መላእክት በትንቢት ውስጥ ................................. 124
13. መላእክትና ሞት ................................................. 136
14. የመላእክት ተመልካቾች ..................................... 145
15. መላእክት በዛሬው ኑሮአችን ውስጥ ..................... 150

# የአሳታሚው መግቢያ

ሰዎች ልዩ ኃይልና የሰማያትን በረከት በሕይወታቸው የሚፈልጉበት ጊዜ ቢኖር ይህ ጊዜ ዛሬ ነው:: የምንኖረው ችግር በበዛበት ጊዜ ውስጥ ነው:: በግል ሕይወታችን ውስጥ የፖለቲካ፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ጉዳዮች የበለጠ ገዝፈው ስለሚታዩ አብዛኛው ጊዜ የሰላምና የደስታ ትርጉም የምናጣ እየመሰለን እንሠጋለን:: ብዙ ሰዎች ደግሞ መሠረታዊ ከሆኑ እሴቶችና እምነቶች ተለያይተዋል:: ኑሮ አስቸጋሪና አሳሳቢ ከመሆኑ የተነሣ ሰዎች ዝም ብለው ከልዕለ ተፈጥሮ የሚገኘውን ውስጣዊ ኃይል ለማወቅ አይጥሩም:: ይህ መጽሐፍ የተጻፈውና በአዲስ እትም እንዲሰራጭ የተፈለገበት ምክንያትም ለዚህ ነው::

በ1975 (እ. ኤ. አ.) ይህ በጣም ታላቅ የሆነ መጽሐፍ በመጀመሪያ በታተመበት ወቅት፣ መላእክትን በሚመለከት የተጻፈ ነገር አልነበረም ለማለት ይቻላል:: በእርግጥ በባዕድ አምልኮ፣ በምሥጢራዊ አምልኮና በአጋንንት አምልኮ ላይ የተጻፉ ብዙ ሥራዎች ነበሩ:: በቻርለስ ማንሰን ዘመን ብዙ ምዕራባውያን መናፍስት በዓለም ላይ መኖራቸውን ያምኑ ነበር:: ነገር ግን እነዚያው ሰዎች The Exorcist (አጋንንት አውጭው) ወይም Rosemary's Baby (የሮዝሜሪ ልጅ) በተሰኙ ፊልሞች ቢደነቁም (ፊልሞቹ በአጋንንት ላይ የሚያጠነጥኑ ነበሩ)፣ የመላእክትን ነገር በተረትና ከአፍአዊ ታሪክ ጋር ማያያዝ ጀመሩ:: በሃይማኖታቸው ጠንካራና የጸና እምነት ያላቸው ሰዎች እንኳን መላእክት ስለ መኖራቸው እርግጠኞች አልነበሩም::

ከ1975 እ. ኤ. አ. በኋላ ግን ብዙ ነገሮች ተለዋውጠዋል:: በአንድ በኩል መንፈሳዊነትን በተመለከተ አዳዲስ እምነቶችና አዳዲስ አሳቦች ተበራክተዋል:: የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ (The New Age Movement) እግዚአብሔርንና ፍጥረቱን በተመለከተ ብዙ እንግዳና ግራ የሚያጋቡ እምነቶችን አስተዋውቋል:: በ1994 እ. ኤ. አ በኒው ዮርክ ታይምስ ከፍተኛ የሽያጭ ዝርዝር ውስጥ በመላእክት ርእሰ ጉዳይ ላይ ስምንት መጻሕፍት ቀርበው ነበር:: እነዚህ ሥራዎች ከስብስብ ሥነ ግጥሞች ጀምሮ ከመላእክት ጋር እንዴት መገናኘት እንደሚቻል የሚያስተምሩ ነበሩ:: ብዙዎች

መጻሕፍት የተጻፉት መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ርእስ ላይ ስለሚያስተምረው እውነት ብዙ እውቀት ለሌላቸውና በአሁኑ ወቅትም በዓለም ውስጥ በሚታዩ መንፈሳዊ ኃይላት ለሚያምኑ ቁጥራቸው እየበረከተ ለመጣው ሰዎች ይመስላል:: ብዙ ሰዎች ከክርስትና ውርሳቸው ግንኙነት በሚያቋርጡበት ጊዜ ውብና የሚማርኩ እየመሰሉ፣ ነገር ግን በሚያስቱና እጅግ አደገኛ በሆኑ አሳቦች የመወሰድ ትልቅ አደጋ ያጋጥማቸዋል::

መላእክት በመካከላችን አሉ፤ ነገር ግን ሁሉም ልዕለ-ተፈጥሯዊ ኃይላት ጥሩ ናቸው ማለት አይቻልም፤ ሁሉም መላእክት ከእግዚአብሔር ናቸው ማለትም አይቻልም:: ጳውሎስ «ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና» ሲል ያስጠነቅቃል:: መንፈሳዊ መሪዎችን ጨምሮ ብዙ ሰዎችን ያታልላል:: ስለሆነም በ2ኛ ቆሮንቶስ 11:14ና 15 ላይ፣ «እንግዲህ አገልጋዮቹ ደግሞ የጽድቅን አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር አይደለም፤ ፍጻሜአቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል» ብሏል::

ስለዚህ ዛሬ ሰዎች ያለባቸው ችግር መላእክት መኖራቸውን ማመን ብቻ ሳይሆን፣ በመላእክትና በአጋንንት መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅ አለመቻላቸው ነው:: ይህንን የቢሊ ግራሃምን አዲስ ውብ የመጽሐፍ እትም ስናወጣና ከአዲሱ ትውልድ ጋር ስናስተዋውቅ ደስ ይለናል:: በጌታ በኢየሱስ ላይ እምነትህን ስትጥል፣ የመላእክትን አስደናቂ መገለጥ አእምሮን ከሚያልፍ ሰላም፣ ከፍጹምነትና ከኃይል ጋር በዕለት ተዕለት ሕይወትህ እንድትለማመድ የሚረዳህ ይሆናል:: ዶ/ር ግራሃም በዚህ በሚማርክ ርእስ ጉዳይ ላይ ያሰፈሯቸው ግላዊ እይታዎች፣ እያንዳንዱ አንባቢ ወደ አዲስ የደስታ ሽግግርና ለወደፊቱም አዲስ ተስፋ እንዲያገኝ እንደሚያስችሉ እናምናለን::

# የሁለተኛው እትም መግቢያ

መላእክትን በተመለከተ አንድ ስብከት ለማዘጋጀት በወሰንኩ ጊዜ በቤተ መጻሕፍቴ ምንም መጽሐፍ ለማግኘት አልቻልኩም። ከዚህ የተነሣ በዚህ ረገድ ጥናት ሳካሂድ፣ በዚህ ክፍለ ዘመን በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ብዙ መጻሕፍት አለመጻፋቸውን ወዲያውኑ ተገነዘብኩ። ይህ እንደገና ሊታለፍ የማይገባው ጉዳይ ይመስላል። ቤተ መጻሕፍትና የመጻሕፍት መደብሮች ስለ አጋንንት፣ ስለ ባዕድ አምልኮና ስለ ዲያብሎስ የሚያወሱ መጻሕፍት መደርደሪያቸውን ሞልተዋል። ከመላእክት ይልቅ ሰይጣን ከጸሐፊዎች የበለጠ ትኩረት የሚያገኘው ለምንድን ነው? አንዳንድ ሰዎች ሰይጣንን ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስተካክሉት ይሞክራሉ። በመሠረቱ፣ ሰይጣን የወደቀ መልአክ ነው።

በዚህ ባለንበት ዘመን እንኳ ሰዎች በመላእክት ርእሰ ጉዳይ ላይ ከጊዜ ወደጊዜ ትኩረት በሚሰጡበት ጊዜ፣ እነዚያ አሳቦች ብዙውን ጊዜ ከእውነታ የራቁ ወይም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ነበሩ። ይህንን የሁለተኛውን እትም መግቢያ እየጻፍኩ ሳለሁ ሰውን ተመስሎ ወደ ምድር ስለ ተላከና ችግር የሚገጥማቸውን ሰዎች ስለሚረዳ «መልአክ» ታሪክ አንድ ዝነኛ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ይናገር ነበር። ፕሮግራሙ ተወዳጅ ሊሆን የቻለው ብዙ ሰዎችን በከፍተኛ ደረጃ በማዝናናቱ ምክንያት ቢሆንም፣ በአንጻሩ መላእክት እንደ ሳንታ ክላውስ (በአፈ-ታሪክ-በገና በዓል ለልጆች ስጦታ የሚሰጥ በዕድሜ የገፉ ሰው) ወይም የጥንቆላ ማታለያዎች የምናባችን ውጤት ናቸው ለሚል አሳብ አጽንኦት ይሰጣል ብዬ አስባለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን እውን እንደሆኑና እግዚአብሔርን በመወከል ሁልጊዜ ያለመታከት የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያገለግሉ መሆናቸውን አጥብቆ ያሳስባል። በዚህ በሚታይ ነገር ላይ በሚያተኩር ክፋትና በመከራ በተሞላ ዓለም ውስጥ መላእክትን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን እውነት እንደ አዲስ መፈተሽ ይኖርብናል።

እንግሊዛዊው ሠዓሊ የተከበሩ ኤድዋርድ ኮሌይ በርን-ጆንስ ለኦስካር ዋይልድ በጻፉት ደብዳቤያቸው ላይ፣ «ሳይንስ የበለጠ በቁስ ላይ እያተኮረ ሲሄድ፣ እኔ ደግሞ የመላእክትን ሥዕል የበለጠ እሥላለሁ፤ ክንፎቻቸው ነፍስ ለዘላለም እንደምትኖር መደገፌን የማሳይበት መቃወሚያዎቼ ናቸው» ብለዋል።

መላእክት ከሰይጣንና ከአጋንንት ይልቅ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የበለጠ ስፍራ አላቸው:: ስለሆነም፣ መላእክትን በሚመለከት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ማካሄድ ጀመርኩ:: ይህ በሕይወቴ ካካሄድኳቸው ጥናቶች ሁሉ የበለጠ የረካሁበት መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ይህ ርእስ ጉዳይ በታሪክ ከነበሩት ዘመናት ይልቅ በአሁኑ ወቅት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ አምናለሁ::

መላእክት በአገር ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ የሚገቡ መሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል:: እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ በአገራት ላይ ፍርድን ለማስፈጸም ይጠቀምባቸዋል:: በመከራና በስደት ውስጥ የሚገኙትን የእግዚአብሔር ሰዎች ይመራሉ፤ ያጽናናሉ፤ የሚያስፈልጋቸውንም ነገሮች ያሟላሉ:: በአንድ ወቅት ማርቲን ሉተር በ«Table Talk» "በጠረጴዛ ዙሪያ ውይይት" ላይ፣ «መልአክ ለክርስቲያን ማኅበረሰብና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሲባል ያለ አካል በእግዚአብሔር የተፈጠረ መንፈሳዊ ፍጥረት ነው» ብሎ ነበር::

እንደ ወንጌላዊ፣ ከጌታ መልእክት ለመስማት በስታዲየም ለተሰበሰቡ ወንዶችና ሴቶች የማካፍላቸው ነገር ከውስጤ ያለቀ መስሎ የተሰማኝ ጊዜ ብዙ ነው:: ሆኖም በየጊዜው ድካሜ እየጠፋ ኃይሌ እንደገና ይታደሳል:: የእግዚአብሔርን ኃይል በነፍሴ ብቻ ሳይሆን፣ በአካሌም ተሞልቻለሁ:: በብዙ ዝግጅቶች ላይ እግዚአብሔር በተለየ ሁኔታ በመገለጥ የማይታዩ መላእክትን ልኮ ሰውነቴን እንዲዳስሱ በማድረግ እንደ ሟች ሰው ለሚሞቱ ሰዎች የሰማያዊ መልእክተኛ እንድሆን አድርጓል::

በማያቋርጥ ቀውስ ውስጥ ለመሆን የተፈረደባት በምትመስል ዓለም ውስጥ፣ በመላእክት ላይ የሚሰጠው ትምህርት በእግዚአብሔር ለሚታመኑ ትልቅ መጽናናትና መነቃቃት የሚሰጥ ሲሆን፣ ለማያምኑ ደግሞ እንዲያምኑ የሚገፋፋቸው ይሆናል::

በአንድ ወቅት ብሌይዝ ፓስካል የተባሉ የፈረንሣይ ፈላስፋና የሒሳብ ምሁር «አንዳንድ ደራስያን ስለ ራሳቸው ሥራ ሲያወሩ 'የእኔ መጽሐፍ፣' 'የእኔ ሐተታ፣' 'የእኔ ታሪክ፣' ይላሉ:: እነዚህ ሰዎች ግን ከራሳቸው ይልቅ ጽሑፎቻቸው የሌሎችን ሰዎች ጥሩ ነገር የያዙ ስለሆኑ 'የእኛ መጽሐፍ፣' 'የእኛ ሐተታ፣' 'የእኛ ታሪክ፣' ቢሉ ይሻላል» ብለው ነበር::

ይህም የእኛ መጽሐፍ ነው:: በዚህ ግልጽ ባልሆነና አንዳንዴም

በሚወሳሰብ ርእሰ ጉዳይ ላይ የረዱኝን ሁሉ ላመሰግን እወዳለሁ::

በዚህ ጽሑፍ፤ በእርማትና በማማከር ላገዙኝ በመጀመሪያው ጽሑፌ ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግ ለረዱኝ ለራልፍ ዊልያምስ፣ የመጀመሪያውን ጽሑፍ በማንበብ ጠቃሚ አስተያየቶችን ለሰጡኝ ለቀድሞው የክርስቲያኒቱ ቱዴይ መጽሔት አዘጋጅ ለዶክተር ሃሮልድ ሊንድሴል፣ በይዘቱ፣ በቅርጽና በአደረጃጀቱ ላይ ለረዱኝ በዊተን ኮሌጅ ፕሮፌሰር ለሆኑት ለሚስተር ፖል ፍሮመር፣ በመተየብ፣ ደግመው በመተየብ፣ ጽሑፉን በማንበብ ሊሻሻሉ የሚገባቸውን ቦታዎች ተመልሼ እንድመለከታቸው በማሳሰብ ላገዙኝ በሞንትሪት ለሚገኙት የሥራ ባልደረቦቼ ለካርሊን አሴቶ፣ ለኤልሲ ብሩክሻየር፣ ለሉስሊ ላይትል፣ ለስቴፋኒ ዊልስና ለሳሊ ዊልሰን፣ አስተያየት ለሰጡኝ ለሞንትሪት ፕሬስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ለካልቪን ቲየልማንና ለዶ/ር ጆን አከርስ፣ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ በማበረታታት ለረዳችኝ ለባለቤቴ ለሩት፣ በተለይም ይህንን የተዘነጋና አስፈላጊ ርእሰ ጉዳይ እንድመለከተው ለረዳኝ ለሰማያዊው አባታችን ምስጋና አቀርባለሁ::

በወራት በሚቆጠሩ ጊዜያት ጥቅሶችና አሳቦችን ከረሳኋቸው ምንጮች ሰብስቤያለሁ:: መላእክት ርእሰ ጉዳይ ላይ አብረን የጸለይንና ያነጋገርኳችሁ ሴት ወይም ወንድ ሁሉ፣ መጻሕፍቶቻችሁንና ርእሰ አንቀጾቻችሁን ላነበብኩት ሁሉ ምስጋናዬን ለመግለጽ እፈልጋለሁ:: እያንዳንዱ ለዚህ መጽሐፍ ያበረከተው ነገር አለ:: እያንዳንዱን በስሙ ለመዘርዘር የማይቻል በመሆኑ አዝናለሁ:: ይህ አዲስ እትም በአብዛኛው በ1975 (እ. ኤ. አ.) የተጻፈው መጽሐፍ ቅጂ ነው:: ሆኖም አንዳንድ አዲስ የሆኑ ነገሮችን በመጨመር የተወሰኑ ነጥቦችን አስፋፍቻለሁ::

እግዚአብሔር ለታመሙና በመሞት ላይ ላሉት መጽናናትን፣ በዕለት ተዕለት ኑሮአቸው ጫና ለሚበዛባቸው ብርታትን፣ በእኛ ትውልድ በሚከሰቱ ሁኔታዎች ለተጨነቁ ምሪትን በመስጠት እንዲጠቀምበት የዘወትር ጸሎቴ ነው::

ቢሊ ግራሃም

ሞንትሪት፣ ሰሜን ካሮላይና

# አንድ

## መላእክት የእግዚአብሔር ምሥጢራዊ መልእክተኞች ናቸው?

በቻይና አገር ተወልዳ ያደገችው ባለቤቴ፣ በለጋ ዕድሜዋ ወቅት በተራራዎች ውስጥ ነብሮች ይኖሩ እንደነበረ ታስታውሳለች:: አንድ ቀን አንድ ምስኪን የሆነች ሴት ሣር ለማጨድ ወደ ተራራው ግርጌ ትሄዳለች:: በጀርባዋ ሕፃን ያዘለች ሲሆን፣ ሌላ ትንሽ ልጅ ደግሞ ከጐኗ ድክ ድክ እያለ ይሄዳል:: ሣር ለማጨድ ማጭድ በእጇ ይዛለች:: ኮረብታው ጫፍ ላይ እንደ ደረሰች የሚያጓራ ድምፅ ትሰማለች:: በፍርሃት እንደ ተዋጠች ዘወር ስትል አንዲት እናት ነብር ሁለት ልጆቿን አስከትላ ወደ እርሷ ስትዘል አየቻት::

ይቺ ያልተማረች ቻይናዊት እናት ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ትምህርት ቤት ገብታ አታውቅም:: መጽሐፍ ቅዱስ አይታ አታውቅም:: ከአንድ ወይም ከሁለት ዓመታት በፊት ግን አንድ ሚሲዮናዊ በችግር ጊዜ ሊረዳት ስለሚችለው ስለ ኢየሱስ ነግሯት ነበር:: የነብሯ ጥፍሮች እጇንና ትከሻዋን መቦጫጨቅ ሲጀምር፣ ሴትዮዋ በደመነፍስ፣ «ኢየሱስ ሆይ፣ እርዳኝ!» ብላ ስትጮኽ፤ ያቺ ጨካኝ አውሬ በቀላሉ ልትበላ የምትችለውን ምግቧን አግኝታ መልሳ ከማጥቃት ይልቅ ድንገት ዘወር ብላ እየሮጠች ሄደች::

መጽሐፍ ቅዱስ በመዝሙረ ዳዊት (91)፣ 11 ላይ፣ «በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና» ይላል:: ይቺን ያልተማረች ቻይናዊ ሴት ለመርዳት እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ ይሆን? ዛሬ በአገራትና በሰዎች ጉዳይ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ልዕለ ፍጥረታት አሉ?

«A Slow and Certain Light» በሚል ርእስ ባሳተመችው መጽሐፍ ውስጥ ኤልሣቤት ኤልየት የመላእክትን እገዛ በተመለከተ የአባቷን ገጠመኝ ስታስታውስ፣

አባቴ፣ ገና ትንሽ ልጅ በነበረበት ጊዜ፣ በመገንባት ላይ ባለ

ቤት ወደ ላይኛው ፎቅ ይወጣ ነበር። በሌላኛው ጫፍ ላይ በምስማር ወዳልተያያዘው ሰፊ እንጨት እየተራመደ እያለ እንጨቱ ቀስ ብሎ ማዘንበል ጀመረ። ያለቀለት እንደሆነ የገባው ቢሆንም፣ ለማስረዳት አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ፣ የሆነ እጅ ወደ ታች የገፋው ይመስል እንጨቱ ወደ ሌላ አቅጣጫ ማዘንበል ጀመረ። አባቴ ከዛን ቀን ጀምሮ ሁልጊዜ «ይህ የመልአክ እጅ ይሆን እንዴ!» ብሎ ይገረም ነበር።

## የመላእክት እርዳታ

አንድ የተከበረ የፊላዴልፊያ የነርቭ ሐኪም ከሌሎች ቀናት በተለየ ሁኔታ በድካም ዝሎ ይተኛል። ድንገት የሆነ ሰው በሩን ሲያንኳኳ ከእንቅልፉ ይነቃል። በሩን ሲከፍት በወጉ ያልለበሰችና በጣም የተረበሸች ትንሽ ልጅ በሩ ላይ ቆማለች። እናቷ በጣም የታመመች ስለሆኑ ከእርሷ ጋር አብሯት እንዲሄድ በትሕትና ጠየቀችው። በጣም ብርዳማና በረዷማ ሌሊት ነበር። ምንም እንኳን ከፍተኛ ድካም የነበረበት ቢሆንም፣ ዶክተሩ ልብሱን ለብሶ ልጅቷን ተከትሏት ሄደ።

ሪደርስ ዳይጀስት የተባለው መጽሔት ታሪኩን እንደ ዘገበው፣ ዶክተሩ እናትየዋን በሳንባ በሽታ ታመው ያገኛቸዋል። ለተጨማሪ ሕክምናም ሁኔታዎችን ካመቻቸላቸው በኋላ የትንሽ ሴት ልጃቸውን ብልህነትና ተስፋ አለመቁረጥ ያደንቅላቸዋል። ሴትዮዋም በመገረም ይመለከቱትና፣ «ሴት ልጄ ካረፈች አንድ ወር ሆኗታል። ጫማዎቿና ኮቷ እዛ የልብስ ቁም ሣጥን ውስጥ አሉ» አሉት። ዶክተሩ በመገረምና ግራ በመጋባት የልብስ ማስቀመጫውን በር ከፈተው። እናቷን እንዲረዳላት ይዛው ስትመጣ የለበሰችው ኮት ተንጠልጥሎ ያየዋል። ልብሱ የሞቀና የደረቀ ስለሆነ በዛችው ክረምት ሌሊት የተለበሰ አይመስልም።

በዚህ ተስፋ በተቆረጠበት ሰዓት መልአክ እንደ ሴትዮዋ ልጅ በመመሰል ዶክተሩን ጠርቶት ይሆን? ይህ የታመመችውን ሴት ለመርዳት በእግዚአብሔር መላእክት የተሠራ ሥራ ይሆን?

በኒው ሄብሪድስ ደሴት ፊር ቀዳጅ ሚሲዮናዊ የሆኑት ቄስ ጆን ጂ. ፓቶን የመላእክትን ጥበቃ በተመለከተ የሚያስደንቅ ታሪክ

ተናገረዋል:: አንድ ሌሊት በቁጣ የተሞሉ የአገሬው ሰዎች የሚሲዮኑን ዋና ጽ/ቤት በመክበብ የፓቶንስን ቤተሰብ ለመግደልና ቤታቸውን ለማቃጠል በሚዘጋጁበት ወቅት ጆን ፓቶንና ባለቤቱ በዚያ እጅግ በሚያስፈራ ሌሊት እግዚአብሔር እንዲታደጋቸው ሲጸልዩ አደሩ:: በነጋ ጊዜ ግን ሊያጠቋቸው የመጡት ሰዎች ያለምንም ምክንያት ጥለዋቸው መሄዳቸው አስገረማቸው:: ስለታደጋቸውም እግዚአብሔርን አመሰገኑ::

ከአንድ ዓመት በኋላ የጎሣው መሪ በኢየሱስ ክርስቶስ አመነ:: በዚህ ጊዜ ሚስተር ፓቶን የተደረገውን ነገር በማስታወስ እርሱና አብረውት የነበሩት ሰዎች ቤቱን ሳያቃጥሉና ሳይገድሏቸው እንዴት ሊቀሩ እንደ ቻሉ የጎሣውን መሪ ጠየቁት:: የጎሣ መሪውም፣ «አብረዋችሁ የነበሩት እነዚያ ሰዎች ሁሉ እነማን ነበሩ?» ብሎ በመገረም ጠየቃቸው:: ሚስዮናዊውም፣ «እኔና ባለቤቴ ብቻ እንጂ ምንም ሰው አልነበረም» ብለው መለሱለት:: የጎሣ መሪውም የሚያብለጨልጭ ልብስ የለበሱና የተሳሉ ሰይፎች የያዙ በመቶዎች የሚቆጠሩ ግዙፍ ሰዎች መመልከቱን በመግለጽ አጥብቆ ተከራከረ:: የአገሬው ሰዎች ለማጥቃት ፍርሃት እስኪገባቸው ድረስ የሚሲዮኑን ጣቢያ የከበቡ መስሏቸው ነበር:: በዚያን ጊዜ ነበር ሚስተር ፓቶን እግዚአብሔር መላእክቱን ልኮ እንደ ጠበቃቸው የተገነዘቡት:: ከዚህ በኋላ የጎሣ መሪው ከዚህ ውጪ ሌላ ማብራሪያ ለመስጠት የማይችል መሆኑን ተስማማበት:: በአደጋ ላይ የነበሩትን የባሪያዎቹን ሕይወት ለመታደግ እግዚአብሔር የመላእክትን ጦር ልኮ ይሆን?

አንድ የፋርስ የመንፈሳዊ ጽሑፎች አሰራጭ አንድ የማያውቀው ሰው መጥቶ መጽሐፍ ቅዱሶችን ለመሸጥ የሚያስችል ሕጋዊ መብት እንዳለው ጠየቀው:: «አዎ፣ በየትኛውም የአገሪቱ ክፍሎች እነዚህን መጻሕፍት ለመሸጥ ተፈቅዶልናል» ብሎ መለሰለት:: ሰውየውም ግራ በመጋባት ተመለከተውና፣ «ታዲያ ሁልጊዜ በወታደሮች የምትከበቡት ለምንድን ነው?» ብሎ ጠየቀው:: «ሦስት ጊዜ አደጋ ልጥልባችሁ ዐቅጄ፣ ሦስቱንም ጊዜያት ወታደሮቹን እያየሁ ትቻችኋለሁ :: ከዚህ በኋላ ልጎዳችሁ አልፈልግም» አለው:: እነዚህ ወታደሮች ሰማያዊ ፍጥረታት ይሆኑ?

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የአውሮፕላን አብራሪ

የነበሩት ካፒቴን ኤዲ ሪከንባከርና አብረዋቸው በቢ-17 ይበሩ የነበሩ ሰዎች ነዳጅ አልቆባቸው በፓሲፊክ ውቅያኖስ ውስጥ ሰጠሙ:: ለወራት ስለ እነዚህ ሰዎች የተሰማ ዜና አልነበረም:: ጋዜጦች መሰወራቸውን እንደ ዘገቡ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ይጸልዩ ነበር:: ከንቲባ ላጉዋርዲያ የኒውዮርክ ከተማ ሕዝብ በሙሉ እንዲጸልዩላቸው ጠየቁ:: ከዚህ በኋላ ሰውየው ተመለሱ:: በእሑድ ጋዜጦች ርእሰ አንቀጾችና በፊት ገጾቻቸው ላይ አብራሪው ሪከንባከር ራሳቸው የሆኑትን ሲናገሩ፣ «ስድስት ምስክሮች አብረውኝ ከመሆናቸው ውጭ ይህንን ሁኔታ ለመናገር ግር ይለኛ ል» ሲሉ ገለጹ:: «አንድ የባሕር ወፍ ከየት እንደ መጣ ሳናውቀው ግንባሬ ላይ ዓይኑን አበራብኝ:: ከዚያ እጄን ቀስ ብዬ ላክሁና ገድዬው ሁላችንም እኩል ተካፍለን በላነው:: ትናንሽ አጥንቱን እንኳን ሳይቀር ምንም ሳናስቀር ነው የበላነው:: እስከዛሬ ድረስ እንደዚህ ጣፍጦኝ የበላሁት ምግብ የለም» ሲሉ ጽፈዋል:: ይህ የባሕር ወፍ የሪከንባከርንና አብረውት የነበሩትን ሰዎች ሕይወት ሊያድን ቻለ:: ይህ ሰው ጌታ ኢየሱስን ማወቅ የቻለው በዚሁ ምክንያት ስለነበረ፣ ከብዙ ዓመታት በኋላ ታሪኩን በግሌ እንዲነግረኝ ጠየቅሁት:: «እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ አዳነኝ ከማለት በስተቀር ሌላ የማስረዳው ተጨማሪ ነገር የለኝም» ብሎ መለሰልኝ::

በአገልግሎት ዘመናቴ በሺዎች የሚቆጠሩ ታሪኮችን ሰምቼያለሁ ወይም አንብቤያለሁ:: እነዚህ ሁሉ እንግዲህ ቅዠት፣ አጋጣሚ ወይስ ዕድል ነበሩ? ወይስ የተወሰኑ ሥራዎችን ለማከናወን ከእግዚአብሔር የተላኩ እውነተኛ መላእክት ነበሩ?

## የዘመናችን አምልኮተ ሰይጣን

ከጥቂት ዓመታት በፊት እንደዚህ ዓይነት አስተሳሰቦች በምሁራን ዘንድ ተቀባይነት አይኖራቸውም ነበር:: ሳይንስ ንግሥ ስለነበረና ሳይንስ ደግሞ በሚታዩና በሚለኩ ነገሮች የሚመራ በመሆኑ ስለ መለኮታዊ ፍጥረታት ማሰብ ትርጉም የለሽና ጤነኛ አእምሮ የሌላቸው ወገኖች ቅዠት መስሎ ይታሰብ ነበር::

ይህ ሁሉ ተለውጧል:: ለምሳሌ፣ ዘመናዊው ኅብረተሰብ ስለ

አጋንንት አሠራር ያለውን የሚያሳዝን አድናቆት ተመልከቱ:: ወደ መጻሕፍት መደብር፣ ወደ ዘመናዊ አየር ማረፊያ ሄዳችሁ፣ ዜና የሚነበቡባቸውን ተቋሞች ብትጐበኙ፣ ወደ ዩኒቨርሲቲ ቤተ መጻሕፍት ብትሄዱ መደርደሪያዎችና ጠረጴዛዎች ስለ ዲያብሎስ፣ ሰይጣንን ስለ ማምለክና በአጋንንት ስለ መያዝ በሚያወሱ መጻሕፍት የታጨቁ ናቸው:: ብዛት ያላቸው የሆሊውድ ፊልሞች፣ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች፣ የሃርድ ሮክ ፖፕ ዘፈኖች ቢያንስ ከአራቶቹ አንደኛው ሙሉ በሙሉ ለሰይጣን የወገነ አሊያም በጭብጣቸው ዲያብሎስን በማጣቀስ መልእክት የሚያስተላልፉ ናቸው:: ከጥቂት ዓመታት በፊት «Rolling Stones» የተባለው የሙዚቃ ቡድን «ለዲያብሎስ መራራት» የሚል እጅግ የተደነቀ ዘፈን አቀንቅኖ ነበር:: ከጊዜ በኋላ ደግሞ ሌላ የሙዚቃ ቡድን ለፊተኞቹ ምላሽ የሚሰጥ ዘፈን አውጥቷል::

ዘ ኤግዞርሲስት (The Exorcist) በታሪክ ከፍተኛ ገንዘብ ካስገኙ ፊልሞች መካከል አንዱ ነው:: አርተር ሊዮንስ ለመጽሐፉ «The Second Coming: Satanism in America» «ዳግም ምጽአት- ሰይጣናዊነት በአሜሪካ» የሚል የሚያስፈራ ግን ትክክለኛ ርእስ ሰጥቶታል:: ከአንድ ትውልድ በፊት ቢሆን ኖሮ ምሁራን የማይቀበሉት ይህ ርእስ፣ ዛሬ እንደ ደራሲ ጆን. አፕዳይክና የሃርቫርድ ፕሮፌሰር የሆኑት ሃርቬይ ኮክስን በመሳሰሉ ሰዎች በአግባቡ በመጠናት ላይ ይገኛል:: በአንዳንድ የሕዝብ አስተያየት መስጫ ውጤቶች መሠረት 70 ከመቶ የሚሆኑ አሜሪካኖች በአካላዊ የዲያብሎስ ህልውና ያምናሉ:: ከጥቂት ዓመታት በፊት ዋልተር ክሮንካይት በሲ.ቢ.ኤስ (CBS) መረባቸው ባስተላለፉት ዜና ላይ በጣቢያው በተደረገ የሕዝብ አስተያየት መስጫ ውጤቶች መሠረት ዲያብሎስ በአካላዊ ህልውና መኖሩን የሚያምኑ አሜሪካኖች 12 በመቶ መጨመሩን አስታውቀው ነበር:: ዛሬ አሃዙ ምን ያህል ይሆን? ከአንድ ትውልድ በፊት የነበሩ ሳይንቲስቶች፣ የሥነ ልቦና ባለሙያዎች፣ የሥነ ማኅበረሰብ አጥኚዎችና አንዳንድ የሥነ መለኮት አዋቂዎች በ1970ዎቹ እ.ኤ.አ. መጨረሻ ልዕለ - ተፈጥሯዊ በሆነ ነገር ላይ ማመን በከፍተኛ ደረጃ እየቀነሰ ይመጣል ብለው ተንብየው ነበር:: ተቃራኒው እውነት መሆኑ ግን ያስገርማል!

ከጥቂት ዓመታት በፊት፣ በአንድ መካከለኛ በሆነች ከተማ አካባቢ ሳለሁ፣ እዚያው በሚታተም ጋዜጣ ላይ የመዝናኛ ገጾችን በጥንቃቄ አየኋቸው:: በዚያ አካባቢ በየቴአትር ቤቱ እየታዩ የነበሩትን የፊልሞች ይዘትና ዋና አሳብ ሳነብ እጅግ ደነገጥኩ:: በጭካኔ፣ በግድያ፣ በአጋንንት ስለመያዝ፣ አምልኮተ ሰይጣንና፣ አስፈሪ የሆኑ ነገሮችን የሚያንጸባርቁ ከመሆናቸው ሌላ የዝሙትን ስሜት የሚያነሣሡም ነበሩ:: እያንዳንዱ ማስታወቂያ ሌሎቹን ማስታወቂያዎች በሚያሽብር፣ በሚያስፈራራና አእምሮን በሚሰልብ ስሜታዊ ጥፋት ለመብለጥ የሚጥር ይመስል ነበር:: ይህ ሥዕል ዛሬም አልተለወጠም:: የሚገርመው ነገር ዛሬ ፊልሞች በከፋ ሁኔታ ውስጥ ነው ያሉት!

በክርስቲያኑ የኅትመት ዓለም እንኳ የፕሮቴስታንትና የካቶሊክ ጸሐፊዎች በሰይጣን ላይ ያተኮሩ መጻሕፍት በብዛት አውጥተዋል:: እኔ ራሴ እንኳ በሰይጣንና በአጋንንቱ ላይ ያተኮረ መጽሐፍ ለመጻፍ ሳስብ ነበር::

## የሰይጣን የህልውናው እውነተኛነትና ኃይሉ

ሰይጣን እውነተኛ ህልውና እንዳለውና ከመልእክተኞቹ ከአጋንንት ጋር በመተባበር እንደሚሠራ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል:: በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔርን ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥራ ለማሸነፍ እያንዳንዷን በጎ ጥረት የማከላሸት እንቅስቃሴያቸውን አጠናክረው ነበር:: ባለንበት ዓለም ሰይጣን ሰዎችን የሚጐዱ ተግባራትን ጨምሮ መንቀሳቀሱ ምናልባትም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት መድረሱን የሚያመለክት ይሆናል:: በእርግጥም የሰይጣን አሠራር በሁሉም አቅጣጫ በገሃድ ይታያል:: ይህ በጦርነቶችና በየዕለቱ ሕዝብን በሚጐዱ ሌሎች ቀውሶች ውስጥ የሚታይ ነው:: በተጨማሪም፣ ይህንን ሰይጣን የክርስቶስ አካላት በሆኑ ግለሰቦች ላይ ከሚሰነዝረው ጥቃት ልንገነዘብ እንችላለን::

ከጥቂት ዓመታት በፊት ካፒቶል ሕንፃ በሚገኝ ምግብ ቤት ውስጥ ከብዙ የሴኔትና የምክር ቤት አባላት ጋር የእራት ግብዣ ነበረኝ:: በዚህ ጊዜ ዘ ኤግዞርሲስት ከተሰኘው ፊልም ጋር እያይዘን

በአጋንንት አምልኮ ላይ እያደገ በመምጣት ላይ ስላለው የሰው ፍላጎት መወያየት ጀመርን። በቅርቡ የጠለቀ የሃይማኖት ልምምድ ውስጥ የገባ አንዱ የሴነት አባል ካለፈው የአጋንንት ልምምዱ የተነሣ ኤግዞርሲስት የተባለውን ፊልም የሚያሳይ ቴአትር ቤት መኖሩን ካወቀ በቴአትር ቤቱ በኩል ላለማለፍ በሌላ መንገድ መኪናውን እንደሚያሽከረክር ነገረን። በአጠገቡ ለመሄድ እንኳ ይፈራ ነበር። አክሎም፣ «አጋንንትና መላእክት መኖራቸውን በእርግጥ አውቃለሁ» አለን።

ከብዙ ዓመታት በፊት የቀድሞው ጳጳስ ፖል ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል የሚያጠቁ የክፋት ኃይላትንና አጋንንትን መንግሥት ከጀርባቸው ሆኖ የሚያዝ ሰይጣን እንዳለ እርግጠኛ መሆናቸውን ተናግረዋል። የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የመናፍስት ዓለም እውን መሆንን በተመለከተ የነበራትን አቋም እንደገና እየፈተሸች ሲሆን፣ ለዘብተኛ አስተሳሰብ ያላቸው የሥነ መለኮት ምሁራንና የፕሮቴስታንት ወንጌላውያን አብያተ ክርስትያናት ለዚህ ርእሰ ጉዳይ ፍላጎት ትኩረት ሰጥተዋል።

## ያልታወቁ በራሪ አካላት (ዩፎዎች)

ሰዎች ልባቸውን በአዲስ ሁኔታ ለልዕለ ተፈጥሯዊ ነገሮች መክፈታቸውን የምንገነዘበው ለጥንቆላና ለሰይጣን ትኩረት በማሳየታቸው ብቻ አይደለም። ከጥቂት ዓመታት በፊት ዩፎዎች (UFOs) ወይም «ያልታወቁ በራሪ አካላት» በተባሉ ነገሮች ላይ በነበረው መላምታዊ እንቅስቃሴም ሰዎች ለልዕለ ተፈጥሯዊ ነገሮች ፍላጐት እንዳላቸው ተገልጧል። ዛሬም እንኳ አንዳንድ ዝነኛ የተባሉ ፊልሞች ማዕከል የሚያደርጉት ከህዋው ውጪ በሚመጡት ጐብኚዎች ላይ ነው።

አንዳንድ ስመ ጥር ሳይንቲስቶች ዩፎዎች በየጊዜው ለሰዎች መታየታቸውን ሲክዱ፣ ሌሎቹ ደግሞ ያምናሉ። አንዳንድ ሳይንቲስቶች ዩፎዎች ከህዋው ውጪ የሚመጡ ጐብኚዎች እንደሆኑ ሊያረጋግጡ የሚችሉበት ደረጃ ላይ እንደ ደረሱ ያስባሉ። አንዳንድ ክርስቲያን ጸሐፍት ዩፎዎች በፍጥረት ዓለም ዙሪያ ያለውን የተፈጥሮ ጉዳዮችን የሚመሩ የእግዚአብሔር መልእክ

ሠራዊት አንድ ክፍል ሊሆኑ ይችላሉ ብለው ይገምታሉ:: ይህንን ዓይነት አመለካከት በሚያሳምን መንገድ ለማረጋገጥ የማይቻል ቢሆንም፣ ብዙ ሰዎች ግን ይህንን ክስተት በተመለከተ መለኮታዊ የሆነ ማብራሪያ ይፈልጋሉ:: ሆኖም ይህ በትክክል ለመረዳት አዳጋች የሆነው ክስተት በዓለም ዙሪያ ባልተጠበቁ ቦታዎች በተደጋጋሚ በመታየት ላይ መሆኑ ሊደበቅ የማይችል እውነት ነው::

ከጥቂት ዓመታት በፊት ለመግለጽ ያልተቻለ ነገር በጃፓን የሌሊት ሰማይ ላይ የታየው አንዱ ምሳሌ ነው:: በታኅሣሥ 15/1975 እ.ኤ.አ. የዩፎን አካላት የሚመስሉ አካላት የተቀጣጠለ የጠፍር የዕንቁ አፍ መስለው የጃፓንን የምሽት ሰማይ ገሚሱን ያህል በመሸፈን ያለምንም ድምፅ በረሩ:: የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ ፖሊስና በሺዎች የሚቆጠሩ የጎሩ ነዋሪዎች ሰማይ ላይ ዓይናቸውን ተክለው በመገረም እየተመለከቱ አንድ ቀጥ ያለ መሥመር በማበጀት፣ ታይቶ በማይታወቅ ጭጋጋማ ደመና ውስጥ ሆነው በጃፓን ላይ በረሩ:: በተጨማሪም ከግማሽ ሰዓት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ሰባት መቶ ማይልስ ርቀት ላይ በሚገኙ ከተማዎች ላይ መታየታቸው ተዘገበ::

ይህ በአስገራሚ ሁኔታ የተደራጀው ነገር ወደ ደቡብ ሲጓዝ በመቶዎች የሚቆጠሩ የተደናገጡ የስልክ ደዋዮች ጥሪ የፖሊስ ጣቢያዎችንና የመንግሥት ተቋማትን አጣበበው:: «ስልክ የሚደውሉት ሁሉ አንድ ግዙፍ ደመና በከተማቸው ላይ ሲያልፍ ማየታቸውን ገለጹ::»

በወቅቱ ተረኛ መኰንን የነበሩት ታኬኦ ኦሂራ እንግዳ የሆኑ አካላት በደመና ውስጥ ሆነው በቀጥተኛ መሥመር ሲሄዱ ማየታቸውን ሰዎች እንደነገሯቸው ያስታውሳሉ:: እነዚህ አውሮፕላኖች ነበሩ ወይ? ተብለው ሂሮሺ ማያዛዋ ሲጠየቁ፣ «አልነበሩም:: ምክንያቱም አውሮፕላን ወይም ሌላ የተፈጥሮ ክስተት በራዳሩ ላይ ሊታይ አይችልም:: ሌሊቱም ከሌላ ጊዜ ይልቅ የጠራ ነበር:: የዚህ አጠቃላይ ጉዳይ ለእኔ ምሥጢር ነው» ሲሉ መልሰዋል::

ፕሮፌሰር ማሳቶሺ ኪታሙራ ከአውሮፕላን ጣቢያው አጠገብ

ከሚገኘው የቶኪዮ የአየር ትንበያ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ውስጥ ሆነው የሚያብረቀርቅ የብርሃን ትዕይንት በምሽት ሰማይ ላይ ተመልክተዋል። እርሳቸውም «ደንቆኝ ነበር። በራዳሬ ላይ የታየ ነገር አልነበረም። የተመለከትኩትን ለአውሮፕላን ማረፊያው መቆጣጠሪያ አስታወቅኩ፣ ነገር ግን እነርሱም ምንም ነገር በራዳራቸው ላይ ያለማየታቸውን ገለጹልኝ» ብለዋል።

## ተጨማሪ ማብራሪያዎች

ከብዙ ዓመታት በፊት የታተመው የኤሪሽ ቮን ዳኒኬን «Chariots of the Gods?» «የአማልክት ሰረገላዎች?» የተባለ መጽሐፋቸው በ1984 እ.ኤ.አ. በበርክሌይ አሳታሚ ድርጅት አማካኝነት እንደገና በጠንካራ ጥራዝ ታትሞ ነበር። ይህ መጽሐፍ የቅድመ-ታሪክ የጠፈር ሰዎች በጠፈር መንኰራኵሮች በመሆን ሩቅ ከሆኑ ከዋክብት በመምጣት ምድርን መጐብኘታቸውን ያትታል። የሰው ልጅ የጣዖታትን ጽንሰ አሳቦች የተገነዘበው ከእነዚህ ጐብኝቶች ነው ይላሉ። ኢማኑኤል ቬሊኮቭስኪ "Worlds in Collision" እና «Ages in Chaos» በተሰኙት በታወቁ መጻሕፍታቸው ችግር የበዛበት የመካከለኛው ምሥራቅ ታሪክ ከክርስቶስ ልደት በፊት በሁለት ሺህ ዓመት በከፍተኛ ደረጃ በመበታተን በምድር ላይ ጉዳት ካደረሰው ከፀሐይ ሥርዓት ጋር ሊያያዝ እንደሚችል ገልጸዋል። በዚያን ጊዜ የነበረው የከባድ ሥቃይ ትዝታ በፍጥነት ቢደበዝዝም፣ በሰው ዘር አእምሮ ውስጥ ተቀብሮ በመቀመጥ የሰውን ልጅ ዘመናዊ ራሱን የማጥፋት ባሕርይ ያንጸባርቃል ይላሉ።

ስለ እነዚህ እጅግ አስገራሚ ስለሆኑ የፍጥረታት ጥናት፣ ቁጥራቸው ብዙ ከሆኑ ሌሎች ጥናቶች ጋር በተደጋጋሚና በአግባቡ ስለቀረበ ማንም ንቆ ሊተዋቸው አይችልም። በብዙ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷቸው በመጠናት ላይ ይገኛሉ። ለውይይት የሚቀርብ ጉዳይን በተመለከተ ከእነዚህ ጉዳዮች የበለጠ ሊነሣ የሚችል ነገር የለም ለማለት ይቻላል።

አንዳንድ አስተሳሰባቸው በእግዚአብሔር ቃል ላይ የታነጸ ቅን ክርስቲያኖች ዩፎዎች መላእክት ናቸው ብለው ይከራከራሉ። እውነት መላእክት ናቸውን? እነዚህ ሰዎች የኢሳይያስን፣

የሕዝቅኤልን፣ የዘካርያስንና የዮሐንስ ራእይን የተወሰኑ ክፍሎች በመጥቀስ በዩፎዎች ተመልካቾች የተዘገቡትንና ዩፎዎች ታይተዋል ተብሎ የተገመተበትን ሁኔታ ያነጻጽሩታል:: ዝርዝር ነገሮች ውስጥ በመግባት በከፍተኛ ደረጃ የታወቁ የአየር መንገድ ሠራተኞችን እንደ ምሳሌ በመውሰድ ከሕዝቅኤል 10 ጋር እያስተያዩ ከጠንካራ ምክንያት ጭምር ያቀርቡታል:: ለሕዝቅኤል 10 ላይ «. . . እኔም አየሁ፣ እነሆም፣ በኪሩቤል አጠገብ አራት መንኰራኩሮች ነበሩ፤ አንዱ መንኰራኩር በአንዱ ኪሩብ፣ አንዱ መንኰራኩር በአንዱ ኪሩብ አጠገብ ነበረ:: የመንኰራኩሮቹም መልክ እንደ ቢረሌ ድንጋይ ነበረ:: የአራቱም መልክ አንድ ይመስል ነበር፣ መልካቸውም በመንኰራኩር ውስጥ እንዳለ መንኰራኩር ነበረ:: ሲሄዱም በአራቱ ጐድናቸው ይሄዱ ነበር፣ ሲሄዱም አይገላመጡም ነበር. . . ኪሩቤልም ከምድር ከፍ ከፍ ይሉ ዘንድ ክንፎቻቸውን ሲዘረጉ መንኰራኩሮች ደግሞ ከአጠገባቸው ፈቀቅ አይሉም ነበር:: ሕይወት ያላቸው የእንስሶች መንፈስ በመንኰራኩሮች ውስጥ ነበረና እነዚህ ሲቆሙ እነዚያ ይቆሙ ነበር፣ እነዚህም ከፍ ከፍ ሲሉ እነዚያ ከእነርሱ ጋር ከፍ ከፍ ይሉ ነበር» (ሕዝቅኤል 10:9-13፣16-17)::

እንደነዚህ ዓይነት ክፍሎችን ከመላእክት መታየት ጋር ማያያዝ በጣሙን ግምታዊ ነው የሚሆነው:: ወይም ደግሞ በአሁኑ ዘመን አስተሳሰቦችና መላምቶች ላይ በእጅጉ በማተኮርና አለመጠን በመጓጓት ያልታወቁ በራሪ አካላትንና ተመሳሳይ ክስተቶችን ከመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ጋር ለማመሳሰል ባንሞክር መልካም ነው:: በዚህ ዓለም ላይ የሕይወት ጅማሬን በተመለከተ ዓለማዊ የሆኑ መላምቶች መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረን ጋር የሚቃረን አስተሳሰብ እንደሚያራምዱ እውነት ነው:: ደስ የሚያሰኘው ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በሚያስተምረው አምላክ ለማመን የማይፈልጉ ሰዎች እንኳ ሳይቀሩ በአሁኑ ጊዜ ለእንደዚህ ዓይነት አስተሳሰቦች የተለየ ትኩረት መስጠታቸው ነው::

ስለ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ነገር የሰዎች ፍላጎት መታደሱን የምናውቅበት ሌላው ማረጋገጫ፣ ሰዎች ከስሜት ሕዋሳቶቻችን ላለፉ ግንኙነቶች (extrasensory perception-ESP) ከፍተኛ ትኩረት መስጠታቸው ነው:: ይህ ልምምድ በሩቅ አገር ካለ ሰው ጋር ስልክ

ሳይጠቀሙ በአሳብ ብቻ የመገናኘት ዓይነት ነው:: በአሁኑ ወቅት በዩኒቨርሲቲዎቻችን ጥናትና ምርምር ከሚካሄዱባቸው የትምህርት ዓይነቶች በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ያለው የሳይንስ አንዱ ክፍል የሆነው ረቂቅ የሥነ ልቦና ጥናት (Parapsychology) ነው::

በዱክ ዩኒቨርሲቲ የሚገኙት ዶ/ር ጆሴፍ ቢ. ራህይን በ1930ዎቹ (እ.ኤ.አ.) ከስሜት ሕዋሳቶቻችን ስላለፉ ግንኙነቶች በማጥናት በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የረቂቅ የሥነ ልቦና ጥናት ክፍል (ዲፓርትመንት) እንዲቋቋም አደረጉ:: ግለሰቡ የዚሁ ክፍል የመጀመሪያ ፕሮፌሰር በመሆንም አገልግለዋል:: ዛሬ ሳይንቲስቶች ከተራው ስሜቶቻችን ያለፉ ግኝቶችን በተመለከተ ከፍተኛ የእውቀት ደረጃ ላይ ለመድረስ ትልቅ ጥናት በማድረግ ላይ ይገኛ ሉ:: በዚሁ ጥናት ላይ የሚሳተፉ ሰዎች ስም ዝርዝር በዓለም ላይ ከላቀ ደረጃ ላይ ደርሷል:: ርእሰ ጉዳዩ ተወዳጅ እየሆነ የመጣበት ምክንያት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ምሁራዊና ሳይንሳዊ ጥናት በመደረጉ ብቻ ሳይሆን፣ ብዙዎች ጠንካራ ደጋፊዎች ሃይማኖት-የለሽ መሆናቸውንና በአደባባይ የሚናገሩ በመሆናቸውም ጭምር ነው:: ይህ ልምምድ ከዩናይትድ ስቴትስ ይልቅ እንደ ሶቭየት ኅብረት ባሉ የኮሙኒስት አገሮች ሰፊ ተቀባይነትን አግኝቷል:: ቀደም ሲል የሰዎችን የአስተሳሰብ አቅጣጫ የመለወጫ ዘዴ አድርገው ይጠቀሙበት የነበረ ቢሆንም፣ በአንዳንድ ሁኔታዎች «ሃይማኖትን የመተካት» ሚናን እየተጫወተ ይገኛል::

በመገናኛ ብዙሃን የሚካሄዱ ውይይቶችን ምላሽ አስተውላችሁ ተመልከቱ:: አንድ የተከበረ ሰው ወለል ብሎ በተከፈተ በር አልፎ የእንግዳ ወንበር ላይ ሲቀመጥ የሚጠየቀው ጥያቄ፣ «ከተራ የስሜት ሕዋሳታችን ባለፉ ልምምዶች ታምናለህ?» የሚል ይሆናል:: ከአንድ ትውልድ በፊት «አዎን አምናለሁ» ማለት በጊዜው ተቀባይነት እንዳልነበረው ሁሉ፣ በ1980ዎቹ አጋማሽ (እ.ኤ.አ.) «አላምንም» ማለት ተቀባይነት አይኖረውም::

## ይህንን መጽሐፍ የጻፍኩበት ምክንያት

መላእክትን በተመለከተ መጽሐፍ መጻፍ ለምን አስፈለገ? ስለ መላእክት መናገር መለኮታዊ ክስተቶችን በተመለከተ

የሚሰራጨውን መላምት ማጠናከር አይሆንም ወይ? የዚህ ዓይነቱ ውይይት ምን ጠቃሚ ነገሮችን ሊያስገኝ ይችላል? መላእክትን በተመለከተ የነበረው አድናቆት ከመካከለኛው ክፍለ ዘመን ጋር አብሮ አላለፈምን?

ክፉ የሆነው የዓለም ሥርዓት ተጽዕኖ ሁሉ የሰዎችን አእምሮ በሚያውክበት፣ በረብሻ በተሞላውና በተጨነቀው በእኛ ትውልድ ውስጥ በክርስቲያን እምነት በጎ አስተሳሰቦች ላይ ማተኮር የሚያስፈልግበት ጊዜ የደረሰ ይመስለኛል:: ሰይጣን ልዕለ ተፈጥሯዊ ነገሮችን ማድረግ ይችላል:: ነገር ግን የወደቀ ስለሆነ ይህንን ማድረግ የሚችለው በእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ብቻ ነው:: «በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና» (1ኛ ዮሐንስ 4:4):: ሁሉንም የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው:: እግዚአብሔር የሚያጠቁበትንና የሚከላከሉበትን መሣሪያ ለክርስቲያኖች ሰጥቷቸዋል:: ልንፈራ አይገባም፤ ልንቆዝም አይገባም፤ ልንታለል አይገባም፤ ልንታወክም አይገባንም:: ይልቁንም፣ በጸጥታና በተጠንቀቅ በስፍራችን ላይ ልንሆን ይገባል:: «በሰይጣን እንዳንታለል፤ የእርሱን አሳብ አንስተውምና» (2ኛ ቆሮንቶስ 2:11)::

ሰይጣን ከሚያታልልባቸው ብልጠት የተሞላባቸው ዘዴዎች አንዱ፣ ከክፉ መናፍስት ጋር በምናካሂደው ውጊያ ላይ እግዚአብሔር ስለሚያደርግልን እገዛ አእምሮአችን እንዳያስብ ማድረግ ነው:: ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ውጊያችን ወቅት እገዛ እንደሚያደርግልን ይመሰክራል:: በዚች ዓለም ላይ ብቻችንን አይደለንም:: መጽሐፍ ቅዱስ ኃይል እንዲሰጠንና እንዲመራን መንፈስ ቅዱስ የተሰጠን መሆኑን ያስተምረናል:: ከዚህ በተጨማሪም እግዚአብሔር ትእዛዙን የሚጠባበቁ ሊቆጠሩ የማይችሉ መላእክት እንዳሉት መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ሦስቱ መቶ በሚጠጉ የተለያዩ ክፍሎች ላይ ያስተምራል:: ከዚህም ሌላ እግዚአብሔር ልጆቹ ከሰይጣን ጋር በሚያካሂዱት ትግል ያግዟቸው ዘንድ እነዚህን መላእክት ወክሏቸዋል:: ምንም እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ እኛ በምንፈልገው መልኩ ስለ መላእክት በቂ መረጃ ባይሰጠንም፣ የሚያስተምረን እውነት በሚገጥሙን ሁኔታዎች ሁሉ የጥንካሬያችንና የጽናታችን መሠረት ሊሆን ይገባል::

እኔ በበኩሌ እነዚህ ሰማያዊ ፍጡራን በትክክል መኖራቸውንና በዓይን የማይታይ እርዳታ የሚሰጡን መሆናቸውን አምናለሁ:: መላእክት መኖራቸውን የማምነው በጣት በሚቆጠሩ ልብን በሚመስጡ ምስክርነቶች እንደምንሰማው አንድ ሰው ተአምራዊ የሆነ የመላእክት ጉብኝት ስላጋጠመው አይደለም:: ዩፎዎች መላእክትን ይመስላሉ ስለተባለም አይደለም:: ከተራው የስሜት ሕዋሳቶቻችን ስላለፉ ግንኙነቶች የሚያጠኑ ባለሙያዎች የመናፍስትን ዓለም የእውቀት ዘርፍ ከቀን ወደ ቀን ተአማኒነት እንዲኖረው እያደረጉት ስለሆነም በመላእክት አላምንም:: በሰይጣን እውን መሆን ላይ የዓለም ትኩረት በድንገት ስለተሳበም በመላእክት አላምንም:: በመላእክት የማምነው ስላየኋቸው አይደለም:: መላእክትን አይቼ አላውቅምና::

በመላእክት የማምንበት ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ መላእክት መኖራቸውን የሚናገር ስለሆነና መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ስለማምን ብቻ ነው::

በመላእክት የማምንበት ሌላ ምክንያት ደግሞ ለየት ባሉ ሁኔታዎች ላይ ሕልውናቸው ስለተሰማኝ ነው::

ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ በሚቀርቡት ምዕራፎች ውስጥ የምለው ነገር ስለ መንፈሳዊው ዓለም ያከማቸሁትን ግላዊ አስተሳሰቤን ወይም ደግሞ ስለ መንፈሳዊው ግዛት ያለኝን የግል መንፈሳዊ ልምምዴን የሚያንጸባርቅ አይሆንም:: በከፊል እንኳን ቢሆንም ላቀርብ የወሰንኩት <u>መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መላእክት ስለሚናገረው የተረዳሁትን ነው</u>:: በእርግጥ ይህ ለርእሰ ጉዳይ የተሟላ ጥናት አይሆንም:: ሆኖም ይህንን መጽሐፍ ካነበባችሁ በኋላ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ተነሣሥቶ ከመጽሐፍ ቅዱስ የበለጠ ጠልቃችሁ እንድትረዱ ያግዛችኋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ:: ስለዚህ በበለጠ በመላእክቱ አገልግሎት ፍላጎታችሁ ጕን መቆሙን እያረጋገጠ በመሆኑ የእግዚአብሔርን ፍቅርና እንክብካቤ እንድታስተውሉና በየዕለቱም በእግዚአብሔር የማያቋርጥ ጥበቃ ውስጥ በእምነት እንድትጓዙ ጸሎቴ ነው::

መንፈሳዊ ኃይላትና ሀብቶች ለሁሉም ክርስቲያኖች ተሰጥተዋል:: የሚያግዙን ኃይላት ገደብ ስለሌላቸው ክርስቲያኖች

አሸናፊዎች ይሆናሉ:: በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ መላእክት እግዚአብሔርን በመታዘዝ ያገለግሉናል:: ከዚህ ምድር ወደ ከበረው ስፍራ በምንጓዝበት ወቅት የሰማያዊ ሠራዊት በከፍተኛ ትኩረት የሚከታተሉን ሲሆን፣ የሰይጣን ቀላል ጠብመንጃዎች ከእግዚአብሔር ከባድ መሣሪያ ጋር ሊመጣጠኑ አይችሉም:: ስለሆነም አትፍሩ:: እግዚአብሔር ከጐናችሁ ቆሟል:: እርሱ በዚህ ግጭት በበዛባቸው ዘመናት መላእክቱ ጦርነት እንዲያውጁ ትእዛዝ ያስተላለፈላቸው ሲሆን፣ በጦርነቱ ድል የሚነሡትም እነርሱው ናቸው:: ሐዋርያው ጳውሎስ በቈላስይስ 2:15 ላይ፣ «አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ፣ ድል በመንሣት በእርሱ እያዘራቸው በግልጥ አሳያቸው» ብሏል:: በሥጋ፣ በዓለምና በሰይጣን ላይ ድሉ አሁን የእኛ ነው:: መላእክቱ እኛን ለመርዳትና ሊገጥመን ላለ ድንገተኛ አደጋም በተጠንቀቅ ላይ ይገኛሉ::

ይህንን መጽሐፍ ስታነቡ፣ እግዚአብሔር ዓይኖቻችሁን ከፍቶ ወደ እርሱ ለሚቀርቡ ለመስጠት ያዘጋጀላቸውን ኃይል እንድትመለከቱ ጸሎቴ ነው:: ሌላው የምጸልየው ደግሞ እግዚአብሔር በየዕለቱ የሚያስፈልጋችሁ መሆኑን እንድታውቁና ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዴት ወደ ዓለም እንደ ላከውና ከሕሊና ጸጸትና ከኃጢአት ጉልበት ሊታደጋችሁ እንደ ቻለ ለማሳየት እንዲጠቅማችሁ ነው::

ልዕልት ቪክቶሪያን ያሳፈረው ፈጣን የብሪታኒያ ባቡር ከባድ መብራቱን አብርቶ በከፍተኛ ፍጥነት ጨለማውን እየሰነጠቀ ይጓዝ ነበር::

በድንገት የባቡሩ ሹፌር ጥቁር ካባ ያደረገ እንግዳ የሆነ ቅርጽ ሐዲዱ መሐል ላይ ቆሞ እጆቹን ሲያወዛውዝ በሞተሩ የፊት መብራት በድንጋጤ ተመለከተ:: የባቡሩ ሹፌርም ፍሬኑን ይዞ ባቡሩን ሲጥጥ አድርጎ ያቆመዋል::

እርሱና ሌሎች የባቡሩ ሠራተኞች ያስቆማቸውን ነገር ለማየት ወረዱ:: ነገር ግን ያንን እንግዳ የሆነ ቅርጽ ለማየት አልቻሉም:: የባቡሩ ሹፌር በጥርጣሬ ስሜት ጥቂት ከፍ ብሎ በሐዲዱ ላይ ሲሄድ በድንገት ቀጥ አለና ጭጋጉ ላይ ዓይኑን ተክሎ በከፍተኛ ድንጋጤ ቆመ:: ድልድዩ ከመሃሉ በውኃ ተወስዶ ፊታቸው በሚገኘ

ው የሞላ ምንጭ ውስጥ ተገንድሶ ወድቋል:: የባቡሩ ሹፌር ያን አስፈሪ ምሥል አይቶ ባቡሩን ባያስቆም ኖሮ ባቡሩ እዚያ አነስተኛ ወንዝ ውስጥ ይወድቅ ነበር::

ድልድዩ በመጠገን ላይ እያለ ሠራተኞቹ ማስጠንቀቂያ ስለ ሰጣቸው እንግዳ ፍጥረት የተቻላቸውን ሁሉ ለማወቅ ጣሩ:: ነገር ግን ለንደን እስኪደርሱ ድረስ ምሥጢሩን ለማወቅ አልቻሉም ነበር::

ነገሩ እንዲህ ነው:: የባቡሩ ሹፌር ከሞተሩ የፊት መብራት ሥር አንድ ግዙፍ የሆነ የእሳት ራት ያገኛል:: ለጥቂት ጊዜ ከተመለከተው በኋላ በመጓጓት ስሜት ክንፎቹን በምራቁ አረጠበና መብራቱ ላይ ለጠፈውና በሹፌሩ ወንበር ላይ ተቀምጦ መብራቱን ሲያበራው ያንን «ባለባንዲራ» በመብራቱ ብርሃን ተመለከተው:: መልሱንም አገኘው:: ባቡሩ በውኃ ከተወሰደው ድልድይ ሊደርስ ጥቂት ሰከንዶች ሲቀሩት የእሳት ራቱ ከመብራቱ ጋር ይላተማል:: በጭጋጉ ውስጥ እጁን የሚያወዛውዝ አካል ያለው መንፈስ መሰለ::

ይህንን አስደናቂ ሁኔታ ንግሥት ቪክቶሪያ ሲሰሙ፣ «ይሄ አጋጣሚ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር እኛን የጠበቀበት መንገድ ነበር» ብለዋል::

በርግጥ የባቡሩ ሹፌር በፊት መብራቱ ብርሃን የተመለከተው ነገር መልአክ አልነበረም:: ሆኖም እግዚአብሔር በማይታዩ መላእክቱ አገልግሎት አማካይነት ያንን የእሳት ራት በአስፈላጊ ወቅት ላይ በመብራቱ መስታወት ላይ አስቀምጦት ይሆናል:: «በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና» የሚለው እውነት ነው [መዝ. (91):11]::

# ሁለት

# መላእክት በትክክል አሉ

የመላእክትን ባሕርይ በተመለከተ ከልዕልት ቪክቶሪያ ዘመን አንሥቶ ዛሬ እስከምንገኝበት ዘመን ድረስ ሲነገር የቆየ ግምታዊ አስተሳሰብ አለ:: እነርሱን በሚመለከት እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚገባ ገልጾልናል:: ከዚህ የተነሣ የሥነ መለኮት ምሁራን በዘመናት ሁሉ ስለ «ሥነ መላእክት» (መላእክትን በሚመለከት በሥርዓት የተቀመጠው የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት) አስፈላጊነት አጠቃላይ ስምምነት ላይ ደርሰዋል:: በሥርዓታዊ የሥነ መለኮት ትምህርት (Systematic Theology) ውስጥ ሁሉ ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኝም ወስነዋል:: በመልካሞቹ መላእክትና በወደቁት ወይም ክፉ መላእክት መካከል ያለውን ልዩነት በማሳየት በስፋት ጽፈዋል:: ዛሬ ብዙ ሰዎች ለዲያብሎስና ለጭፍሮቹ ከፍተኛ ትኩረት በሚሰጡበትና እስከ ማምለክ በደረሱበት ጊዜ መልካም መላእክትን የሚመለከት ርእስ ጉዳይ በፍጹም ተዘንግቷል::

መላእክት ፍጹም በተለየ የፍጥረት ዓለም ውስጥ የሚመደቡ ሲሆን፣ ይህም እኛ በተፈጥሮ ሥርዓት ውስጥ ተወስነን የምንኖር ሰዎች የማንረዳው ነው:: በዚህ የመላእክት ግዛት ውስጥ ውስንነታቸው በእኛ ላይ ከተገደበው የተፈጥሮ ሥርዓት ፈጽሞ የተለየ ነው:: እግዚአብሔር ከእኛ ይልቅ ከፍተኛ እውቀት፣ ኃይልና የመንቀሳቀስ ነጻነት ሰጥቷቸዋል:: እነዚህ መላእክት የተባሉትን ኃያላን ፍጥረታት አይታችሁ ወይም ተገናኝታችሁ ታውቃላችሁ? ላይሆን ይችላል:: ለሥጋ ዓይን የሚታዩት መላእክት እምብዛም እንዳይደሉ መጽሐፍ ቅዱስና የሰዎች ልምምድ የሚነግሩን ቢሆንም፣ ይህ ማለት ግን የመላእክትን እውነታነት ወይም ኃያልነት ያሳንሰዋል ማለት አይደለም:: ዋና ሥራቸው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በዓለም ላይ ማስፈጸም ነው:: እግዚአብሔር የአምባሳደርነትን ሥልጣን ሰጥቷቸዋል:: የጽድቅ ሥራን እንዲያከናውኑ የወከላቸውና ሕጋዊ ሥልጣን የሰጣቸው

የተቀደሱ ተወካዮች ናቸው፡፡ በዚህ መንገድ በሥልጣኑ ዓለማትን ሁሉ በፍጹም የበላይነት ሲቆጣጠር እነርሱ ደግሞ እንደ ፈጣሪያቸው ያገለግሉታል፡፡ ስለሆነም የተቀደሱ ተግባሮቹን ወደ ፍሬያማ ፍጻሜ የሚያደርሱበትን ችሎታ ሰጥቷቸዋል፡፡

## መላእክት ፍጡራን ናቸው

ስለ መላእክት የምትሰማውን (የምታነበውን) ሁሉ ማመን የለብህም፡፡ አንዳንዶቹ የሚያምሩ ክንፎች ያሏቸውና ከአንገታቸው ዝቅ የሚሉ ሰማያዊ ፍጥረት አድርገው ያዩአቸዋል፡፡ ሌሎቹ ደግሞ እንስታዊ ነገሮች አድርገው ያስቧቸዋል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ መላእክት እንደ ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር የተፈጠሩ መሆናቸውን ይገልጻል፡፡ በአንድ ወቅት መላእክት አልነበሩም፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ አሐዱ-ሥሉስ ከሆነው ከአብ፣ ከወልድና፤ ከመንፈስ ቅዱስ በስተቀር ምንም ነገር አልነበረም፡፡ ጳውሎስ በቈላስይስ 1:16 ላይ፣ «. . . የሚታዩትና የማይታዩትም. . . በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና» ይላል፡፡ በእርግጥ መላእክት በእግዚአብሔር ከተፈጠሩት የማይታዩ ነገሮች መካከል ናቸው፡፡ ምክንያቱም «ሁሉም ነገር የተፈጠሩት በእርሱና ለእርሱ ስለሆነ ነው፡፡» ይህ ፈጣሪ ኢየሱስ በቈላስይስ 1:17 ላይ እንደተጻፈው፣ «ከሁሉ በፊት ነው፡፡ ሁሉም በእርሱ ተጋጥሟል፡፡» ሁሉን ቻይ የሆነው ጌታ ኢየሱስ በኃይሉ ባያጸናቸውና ባያቆማቸው ኖሮ መላእክት እንኳ በሕይወት ለመኖር አይችሉም ነበር፡፡

መላእክት መልካቸውን የመለወጥና ከሰማያዊው የክብር ማዕከል ወደ ምድር የመመላለስ ችሎታ ያላቸው ይመስላል፡፡ ምንም እንኳ አንዳንድ ተርጓሚዎች በዘፍጥረት 6:2 ላይ የሚገኘውን «የሰው ልጆች» የሚለው ሐረግ መላእክትን እንደሚያመለክት ቢናገሩም፣ መላእክት ቁስ አካላዊ አለመሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ግልጽ አድርጎታል፡፡ ዕብራውያን 1:14 ላይ እንደ ጻፈው «የሚያገለግሉ መናፍስት» ብሎ ይጠራቸዋል፡፡ ምንም እንኳ እግዚአብሔር ለልዩ ሥራ ሲልካቸው በሥጋዊ አካል ሊገለጡ ቢችሉም፣ በአፈጣጠራቸው ግን የሚታይ ሰውነት የላቸውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እግዚአብሔር የመዋለድ፣ የማግባት ወይም

ለጋብቻ የመሰጠት ብቃት አልሰጣቸውም (ማርቆስ 12:25)::

የመላእክት ግዛት እንደ እግዚአብሔር ፍጥረታት ሰፊ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስን የምታምን ከሆንህ አገልግሎታቸውን ደግሞ ታምናለህ:: በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ለ300 ጊዜያት ያህል በመጠራት ብሉይና አዲስ ኪዳናት ሞልተውታል:: አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን በዕብራውያን 12:22 ላይ «ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት» ስለሚል፣ የመላእክት ግምታዊ አሃዝ በሚሊዮኖች ሊቆጠር እንደሚችል ያምናሉ:: ቍጥራቸውን በተመለከተ ዳዊት ወደ ሰማይ ከዋክብት አቅጣጫ ሲጓዙ የተመለከታቸውን 20,000 ብሎ መዝግቧል:: ውስን በሆነች ዕይታው በመዝሙረ ዳዊት (68)፣17 ላይ «የእግዚአብሔር ሰረገላዎች የብዙ ብዙ ሺህ ናቸው» ብሎ በመገረም ገልጾአል:: ማቲው ሄንሪ ይህን ምንባብ በማስመልከት ጠላቶቹን «የሚገጥምበት የጦርነት ጊዜ ሰረገላዎቹ፣ ለኤልያስ እንዳደረገው ለወዳጆቹ የሚልካቸው የመጓጓዣ ሰረገላዎቹ. . . የመንግሥቱ ሰረገላዎች በዚህም ክብሩንና ኃይሉን የሚያሳይባቸው ናቸው» ብለዋል:: «በሃያ ሺዎች ሳይሆን በሺዎች እንኳ ቢባዛ እጅግ በርካታ ቁጥር አላቸው::»

ዘዳግም 33:2 ላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔር ሕግጋቱን ለሙሴ በሰጠበት ጊዜ የተቀደሰ ህልውናውን ለማረጋገጥ 10,000 መላእክት በሲና ተራራ ላይ ወርደው ነበር:: በዚህም ጊዜ የመሬት መንቀጥቀጥ ተራራውን አንቀጠቀጠው:: ሙሴ በእነዚህ ሰማያዊ ፍጡራን አማካኝነት የተካሄደውን ታላቅና ድንገተኛ ትዕይንት መናገር እስኪሳነው ድረስ በመገረም ተመልክቷል:: በተጨማሪም በአዲስ ኪዳን ውስጥ በዮሐንስ ራእይ 5:11 ላይ ዮሐንስ በሰማያዊው የዙፋን ክፍል ውስጥ ቁጥራቸው አእላፋት ጊዜ አእላፋትና ሺህ ጊዜ ሺህ የሆኑ መላእክት የእግዚአብሔርን በግ ሲያገለግሉ መመልከቱን ይናገራል:: በተጨማሪም የዮሐንስ ራእይ በአርማጌዶን ጦርነት ወቅት ጌታ ኢየሱስ የመላእክትን ሠራዊት ይዞ በመገለጥ የተከማቹትን የእግዚአብሔር ጠላቶች ለመጨረሻ ጊዜ ድል እንደሚነሣቸው ይናገራል:: ጳውሎስ በ2ኛ ተሰሎንቄ 1:7 ላይ፣ «ጌታ ኢየሱስ ከሥልጣኑ መላእክት ጋር ከሰማይ በእሳት ነበልባል» እንደሚገለጥ አስረድቷል::

እስኪ አስበው! መግለጽ ከሚቻለው በላይ ኃያላን የሆኑ፣ ቍጥር ሥፍር የሌላቸው መላእክት የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሲፈጽሙ! የሚደንቀው ነገር አንድ መልአክ እንኳን ከሚገመተው በላይ ኃያል ነው:: እነዚህ ሁሉ እንደ እግዚአብሔር እጅ ተቀጥላ ሆነው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ያከናውናሉ:: በግልም ይሁን በኅብረት መላእክት እውን ናቸው:: ከታላቁ አሌክሳንደር፣ ከናፖሊዮን ወይም ከአይዘናወር የጦር ሠራዊት ይልቅ እጅግ በተሻለ መንገድ የተደራጁ ናቸው:: ከጥንት ዘመን ማለትም ወደ አዳምና ሔዋን መኖሪያ የሚወስደው መግቢያ በመልአክ ጠባቂዎች ከተዘጋበት ወቅት ጀምሮ መላእክት ህልውናቸውን በዓለም ውስጥ ገልጸዋል:: እግዚአብሔር ኪሩቤል የተባሉትን የመልአክ ጠባቂዎች በዔድን ገነት በስተምሥራቅ አስቀመጠ:: የተሰጣቸው ኃላፊነት ሰው ወደ ዔድን ገነት እንዳይመለስ ለመከልከል ብቻ ሳይሆን፣ በዘፍጥረት 3:24 ላይ እንደተጻፈው «ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን በዔድን ገነት ምሥራቅ አስቀመጠ::» እንዲህ ባይሆን ኖሮ ከሕይወት ዛፍ የተከለከለውን ፍሬ እየበላ ለዘላለም በኖረ ነበረ:: አዳም በኃጢአቱ ለዘላለም የሚኖር ቢሆን ኖሮ ይቺ ዓለም ከብዙ ጊዜ በፊት ገሃነም በሆነች ነበር:: ስለዚህ በአንድ መልኩ ሞት ለሰው ልጅ በረከት ሆኗል::

## መላእክት እግዚአብሔርን ያገለግላሉ፣ ሰዎችንም ይለውጣሉ

እስቲ በሲና ተራራ ላይ ታይቶ የማይታወቅና ሊደገም የማይችል ታሪካዊ በዓል ተመልከቱ:: እግዚአብሔር ወደ ሰው መምጣቱ እጅግ አስደናቂ ሁኔታ የመላእክት ጭፍራ መገለጥንም ሊያካትት ይችላል:: የሲናን ተራራ በሸፈነው በዚያ ጭጋጋማ ደመና ውስጥ የመልአክ መለከት ነፊ የእግዚአብሔርን ህልውና አውጇል:: ተራራው በሙሉ ሕይወት እንዳለው ሁሉ ይናወጥ ነበር:: ከሥር የነበሩትን ሰዎች ግራ የሚያጋባ መደነቅ ሞላባቸው:: መሬት ቃላት ሊገልጸው በማይችል ፍርሃት ተዋጠች:: እግዚአብሔር ወደ ተራራው ራስ ላይ ሲመጣ፣ በሺዎች በሚቆጠሩ

መላእክት ታጅቦ ነበር:: በዚያ ውሱን በሆነ ደረጃ ብቻ በተመለከተው ራእይ ዝምተኛውና ብቸኛ የሆነው መስካሪ ሙሴ እጅግ ተገርሞ ነበር:: ከሰዎች ዕይታ አንጻር እንኳ ቢሆን ይህንን ታላቅ ሰማያዊ ጉብኝት ጋዜጦች በምን ዓይነት ርእስ ለማውጣት እንደሚነሣሡ ለመገመት እጅግ ያስቸግራል:: «ሙሴም እጅግ እፈራለሁ እንቀጠቀጥማለሁ እስኪል ድረስ የሚታየው እጅግ የሚያስፈራ ነበረ» (ዕብራውያን 12:21)::

የእግዚአብሔር መገለጥ በክብር የተሞላ ነበረ:: ስለ ኃይሉ ካነሣን እንደ ፀሐይ ያበራል:: ማቲው ሄንሪ በማብራሪያ መጽሐፋቸው ውስጥ፣ «በቅርብ ርቀት የሚገኙት የሴይርና የፋራን ተራራዎች ሳይቀሩ በሲና ተራራ ላይ በተገለጠው ሰማያዊ ክብር በብርሃን ተጥለቅልቀዋልና ብርሃኑ በሌሎች ስፍራዎችም ተንጸባርቋል:: መገለጡ በታላቅ ብርሃን ስለነበረ መለኮታዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን መገለጥ ለመገንዘብ ተችሏል» ብለዋል:: [ዕንባቆም 3:3-4፤ መዝሙረ ዳዊት (18):7-9]:: ጀሩሳሌም ታርገም (Jerusalem Targum) ይህንን በተመለከተ ለየት ያለ ማብራሪያ ይሰጣል:: «እግዚአብሔር ሕግን ለመስጠት ከሰማይ በወረደ ጊዜ በሴይር ተራራ ለኤዶማውያን ሰጣቸው:: ሆኖም "*አትግደል*" የሚለውን በውስጡ በማግኘታቸው ምክንያት ለመቀበል ፈቃደኞች አልሆኑም:: ከዚያም በፋራን ተራራ ለእስማኤላውያን ቢሰጣቸውም "*አትስረቅ*" የሚለውን ውስጡ ስላገኙ ሊቀበሉት አልፈለጉም:: ከዚያም ወደ ሲና ተራራ በመምጣት ለእስራኤላውያን ሲሰጥ "*ጌታ የሚለንን ሁሉ እናደርጋለን*" አሉ» ይላል:: በእርግጥ ይሄ የ«ጀሩሳሌም ታርገም» ማብራሪያ ልብ ወለድ ቢሆንም፣ አንዳንድ አይሁዳውያን ይህንን ፍጹም የተለየና አስደናቂ ትዕይንት በመጨረሻ እንዴት እንደ ተቀበሉት በጥሩ ሁኔታ ያሳያል::

## በመላእክት ስለ ማመን አጠቃላይ ሁኔታ

የሁሉም አገሮችና ባህሎች ታሪክ ማለት ይቻላል፣ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በመላእክት ፍጥረታት የማመን ነገር ይታይበታል:: የጥንት ግብፃውያን መላእክት የሞቱትን ሰዎች በሚቀጥሉት ዘመናቸው ሊጐበኟቸው ይችላሉ ብለው ስለሚያስቡ መቃብራቸውን

ጠንካራና ከመኖሪያ ቤታቸው የተሻለ አድርገው ይሠሩት ነበር:: የእስልምና ምሁራን ለአንድ ሰው ቢያንስ ሁለት መላእክት እንደ ተመደበለትና አንደኛው መልአክ ጥሩውን ሥራውን ሲዘግብ፣ ሌላኛው ደግሞ መጥፎውን ሥራ እንደሚዘግብ ያስባሉ:: እስልምና ከመነሣቱ ከብዙ ጊዜ አስቀድሞና ገና ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ግንኙነት ሳይፈጠር፣ አንዳንድ ሃይማኖቶች የመላእክትን ህልውና አስተምረዋል:: ትውፊታዊ አገላለጹ በየትኛውም መንገድ ይሁን መመሪያችንና በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ የእኛ ፍጹም ባለሥልጣን ሊሆን የሚገባው መጽሐፍ ቅዱስ ነው::

ዛሬ አንዳንድ ግትር ሳይንቲስቶች ሊታይ የማይችል ረቂቅ የማሰብ ችሎታ መኖሩን በመቀበላቸው ሳይንስ ስለ መላእክት መኖር ያቀረበውን መላምት ማመን ጀምረዋል:: ዓለማችን ጥንቆላንና የሰይጣን ኃይላትን መኖር እንድትገነዘብ እየተደረገ ነው:: ከምንጊዜውም ይልቅ ሰዎች ስለ ጥንቆላ፣ ስለ መተትና ስለ ሰይጣን ኃይላት ለሚናገሩ መጻሕፍት ከፍተኛ ትኵረት ይሰጣሉ:: እንግዳ ክስተቶችን የሚዘግቡ ዜናዎች በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚገኙ አንባቢዎችንና የቴሌቪዥን ተመልካቾችን ስሜት በእጅጉ ይስባሉ:: ታዲያ የዘላለም ሕይወትን ግዛት የጨበጡ ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር በመተባበር በእኛ ምትክ ሥራውን የሚያሽከረክሩትን፣ የሚመሩትን፣ እውን የሆኑትንና ኃጢአት ስለሌለባቸው የመላእክት ኃይላት ሊያስተውሉ አይገባም? በመሠረቱ ስለ ቅዱሳን መላእክት በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው ስለ ሰይጣንና ስለ ተከታዮቹ ከተጠቀሰው ቊጥር ይልቃል::

## የሰማይ ኃይላት ሥልጣን

የሰይጣንና የርኵሳን መናፍስት ሥራዎች በዚህ ዘመን እያየሉ የሚመጡ ከመሰሉ፣ እጅግ አስገራሚና ታላቅ የሆነው የእግዚአብሔር መላእክት መለኮታዊ ኃይላት እንዴት እምነት ባላቸው ሰዎች አእምሮ በማይደበዝዝ ሁኔታ ሊታተም አይገባውም? የእምነት ዓይን መለኮታዊ የሆነውን የእግዚአብሔር ትዕይንታዊ የኃይልና የክብር ማረጋገጫዎች ሊመለከት ይችላል:: እግዚአብሔር ዛሬም በሥራ ላይ ነው::

ክርስቲያኖች የመላእክትን የክብር አሠራር መዘንጋት የለባቸውም:: ፀሐይ በሸማ መብራቶች ላይ እንደሚያይል ሁሉ በአጋንንታዊ የዓለም ኃይላት ላይ ለዘላለም ያይላል::

አማኝ ከሆንህ በሕይወት ልምምዶችህ ኃያላን መላእክት እንደሚከቡህ አስብ:: እነዚያ ሁኔታዎች ዳንኤል «ቅዱሳን» ብሎ የሚጠራቸውን የእነዚህ መላእክት የወዳጅነት ህልውና የሚገልጽ ነው::

መላእክት ይናገራሉ:: ህልውናቸውን ይገልጻሉ:: ስሜት ያላቸው ፍጡራን ናቸው:: መላእክት በምርጫቸው ሊታዩ የሚችሉበት ሁኔታ ሊኖር ቢችልም፣ የሥጋ ዓይኖቻችን ተራ ነገር እንደምንመለከተው እነርሱን ለማየት የተሠሩ አይደሉም:: የኒኩሊየር መስክ፣ በመዳብ በተጠቀለለ ሽቦ ውስጥ የሚያልፈውን የኤሌትሪክ ኃይል፣ የአቶምን መዋቅር ለማየት እንደማንችል ሁሉ መላእክትንም ልንመለከት አንችልም:: እውነታን የመረዳት ችሎታችን ውስን ነው:: የዱር አጋዘን የማሽተት ችሎታ የሰውን የማሽተት ችሎታ በእጅጉ ይበልጣል:: የሌሊት ወፎች፣ በሚያስገርም ሁኔታ በውስጣቸው የተገነባ የራዳር ሥርዓት አላቸው:: አንዳንድ እንስሳት በጨለማ ሳናይ የምናልፋቸውን ነገሮች ለመመልከት ይችላሉ:: ከወፍ ዝርያዎች አንዱ ስዋሎው የተባለውና ዝይ ከመለኮታዊ ነገር ጋር የሚጠጋጋ በሚመስል መንገድ የተራቀቀ የሚመሩበት ሥርዓት አላቸው:: ታዲያ ሰዎች የመላእክትን መኖር መገንዘብ ባይችሉ ለምን እንግዳ ይሆንብናል? እግዚአብሔር ለበለዓምና ለአህያው መልአኩን ሊያዩ የሚችሉበትን አዲስ እይታን ስለ ሰጣቸው ይሆን? (ዘኍልቍ 22:23፣ 31ን ተመልከት):: ይህ ልዩ የሆነ የመለየት ስሜት ባይሰጣቸው ኖሮ መልአኩ ስለ ራሳቸው ያፈለቁት የአሳባቸው ቅንጫቢ ብቻ መስሎ ይታያቸው ነበረ::

የመልአክ ሥርዓት እንዳዩ፣ እንደ ተገለገሉ፣ ኅብረት እንዳደረጉና እንደ ተሰወረባቸው በማይቋርጥ መልኩ ከዓለም ዙሪያ ምስክርነቶች ይሰጣሉ:: ስለ እግዚአብሔር የሚያስፈራ ፍርድ ያስጠነቅቃሉ፣ በርኅራኄ የተሞላ ፍቅሩንም ይገልጻሉ:: የተፈለገውን ተግባር ካከናወኑ በኋላ ይሰወራሉ:: መላእክት ለእግዚአብሔር ክብርን በመስጠት መልእክቱ ነፃ የሚያወጣና የጸና መሆኑን አጥብቀው

ያሳስባሉ እንጂ የሰዎችን ትኩረት ወደ ራሳቸው አይስቡም።

የአጋንንት አሠራርና አምልኮተ ሰይጣን በየትኛውም የዓለም ክፍሎች በመጨመር ላይ ይገኛል። ሰይጣን ከየትኛውም ጊዜ የበለጠ በመሥራት ላይ ይገኛል። መጽሐፍ ቅዱስ ጊዜው አጭር መሆኑን ስለሚገነዘብ ሥራውንም እንደሚያጣድፍ ይናገራል። በአጋንንታዊ ስልቶቹ ብዙዎቹን እውነተኛ ከሆነው እምነት በማሰናከል ድልን ሊያገኝ ይችላል። ሆኖም ቅዱሳን በሆኑና በሚያገለግሉት የመላእክት የሥልጣን ተዋረድ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ክፉ ሥራቸውን እንዳይሠሩ በመቃወም እንደሚከላከሉልን ዛሬም መናገር እንችላለን። የደኅንነት ወራሾችን ከክፉ ሰዎች ሤራ ለማዳን ብርቱዎች ናቸው። ሊሸነፉ አይችሉም።

ስለዚህ አማኞች ይህንን ተመልክታችሁ ተበራቱ። መላእክት ከምታስቡት ይልቅ ቅርብ ናቸው። ቀደም ሲል እንደ ተገነዘብነው እግዚአብሔር በመዝሙረ ዳዊት (91)፡11-12 ላይ እንደተጻፈው፣ «በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና፤ እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡሃል።»

# ሦስት

# መላእክት - ይታያሉ ወይስ አይታዩም?

ዛሬ ስለ መናፍስት ዓለምና ስለ ሥራዎቻቸው የሚቀርብ ዜና ከፍተኛ ትኩረት ይሰጠዋል:: የመለኮታዊነት አሳብ ከፍተኛ ትኩረት የመሰጠት ብቻ ሳይሆን እርግጠኛነቱም ተቀባይነትን አግኝቷል:: በዚህ ርእስ ላይ የተጻፉት ብዙዎቹ መጻሕፍት ስሜት የሚቀሰቅሱ፣ ፍጹም ግምታዊ ወይም በአንድ በሆነ ሰው ምናብ ላይ ተመሥርተው የተዘጋጁ ይመስላሉ:: መጽሐፍ ቅዱስን በፍጹምነቱ የሚቀበሉት ሰዎች ግን የመላእክትን ርእሰ ጉዳይ እንደ መላምት ወይም ከንቱ ግምት አቃልለው ሊጥሉት አይችሉም:: የሆነ ሆኖ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ሕልውናቸውን ሦስት መቶ ጊዜ ያህል ይጠቅሳል::

## ለመሆኑ መልአክ አይተህ ታውቃለህ?

ቀደም ብዬ እንደ ገለጽኩት፣ መላእክት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ብቻ ለዓይን ሊታዩ የሚችሉ የተፈጠሩ መንፈሳዊ ፍጡራን ናቸው:: ለሰዎች ሊታዩም ሊሰወሩም ይችላሉ:: የሚያስቡ፣ ስሜት ያላቸው፣ ፈቃድ ያላቸውና ስሜታቸውን መግለጽ የሚችሉ ናቸው:: እኛን የሚመለከተን ባይሆንም፣ አንዳንድ ሰዎች መላእክትን በተመለከተ ጥያቄዎች አሏቸው:: በመርፌ ጫፍ ላይ ምን ያህል መላእክቶች ሊደንሱ ይችላሉ? የሚለው የጥንት ክርክር የስንፍና አስተሳሰብ ነው:: በአንድ የስልክ መነጋገሪያ ሳጥን ወይም በቮልስዋገን መኪና ውስጥ ምን ያህል መላእክት ሊገቡ ይችላሉ ብሎ መጠየቅ ቀልባችንን አይስብም:: በሌላም አንጻር መጽሐፍ ቅዱስ መላእክት የእግዚአብሔር መልእክተኞች በመሆን መለኮታዊ ወይም የትእዛዝ ውሳኔዎችን የሚሰጡና ከእግዚአብሔር ወደ ሰዎች መልእክት የሚያመጡ መሆናቸውን በመግለጹ የሚያቀርበውን ትምህርት ልናውቅ ይገባናል:: ይህንን ተግባር ለማከናወን ብዙ ጊዜ

የሰውን ቅርጽ ይዘው አይቀርቡም:: የዕብራውያን ጸሐፊ «ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?» (1:14) ብሎ ይጠይቃል:: ሙሉ በሙሉ መንፈስ የሆነ ነገር አይታችሁ ታውቃላችሁ? እኔ አይቻለሁ ማለት አልችልም:: ሆኖም እግዚአብሔር መንፈሳዊ ሕልውናውን ለመግለጽ የተለያዩ መንገዶችን ተጠቅሟል:: ኢየሱስ በተጠመቀበት ወቅት እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ተገልጧል:: ስለዚህ እግዚአብሔር በአፈጣጠራቸው ዝቅተኛ የሆኑ መላእክትን ሕልውናውን እንዲገልጹ የመረጣቸው ስለሆነ የተለያዩ ቅርጽ እንዲይዙ ሆነው አንዳንድ ጊዜ ለሰዎች የሚገለጹበትን ሥልጣን ሰጥቷቸዋል::

## መላእክት ሊመለኩ ይገባል?

መላእክት ብዙውን ጊዜ አለመታየታቸው የአጋጣሚ ጉዳይ አይደለም:: ምንም እንኳ እግዚአብሔር በማይወሰን ጥበቡ መላእክት ሥጋዊ አካል እንዲኖራቸው እንደ ሕግ ያልፈቀደ ቢሆንም፣ ሰዎች ከፍተኛ ከበሬታ በመስጠት ሊያመልኳቸው ሲዳዱ ይታያል:: ፈጣሪን እንጂ የተፈጠረውን እንዳናመልክ መጽሐፍ ቅዱስ ያስጠነቅቀናል (ሮሜ 1:24-25):: ይህ ከስሕተት ትምህርት ያልተለየ ሲሆን፣ ለማንኛውም ዓይነት የመላእክት መገለጥ፣ ጉብኝት ወይም መባረክ መስገድ የብሉይ ኪዳንን የመጀመሪያ ትእዛዝ መተላለፍ ነው::

ያልተለመዱ መገለጦች እጅግ አስፈላጊ ሊሆኑ ቢችሉም፣ ልንሰግድ የሚገባው ሥጋ ለለበሰው፣ የሥላሴ ሁለተኛ አካል ለሆነው፣ ሁሉን ለፈጠረውና ሁሉንም በሕይወት ለሚያኖረው ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ጳውሎስ ገልጿል (ቈላስይስ 2:18):: ለመላእክት ልንጸልይ ወይም ደግሞ በራሳችን ፈቃድ ተነሣስተን ልናመልካቸው አይገባም:: የምንጸልየውና የምናመልከው አሐዱ-ሥሉስ ለሆነው አምላክ ብቻ ሊሆን ይገባል::

በተጨማሪም የሚታዩትንም ሆነ የማይታዩትን መላእክትን የሥላሴ ሦስተኛው አካልና ራሱም አምላክ ከሆነው መንፈስ ቅዱስ ጋር ልናምታታ አይገባም:: መላእክት በሰዎች ውስጥ አያድሩም::

መንፈስ ቅዱስ ግን ከለወጣቸውና ካተማቸው በኋላ በውስጣቸው ያድራል:: መንፈስ ቅዱስ ሁሉን አዋቂ፣ በሁሉ ስፍራ የሚገኝ፣ ሁሉንም ቻይ ነው:: መላእክት ከሰዎች ይልቅ ኃያላን ቢሆኑም፣ አማልክት ስላልሆኑ የሥላሴን ባሕርይ አያንጸባርቁም::

ሰዎችን ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ የሚያሳስበው መንፈስ ቅዱስ እንጂ መላእክት አይደሉም (ዮሐንስ 16:7):: ለሰዎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚገልጽና የሚያብራራ እርሱ ሲሆን፣ መላእክት እንደ አገልጋይ መናፍስት የእግዚአብሔር መልእክተኞች ሆነው ሰዎችን ያገለግላሉ (ዕብራውያን 1:14):: እኔ እስከማውቀው ድረስ መጽሐፍ ቅዱስም መንፈስ ቅዱስ ራሱን በሰው አምሳል የገለጸበት ጊዜ መኖሩን አያሳይም:: ኢየሱስ ሥጋ በለበሰበት ወቅት ይህንን አድርጓል:: ክቡር የሆነው መንፈስ ቅዱስ በአንድ ጊዜ በሁሉም ቦታ ሊገኝ የሚችል ሲሆን፣ ማንኛውም መልአክ ግን በአንድ ጊዜ ከአንድ ስፍራ በስተቀር በሌላ ቦታ ሊገኝ አይችልም:: መንፈስ ቅዱስን እንደ መንፈስ እንጂ እንደ ሥጋ ልናውቀው አንችልም:: መላእክትን ግን እንደ መንፈስ ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ጊዜ ሊታይ በሚችል ቅርጽ ልናገኛቸው እንችላለን::

በተመሳሳይ ሁኔታ መላእክትና መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ፍጹማዊ ፈቃድ ለማከናወን በዓለማችን ውስጥ በመሥራት ላይ ይገኛሉ:: የእግዚአብሔር እጅ በሥራ ላይ መሆኑን በምንገነዘብበት ወቅት እግዚአብሔር እየተጠቀመበት ያለው ወኪል ወይም መንገድ መንፈስ ቅዱስ ይሁን ወይም መላእክት በግልጽ ላናውቅ እንችል ይሆናል:: እርግጠኛ የምንሆንበት ነገር ቢኖር ግን በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስና የእግዚአብሔር ታዛዦች በሆኑት በመላእክት ሠራዊት መካከል ምንም ዓይነት ውድድር ወይም ቅራኔ አለመኖሩን ነው:: እግዚአብሔር ራሱ የራሱን ፈቃድ ለመፈጸም በበላይነት እየተቆጣጠረ ስለሆነ፣ ሐሴት ልናደርግ ይገባናል::

እግዚአብሔር የሰዎችንና የአገራትን የወደፊት ዕድል ለመቅረጽ መላእክትን ይጠቀማል:: ብዙ ጊዜ መላእክትን በመላክ ውስብስብ የሆነውን የኅብረተሰባችንን የፖለቲካና ማኅበራዊ የችግር መድረኮች እንዲሁም የሰዎችን ዕድል ለመልካም ለውጦታል:: ልብ ልንለው የሚገባን ነገር ቢኖር መላእክት በምድር ላይ የሚካሄዱትን ነገሮች በከፍተኛ ቅርበት ይከታተሉታል:: ምድራዊ ጉዳዮችን ከሰዎች

የበለጠ ያውቃሉ:: ባናያቸው እንኳ መኖራቸውንና የማያቋርጥ ትጋታቸውን ልንመሰክር ይገባናል:: እዚህ በመካከላችን መሆናቸውን እንመን:: ከእኛ ጋር ሊስቁ ወይንም ሊያለቅሱ አይችሉ ይሆናል፤ ነገር ግን በምናገኛቸው የወንጌል ስርጭት ድሎች ሁሉ ከእኛ ጋር ሐሴትን እንደሚያደርጉ እናውቃለን:: ኢየሱስ በሉቃስ ወንጌል 15:10 ላይ፣ «እንዲሁ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል» ብሎ ያስተምራል::

## መላእክት ይታያሉ ወይስ አይታዩም?

በትንቢተ ዳንኤል 6:22 ላይ፣ «አምላኬ መልአኩን ልኮ የአንበሶችን አፍ ዘጋ» የሚል እናነባለን:: በጉድጓዱ ውስጥ የዳንኤል ዓይን የመልአክን መኖር በትክክል የተገነዘበ ሲሆን፣ የአንበሳው ጉልበት ከመልአኩ ጉልበት ጋር ሲመዛዘን ምንም አልነበረም ለማለት ይቻላል:: መላእክት ለሰዎች በሚታዩበት ጊዜ በሚያስደነግጥና በሚያስገርም ክብር የተሞሉ ናቸው::

ነጭና እንደ መብረቅ የሚያብረቀርቅ ፍጥረት ምን እንደሚመስል መገመት ትችላላችሁ? የሳልቬሽን አርሚ (Salvation Army) መሥራች የነበሩት ጄኔራል ዊልያም ቡዝ የመላእክት ፍጥረታት ራእይን አስመልክተው ሲገልጹ፣ እያንዳንዱ መልአክ በቀስተ ደመና የብርሃን አክሊል የተከበበ ሲሆን፣ ብርሃኑ እጅግ ታላቅ ከመሆኑ የተነሣ ባይገታ ኖሮ የሰው ፍጥረት ዕይታውን ለመቋቋም በፍጹም አይችልም ነበር ብለዋል::

ለብዙ ማይሎች የገጠሩን አካባቢ የሚያደምቀውንና የሚያንጸባርቀውን የብርሃን ጉርፍ ማን ሊገነዘበው ይችላል? ከኢየሱስ መቃብር ላይ ድንጋዩን ያንከባለለው መልአክ ዓይንን በሚያጭበረብር ከፍተኛ ብርሃን እንደ መብረቅ ብርሃን ያበራ ነበር እንጂ ነጭ ልብስ የለበሰ ብቻ አልነበረም (ማቴዎስ 28:30):: የመቃብሩ ጠባቂዎች ተንቀጥቅጠው እንደ ሞተ ሰው ሆኑ:: በነገራችን ላይ ያ ድንጋይ አንድ ሰው ሊያነሣው ከሚችለው በላይ ብዙ እጥፍ የሚመዝን ቢሆንም፣ የመልአኩ አካላዊ ጉልበት ድንጋዩን ለማንከባለል አላገደውም::

እግዚአብሔር አካል ሰጥቶ መላእክቱ እንዲገለጡ በፈቀደላቸው

ጊዜ አብርሃም፣ ሎጥና ሌሎቹም እነርሱን ለማወቅ ችግር አልነበረባቸውም:: ለምሳሌ፣ በዘፍጥረት 32:1-2 ላይ ያዕቆብ ከመቅጽበት መላእክት እንደሆኑ መገንዘቡን ተመልከት:: «ያዕቆብም መንገዱን ሄደ፣ የእግዚአብሔር መላእክትም ተገናኙት:: ያዕቆብም ባያቸው ጊዜ:- እነዚህ የእግዚአብሔር ሠራዊት ናቸው አለ፤ የዚያንም ስፍራ ስም መሃናይም ብሎ ጠራው::»

በተጨማሪም፣ ዮሐንስና ዳንኤል መላእክት እንደ ፀሐይ ደምቀው ከሰማይ መውረዳቸውን ገልጸዋል (ዳንኤል 10:6 እና የዮሐንስ ራእይ 10:1):: ለመሆኑ የሦስቱ የዕብራውያን ልጆች የሆኑትን የሲድራቅ፣ የሚሳቅና የአብደናጎምን ታሪክ ለማንበብ የማይጓጓ ማን ነው? በሙዚቃው የአምልኮ እንቅስቃሴ ለመመላለስና ለባቢሎን ንጉሥ ለመስገድ ፈቃደኞች አልሆኑም:: ለማያምነው ዓለም የመልአክ መገኘት በተለየ ሁኔታ ውስጥ በግልጽ ለሰዎች ሊታይ እንደሚችል ተምረዋል:: ለመስገድ ፈቃደኞች ባልሆኑ ጊዜ በሕይወት እያሉ ከመቃጠል፣ ወይም ሰባት ጊዜ እጥፍ የነደደው እሳት ሽታ ልብሳቸውን እንኳ እስከማይነካ ድረስ በመልአኩ ተጠብቀዋል:: መልአኩ ካለምንም ጉዳት በነበልባሉ መካከል ወደ እነርሱ የመጣ ሲሆን፣ በዳንኤል 3:25 ላይ እንደተጻፈው ንጉሡ፣ «እነሆ፣ እኔ የተፈቱ በእሳቱም መካከል የሚመላለሱ አራት ሰዎች አያለሁ» ብሏል::

በሌላም በኩል መጽሐፍ ቅዱስ ብዙውን ጊዜ መላእክት ለሰዎች ዓይን ሊታዩ እንደማይችሉ ያመለክታል:: የሚታዩ ቢሆኑም ባይሆኑም፣ እግዚአብሔር መላእክቱን ከፊታችን እንዲሄዱ፣ አብረውን እንዲሆኑና ከኋላችን እንዲጠብቁን ያደርጋል::

ይህንን ሊገነዘቡ የሚችሉ በመላእክት መገኘት ምክንያት በእኛ ላይ የሚካሄደው ጦርነት በቍጥጥራቸው ሥር እንደሆነ የሚያውቁ አማኞች ሲሆኑ፣ ይህም ደግሞ፣ በጦርነት ውስጥ በፍጹም መተማመን ጸንተን እንድንቆም የሚያስችለን ይሆናል:: «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?» (ሮሜ 8:31)::

## መልአክ ስትመለከቱ ምን ታያላችሁ?

እግዚአብሔር የሚሠራቸው ነገሮች ከዘላለማዊነት አንጻር

የሚታሰቡ፣ ውብና በክብር የተሞሉ ናቸው:: በሕዝቅኤል 28 ላይ ስለ አንደኛው ሉሲፈር እንደተጠቀሰው፣ መላእክትን በሚመለከት የሚደረጉ አንዳንድ ገለጻዎች ከሰዎች አእምሮና ዓይን ፍጹም እንግዳ እንደሆኑ ነው የሚያመለክቱት:: በእርግጥ መላእክት ከሰዎች የእውቀት አድማስ ያለፈ የአቀራረብ ዓይነትና ውበት አላቸው:: የእግዚአብሔር ቃል መላእክት ከምን እንደ ተሠሩ አይነግረንም:: ወይም ደግሞ የማይታየውን የግዛት ዓለም በቅርቡ መመርመር የጀመረው ዘመናዊ ሳይንስም የመላእክት ተግባራትና ስለተፈጠሩበት ነገር የሚነግረን ነገር የለም::

መጽሐፍ ቅዱስ መላእክት እንደማያረጁ የሚያመለክት የሚመስል ሲሆን፣ አንድ እንኳ መታመሙን በፍጹም አይናገርም:: በኃጢአት ጥፋት ምክንያት ከሉሲፈር ጋር ከወደቁት በስተቀር በምድራችን የሚገኙት በሽታና ትርምስ አልነኳቸውም:: ቅዱሳን መላእክት በፍጹም አይሞቱም::

መጽሐፍ ቅዱስ መላእክት ጾታ አልባ መሆናቸውንም ይናገራል:: ጌታ ኢየሱስ ሰዎች «እንደ እግዚአብሔር መላእክት በሰማይ ይሆናሉ እንጂ አያገቡም አይጋቡምም» ሲል በማቴዎስ 22:30 ላይ ይናገራል:: ይህ መላእክት ከጾታዊ ግንኙነቶች እጅግ የበለጠ በሚያረካና በሚያጓጓ ኅብረት የሚደሰቱ መሆናቸውን የሚገልጽ ይመስላል:: በዚህ ሕይወት ውስጥ የሚገኘው የወሲብ ደስታ አማኞች በመንግሥተ ሰማይ የሚያገኙት ነገር ቅምሻ ብቻ ነው:: በመንግሥተ ሰማይ የምናገኘው ነገር የሰው ልጅ ከሚያውቀው ሁሉ የላቀ ነው::

«ቲዎፋኒስ»ን እንዴት እንረዳዋለን? (ይህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከማረጉ በፊት በተለያዩ ዓይነት አካላት በገሃድ የታየበትን ሁኔታ ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ሥነ መለኮታዊ ቃል ነው::) በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ክፍሎች እንደሚነግሩን የሥላሴ ሁለተኛው አካል ሲገለጽ «ጌታ» ወይም «የጌታ መልአክ» ተብሎ ይጠራ ነበረ:: በየትኛውም ቦታ ቢሆን በዘፍጥረት 18 ላይ እንደተጻፈውና ለአብርሃም እንደታዩት እንደ ሦስቱ ሰዎች ግልጽ ሆኖ የተቀመጠ የለም:: ሁለቱ ተራ መላእክት ሲሆኑ፣ መሪያቸው ግን ከጌታ ጋር ተስተካክሏል:: በዚህ ረገድ የሥላሴ ሁለተኛው አካል በሥጋ ከመገለጡ በፊት «ጌታ» ወይም «የጌታ መልአክ»

እየተባለ ሲገለጥ መቆየቱን የሚያስረዳውን ትውፊታዊ የክርስትና አተረጓጐም ለመጠራጠር የሚያስችል መሠረት የለንም («Zondervan Pictorial Encyclopedia of the Bible» «ዞንደርቫን ሥዕላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ኢንሳይክሎፒዲያ»)::

ልናስታውስ የሚገባን፣ በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ራሱ በአንዳንድ ሁኔታዎች በመልአክ ተመስሎ በሰው አካል የተገለጠ መሆኑን ነው:: ይህ በእግዚአብሔርና በመላእክቱ መካከል ያለውን ግንኙነት የበለጠ የሚያጠናክር አሳብ ነው:: ሆኖም በሁሉም ቦታዎች ማለት ይቻላል፤ መላእክቱ በአካል በሚገለጡበት ወቅት በእግዚአብሔር የተፈጠሩ መልአካዊ ፍጥረታት እንጂ እግዚአብሔር ራሱ ናቸው ማለት አይደለም::

አዎ፣ መላእክት እውን ናቸው:: በራሱ በእግዚአብሔር የተሠሩ ናቸው እንጂ የምናባችን ውጤቶች አይደሉም:: ይህንን ጉዳይ አስተውሉ! የምናያቸው ቢሆኑም ባይሆኑም እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ውስጥ ያለውን ሥራ ለማጠናቀቅ ይረዱት ዘንድ ብዛት ያላቸው የመላእክት ሠራዊት ፈጥሯል:: በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እግዚአብሔርን በግል ስናውቀው የእርሱ እንደ መሆናችን የእግዚአብሔር መላእክት እንደሚጠብቁንና እንደሚረዱን እርግጠኞች ለመሆን እንችላለን::

## አራት

# መላእክት - ከሰው እንዴት እንደሚለዩ

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሰውን «ከመላእክት ጥቂት አሳንሶ» እንደ ሠራው ይናገራል:: በሌላም በኩል ስለ መላእክት «ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?» ሲል ይናገራል (ዕብራውያን 2:5-7፤ 1:13-14):: ይህ እርስ በርሱ የሚጋጭ ይመስላል:: ሰው ዝቅ ያለ ቢሆንም፣ ካገኘው ደኅንነት የተነሣ ግን ከፍ ያለ መሆኑን እንዴት ልናስረዳ እንችላለን?

በመጀመሪያ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚናገረው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስና ስለ ሰዎች እንደሆነ ማስታወስ ይኖርብናል:: ኢየሱስ ሰው በሆነ ጊዜ «ዝቅ» ብሏል:: በየትኛውም መመዘኛ መለኮታዊ ተፈጥሮውን የተወ ባይሆንም፣ በሰብአዊነቱ ግን እንደ ሰው ከመላእክት ጥቂት አንሶ ነበር:: ክፍሉ ከኢየሱስ በተጨማሪ ስለ ሰዎችም ደግሞ ይናገራል:: እግዚአብሔር በዚህ ምድራዊ ዓለም ውስጥ ሰዎችን የፍጥረታት ሁሉ የበላይ እንዲሆኑ ቢያደርግም፣ አካላቸውንና በዚህ ምድር በሚኖሩበት ወቅት የሚቀመጡበትን ስፍራ በተመለከተ ግን ከመላእክት ጥቂት ያንሳሉ:: ጆን ካልቪን «Institutes» በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ፣ «መላእክት መለኮታዊ ስጦታዎችን የሚያከፋፍሉና የሚያስተዳድሩ፣ ስለ ደኅንነታችን የሚያስቡ፣ ስለ እኛ የሚዋጉ፣ በመንገዳችን የሚመሩንና ክፉ እንዳያጠቃን የማያቋርጥ ጥበቃ የሚያደርጉልን ናቸው» ብለዋል::

ከትንሣኤ በኋላ ሰዎች ከመላእክት ይልቅ ከፍ የሚደረጉ ስለሆነ እግዚአብሔር መላእክት ሰዎችን እንዲረዱ ያዛቸዋል:: ስለሆነም ኢየሱስ በሉቃስ 20:36 ላይ የእግዚአብሔር መንግሥት በሙላት በሚገለጥበት ወቅት እግዚአብሔር የሰውን ጊዜያዊ የሆነ ዝቅተኛ ስፍራ እንደሚለውጥ ይናገራል::

እስቲ አሁን ደግሞ እግዚአብሔር ሰዎች ከመላእክት ይለያሉ

ያለበትን ምክንያት በዝርዝር እንመርምር:: መላእክት በክብር የተሞሉ ፍጡራን ቢሆኑም፣ አዲስ ፍጥረት ከሆኑ ሰዎች በከፍተኛ ደረጃ እንደሚለያዩ የእግዚአብሔር ቃል ግልጽ ያደርጋል:: ምንም ኃጢአት ሠርተው የማያውቁ መላእክት ከኃጢአት ነፃ መውጣት ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዴት ሙሉ በሙሉ ሊገባቸው ይችላል? ኢየሱስ በቀራንዮ ላይ በመሞቱ ምክንያት ብርሃን፣ ሕይወትና ለዘላለም መኖርን ላመጣላቸው ምን ያህል ውድ እንደሚሆንባቸው እንዴት ሊገባቸው ይችላል? በአንድ ወቅት ኃጢአተኞች የነበሩ አማኞች ገና በመላእክት ላይ የሚፈርዱ መሆኑ እንግዳና አስገራሚ ነገር አይደለምን? በነገራችን ላይ እንደዚህ ዓይነቱ ፍርድ የሚሠራው ሉሲፈርን ተከትለው በወደቁት መላእክት ላይ ብቻ ነው::

ስለሆነም ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 6:3 ላይ፣ «በመላእክት እንኳ እንድንፈርድ አታውቁምን?» ብሎ ይጽፋል:: ምንም እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ ከሰዎች ይልቅ በብዙ መንገዶች የበላይነት እንዳላቸው የሚናገር ቢሆንም፣ ቅዱሳን መላእክትም እንኳ ውስንነት አለባቸው::

## እግዚአብሔር ለመላእክት «አባት» ነው?

ቅዱሳን መላእክት ኃጢአት ያልሠሩ በመሆናቸውና መዋጀት የማያስፈልጋቸው ስለሆነ እግዚአብሔርን «አባት» ብለው አይጠሩትም:: ሊዋጁ ስለማይችሉ የወደቁት መላእክትም ሁሉ እግዚአብሔርን «አባት» ብለው ሊጠሩት አይችሉም:: የኋለኛው ምክንያት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ምሥጢራዊ ከሆኑት ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው:: እግዚአብሔር ለወደቁት የሰው ልጆች የደኅንነትን መንገድ ሲያዘጋጅ፣ ለወደቁት መላእክት ግን ደኅንነትን አላዘጋጀም:: ለምን? ምናልባት በኃጢአተኞች ምክንያት ኃጠአትን እንዲፈጽሙ ከተታለሉት ከአዳምና ከሔዋን በተቃራኒው መላእክቱ የወደቁት ኃጢአተኞች ባልነበሩበት ወቅት ስለነበረ ማንም ኃጢአትን እንዲሠሩ ስላልገፋፋቸው ሊሆን ይችል ይሆናል:: ስለ-ሆነም የነበሩበት የኃጢአት ይዞታ ሊለወጥ አይችልም:: ኃጢአታቸው ይቅር ሊባልላቸው አይችልም፤ ደኅንነትንም ሊያገኙ

አይችሉም።

ብዙ የሰይጣን አምላኪዎች ሰይጣንን «አባት» ብለው ቢጠሩትም እንኳ፣ ክፉ መላእክት ግን እግዚአብሔርን «አባት» ብለው ሊጠሩት አይፈልጉም። በእግዚአብሔር ላይ እያመፁ በመሆናቸው ጉልበት ሁሉ በሚንበረከክበትና ምላስ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ በሚመሰክርበት በዚያ የፍርድ ዕለት ካልሆነ በስተቀር በገዛ ፈቃዳቸው የእርሱን ከፍተኛ ገዥነት ለመቀበል በፍጹም አይፈልጉም (ፊልጵስዩስ 2:9-10)። እግዚአብሔርን አባት ብለው ሊጠሩት የሚፈልጉት መላእክት እንኳ በላላ ትርጉም ነው ሊጠሩት የሚችሉት። እግዚአብሔር እንደ ፈጣሪነቱ የፍጥረታት ሁሉ አባት ነው። መላእክትም የተፈጠሩ ፍጥረታት መሆናቸው ስለ እግዚአብሔር በዚህ መንገድ ሊያስቡ ይችሉ ይሆናል። ይህ ስያሜ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ጠፍተው ለነበሩና ለተዋጁ ሰዎች ብቻ የተሰጠ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ሌሎች ሰዎች እንኳ ዳግም እስኪወለዱ ድረስ እግዚአብሔርን እንደ ፈጣሪያቸው እንጂ እንደ አባታቸው ሊያስቡት አይችሉም።

## መላእክት የእግዚአብሔር ወራሾች አይደሉም

ክርስቲያኖች በመዋጀታቸው ምክንያት ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አብረው ወራሾች ናቸው። ይህም በቀራንዮ ሞቱ ላይ በመሠረቱት በክርስቶስ በማመናቸው ምክንያት የራሳቸው ያደረጉት ነው (ሮሜ 8:17)። አማኞች ዘለዓለማዊና ገደብ ከሌለው ሀብታቸው ጋር ሲተዋወቁ፣ አብረው የማይወርሱት መላእክት ዳር ይዘው መቆም ይኖርባቸዋል። ሆኖም የሚያገለግሉ መናፍስት የሆኑት ቅዱሳን መላእክት የመጀመሪያውን ክብራቸውንና ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን መንፈሳዊ ግንኙነት አልጣሉም። ይህ ደግሞ በእግዚአብሔር ንጉሣዊ የፍጥረት ሥርዓት ውስጥ የክብር ስፍራ እንዳላቸው ያረጋግጥላቸዋል። በአንጻሩ ደግሞ «በሞቱና በሥቃዩ ምክንያት ከመላእክት ጥቂት ባነሰ ጊዜ» ጌታ ኢየሱስ ከወደቀው የሰው ልጅ ጋር በትስብእቱ ራሱን አመሳስሏል (ዕብራውያን 2:9)። እርሱ እኛ የሚገባንን ሞት ለመቅመስ መምረጡ መላእክት የእኛን ኃጢአተኝነትና መዋጀትን እንደማይጋሩን ያሳያል።

# መላእክት የእግዚአብሔር ጸጋ በእምነት አማካኝነት ስለሚያስገኝልን ደኅንነት ሊመሰክሩ አይችሉም

መላእክት እንኳ የማያውቁትን የደኅንነት ደስታና ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ ማራኪ ኅብረት ከቶ ማን ሊረዳው ይችላል? የአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ስብሰባ የክርስቲያን እምነት ተከታዮች በሰብአዊ ዓለም ውስጥ ከሁሉም የላቀውን የእግዚአብሔርን የፍቅር ሥርዓት ይወክላል:: አንድያ ልጁን እንዲሰጥ ከገፋፋው ፍቅሩ የሚያስደንቅ፣ የጠለቀ፣ ከፍ የሚልና የሚሰፋ ምንም ዓይነት ፍቅር የለም:: መላእክት የደኅንነትን ደስታ ያውቁታል (ሉቃስ 15:10):: አንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነውን የዘላለም ሕይወትን በሚያገኝበት ወቅት፣ መላእክት በእግዚአብሔር በግ ፊት የሰማያትን ደውሎች ሁሉ በመደወል ሐሴትን ያደርጋሉ::

ምንም እንኳ መላእክት ሰዎች ደኅንነትን በሚያገኙበት ወቅት ደስ የሚሰኙና ይህንን ያደረገውን እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ የሚያደርጉ ቢሆኑም፣ አንድ ነገር ማድረግ አይችሉም:: ይኸውም በሕይወታቸው ያልተለማመዱትን ነገር ለመመስከር አይችሉም:: ሊያደርጉ የሚችሉት ነገር ቢኖር ወደ ተዋጁት ሰዎች ልምምድ በማመልከት እግዚአብሔር ስላዳናቸው ሐሴትን ማድረግ ብቻ ነው:: ይህ ማለት በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእምነት ስለተቀበልነው እግዚአብሔር በጸጋው ስላከናወነው ደኅንነታችን እስከ ዘለዓለሙ ምስክርነት ልንሰጥ የምንችለው እኛ ሰዎች ብቻ ነን ማለት ነው:: አግብቶ የማያውቅ ሰው በጋብቻ ውስጥ ያለውን አስገራሚ ግንኙነት በሙላት ሊያደንቅ አይችልም:: እናቱ ወይም አባቱ ያልሞቱበት ሰው ደግሞ ሞት ምን እንደሆነ ሊገባው አይችልም:: በተመሳሳይ ሁኔታም፣ መላእክት ደኅንነትን እንደተለማመዱት ሰዎች ለመመስከር አይቻላቸውም::

# መላእክት በሰው ልብ ውስጥ ስለሚያድረው እግዚአብሔር የልምምድ እውቀት የላቸውም

መንፈስ ቅዱስ በተዋጁት ሰዎች ልብ ውስጥ እንደሚያድር ሁሉ በመላእክት ውስጥ እንደሚያድር የሚያመለክት አሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጠቀሰም። አማኞች ኢየሱስ ክርስቶስን በሚቀበሉበት ወቅት በመንፈስ ቅዱስ ይታተማሉ። መላእክት ግን በኃጢአት ወድቀው ስለማያውቁና ደኅንነት ስለማያስፈልጋቸው እንዲህ ዓይነቱ መታተም አያስፈልጋቸውም።

ለዚህ ልዩነት ሌላም ምክንያት አለ። በምድር ላይ የተዋጁት ሰዎች ገና አልከበሩም። እግዚአብሔር ፍጹማን ናችሁ ብሎ ሕይወትን ከሰጣቸው በኋላ፣ እዚሁ በምድር ላይ ሰውነታቸውን የመቀደሱን ሂደት ይቀጥላል። ስለሆነም መንፈስ ቅዱስ አማኞች በምድር ላይ በሚኖሩበት ወቅት በልባቸው ውስጥ በማደር ልዩ አገልግሎቱን ያከናውናል። ይህም ተግባር መላእክት ሊያከናውኑት የማይችሉት ነው። እግዚአብሔር አብ ልጁን ኢየሱስን እንዲሞት ልኮታል። ኢየሱስ በእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ውስጥ የራሱ ድርሻ የሆነውን ልዩ አገልግሎት አከናውኗል። እንደዚሁም፣ መንፈስ ቅዱስ ከልጁ የተለየ የሥራ ድርሻ አለው። በአብና በወልድ የተላከው መንፈስ ቅዱስ አማኞችን የመምራትና አቅጣጫ የማሳየት ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔርን እየመሰሉ እንዲሄዱና እንደ ክርስቶስ የተቀደሱ እንዲሆኑ በማድረግ የጸጋን ሥራ ያከናውናል። መላእክት ይህንን የመቀደስ ኃይል ሊሰጡን አይችሉም።

በተጨማሪም፣ መላእክት አማኞች በሚፈልጉበት መልኩ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት አያስፈልጋቸውም። መላእክት በአፈጣጠራቸው፣ በማያቋርጥ መታዘዛቸውና ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት ሳቢያ ቀድሞውኑ ሥልጣን ታድሏቸዋል። በኃጢአት አልረከሱም። ሰዎች ግን ፍጹማን ስላልሆኑ መንፈስ ቅዱስ ብቻ የሚሰጠውን እገዛ ማግኘት ይኖርባቸዋል። አንድ ቀን አሁን መላእክት እንደሆኑት ሁሉ ፍጹማን የምንሆንበት ጊዜ ይመጣል።

# መላእክት አያገቡም አይዋለዱም

ቀደም ሲል መላእክት እንደማያገቡ ገልጫለሁ:: በማቴዎስ 22:30 ላይ፣ ኢየሱስ፣ «በትንሣኤ (ሰዎች) እንደ እግዚአብሔር መላእክት ይሆናሉ እንጂ አያገቡም አይጋቡምም» ብሏል:: በዚህ የተነሣ የመላእክት ቍጥር በጊዜ ሂደት ውስጥ አይለዋወጥም ወደሚል ድምዳሜ ለመምጣት እንችላለን:: ታዛዥ የሆኑት መላእክት ካለመዋለዳቸውም በላይ ከቶ አይሞቱምና:: የወደቁት መላእክት እግዚአብሔር ጉዳያቸውን ሲያጠናቅቅ የመጨረሻውን ፍርድ ይቀበላሉ:: እርግጠኞች ለመሆን ባንችልም፣ ሰይጣን በምሥጢር በፈጠረው ላይ ባመፀበት ወቅት ሢሦ (አንድ ሦስተኛ) የሚሆኑ መላእክት እንደ ተባበሩት አንዳንድ ምሁራን ይገምታሉ:: ያም ቢሆን የዕብራውያን መጽሐፍ መላእክት ከምናባችን የዘለቁ እጅግ ብዙ ሠራዊት መሆናቸውን ይናገራል:: ክፉ አጋንንት ሆነው የሚገኙት ሢሦዎቹ ምናልባት በመቶ ሺዎች ሊቆጠሩ ይችሉ ይሆናል::

መላእክት በጋብቻ ጉዳይ ከሰዎች እንደሚለዩ ሁሉ፣ በሌሎች መንገዶችም ይለያሉ:: በየትኛውም የእግዚአብሔር ቃል ውስጥ መላእክት ለመኖር ይችሉ ዘንድ መብላት ይኖርባቸዋል የሚል አልተጻፈም:: ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ መላእክት በተወሰኑ ሁኔታዎች ሰው ሆነው በመምጣት በትክክል የተመገቡ መሆኑን ይናገራል:: ዳዊት የእስራኤል ልጆች በበረሃ የበሉት መና የመላእክት ምግብ እንደሆነ ገልጿል:: በመዝሙረ ዳዊት (78):25 ላይ አሳፍ፣ «የመላእክትንም እንጀራ ሰው በላ» ብሏል:: ኤልያስ በቀርሜሎስ ተራራ በበኣል ካህናት ላይ ታላቅ ድል ከተጐናጸፈ በኋላ የደረሰበትን ሁኔታ በቸልታ ልናልፍ አንችልም:: ምክንያቱም ኤልዛቤል ሕይወቱን ከአደጋ ላይ ስለጣለችው ከእግዚአብሔር እርዳታን ፈልጓል:: ስለሆነም የእግዚአብሔር መልአክ ወደ ተዳከመውና ተስፋ ወደ ቆረጠው ነቢይ መጥቶ የሚበላውንና የሚጠጣውን በፊቱ አቀረበለት:: ሁለት ጊዜ ከበላ በኋላም መንገዱን እንዲቀጥል ተደረገ:: የበላውም ምግብ 40 ቀንና 40 ሌሊት አኖረው (1ኛ ነገሥት 19:5):: አንዳንድ ሰዎች ኤልያስ የመላእክትን ምግብ በልቷል የሚሉት ያለ ምክንያት አይደለም::

አብርሃም በመምሬ ሜዳ በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ ሦስት መላእክት ጉበኙት:: ከእነዚህም መላእክት አንዱ ጌታ ኢየሱስ ሳይሆን አይቀርም (ዘፍጥረት 18:1-2):: እነዚህ ሰማያዊ ፍጥረታት በእንግድነት ተጋብዘው ያቀረበላቸውን ነገር በሉ ጠጡም:: ወዲያውም እግዚአብሔር ሰዶምንና ገሞራን ለማጥፋት በወሰነ ጊዜ ሁለት መላእክት በእምነታቸው የደከሙትን ሎጥንና ቤተሰቡን ለማዳን መጡ:: እንደገናም ሎጥ ግብዣ አድርጎላቸው የተጋገረ ቂጣን ጨምሮ ምግብን በሉ (ዘፍጥረት 19)::

ከትንሣኤው በኋላ ጌታ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር መብላቱ አስገራሚ ነገር ነው:: የሉቃስ ዘገባ፣ ደቀ መዛሙርቱ «ከተጠበሰ ዓሣ አንድ ቁራጭ፣ ከማር ወለላም ሰጡት ተቀብሎም በፊታቸው በላ» ይላል (ሉቃስ 24:42-43)::

## የመላእክት እውቀት

መላእክት በእውቀታቸው ከሰው ልጆች ይልቃሉ:: ንጉሥ ዳዊት አቤሴሎምን ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለስ ግፊት እየተደረገበት በነበረበት ወቅት ኢዮአብ ከቴቁሔ የሆነች አንዲት ሴት ንጉሡን እንድታነጋግር ጠየቃት:: እርሷም «የእግዚአብሔር መልአክ ጠቢብ እንደሆነ፣ አንተም ጌታዬ በምድር ላይ ያለውን ነገር ሁሉ ታውቅ ዘንድ ጠቢብ ነህ አለች» (2ኛ ሳሙኤል 14:20):: ስለሆነም መላእክት ሰዎች የሌላቸው እውቀት አላቸው:: ነገር ግን እውቀታቸው ምንም ያህል ሰፊ ቢሆንም፣ ሁሉን አዋቂ እንዳልሆኑ እርግጠኛ መሆን እንችላለን:: እንደ እግዚአብሔር ስላልሆኑ ሁሉንም ነገር አያውቁም:: ጌታ ኢየሱስ ስለ ዳግም ምጽአት በሚናገርበት ወቅት መላእክት የተገደበ እውቀት እንዳላቸው መስክሯል:: በማርቆስ 13:32 ላይ «ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያች ሰዓት ግን የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን ከአባት በቀር የሚያውቅ የለም» ብሏል::

መላእክት ስለ ራሳችን የማናውቀውን ነገር ሊያውቁ ይችሉ ይሆናል:: የሚያገለግሉ መናፍስት እንደ መሆናቸው፣ እውቀታቸውን ለእኛ መልካም ነገርን ለማድረግ እንጂ፣ ለክፉ

ዓላማ አያውሉትም:: ብዙ ሰዎች ምሥጢር ለመጠበቅ በማይታመኑበት በዚህ ዘመን መላእክት ከፍተኛ እውቀታቸውን እኛን ለመጉዳት እንደማያውሉት ማወቁ ያጽናናናል:: እውቀታቸውን ለእኛ መልካም ነገርን ለማድረግ ይጠቀሙበታል::

## የመላእክት ኃይል

መላእክት ከሰዎች የላቀ ኃይል ያላቸው ቢሆንም፣ ሁሉን ቻይ ግን አይደሉም:: በ2ኛ ተሰሎንቄ 1:7 ጳውሎስ እግዚአብሔር ኃያላን መላእክት እንዳሉት ገልጿል:: በዚህ ስፍራ «ኃያል» ተብሎ ከተተረጐመው ቃል «ድማሚት» የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል እናገኛለን:: በቊሳዊው ኃይል አንጻር፣ መላእክት የእግዚአብሔር ድማሚቶች ናቸው:: በ2ኛ ጴጥሮስ ላይ፣ «ዳሩ ግን መላእክት በኃይልና በብርታት ከእነርሱ ይልቅ ምንም ቢበልጡ በጌታ ፊት በእነርሱ ላይ የስድብን ፍርድ አያመጡም» ይላል (2ኛ ጴጥሮስ 2:11):: በዚህ ስፍራ የጴጥሮስ ምስክርነት ጳውሎስ የተናገረውን ያጠናክረዋል:: ልንገነዘብ የሚገባን ደግሞ በሙሴ ዘመን በግብፅ አገር በኵር ሆነው የተወለዱትን ሁሉ የገደለውም ሆነ ለዳንኤል የአንበሶችን አፍ የዘጋለት አንድ መልአክ ብቻ መሆኑን ነው::

ዳዊት በመዝሙር (103):20 ላይ የእግዚአብሔር መላእክት «ብርቱዎችና ኃያላን» መሆናቸውን ይናገራል:: ያ ኃያልነት በዚህ የፍጻሜ ዘመን ከሚታየው አስደናቂ ክንውን የበለጠ በየትኛውም የእግዚአብሔር ቃል ውስጥ አልተገለጸም:: የእግዚአብሔር ቃል የአርማጌዶንን ሥርዓት ተከትሎ በሰይጣን ላይ ምን እንደሚደርስ በግልጽ ያሳያል:: በዚያን ጊዜ ታስሮ ወደ ጥልቅ ጉድጓድ ይጣላል:: ነገር ግን ኃይሉና የተንኰል ሤራዎቹ በግልጽ የሚታወቁለትን ሰይጣን ከራሱ ከእግዚአብሔር በስተቀር ምን ዓይነት ኃይል ይሆን የሚያስረው? መጽሐፍ ቅዱስ አንድ መልአክ ጠንካራ ሰንሰለት ይዞ እንደሚመጣና ሰይጣንን እንደሚያስር ይናገራል:: ከእግዚአብሔር ኃያላን መላእክት የአንዱ ኃይል ምንኛ ታላቅ ነው::

# መላእክት ይዘምራሉ?

የመላእክትን የኅብረት ዝማሬ በተመለከተ የተለያዩ ግምታዊ አሳቦች ሲሰነዘሩ ቆይተዋል። የእግዚአብሔር ቃል ስለ መዘመራቸው በግልጽ ባይናገርም፣ መላእክት ሊዘምሩ እንደሚችሉና እንደሚዘምሩም እናስባለን። ዊልያም ሼክስፒር በሐምሌት ውስጥ መላእክት እንደሚዘምሩ ሲያመለክት፣ «የተከበረ ሰው ልብ አሁን ተሰበረ፤ ሰላም ይደሩ የተወደዱ ልዑል ሆይ። የሚበርሩ መላእክት በዕረፍትዎ ሆነው ሳሉ ይዘምሩልዎት» ብሏል።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች መላእክት አይዘምሩም ብለው ይከራከራሉ። ይህ የሚታመን አይመስልም። መላእክት ምስጋናን የማቅረብ የላቀ ችሎታ ያላቸው ሲሆን፣ ሙዚቃቸውም ክብር ሁሉ ለሚገባው ለእግዚአብሔር ከዘመናት በፊት ውዳሴን የሚያቀርቡለት ዋና መሣሪያቸው ነበር። መዝሙር ዓለም አቀፍ ቋንቋ ነው። ዮሐንስ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ መላእክት ስለ ሰማያዊው በግ ዕፁብ ድንቅ በሆነ ሙዚቃ ታጅበው ምስጋናቸውን ሲያቀርቡ የተመለከተ ይመስላል (የዮሐንስ ራእይ 5:11-12)። የመላእክት የዝማሬ ቡድን (ኳዩር) ለእግዚአብሔር ክብርና ለተዋጁት ከፍተኛ ደስታ ሲሉ ለዘለዓለም እንደሚዘምሩ አምናለሁ።

ምንም እንኳ በከፊል ግምታዊ ሊሆን ቢችልም፣ መላእክት ሰማያዊና መለኮታዊ ሙዚቃን የመሥራት ችሎታ እንዳላቸው አምናለሁ። ብዙ በመሞት ላይ የነበሩ አማኞች ሰማያዊ ሙዚቃን ለማዳመጣቸው ምስክርነትን ሰጥተዋል። ብዙ የቅርብ ጓደኞቼ ዜማን በአግባቡ መያዝ ስለማልችል ይቀልዱብኛል። በጉባኤ ላይ ከሰዎች አጠገብ ሆኜ የምዘምር ከሆነ ብዙ ጊዜ ከቅኝት እወጣባቸዋለሁ። ራሴ ላደርገው እንኳ ባልችልም ከብዙ ዓመታት የማዳመጥ ልምዴ የተነሣ ጥሩ ሙዚቃን በመስማት ብቻ አውቀዋለሁ። በአንድ ወቅት የማልወደውን ረቀቅ ያለ ኦፔራም ሆነ ሮክ ሙዚቃን ለመረዳትና ለማድነቅ ከፍተኛ ጥረት አደርግ ነበር። የሰማያዊውን ሙዚቃ ከመረዳታችን በፊት ከምድራዊው የሙዚቃ ጽንሰ አሳብ በእጅጉ ማለፍ የሚኖርብን ይመስለኛል። ከሰማያዊ ሙዚቃ ጋር ሲነጻጸሩ ምድራዊ ሙዚቃዎች እጅግ ዝቅተኛ

መሆናቸውን እንረዳለን::

መጽሐፍ ቅዱስ ዝማሬን ስላቀረቡ ብዙ ሰዎች ይነግረናል:: ሙሴ (ዘጸአት 15:1)፣ ማርያም (ዘጸአት 15:20፣21)፣ ዳዊት (በመዝሙረ ዳዊት)፣ እና ሌሎችም:: በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በቤተ መቅደሱ ውስጥ ሆነው ጌታን እያመሰገኑ በዝማሬ አምልከውታል (2ኛ ዜና 5:12):: በሺዎች የሚቆጠሩ መዘምራን በቃል ኪዳን ታቦቱ ፊት ይዘምሩ ነበር (1ኛ ዜና 15:27-28):: ሁላችንም መዝሙረ ዳዊትን የመጽሐፍ ቅዱስ የዝማሬ መጽሐፍ አድርገን እንወስደዋለን::

የአዲስ ኪዳን አማኞች ደግሞ በታላቅ ደስታ ዘምረዋል:: ምንም እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ ባይነግረንም፣ በከፍተኛ የተፈጥሮ ሥርዓት ውስጥ የሚገኙት መላእክት ለእግዚአብሔርና ለበጉ የሚዘምሩት በተስተካከለና እጅግ በተቀነባበረ ድምፅ ነው:: ጳውሎስ የመላእክት ቋንቋና የሰው ቋንቋ እንዳለ ይነግረናል (1ኛ ቆሮንቶስ 13:1):: መላእክት መለኮታዊ ቋንቋ ያላቸው ሲሆን፣ የፈጠራቸውን እግዚአብሔርን እንደሚገባ የሚያከብሩበትን ሙዚቃ ይጫወታሉ:: በሰማይ የመለኮታዊውን ዓለም ቋንቋና ሙዚቃ እንደምንማር አምናለሁ:: «ቅዱስ ቅዱስ እያሉ ነው መላእክት የሚዘምሩት» በሚለው በጆንሰን ኦትማን፣ በጄ. ስዊኒ በተደረሰው በአራተኛው ቍጥር መዝሙር ውስጥ ይህን አሳብ እናገኛለን::

*ስለዚህ ምንም እንኳ መልአክ ባልሆንም፣*

*ግን እዚያ ማዶ የሚገኘውን*

*መላእክት ሊካፈሉ የማይችሉትን*

*የተባረከ የመዘምራን ቡድን እንድቀላቀል አውቃለሁ፤*

*እኔን ከኃጢአት ለማዳን በጨለማው ቀራንዮ ላይ ሞቶ*

*የእኔን በደለኛነት በነፃ ይቅር ላለኝ*

*ለመድኃኒቴ እዘምራለሁ::*

# መላእክት በዙፋኑ ፊት ያመልካሉ

መላእክት ለእግዚአብሔር በግ ምስጋናና ክብር የሚሰጡ መሆናቸው አያጠያይቅም። ሆኖም መላእክት ጊዜያቸውን ሁሉ በሰማይ አያሳልፉትም። በአንድ ጊዜ በሁሉም ቦታ ስለማይገኙ፣ በተወሰነ ጊዜ በአንድ ስፍራ ብቻ ይገኛሉ። እንደ እግዚአብሔር መልእክተኞች፣ በዓለም ዙሪያ በመዞር የእግዚአብሔርን መመሪያዎች ያስፈጽማሉ። ታዲያ እዚህ በአገልግሎት ላይ ተጠምደው በሚገኙበት ጊዜ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ለመቆማቸው ግልጽ አይደለምን? ሆኖም መላእክት በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት በሚቆሙበት ጊዜ በእርግጥ ፈጣሪያቸውን ያመልኩታል ያከብሩታልም።

መላእክት የምድር አገልግሎታቸውን የሚፈጽሙበትን የወደፊት ጊዜ እንጠብቃለን። በዚያን ጊዜ ከተዋጁት ሁሉ ጋር በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት በሰማይ ይሰበሰባሉ። በዚያ ምስጋናቸውን ያቀርባሉ፤ ዝማሬያቸውንም ይዘምራሉ። ኢየሱስ በተሰቀለ ጊዜ ፊታቸውን ሸፍነው በዝምታ ተውጠው የነበሩት መላእክት በዚያን ዕለት መንግሥቱ ለመጣችለትና ሥራውን ለፈጸመው ለበጉ ክብርን ይሰጣሉ። ምናልባትም የተዋጁት የእግዚአብሔር ልጆች ደኅንነታቸውን በተመለከተ የራሳቸውን ምስጋና በሚያቀርቡበት ወቅት መላእክት ጸጥ ብለው ያዳምጡ ይሆናል። «ቅዱስ ቅዱስ እያሉ ነው መላእክት የሚዘምሩት» በተሰኘውና በ3ኛው ቁጥር ላይ በሚገኘው መዝሙር ላይ

*ልክ እንደ ብዙ ፈሳሽ ውኃ*

*በደሙ በታጠበው በዚያ ሐሴት ባደረገ ሕዝብ*

*ያንን ዝማሬ መካፈል ስለማይችሉ*

*መላእክት ቆመው ያዳምጣሉ*

ተብሎ በጸሐፊው የተገለጸው እውነት ይሆናል።

ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጆችም መላእክትን ለመስማት ጸጥ ይላሉ። እነርሱ የሚዘምሩበት ከእኛ የተለየ ምክንያት አላቸው። ራሳቸውን ለኃያሉ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ሰጥተዋል።

የእግዚአብሔር መንግሥትም እንድትመጣ የበኩላቸውን ድርሻ ተወጥተዋል:: በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ የእግዚአብሔርን ልጆች አግዘዋቸዋል:: ስለሆነም የእነርሱ የድል ጩኸትና ዝማሬ ይሆናል:: የተወከሉበት ጉዳይ በድል ተጠናቅቋል፤ የተዋጉት ውጊያ በድል ተደምድሟል፤ የተጋፈጡት ጠላት ድል ተመትቷል፤ የወደቁትና አብረዋቸው የነበሩት መላእክት ከዚህ በኋላ አያበሳጯቸውም:: ስለሆነም መላእክት የሚዘምሩት የተለየ መዝሙር ነው:: መላእክትና የተዋጀነው እኛ መጨረሻ በሌለው ዘላለማዊነት ውስጥ ሆነን ለእግዚአብሔር የበለጠ ክብርና ውዳሴ ሊሰጥ የሚችለው ማን እንደሆነ ለማየት የምንወዳደር ይመስለኛል::

ያ ዘላለማዊ ተስፋ በልብህ ውስጥ አሁን አለ? ያለምንም ጥርጥር አንድ ቀን ከመላእክት ጋር የምስጋናን መዝሙር ለእግዚአብሔር እንደምትዘምር በእርግጠኝነት ታውቃለህ? ይህንን እርግጠኛ ካልሆንህ ዛሬ ለጌታ ለኢየሱስ ራስህን አስረክብ:: ካለ ጌታ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር የተለየህና የዘላለም ተስፋ የሌለህ ነህ:: ኃጢአትህ ይቅር ሊባልልህ፣ በእግዚአብሔር ኃይል ልትታደስና ልትነጻ ያስፈልግሃል:: ይህ ሊሆን የሚችለው ግን ለጌታ ለኢየሱስ ሕይወትህን ስትሰጠውና እንደ ግል አዳኝህና እንደ አምላክህ ስትደገፍበት ብቻ ነው:: ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቶ ኃጢአትህን ሊወስድ ነው የመጣው:: አንተ መሞት ሲገባህ እርሱ በአንተ ምትክ ሞቷል:: «ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና» (1ኛ ጴጥሮስ 3:18):: አሁን እንኳ አምነህ በምታደርገው ትንሽ ጸሎት ከመላእክትና በዘመናት ሁሉ ከኖሩ በሚሊዮኖች ከሚቆጠሩ አማኞች ጋር ለእግዚአብሔር የምስጋናን ዝማሬ በሰማይ እንደምታቀርብ ለማወቅ ትችላለህ:: ዛሬውኑ የእምነት እርምጃን ተራመድ::

# <u>አምስት</u>

# የመላእክት አደረጃጀት

ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ መላእክት በምናጠናበት ጊዜ በመላእክት መካከል ስላለው የሥልጣን ተዋረድ ግንዛቤ ማግኘታችን የግድ ይሆናል:: መላእክት ከሥልጣንና ከክብር አንጻር የተደራጁ መሆናቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንረዳለን::

ምንም እንኳ አንዳንዶች የመለኮታዊ ኃይላትን የደረጃ ተዋረድ እንደ መላምት ቢያዩትም፣ የሚከተለውን ቅደም ተከተል የሚይዝ ይመስላል:- ሊቀ መላእክት፣ መላእክት፣ ሱራፌል፣ ኪሩቤል፣ አለቅነት፣ ሥልጣናት፣ ዙፋናት፣ ኃይላትና ግዛት (ቈላስይስ 1:16፤ ሮሜ 8:38)::

የመካከለኛው ክፍለ ዘመን የሥነ መለኮት ምሁራን የመላእክትን ደረጃዎች በአሥር ከፍለዋቸው ነበር:: ሆኖም አንዳንድ ሰዎች እንደ ጌትነት፣ ሥልጣናት፣ አለቅነት፣ ዙፋናት፣ ኃይላትና ግዛት ያሉት ደረጃዎች ስለ ሰው ልጆችና ሰብአዊ ተቋማት የሚናገሩ ይሆኑ? ብለው ጠይቀዋል:: ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ቈላስይስ 1:16ን መረዳት ይኖርብናል:: ጳውሎስ በዓይን ስለሚታዩና ስለማይታዩ ነገሮች ፍጥረት ነው የሚናገረው:: ይህንን ጥቅስ አስመልክተው ማቲው ሄነሪ የተባሉ ሰው ሲናገሩ፣ ጌታ ኢየሱስ «በሰማያት ውስጥ ከፍ ብሎ ያለውን መልአክ ቢሆን ወይም በምድር ላይ የሚገኙትን ሰዎች የፈጠራቸው ከምንም ነው:: ዓለምን ማለትም በላይ ያለውንና በታች የሚገኘውን ዓለም ፈጥሮ በሁለቱም ነዋሪዎችን አስቀመጠበት:: ... እዚህ ላይ እርሱ (ጳውሎስ) የተለያዩ የመላእክት ሥርዓቶች እንዳሉ ነው የሚናገረው:: ዙፋናት ቢሆኑ፣ ወይም ግዛት ወይም ኃይላት ወይም ሥልጣናት ስለ የተለያዩ ችሎታዎች፣ ቢሮዎችና ኃላፊነቶች የሚያሳይ ይመስላል::» የመላእክትን የደረጃ ተዋረድ የሚገልጽ ማንኛውም ዝርዝር የተወሰኑት ሥልጣን ሲኖራቸው፣ ሌሎቹ ደግሞ

ላይኖራቸው ይችላል:: የተሳሳተ ሊሆን ቢችልም፣ በሥልጣን እንደሚለያዩ እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን:: ግትር ለመሆን ባልፈልግም፣ የተለያዩ የመላእክት የሥልጣን ደረጃዎች መኖራቸውንና በቈላስይስ ውስጥ የተጻፉት ዝርዝሮች እነዚህን ለማያዊ ፍጥረቶች እንደሚያመለክቱ አምናለሁ:: እስቲ አራቱቹን እንመልከታቸው::

## ሊቀ መላእክት

የእግዚአብሔር ቃል እንደ መላእክት አለቃ የጠቀሰው ሚካኤልን ብቻ ቢሆንም (ይሁዳ 9)፣ ሉሲፈር ከመውደቁ በፊት ከሚካኤል እኩል ወይም የበላይ በሆነ ደረጃ ሊቀ መላእክት ነበረ:: ለማመን የሚያስችሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቶች አሉን:: «አለቃ» የሚለው የመነሻ ቃል የበላይ፣ ዋና ወይም ታላቅ መልአክ የሚለውን ይመስላል:: ስለሆነም አሁን ሚካኤል የመላእክት ሁሉ የበላይ የሆነ መልአክና በሥልጣን ደረጃው የመጀመሪያ መሆኑ የታወቀለት የሰማይ ልዑል ነው:: በሌላ አነጋገር በእግዚአብሔር የዓለማት አስተዳደር ውስጥ የጠቅላይ ሚኒስትርነት ማዕረግ ያለውና ለእግዚአብሔር ፍርድም «የመልአክ አስተዳዳሪ» ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ የመልአክ አለቃ ብቻ እንጂ የመላእክት አለቆች እንዳሉ ስለማይገልጽ፣ እርሱ ብቸኛ አዛዥ መሆን ይኖርበታል:: የስሙ ትርጉምም «እንደ ጌታ ያለ ማን አለ?» ማለት ነው::

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሚካኤል በቀዳሚነት የእስራኤል መልአክ ነበር:: ስለሆነም እግዚአብሔር እንደተመረጠው ሕዝብ ልዑል አድርጎ ስለ ሚካኤል ይናገራል:: «በዚያም ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ» (ዳንኤል 12:1):: በተለይም በየትኛውም ስፍራ የሚገኘውን የእግዚአብሔር ሕዝብ ይጠብቃል፣ ይከላከልላቸውማል::

በተጨማሪም በዳንኤል፣ «አለቃችሁ ሚካኤል» ተብሎ ተጠቅሷል (ዳንኤል 10:21):: እርሱ የእግዚአብሔር የሕግና የፍርድ መልእክተኛ ነው:: በዚህ ረገድ በዮሐንስ ራእይ 12:7-12 እንደተጻፈው፣ ሰይጣንን፣ ታላቁን ዘንዶና አጋንንቶችን የሚዋጋውን

ጦር የሚመራ መሆኑ ተጠቅሷል። ሚካኤልና መላእክቱ በመጨረሻው ዘመን በሚካሄደው ውጊያ እጅግ ታላቅ የሆነ ትግል ውስጥ በመግባት የሰይጣንንና የጨለማ ኃይላትን ሁሉ ድል መመታት ያረጋግጣሉ። ሚካኤል በጦርነቱ ውስጥ ድል አድራጊ እንደሚሆን የእግዚአብሔር ቃል አስቀድሞ ይናገራል። ገሃነም ይንቀጠቀጣል፤ በሰማይ ሐሴት ይሆናል።

ሚካኤል ሉሲፈርንና የወደቁ መላእክትን ከሰማይ እንደ ጣላቸውና ዛሬ ሚካኤል ከሰይጣንና ከክፉ መላእክቱ ጋር ታግሉ ኃይላቸውን በመደምሰስ የመጨረሻውን የድል ተስፋ ለእግዚአብሔር ሕዝብ እንደሚሰጥ የሚያመለክት አሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ዘንድ አለ። የመላእክት አለቃ የሆነው ሚካኤል በዳግም ምጽአቱ ወቅት ኢየሱስን በማጀብ የሚጮኽ ይሆናል። ምንም ተወዳዳሪ የሌለውንና ደስ የሚያሰኘውን የኢየሱስ ክርስቶስን መመለስ ከማወጁም በላይ፣ በክርስቶስ ሆነው ለሞቱትና ትንሣኤያቸውን ለሚጠባበቁ ሁሉ የሕይወትን ቃል ይናገራል። «ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፣ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ» (1ኛ ተሰሎንቄ 4:16)።

## መልአኩ ገብርኤል

በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ከተጠቀሱት ዋነኛ መላእክት መካከል አንዱ ገብርኤል ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ «ገብርኤል» ማለት «የእግዚአብሔር ጀግና» ወይም «ኃያሉ» ወይም «እግዚአብሔር ታላቅ ነው» ማለት ነው። የእግዚአብሔር ቃል ብዙ ጊዜ «የያህዌ መልእክተኛ» ወይም «የጌታ መልእክተኛ» ብሎ ይጠራዋል። ቢሆንም ብዙዎች እንደሚያስቡት ወይንም ገጣሚው ጆን ሚልተን ካሉት በተቃራኒ፣ የመላእክት አለቃ ብሎ አይጠራውም። ነገር ግን ከሚካኤል ይልቅ የገብርኤል ሥራ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል።

# የገብርኤል አገልግሎት

ገብርኤል በዋናነት የእግዚአብሔር የምሕረትና የተስፋ ቃል መልእክተኛ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለአራት ጊዜያት ያህል መልካም ዜናን ሲያበስር እንመለከታለን (ዳንኤል 8:16፤ 9:21፤ ሉቃስ 1:19፣ 26)። የብር መለከት ስለ መንፋቱ ጉዳይ እንጠይቅ ይሆናል። ይህ ከሀገረሰብ የሙዚቃ አስተሳሰብ የመነጨና በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በተዘዋዋሪ መንገድ ብቻ ድጋፍ የተሰጠው ጉዳይ ነው። ሆኖም የእግዚአብሔርን ዕቅድ፣ ዓላማና ፍርድ ለማሳወቅ ገብርኤል የሚያስተላልፋቸው አወጃዎች ትልቅ ጠቀሜታ አላቸው።

በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ገብርኤልን መጀመሪያ የምናገኘው በዳንኤል 8:15፣ 16 ነው። በዚህ ክፍል እግዚአብሔር ስለ «መጨረሻው ዘመን» ያለውን ራእይ ያውጃል። እግዚአብሔር በታሪክ ዕቅዱን የሚገልጽ መልእክትን ከሰማይ እንዲያስተላልፍ ሾሞታል። በቍጥር 17 ላይ ገብርኤል፣ «የሰው ልጅ ሆይ፣ ራእዩ ለፍጻሜ ዘመን እንደ ሆነ አስተውል አለኝ» ይላል።

ዳንኤል በጸሎት ላይ እያለ የገብርኤልን ሁለተኛ መገለጥ መዝግቦታል። «ገናም በጸሎት ስናገር አስቀድሜ በራእይ አይቼው የነበረው ሰው ገብርኤል እነሆ እየበረረ መጣ፣ በማታም መሥዋዕት ጊዜ ዳሰሰኝ» (ዳንኤል 9:21)። ለዳንኤልም «ራእዩንም አስተውል» አለው (ዳንኤል 9:23)። ከዚህ በኋላ በመጨረሻው ዘመን በየዘመኑ ሊሆን ስላለው አስገራሚ ክስተት ገለጸለት። ገብርኤል የምድር መንግሥታት ሂደት ጠቅለል አድርጎ በማሳየት ታሪክ «በአለቆች አለቃ» (ዳንኤል 8:25) «የጨካኙ ንጉሥ» ድል አድራጊ (ዳንኤል 8:23) በሆነው በክርስቶስ ምጽአት የሚደመደም መሆኑን ገለጸለት። ለእግዚአብሔር በሚያቀርበው ጸሎት የዳንኤል ትንቢታዊ መግለጫ ሁለት መልክ አለው። ይኸውም በእስራኤል ላይ ሊመጣ ስላለው ፈጣን ፍርድ (ዳንኤል 9:16)፣ ከዚያም «ስለ መጨረሻው ዘመን ፍርድ» የሚያስፈራ ምልክት እና «ለሰባት ዓመታት» ስለሚኖረው «መከራና ችግር» የሚናገር ነው። «መላእክት በትንቢት ውስጥ» በሚለው ምዕራፍ ውስጥ መላእክት አስፈሪ የሆኑትን የመጨረሻውን ዘመን ክስተቶች እንዴት እንደሚቆጣጠሩ

እንመለከታለን::

## ገብርኤል በአዲስ ኪዳን ውስጥ

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ገብርኤልን ለመጀመሪያ ጊዜ የምናየው በሉቃስ 1 ነው:: በዚህ ስፍራ፣ ገብርኤል ራሱን ለዘካርያስ በመግለጥ (ቍጥር 19) ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ልደት፣ ሕይወትና የኢየሱስ መንገድ ጠራጊ ስለ መሆኑ ገለጻ ያደርግለታል::

ከፍተኛ ጠቀሜታ የነበረው የገብርኤል መገለጥ ሥጋ ስለ ለበሰው አምላክ፣ ማለትም ስለ ኢየሱስ ለድንግል ማርያም ያበሰራት ነው:: ይህ ወጣት በሆነች ልጃገረድ በኩል ለዓለም የገለጠው እንዴት ዓይነት መልእክት ነው? በኃያሉ ገብርኤል የተጐበኘችው እንዴት ዓይነት የተቀደሰች ሴት ብትሆን ነው? እርሱም

> «ማርያም ሆይ፣ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ:: እነሆም፣ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፣ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ:: እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፣ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሣል» አላት (ሉቃስ 1:30-33)::

በዘመናት ሁሉ ይህ መለኮታዊ የሆነው የገብርኤል አዋጅ መለኮት ሥጋን የመልበሱ ሕጋዊ ሰነድና ሊመጣ ላለውም ዓለም የመሠረት ድንጋይ ነው:: እግዚአብሔር እኛን ይዋጅ ዘንድ ሥጋን ለበሰ::

## ሱራፌል

ሰማያዊና ከምድር ውጪ ያሉ ፍጥረታት በደረጃና በሥልጣን እንደሚለያዩ መጽሐፍ ቅዱስ የሚገልጽ ይመስላል:: ሱራፌልና ኪሩቤል ከመላእክት አለቃና ከመላእክት ቀጥሎ ባለ ደረጃ የሚመደቡ ናቸው:: እነዚህ ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ሲናገር የተጠቀሰውን የመላእክትን የሥልጣን ትርጒም ሊሰጡ ይችሉ

ይሆናል:: « እርሱም መላእክትና ሥልጣናት ኃይላትም ከተገዙለት በኋላ ወደ ሰማይ ሄዶ በእግዚአብሔር ቀኝ አለ» (1ኛ ጴጥሮስ 3:22):: ሱራፌል የሚለው ቃል «ፍቅር» ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል የተገኘ ሳይሆን አይቀርም:: (ምንም እንኳ አንዳንድ ሰዎች ቃሉ «የእሳት ነበልባል» ወይም «የተከበሩ» ማለት ነው ብለው ቢያስቡም::) ስለ ሱራፌል የምናገኘው በትንቢተ ኢሳይያስ 6:1-6 ውስጥ ብቻ ነው:: በአምልኮ ላይ የነበረው ነቢይ ስድስት ክንፎች ያሏቸው ሱራፌል ከጌታ ዙፋን በላይ ሆነው ሲመለከት በአድናቆት ተዋጠ:: ኢሳይያስ «ስለ እያንዳንዱ» እና «አንዱ ለሌላው ጮኸ» ስለሚል ብዙ ሱራፌሎች እንደ ነበሩ መገመት እንችላለን::

የሱራፌል አገልግሎት በሰማይ የእግዚአብሔርን ስምና ባሕርይ ማወደስ ነው:: የሱራፌል አገልግሎት በቀጥታ የሚገናኘው ከእግዚአብሔርና ከሰማያዊው ዙፋን ጋር ነው:: ምክንያቱም ስፍራቸው እንደ ኪሩቤል ከጐን ሳይሆን ከዙፋኑ በላይ ስለሆነ ነው:: የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች የሱራፌልን አገልግሎት በተመለከተ በአሳብ ቢለያዩም፣ አንድ የምናውቀው ነገር አለ:: ይኸውም ሱራፌል እግዚአብሔርን ያለማቋረጥ ማክበራቸው ነው:: በኢሳይያስ 6:7 መሠረት ደግሞ፣ እግዚአብሔር ባሪያዎቹን እንዲያነጹና እንዲያጠሩ ለማድረግ ሲጠቀምባቸው እናያለን::

ሱራፌል መግለጽ ከሚቻለው በላይ ውቦች ናቸው:: «በሁለቱ (ክንፎቹ) ፊታቸውን ይሸፍኑ ነበር፤ በሁለቱ እግራቸውን ይሸፍኑ ነበር፤ በሁለቱም ይበሩ ነበር::» (ይህ የሚያመለክተው አንዳንድ መላእክት መብረር መቻላቸውን ነው::) ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል መላእክት ሁሉ ክንፎች አሏቸው የሚለውን የተለመደ አስተሳሰብ አይደግፈውም:: መላእክት ክንፎች አሏቸው የሚለው ልማዳዊ ጽንሰ አሳብ የመነጨው ወዲያው ለመንቀሳቀስና በከፍተኛ ፍጥነት ከቦታ ቦታ ለመዘዋወር ካላቸው ችሎታ ሲሆን፣ ክንፎች ይህንን ገደብ የሌለው እንቅስቃሴ ሊያግዙ እንደሚችሉ ከመገመት ነው:: በኢሳይያስ 6 ውስጥ ግን ለበረራ አገልግሎት የሰጡት የሱራፌል ክንፎች ሁለት ብቻ ናቸው::

የሱራፌል ክንፍ ሕዝቅኤል ስለ አራቱ ሕያው ፍጥረታት ያቀረበውን ገለጻ ያስታውሰናል:: ሕዝቅኤል ሱራፌል ብሎ

ባይጠራቸውም፣ እነርሱም የእግዚአብሔርን አገልግሎት አከናውነዋል:: ልክ እንደ ሱራፌል የእግዚአብሔር ቃል አቀባዮችና ወኪሎች ሆነው ቀርበዋል:: ምንም እንኳ እግዚአብሔርን ማክበር ዋነኛ ሥራቸው የሆነው ሱራፌል ብቻ በሰማያዊው ዙፋን ዙሪያ በማንዣበብ የሚሠሩ ቢሆኑም፣ ሁለቱም የሰጡት ክብር ስለ እግዚአብሔር የሚመሰክር ነበር:: በእነዚህ ሁሉ መገለጦች እግዚአብሔር ሰዎች ክብሩን እንዲያውቁ የፈቀደ መሆኑን እንመለከታለን:: በምድርና በሰማይ ግዛቶች ውስጥ በቂ ምስክርነት እንዲኖረው ወስኗል::

## ኪሩቤል

ኪሩቤል ኃያላንና እውን ናቸው:: ሆኖም ኪሩቤል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ጊዜ የሰማያዊው ፍጥረታት ምሳሌዎች ናቸው:: «በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሠረት በቃል ኪዳን ታቦቱ ላይና በሙሴ ፅላት ላይ እንዲካተቱ ተደርጓል:: የሰሎሞን ቤተ መቅደስም በጌጥ ሥራው ላይ አስገብቷቸዋል» («Zondervan Pictorial Encyclopedia»/ ዞንደርቫን ፒክቶሪያል ኢንሳይክሎፒዲያ):: ኪሩቤል ክንፎች፣ እግሮችና እጆች ነበሯቸው:: ሕዝቅኤል ምዕራፍ 10 ኪሩቤልን በዝርዝር ሲሥል ክንፎችና እጆች ብቻ ሳይሆን፣ «ዓይን የሞሉባቸው» እና «መንኰራኵር በመንኰራኵር» የሆኑ ናቸው ይላል::

በምዕራፍ 10 ሕዝቅኤል የሐዘን እንጉርጉሮ ሲያሰማ ኪሩቤል ፍንጭ በመስጠት አገልግለዋል:: ነቢዩ የኢየሩሳሌምን ጥፋት የሚተነብየውን የትንቢት ራእይ ያቀርባል:: በሕዝቅኤል 9:3 ላይ ጌታ ከኪሩቤል በላይ ከነበረው ዙፋኑ ወደ ቤተ መቅደሱ መግቢያ የወረደ ሲሆን፣ በ10:1 ላይ ደግሞ ከእነርሱ በላይ ለመቀመጥ እንደገና ይመለሳል:: ማዕበሉ ከመነሣቱ በፊት በጸጥታ ውስጥ ሆነው ሳሉ ኪሩቤልን በደቡብ አቅጣጫ ካለው ቤተ መቅደስ ውስጥ ተቀምጠው እናያለን:: ከከተማዋ አንጻርም ስፍራ ይዘው የእግዚአብሔር ክብር ከኢየሩሳሌም ቀስ በቀስ እየለቀቀ እንደሚሄድ መሰከሩ:: የክንፎቻቸው መርገብገብ እጅግ በጣም አስፈላጊ ክስተቶች የሚከተሉ መሆናቸውን ያመለክታል (10:5):: ከዚያም በኋላ

ኪሩቤል ለመለየት ከፍ ከፍ በማለት ዝግጅት ያደርጋሉ::

ሕዝቅኤል 10ን ለመረዳት አስቸጋሪ ቢሆንም፣ በግልጽ የሚታይ አንድ ነጥብ ግን አለ:: ኪሩቤል ከእግዚአብሔር ክብር ጋር በተያያዘ ሁኔታ ይንቀሳቀሳሉ:: ይህ ምዕራፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙ ምሥጢራዊ፣ ዳሩ ግን ስለ እግዚአብሔር ክብር ከሚናገሩ እጅግ ገላጭ ምንባቦች አንዱ ሲሆን፣ መላእክትን ያሳትፋል:: ስለሆነም በጥንቃቄና በጸሎት መንፈስ ሊነበብ ይገባል:: ከዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ታላቅነትና ክብሩ እንረዳለን:: ይህም በሌሎች ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ የሚገኝ ዓይነት አይደለም::

ሱራፌልና ኪሩቤል በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙና በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በብዙ ምሥጢር የተከበቡ ቢሆኑም፣ ሁለቱም በአንድ ነገር ይመሳሰላሉ:: ይኸውም እግዚአብሔርን ባለማቋረጥ የሚያከብሩ መሆናቸው ነው:: ኪሩቤልን የምናያቸው ከእግዚአብሔር ዙፋን አጠገብ ነው:: «በኪሩቤል ላይ የምትቀመጥ ተገለጥ» [መዝሙረ ዳዊት (80):1]:: «በኪሩቤል ላይ ተቀመጠ»፣ [መዝሙረ ዳዊት (99):1]:: የእግዚአብሔር ክብር ሊካድ የሚችል ስላልሆነ፣ የሰማያዊው ፍጥረታት ሁሉ በዝምታም ሆነ ድምፃቸውን በማሰማት ለእግዚአብሔር ክብር ምስክርነትን ይሰጣሉ:: በዘፍጥረት 3:24 ላይ ኪሩቤል በዔድን ገነት የሚገኘውን የሕይወት ዛፍ ሲጠብቁ እናያለን:: በበረሃ በነበረው የሙሴ ፅላት ውስጥ ጠባቂውን ኪሩቤል የሚወክሉ ቅርጾች በወርቅ ተሠርተው የምሕረት መቀመጫውን የተወሰነ ክፍል ሸፍነው ነበር (ዘፀአት 25:18)::

ኪሩቤል ያልተፈቀደላቸው ሰዎች ወደ እግዚአብሔር እንዳይገቡ ቅድስተ ቅዱሳኑን ከመሸፈን የበለጠ ተግባር ያከናውናሉ:: ሊቀ ካህኑ የእግዚአብሔር መካከለኛ በመሆንና ሕዝቡን በመወከል ወደ ተቀደሰው ስፍራ በደም የመግባት ሥልጣን እንዳለውም ያረጋግጣሉ:: ወደ ውስጠኛው መቅደስ ለመግባት የሚችለው እርሱና እርሱ ብቻ ነበር:: ከመዋጀት መብታቸውና ካላቸው ስፍራ ሳቢያ፣ አሁን እያንዳንዱ እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ እማኝ ካህን በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ መንገዱ ተከፍቶለታል:: ኪሩቤል የመጨረሻው ዝቅተኛ

ክርስቲያን ወደ ዙፋኑ እንዳይገባ አይከለክሉም። ከክርስቶስ የመስቀል ሥራ የተነሣ በድፍረት መግባት የምንችል መሆኑን ያረጋግጡልናል። የቤተ መቅደስ የነበረው መጋረጃ ለሁለት ተከፍሏል። ጳውሎስ እንደሚለው «እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም» (ኤፌሶን 2:19)። በተጨማሪም ጴጥሮስ፣ «እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ የንጉሥ ካህናት ቅዱስ ሕዝብ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ» (1ኛ ጴጥሮስ 2:9) ሲል ያረጋግጥልናል።

ኃጢአታቸውን ለተናዘዙ በክርስቶስ አዳኝነት ለሚታመኑ የእግዚአብሔር ዙፋን የሚገኝበት ውስጠኛው መቅደስ ምን ጊዜም ክፍት ነው።

ብዙዎች በዮሐንስ ራእይ ውስጥ የተጠቀሱት «ሕያዋን ፍጥረታት» ኪሩቤል ናቸው ብለው ያምናሉ። ምንም እንኳ እነዚህ መልአካዊና መለኮታዊ ፍጥረታት ታላቅ ሞገስ ያላቸው ቢሆኑም፣ በሰማይና በምድር ያሉ ኃይላት ሁሉ በተቀደሰ አምልኮና ቃላት ሊገልጹ የማይችሉትን አክብሮት በሚሰጡለት በሰማያዊው በግ በጌታ ክብር ፊት ደብዘዝ ይላሉ።

# ስድስት

## ሉሲፈርና የመላእክት ዓመፅ

በሰው ልጆች ሁኔታዎች ውስጥ የመላእክት ኃይላት ከፍተኛውን ሚና እንደሚጫወቱ ብዙ ሰዎች አይገነዘቡም። ነቢዩ ዳንኤል ለእግዚአብሔር ታማኝ በሆኑት ቅዱሳን መላእክትና ከሰይጣን ጋር በተባበሩት የጨለማ መላእክት መካከል ስለሚካሄደው የማያቋርጥ መራራ ትግል በግሩም ሁኔታ አብራርቷል (ዳንኤል 10:11-14)። ይህ ሰይጣን ወይም ዲያብሎስ በአንድ ወቅት «ሉሲፈር፣ የንጋት ልጅ» ተብሎ ይጠራ ነበር። ከሚካኤል ጋር አብሮ የሚሠራ ሁለተኛው የመላእክት አለቃ የነበረ ሊሆን ቢችልም፣ ካመፁት ግብረ አበሮቹ ጋር ከሰማይ ተወርውሮ መዋጋቱን ቀጥሏል። አንዳንድ ጊዜ ሰይጣን ጠቃሚ ጦርነቶችን ስለሚያሸንፍ ድል ያደረገ ሊመስል ይችላል። ሆኖም የመጨረሻው ውጤት ለማን እንደሚሆን የተረጋገጠ ነው። አንድ ቀን ተሸንፎ ሥልጣኑን ለዘላለም እንደሚገፈፍ የታወቀ ነው። እግዚአብሔር የጨለማን ሥልጣን ይሰብራል።

አንዳንድ ሰዎች፣ «ፍጹም ሆኖ በተሠራው የእግዚአብሔር ዓለም ውስጥ እንዲህ ዓይነት ግጭት እንዴት ሊነሣ ይችላል? » ብለው ይጠይቃሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን «የዓመፅ ምሥጢር» ብሎ ይጠራዋል (2ኛ ተሰ. 2:7)። ምንም እንኳ በምንፈልገው መጠን በቂ መረጃ ባይሰጠንም፣ አንድ ነገርን ግን በእርግጠኝነት እናውቃለን። ይኸውም የወደቁት መላእክት የወደቁበት ምክንያት በእግዚአብሔር ላይ በማመፃቸው ነው። የእግዚአብሔር ቃል በ2ኛ ጴጥሮስ 2:4 ላይ፣ «እግዚአብሔር ኃጢአትን ላደረጉ መላእክት ሳይራራላቸው ወደ ገሃነም ጥሎ በጨለማ ጉድጓድ ለፍርድ ሊጠበቁ አሳልፎ ከሰጣቸው. . .» ይላል። በይሁዳ 6 ውስጥ የሚገኘው ተመሳሳይ ክፍል የኃላፊነቱን ቀንበር በቀጥታ በራሳቸው በመላእክት ትከሻ ላይ የሚጭን ይመስላል። ይሁዳ ይህንን በመገንዘብ «መላእክት

የመጀመሪያ ርስታቸውን ሳይዙ መኖሪያቸውን ትተዋል» ሲል ገልጿል::

በዓለማት የፍጥረታት ታሪክ ውስጥ ከፍተኛው ጥፋት የሉሲፈር በእግዚአብሔር ላይ ማመፅና በዓመፅ ሥራው የተባበሩት ሚሦዎቹ መላእክት ውድቀት ነው::

ይሄ መቼ ተከናወነ? በፍጥረት መጀመሪያና ሰይጣን ወደ ዔድን ገነት ካለ ፈቃድ በገባበት ወቅት መካከል ነው:: ዳንቴ የተባለው ገጣሚ የዓመፀኛ መላእክቱ ውድቀት በተፈጠሩ በ20 ሰከንዶች ውስጥ የተከናወነ ሲሆን፣ ይህም ሉሲፈር እውቀቱ ፍጹም የሚሆንበትን ጊዜ መጠበቅ ባለመፈለጉ ምክንያት ባደረበት ኵራት የተነሣ እንደ ተከሰተ አመልክቷል:: እንደ ሚልተን ያሉ ሌሎች ገጣሚዎች አዳምና ሔዋን በዔድን ገነት ከመፈተናቸው ቀደም ብሎ መላእክት እንደ ተፈጠሩና እንዳመፁ ያስረዳሉ::

ዋናው ጥያቄ ግን፣ «መላእክት መቼ ነው የተፈጠሩት?» የሚለው ሳይሆን፣ «መቼ ወደቁ?» የሚለው ነው:: ውድቀታቸው የተከሰተው እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን በአትክልቱ በታ ከማስቀመጡ በፊት ነው ብሎ መገመት አስቸጋሪ ነው:: እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ማረፉንና ሁሉም ነገር መልካም እንደ ሆነ ማወጁን በትክክል እናውቃለን:: ከዚህ እንደምንረዳው፣ እስከዚህ ጊዜ ድረስ የመላእክት ፍጥረትም መልካም ነበር ማለት ነው:: «መላእክት ከመውደቃቸውና ሰይጣን የመጀመሪያዎቹን ሰዎች ከመፈተኑ አስቀድሞ አዳምና ሔዋን በአትክልቱ ውስጥ ለስንት ጊዜያት ነበሩ?» ብለን እንጠይቅ ይሆናል:: ይህ ጥያቄ ምላሽ ሳያገኝ መቆየት ይኖርበታል:: በአዎንታዊው ገጽታ ለማለት የምንችለው አዳምና ሔዋንን ከመፈተኑ በፊት የወደቀው ሰይጣን የጥፋት መልእክተኛ በመሆኑ ከፍተኛ በደል እንደ ፈጸመ ነው:: ምክንያቱም ኃጢአትን በፈጸመ ጊዜ ማንም ኃጢአትን እንዲሠራ ያልፈተነው በመሆኑ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ አዳምና ሔዋን ፈታኝ አጋጥሟቸዋል::

ስለሆነም ታሪኩ ከሚጀምርበት መነሣት አለብን:: ታሪኩ እጅግ ምሥጢራዊ በሆነ መንገድ የተጀመረው በሉሲፈር ነው:: ሉሲፈር በሰማይ ከተፈጠሩት ፍጥረታት ሁሉ በእውቀት የተሞላና እጅግ

የተዋበም ነበር። ምናልባትም ከመቅጽበት ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ዓለማትን የሚገዛ ልዑል ነበር። ውጤቱ በሰማይ ሁከትና ጦርነት መከሰቱ ነበረ። ኃጢአትን በሠራባት ደቂቃ በሰማይ ላይ የሚቀጣጠል ጦርነትን ጀመረ። ከዚያም ከሰው ልጆች ታሪክ መጀመር ጥቂት ቀደም ብሎ ወደ ምድር ተጣለ። ይህ የዘመናችንን የዓለም ቀውስ ይመስላል።

ትንቢተ ኢሳይያስ 14:12-14 የግጭቱን ጅማሬ ይዘግባል። ዓመፅን ከማካሄዱ በፊት የብርሃን መልአክ የነበረው ሉሲፈር በሕዝቅኤል 28:12-27 በሚያስደስት ሁኔታ ተገልጿል። «ጥበብን የተሞላህ ውበትህም የተፈጸመ መደምደሚያ አንተ ነህ። ... አንተ ልትጋርድ የተቀባህ ኪሩብ ነበርህ፤ በተቀደሰው በእግዚአብሔር ተራራ ላይ አኖርሁህ፤ በእሳት ድንጋዮች መካከል ተመላለስህ። ከተፈጠርህበት ቀን ጀምረህ በደል እስኪገኝብህ ድረስ በመንገድህ ፍጹም ነበርህ ... በውበትህ ምክንያት ልብህ ኰርቶአል፤ ከክብርህ የተነሣ ጥበብህን አረከስህ።» መልአኩ ሉሲፈር በእግዚአብሔርና በሥራዎቹ ላይ ባመፀ ጊዜ ከሲሶ የማያንሱ የሰማይ የመላእክት ሠራዊት በዓመፁ እንደ ተባበሩ አንዳንዶች ገምተዋል። ስለሆነም በሰማይ የተጀመረው ጦርነት በምድር ላይም የሚቀጥል ሲሆን፣ የመጨረሻ ፍጻሜውን የሚያገኘው ክርስቶስና መልአካዊ ሠራዊቱ ድል በሚቀዳጁበት በአርማጌዶን ጦርነት ይሆናል።

ሌስሊ ሚለር "All About Angels" በተሰኘች ግሩም አነስተኛ መጽሐፋቸው ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል መላእክትን ከከዋክብት ጋር እንደሚያመሳስላቸው ይጠቅሳሉ። ይህ ደግሞ ሰይጣን ከውድቀቱ በፊት ለምን «የንጋት ኮከብ» ተብሎ እንደ ተጠራ የሚያስረዳ ነው። ዮሐንስ ይህንን ገለጻ ሲያብራራ፣ «ጅራቱም የሰማይን ከዋክብት ሲሶ እየሳበ ወደ ምድር ጣላቸው» ብሏል (የዮሐንስ ራእይ 12:4)።

## ዓመፅ በሰማይ ውስጥ

ሐዋርያው ጳውሎስ አሁን ሰይጣን ስለሆነው የቀድሞው ሉሲፈር፣ «በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ

አለቃ እንደሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ» እያለ ያብራራው በሰማያት የሚካሄደውን የዓመፅ ጦርነት ስለተገነዘበ ነው (ኤፌሶን 2:2)። ከዚህ በተጨማሪም የሰይጣንን የተደራጀ የጨለማ መንግሥት በምንዋጋበት ወቅት የምንጋደለው «ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዢዎች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካሉ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር» እንደሆነ ያስረዳል (ኤፌሶን 6:12)።

በእግዚአብሔር ላይ የሚፈጸም ዓመፅና በደል ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ «የራስን ፈቃድ» ለመጫን የሚደረግ ጥረት ነው ብለን ልንገልጸው እንችላለን። ይህ አገላለጽ ለመላእክትም ሆነ ለሰው ልጆች የሚሠራ ነው።

### የሉሲፈር አምስት «የእኔ ፈቃዶች»

የንጋት ልጅ የሆነው ሉሲፈር የተፈጠረበት ምክንያት እንደ ሌሎቹ መላእክት ሁሉ እግዚአብሔርን ያከብር ዘንድ ነበር። ሆኖም እግዚአብሔርን ለዘላለም ከማገልገልና ከማመስገን ይልቅ ሰይጣን በእግዚአብሔር ምትክ በሰማይና በፍጥረታት ላይ ገዢ ለመሆን ፈለገ። ፍጹማዊ ሥልጣንን ፈለገ። በኢሳይያስ 14፣ «[እኔ] ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ»፤ «[እኔ] ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ»፤ « [እኔ] በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ»፤ « [እኔ] ከዳመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ»፤ «[እኔ] በልዑልም እመሰላለሁ» እኔ. . . እኔ. . . እኔ. . . እኔ . . . እኔ።

ሉሲፈር በፈጣሪው ሥር መሆን ስላላረካው የእግዚአብሔርን ዙፋን ያለአግባብ ለመያዝ ፈለገ። የፍጥረታት ሁሉ የሥልጣን ማዕከል የመሆን አሳቡ አስፈነደቀው። የዓለማት ሁሉ ቄሳር፣ ናፖሊዮን፣ ሂትለር ለመሆን ፈለገ። «የእኔ ፈቃድ» የሚለው መንፈስ የዓመፅ መንፈስ ነው። የድፍረት ተግባሩ ከፍ ያለውን ጌታ ከዙፋን ለማውረድ የቆረጠ ነበር። የሥልጣንና የክብርን የመጨረሻ ደረጃ ለመያዝ በመጓጓት የዓመፅ ዱለታን አካሄደ። ለመመሰል እንጂ ለማምለክ አልፈለገም።

ሰይጣን የዓለማት ሁሉ ገዢ ሆኖ እግዚአብሔርን ለመተካት የነበረው ፍላጎት ቀደም ብዬ እንደ ጠቀስኩት ወደ ኩራት ሲያመጣ

በሚችል በቀደመ ኃጢአት ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይችላል:: ከሰይጣን ኵራት በስተጀርባ ከኃጢአቶች ሁሉ ክፉ የሆነው ክፉ ምኞት ነበር:: የእርሱ ያልሆነውን ፈለገ:: ሁሉም ጦርነቶች ማለት ይቻላል የሚቀሰቀሱት ከምኞት የተነሣ ነው:: በሰማይና በምድር በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል የተካሄደው ጦርነት የተጀመረው በተመሳሳይ ስሜት ማለትም የእግዚአብሔር ብቻ የሆነውን ነገር በከፍተኛ ደረጃ ከመመኘት ነው::

ዛሬም፣ እንደ ቀድሞው ሁሉ፣ ማንም ኃጢአትን ብቻውን ሊሠራ አይችልም:: የኃጢአት ማታለያዎች ተላላፊዎች ናቸው:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለ «ዘንዶውና. . . መላእክቱ» ይናገራል (የዮሐንስ ራእይ 12:7):: ይኸውም ከሉሲፈር ጋር ቊጥር ስፍር የሌላቸው መላእክት የእግዚአብሔርን ባለሥልጣንነት መካድ መርጠው ከፍተኛ ስፍራቸውን የጣሉ መሆናቸውን ያሳያል:: የሉሲፈር «የጦርነት መርሐ ግብር» ተካፋዮች ለመሆን መረጡ:: ከውድቀታቸው በኋላም እነዚያ መላእክት «ለፍርድ የተጠበቁ» ሊሆን (2ኛ ጴጥሮስ 2:4)፣ ክፍላቸውም በማቴዎስ 25:41 በተጻፈው መሠረት ከሉሲፈር ጋር «ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀው ወደ ዘላለም እሳት» መጣል ይሆናል:: ይህ እስከሚሆን ድረስ ግን ኃይላቸውን አስተባብረው በአገራት፣ በቤተሰብና በግለሰቦች መካከል ግጭት ከመፍጠር አይታቀቡም:: ተጠንቀቁ አደገኞች፣ በተንኰል የተሞሉ አረመኔዎችና ክፉዎች ናቸው:: ከቊጥጥራቸው ሥር እንድትሆኑ ከመፈለጋቸውም በላይ እናንተን ለማግኘት ማንኛውንም ዋጋ የሚከፍሉ ናቸው!

የወደቀው የሰማይ ልዑል ከእግዚአብሔር ጋር እስከ ሞት ድረስ ለመዋጋት ቆርጧል:: ዓመፃን ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ በዘመናት ሁሉ የተካሄዱትን ጥፋቶች በበላይነት የነደፈው እርሱ ነው:: የእርሱ «የእኔ ፈቃድ» መንፈሱ በእግዚአብሔር ላይ ባለው ጽኑ ጥላቻ አማካኝነት በሰው ልጆች የታሪክ ሂደት ውስጥ ጭፍግ ታሪክ እንዲጽፍ አድርጎታል:: ሰይጣን ከእግዚአብሔር ጋር በሚያካሂደው ጦርነት እግዚአብሔር የፈጠረውንና የወደደውን የሰው ዘር ይጠቀማል:: ስለሆነም የእግዚአብሔር በጎ ሠራዊትና የሰይጣን ክፉ ሠራዊት እጅግ አደገኛ በሆነ ግጭት ውስጥ የገቡት ከታሪካችን መጀመሪያ ጀምሮ ነው:: የአገር መሪዎችና የመንግሥት

ባለሥልጣኖች የዚህን ሥርዓት እውነተኛ ባሕርይ ካልተገነዘቡ፣ በዕውርነት ዕውራንን የሚመሩ ሆነው ይቀጥላሉ:: ግጭቶችን ሙሉ ለሙሉ ሊያስቆሙ አይችሉም:: ይህ መንፈሳዊ ጦርነት መፍትሔ እስካላገኘ ድረስ የዓለም ግዙፍ ችግሮች መልስ ሊያገኙ አይችሉም:: ይህም መፍትሔ የሚገኘው በመጨረሻው የታሪክ ጦርነት በአርማጌዶን ነው:: ከዚያም ክርስቶስና መልአካዊ ሠራዊቱ ድል አድራጊዎች ይሆናሉ::

## ያለፈው፣ የዛሬውና የነገው ገጽታ

ሉሲፈር ዲያብሎስ የኃጢአት ደራሲ ሆነ:: ይህ የነካውን ሁሉ ሲያታልል፣ ሲረብሽ፣ ሲነጥቅና ሲያጠፋ የኖረው ኃጢአት ነው::

ታዲያ ይህ በክፉ ምኞት በሰይጣን የተጠነሰሰውና ወደ ምድር ዘልቆ የገባው፣ ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ ጦርነት ማቆሚያ አይኖረውም ማለት ነው?

ጦርነቱ የሚቀጣጠለው በምድር ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በሰማይም ጭምር ነው:: «በሰማይም ሰልፍ ሆነ፤ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ:: ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ፤ አልቻላቸውምም፤ . . . ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ::» (የዮሐንስ ራእይ 12:7፣9)::

ሰይጣንና ጭፍሮቹ ብጥብጥ በማባባስ፣ ጦርነትን በመቀስቀስ፣ ጥላቻን በመፍጠር፣ ግድያዎችን በመገፋፋት፣ እግዚአብሔርንና ትእዛዛቱን በመቃወም የታወቁ ናቸው:: እነዚህ ኃይላት ለጥፋት መንፈስ ቆርጠው የተነሡ ናቸው:: በሌላ በኩል ቅዱሳን መላእክቱ ለፈጣሪያቸው ይታዘዛሉ:: በሰማይ መላእክት መካከል ምንም ዓይነት የማይጣጣም ቅራኔ አይደመጥም:: ቅዱሳን መላእክት እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች የሚጸልዩበትን ዓላማ ለማስፈጸም ራሳቸውን የሰጡ ናቸው:: «መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን. . . » (ማቴዎስ 6:10)::

መጽሐፍ ቅዱስ ሉሲፈርና የወደቁት መላእክት ኃጢአተኞችና የመጀመሪያ ሥልጣናቸውን የጣሉ መሆናቸውን ይናገራል (ይሁዳ 6):: የፍጹም ትዕቢትና የምኞትን ኃጢአት ፈጽመዋል:: ሉሲፈርን

ከሰማይ እንዲወድቅ ያደረገው የትዕቢት ኃጢአት ሲሆን፣ ይህ ኃጢአት ማች የሆነውንም ሰው ሊጥል ይችላል። ራሳችንን ከትዕቢት ልንጠብቅ ያስፈልገናል። አለበለዚያ ዛሬ ወደ አጋንንት እንደተለወጡት እንደ ሉሲፈርና መላእክቱ ወደ ውድቀት እናመራለን።

ምናልባት እግዚአብሔር ሰዎች የሰይጣንና የአጋንንት ጭፍሮችን መኖር እንዳይጠራጠሩ ለማረጋገጥ ፈልጎ ይሆን? ምናልባት በምድራዊ ሁኔታ የሰይጣንን አጠቃላይ ገጽታ የሚያሳየው ሕዝቅኤል 28 እንዲጻፍ ማነሣሣቱ ይህንን የሚያመለክት ይሆናል። ይህ በነቢዩ ሕዝቅኤል የቀረበው ዘገባ ስለ ጢሮስ ከተማ ምድራዊ ልዑል የሚናገረው ነው። ይህ ሰው ምድራዊው የሰይጣን ተምሳሌት ይመስላል። ከምንባቡ እንደምንረዳው፣ የጢሮስ ንጉሥ ሥጋ የለበሰ ሰይጣን ሆኗል። ይህም ሰይጣን የሆነው የሰማያዊው ሉሲፈር ምድራዊ ምሳሌ ነው።

የምንኖረው በማያቋርጥ ጦርነት ውስጥ ነው። በዘመናት ሁሉ ታላቅ የሆነው ጦርነት እየተባባሰ መሄዱን ይቀጥላል። የጦርነቱ ቀጠና በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ እየጠበቀ ነው። የሚመጣው ከመንፈሳዊውና ከማይታየው ዓለም መራራ ጦርነት ጋር ሲነጻጸር፣ በምድር ላይ በአገራት መካከል የሚካሄዱት ጦርነቶች በጣም ተራ ጉዳዮች ናቸው ማለት ይቻላል። በዙሪያችን የሚካሄደው ይህ የማይታየው መንፈሳዊ ውጊያ የማያቋርጥና ተከታታይ ነው። የጌታ ሥራ በሚሠራበት ጊዜ የሰይጣን ኃይላት እንቅፋት ይሆናሉ፤ የመላእክት ፍጥረታት መለኮታዊ መመሪያዎችን ለማስፈጸም በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ አጋንንት ይቆጣሉ። ይህ ሁሉ የሚከሰተው ደግሞ የጨለማ ኃይላት ለእግዚአብሔር ክብር እንዲሆን የተጠበቀውን ስፍራ እንደገና ለመውሰድ ከሚያደርጉት ውጊያ የተነሣ ነው።

እግዚአብሔር ሰይጣንንና ጭፍሮቹን እንዲቋቋሙ ለመላእክት ሠራዊቱ ሥልጣን ባይሰጣቸው ኖሮ የእነዚህን የጨካኝ አጋንንቶች ምሽግ በማለፍ ማን ወደ ጌታ ዘለዓለማዊ ነጻነትና ደኅንነት ለመድረስ ተስፋ ያደርግ ነበር? ጳውሎስ የጨለማ ኃይላት ምሽጎች እጅግ ጠንካራ ስለመሆናቸው ይናገራል። ሆኖም የመላእክቱ

ሠራዊት ድልን ለመቀዳጀት ወደፊት እየገፉ ሲሄዱ ለብርሃንና ለእምነት ተዋጊዎች እጃቸውን ይሰጣሉ (2ኛ ቆሮንቶስ 10:4-5)።

## ሰይጣን በጥቃት ላይ

የዮሐንስ ራእይ 12:10 ሰይጣንን፣ «የወንድሞች ከሳሽ» ሲለው፣ ኤፌሶን 6:12 ደግሞ፣ «አለቆች. . . ሥልጣናት. . . የጨለማ ዓለም ገዢዎች . . . በሰማያዊ ስፍራ ያሉ የክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት» ብሎ ይገልጻቸዋል። ምንም እንኳ ሰይጣንና የክፋት ተከታዮቹ ውጊያቸውን በሰማያት ውስጥ የሚያፋፍሙ ቢሆንም፣ ዋናው ጥረታቸው ግን ከዓለም ውስጥ እምነትን ማጥፋት ይመስላል።

ኢሳይያስ 13:12-14 የሰይጣንን ዓላማዎች ይዘረዝራል። ሰይጣን አገራት እንዲወድቁ ይጥራል፤ የሥነ ምግባር መለኪያዎች እንዲበላሹና የሰው ኃይል ጥቅም ላይ እንዳይውል ያደርጋል። የኅብረተሰብን ሥርዓት በማዛባትና ሥርዓት በአግባቡ እንዳይመሠረት በመከላከል የእምላካችን የእግዚአብሔር ግዛቶች እንዲናጉ ለማድረግ ይጥራል። የአጥፊነት ሥልጣኑን በመጠቀም ጥፋትን፣ እሳትን፣ ጉርፍን፣ የመሬት መንቀጥቀጥን፣ አውሎ ነፋስን፣ ቸነፈርን፣ በሽታንና ውድመትን ይፈጥራል። ስለ ሰይጣን ታላቅ ኃይል የሚሰጠው መግለጫ የሚደመደመው «ምርኮኞቹንም ወደ ቤታቸው ያልሰደደ» በሚሉ ቃላት ነው (ኢሳይያስ 14:17)። ይህ ያለምንም ጥርጥር ስለ ሰይጣን እስር ቤት ወይም ሲኦል ወይም በሉቃስ 16:19-31 በግልጽ ስለ ተሣለው የሙታን መኖሪያ የሚያመለክት ነው።

ሰይጣን ትልቅ ኃይል አለው። ከእግዚአብሔርና ከሕዝቡ ጋር ለመዋጋት ራሱን ያዘጋጀ መሠሪና ብልጥ ነው። ሰዎች በኃጢአት ታስረው እንዲቆዩና ከእግዚአብሔር ተለይተው ወደ ዘለዓለማዊ እስር ቤት እንዲወርዱ ለማድረግ ማንኛውንም ነገር ያደርጋል።

የብርሃን መልአክና የንጋት ልጅ ከነበረው ከሉሲፈር ውድቀት ጀምሮ በዘመናት የመረረ ጦርነት ሲካሄድ ምንም ዓይነት ዕረፍት አልነበረም። የጨለማው የፈጠራ ጠቢብ የሆነው ሉሲፈር

የእግዚአብሔርን የዘመናት ዕቅድ ለማጨናገፍ ቀንና ሌሊት ይሠራል:: በጨለማው ኃያላትና በሰይጣን አዛዥነት ለፍሬ የበቁትን የልፋት ውጤቶች በእያንዳንዱ የሰው ልጅ ታሪክ ገጽ ላይ በቅደም ተከተል ተቀርጸው እናገኛቸዋለን:: ሰይጣን አንዲት ቅንጣት እንኳ አሳልፎ አይሰጥም:: እግዚአብሔር ዓለምን ከእርሱ ቍጥጥር ነፃ ለማውጣት ያለውን ዓላማ ከመቃወም ለአፍታም አይቦዝንም:: የእግዚአብሔርን ቃል እውነተኛነት ዋጋ ለማሳጣት ዘላለም ይጥራል:: ሰዎች የእግዚአብሔርን ባለሥልጣንነት እንዲክዱ ያባብላቸዋል:: እናም በዓለም ከንቱ የኃጢአት ምኞት እንዲንከባለሉ ይገፋፋቸዋል:: «እርሱ ከመጀመሪያ ነፍስ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለሌለ በእውነት አልቆመም:: ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፤ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና» (ዮሐንስ 8:44):: ኃጢአት የዓለማችን አስፈሪ እውነታ ነው:: ጥፋቱን በመጥፎ ምግባርና በክፉ ምኞት፣ በሚያንቀጠቅጥ ጦርነት ውስጥ፣ በራስ ወዳድነትና በኀዘን፣ በተሰበሩ ልቦችና በጠፉ ነፍሳት ውስጥ ይጽፋል:: ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሥራዎች ለማጥፋት ወይም ለማደነዝ የሚያደርገው ጥረት የዓለም አሳዛኝ ክስተት እንደሆነ ቀርቷል::

## የሰይጣን ሤራ

እግዚአብሔር ፍትሐዊ ከሆነ ኃጢአትን ለዘላለም መታገሥ አይችልም:: የሉሲፈር ብልሹ ተግባራት እንዲያላግጡበት አይፈቅድም:: ምክንያቱም ለዓለም የክፋት ሥራ የተሰጠው መልስ ሊለወጥ በማይችል የእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እንደሚከተለው ተገልጿል:: ይህም «የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው» (ሮሜ 6:23):: በታሪክ መግቢያ ላይ የተጀመሩት የሰይጣን ጥቃቶች በአርማጌዶን ጦርነት ወቅት እግዚአብሔር አስፈሪውን የድራማ መጋረጃ ማውረድ እስከሚጀምር ድረስ የሚቀጥል ይሆናል::

የሰይጣን አስተሳሰብ የተመሠረተው «ከሆነ» በምትለው ትንሽ ቃል ላይ ነው:: በዘመናት ሁሉ እግዚአብሔርን በሰዎች ፊት እንደ

ውሸታም ለማስቆጠር፣ ዋጋ ለማሳጣትና የሰውን ልጅ እምነት የሚያገናኘውን ተድላ እንዳያገኝ ለማቀብ ከመሞከር በዝና አያውቅም:: የሉሲፈር የሁልጊዜ መሣሪያው «ከሆነ» የሚል ሲሆን፣ እግዚአብሔር ግን በደኅንነት መርሐ ግብሩ ውስጥ ምንም ዓይነት «ከሆነ»፣ «ነገር ግን»፣ ወይም «እና» እንደሌለ ያስረዳል:: የእግዚአብሔር ዕቅዶች የማይለወጡ ናቸው:: እግዚአብሔር ለሰይጣን «ከሆነ» የሚሰጠው ማርከሻ የሚሠራና የማይለወጥም ነው:: እግዚአብሔር በክርስቶስ ሥራና ረዳቶቹ በሆኑት መላእክት ጥረት በሉሲፈር ሠራዊት ላይ ድልን እንደምንቀዳጅ አረጋግጦልናል::

የወደቀው ሉሲፈር ሜራውን የፈለፈለው እግዚአብሔር በፈጠረው ነገር ላይ የነበረውን ፍጹም የበላይነት ለመንጠቅ መሆኑ አያስገርምም:: በገነት ውስጥ በተካሄደው የመጀመሪያው ውይይት ላይ በእባብ የተመሰለው ሉሲፈር፣ «በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን?» ብሎ ነበር የጠየቀው (ዘፍጥረት 3:1):: ለዚህም ጥያቄ ሔዋን ስትመልስ፣ «ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፉ ፍሬ እግዚአብሔር አለ፣ እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም» (ዘፍጥረት 3:3)::

እዚህ ላይ ሉሲፈር ሲመልስ ከዚህ የዛፍ ፍሬ ብትበሉ «ሞትን አትሞቱም» አላቸው (ዘፍጥረት 3:4):: በሌላ አነጋገር፣ እግዚአብሔር ስለሚናገረው ነገር አያውቅም ማለቱ ነበር::

ሰይጣን ብዙ ጊዜ ሥራውን የሚሠራው በነገሮች መካከል ጥያቄን በመወርወርና ጥርጣሬን በመፍጠር ነው:: የእግዚአብሔርን ቃል መጠራጠር አስከፊ ነገር ነው:: የሰይጣን ስልት ነገሮችን በምክንያታዊነት እንድንገነዘብ መገፋፋት ነው:: ሔዋን ከጠላቷ ጋር ነገሮችን በራሷ መንገድ መጠየቅ ጀምራ ይሆናል:: እግዚአብሔር ይህንን መልካም ነገር ለመከልከል ፍትሕ አልባና ክፉ ሊሆን ይችላል?- «ፍሬው ለዓይን የሚያስጐመጅ መሆኑን አመነች» (ዘፍጥረት 3:6)::

ሔዋን ከፈታኙ ጋር በሞኝነት ተወያየች:: የእግዚአብሔርን እውነተኛ ጥበብ በራሷ አእምሮ መጠራጠር ጀመረች:: ሰይጣን ጨለማ የሆኑ አሳቦቹን የብርሃን ቀለም መቀባት ያውቅበታል::

ተንኮሎቹ ከራሳችን ፍላጎት አንጻር አምረው ይቀርባሉ:: ቀስ በቀስ መሠሪ «ከሆነስ»ን ጣልቃ ያስገባል:: «ይህ ዛፍ አንድን ሰው አዋቂ ለማድረግ የሚረዳ ነው» የሚለውን ሔዋን አዳመጠች:: ነገሩን በራሷ ውስጥ ማውጣትና ማውረድ ጀመረች:: ከዚያም ወስዳ ቀመሰችው:: ሰይጣን ለሥጋ ምኞትና ከኃጢአት ምንጮች ለሚመጡ የስሜት ማርኪያዎች አጓጊ ነገር ለማቅረብ አይሰንፍም:: ሰይጣን «ከሆነስ» የሚላቸውን አስከፊ አሳቦች የሚያስገባብንና እንድንነሣሣ የሚጠቀምባቸው ቀዳዳዎቹ ስሜቶቻችን ናቸው::

የዘፍጥረት ዘገባ በመጀመሪያ የበላችው ሔዋን ስትሆን፣ በኋላ ደግሞ ጥቂቱን ለአዳም እንደ ሰጠችው ይናገራል:: የከለከላቸው ፍሬ አደጋ እንደ ነበረበት ቢገነዘቡና አሳባቸውን በእግዚአብሔር ላይ በመጣል በጥበቡ ቢደገፉ ኖሮ ታሪክ ሁሉ ፍጹም የተለየና ድምዳሜውም ሌላ በሆነ ነበር:: ካለመታዘዝ የተነሣ የሚመጡትን ውጤቶች ቢገነዘቡ ኖሮ፣ የሰይጣንን የ«ከሆነስ» አደጋ ቢመለከቱ ኖሮ፣ ከገነት ለዘላለም ያገዳቸውን የነበልባል ሰይፍ በዓይነ ሕሊናቸው ለማየት ቢችሉ ኖሮ፣ የአንዲት «የየዋህነት» ደቂቃ መዘዞች ምን ያህል የከፉ እንደሆኑ ቢገነዘቡ ኖሮ፣ በዝምታ በተዋጠውና ሕይወት በሌለው በልጃቸው አቤል፣ አስከሬን አጠገብ ባልቆሙ ነበር:: የእርሱ አሳዛኝ ሞት የመጣው በራሳቸው ሕይወት በተፈጸመው ያለመታዘዝ ኃጢአት ኃይል ምክንያት ነበር:: ይህ ባይሆን ኖሮ የእኛ ዓለም ምድረ ገነት በሆነች ነበር!!

አዳምና ሔዋን ሰይጣንን ቢቃወሙት ኖሮ ሽንፈቱን ተከናንቦ ለዘላለም በሸሸ ነበር:: ሆኖም ስለ ወደቁ ሞት በሰው ልጅ ላይ ሁሉ ነገሠ (ዘፍጥረት 3:13):: እዚህ ላይ ነው ሞት የበቀለው:: በምንም ዓይነት ሁኔታ፣ ባሕርይ ወይም አካባቢ ውስጥ ብንሆን ኃጢአት በሁላችንም ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ ይሠራል:: ከወላጆቻችን የወረስነው በመሆኑ በተፈጥሮ የተበላሸ ሥነ ምግባር አለን (ሮሜ 3:19):: ምንጩ የተበረዘ በመሆኑ፣ የጥፋተኝነትን ፍርድና የኃጢአትን አሻራ መሸከም ይኖርብናል:: እያንዳንዱ ሰው የራሱን መልስ ለእግዚአብሔር መስጠት አለበት::

ሰይጣን የሞት «ከሆነስ»ን በሰዎች አእምሮ ውስጥ ጣልቃ ያስገባል:: ጥሩ ኑሮ «ብትኖር»፣ ትክክል የሆነውን ነገር ብታደርግ፣

ቤተ ክርስቲያን «ብትሄድ»፣ ለሌሎች ጥቅም ብትሠራ፣ እንዲህ ቢሆን፣ እንዲህ ቢሆን፣ እንዲህ ቢሆን ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን እነዚህ ነገሮች ደኅንነትን ለማግኘት የእግዚአብሔርን መመዘኛዎች ሊያሟሉ የማይችሉ መሆናቸውን ይናገራል። የእኛ መልካም ሥራዎችና ፍላጎቶች በቂ አይደሉም። ኢየሱስ «ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል» ብሏል (ዮሐንስ 3:7)። ደኅንነታችንን ልናረጋግጥ የምንችለው በእምነት ወደ ክርስቶስ ተመልሰን ስንታመንበትና ኃጢአታችንን ለእርሱ ተናዝዘን ይቅርታን ስንሻ ብቻ ነው። ሰይጣን ከክርስቶስ ይልቅ በራሳችን ላይ እንድንታመን ለማድረግ የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል። ሆኖም ክርስቶስ ብቻ ነው የሚያድነን። ይህንንም የሚያደርገው ሕይወታችንን ለእርሱ ስናስገዛና በመስቀል ላይ ለደኅንነታችን ያከናወነውን ስናምን ነው። «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» (ዮሐንስ 3:16)።

ዛሬ ሰይጣን የሚቀርበን በእባቡ የ«ቢሆንስ» የሞት ንግግር ነው። ዛሬ የሞት ሽታ በየትኛውም ስፍራ አለ። ሲ. ኤስ. ሌዊስ «ጦርነት ሞትን አይጨምርም፣ ምክንያቱም በእያንዳንዱ ትውልድ ውስጥ ሞት በብዛት አለና» ብለዋል። ሆኖም በኢየሱስ ክርስቶስ አምነን የዘላለም ሕይወትን ማግኘት እንችላለን።

ከክርስቶስ ጋር ለመሆን ውሳኔ አድርገሃል? ለደኅንነትህስ በእርሱ ላይ እየተደገፍክ ነው? ይህንን የእምነት እርምጃ ካልወሰድክ ወይም ከክርስቶስ ጋር ባለህ ግንኙነት ላይ እርግጠኛ ካልሆንክ ዛሬ ወደ እርሱ ተመልሰህ እንደ ጌታህና አዳኝህ አድርገህ ተቀበለው። «ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው» (ዮሐንስ 1:12)። ዛሬ ኢየሱስን በእምነት ወደ ልብህ እንዲገባ ብትፈቅድለት ይህንን በሕይወትህ መለማመድ ትጀምራለህ።

## ሰባት

# መላእክት እንደ እግዚአብሔር መልእክተኞች

መላእክት ለግላችን ያገለግሉናል:: መላእክት የግል ትኵረት እንደሚያደርጉልን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የሚገኙ ዘገባዎች ያረጋግጣሉ:: ማርቲን ሉተር "Table Talk" በተሰኘ መጽሐፋቸው ውስጥ፣ «መልአክ ለክርስቲያን ኅብረተሰብና ለቤተ ክርስቲያን ሲባል በእግዚአብሔር የተፈጠረ መንፈሳዊ ፍጥረት ነው» ይላሉ::

ሁልጊዜም የመላእክትን መኖር ላንገነዘብ እንችል ይሆናል:: እንዴት ሊገለጡ እንደሚችሉም ልንተነብይ አንችልም:: ሆኖም መላእክት ጎረቤቶቻችን እንደሆኑ ይነገራል:: ብዙ ጊዜ መኖራቸውን ሳንገነዘብ አብረውን ይኖሩ ይሆናል:: ስለማያቋርጥ አገልግሎታቸው የምናውቀው በጥቂቱ ነው:: ሆኖም መላእክት ይሰጡን የነበረውን የትኵረት ደረጃ ዓይኖቻችን ተከፍተው የምናይበትና የምንገነዘብበት ጊዜ እንደሚመጣ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (1ኛ ቆሮንቶስ 13:11፣ 12)::

የብዙ ክርስቲያኖች ተሞክሮ መላእክት ያገለግሏቸው እንደ ነበረ ያስረዳል:: ሌሎች ደግሞ መገልገላቸውን ላይገነዘቡ ቢችሉም፣ በመላእክት መጐብኘታቸው ግን እውነት ነበር:: መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በክርስቶስ ደም የተዋጁትን እንዲያገለግሉ መላእክትን እንዳዘዘ ይናገራል::

## ዳንኤልና መልአኩ

ዳንኤል በብሉይ ኪዳን ውስጥ በእግዚአብሔር መልአካዊ ኃይላትና በተቃዋሚው የጨለማው መናፍስት መካከል የተካሄደውን የመረረ ውጊያ በግልጽ ያብራራል:: መልአኩ ወደ እርሱ ከመምጣቱ በፊት ለሦስት ሳምንታት ሲያለቅስ ቆይቷል (ዳንኤል 10:3):: እንጀራና ሥጋ አልበላም፣ ወይን አልጠጣም፣

ቅባትም አልተቀባም:: ጤግሮስ በተባለው ወንዝ አጠገብ ቆሞ ሳለ በፍታ የለበሰውን ሰው አየ:: የሰውዬው ፊት እንደ መብረቅ፣ ዓይኖቹም እንደሚንበለበል ፋና፣ ድምፁም እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ ነበር::

ዳንኤል ራእዩን የተመለከተው ብቻውን ነበር:: አብረውት የነበሩት ሰዎች ራእዩን ያልተመለከቱት ሲሆን፣ ትልቅ ፍርሃት ስለወደቀባቸው ሊደበቁ ሮጡ:: የሰማያዊው ፍጥረት ጉብኝት የዳንኤልን ጉልበት አዛለው::

ዳንኤል የመልአኩን ድምፅ የሰማው በታላቅ እንቅልፍ ውስጥ ሳለ ነበር:: አንድ እጅ ከነካው በኋላ መልአኩ የራሱን ተሞክሮ ገለጸለት:: ዳንኤል መጸለይ ከጀመረበት ወቅት አንሥቶ መልአኩ ወደ እርሱ መምጣት የጀመረ ቢሆንም፣ የሰይጣን ልዑል በመንገዱ ላይ ሸምቆ በመዋጋት አዘገየው:: ከዚያም ሚካኤል መጥቶ ይህንን ተራ መልአክ በመርዳት የተላከውን ተልዕኮ ለዳንኤል እንዲያደርስለት አስቻለው::

መልአኩ ለዳንኤል የሚያደርሰው መልእክት ነበረው:: እግዚአብሔር ለዳንኤል በዓለም ላይ በተለይም በመጨረሻው ዘመን በእስራኤል ላይ ሊሆን ያለውን ሊያሳየው ፈልጎ ነበር:: ዳንኤል መልእክቱን ከሰማ በኋላ ለመናገር አቅም በማጣቱ መልአኩ ከንፈሩን በመዳሰስ ጉልበቱን አበረታው:: መልአኩ ተልዕኮውን ከፈጸመ በኋላ በመልካምና በክፉ ኃይላት መካከል በሚካሄደው የማያቋርጥ ጦርነት ውስጥ ከአጋንንት አለቃ ጋር ለመዋጋት እንደሚመለስ ለዳንኤል ነገረው:: በዚህ ሁሉ ዳንኤል ቅዠት ወይም ሕልም እያለመ አልነበረም:: ከእውነተኛ ሰው ጋር እውነተኛ ውይይት እያካሄደ ነበር:: ዳንኤልም የተገነዘበው ይህንኑ ነበር::

ዳንኤል ስለ እስራኤል ልጆች እግዚአብሔርን ይለምን ነበር:: ከጾም ጋር ያደረገው የጸሎት ክፍለ ጊዜ ሦስት ሳምንታት የቆየ ነበረ:: በዚያው ጊዜ ጸሎቱ ለመሰማቱ «ከጉብኚው መልአክ» መልእክቱን ተቀበለ:: ይህ ሁኔታ መዘግየት መቅረት አለመሆኑንና የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ በሕይወታችን ሁሉ እንደሚገለጥ በግልጥ ያሳያል::

# በሥራ ላይ ያሉ የማይታዩ ኃይላት

በተለያዩ የዓለም ቀውሶች ወቅት ከተለያዩ ርእሰ ብሔሮችና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ጋር የመነጋገር ዕድሉ ገጥሞኝ ነበረ:: ለምሳሌ ያህል፣ (እ.አ.አ.) በ1967 ዓ.ም በተካሄደው የመካከለኛው ምሥራቅ ጦርነት ወቅት በወቅቱ የምኖርባትን የደቡብ ካሮላይና ከተማን ይጎበኙ የነበሩትና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ዲን ሩስክ ወደ ማረፊያ ክፍላቸው ጋብዘውኝ ነበር:: በዚያን ወቅት ስለተቀሰቀሰው ጦርነት እየተነጋገርን ሳለ፣ «መለኮታዊ ኃይላት በሥራ ላይ መሆናቸውን» እንደማምን ነገርኳቸው::

በፎርድ አስተዳደር ወቅት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ኪሲንጀር በአንድ ምሽት ከአገር ውጭ ወደ ተላኩበት ተልዕኮ በሚሄዱበት ዋዜማ ዓለምን እያንገዳገዷት ስላሉ አንዳንድ ችግሮች ገለጻ አደረጉልኝ:: እኔም ዓለም የማይታይ መንፈሳዊ ጦርነትን እየተጋፈጠች መሆኗን፣ የጨለማው ኃይላት የእግዚአብሔርን ኃይላት በመዋጋት ላይ መሆናቸውን እንደማምን ነገርኳቸው:: ያለፉትን አሥርት ዓመታት በሚያስቸግር ሁኔታ እንዳሳለፍን ሁሉ፣ የማይታዩ የአጋንንት አሠራሮች እየጨመሩ ስለመሄዳቸው የበለጠ እርግጠኛ እየሆንሁ መጥቻለሁ:: በአንድ በታወቀ የቴሌቪዥን ዜና ዘጋቢ ቢሮ ውስጥ ሳለን፣ «ዓለም ከቁጥጥር ውጪ ሆናለች» አለኝ:: እንዲህ ዓይነት ጦርነት መካሄዱ የማይታመን ቢመስልም፤ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ይህንኑ እውነታ ያረጋግጣል!

ዶ/ር ኤ. ሲ. ጋቤለይን ይህን «የዘመናት ግጭት» ብለው ይጠሩታል:: መፍትሔ የሚያገኘውም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር በሚመለስበት ወቅት ብቻ ነው:: ለዚህም ነው ዓለም «የመሪ ያለህ» እያለ የሚጮኸው:: የሰይጣን «ግንባር» የሆነው ፀረ ክርስቶስ ለጥቂት ጊዜ ስፍራውን በመያዝ የይምሰል ምላሽ ይሰጣል:: ሆኖም ከጥቂት ወራት በኋላ ዓለም ወደ ግጭትና ወደ ሁከት ታመራለች:: የተገኘውም መፍትሔ «ውሸት» መሆኑ ይረጋገጣል (2ኛ ተሰሎንቄ 2:3-10):: ከዚያም እግዚአብሔር ከዘመናት በፊት የመረጠውና የቀባው ክርስቶስ ከኃይሉና ከቅዱሳን መላእክቱ ጋር ወደ ምድር

ይመስላል፡፡ በዘመኑ መጨረሻ ሰይጣንና ጭፍሮቹን ወደ ዘለዓለም ባሕር ይጥላቸዋል፡፡ ስለሆነም እውነተኛ አማኝ ለሆነው አሁን የተቀጣጠለው ውጊያ እግዚአብሔር እጁን በሚዘረጋበት ወቅት ይጠናቀቃል፡፡ ያን ጊዜ ጽድቅ ያሸንፋል፡፡

## የያዕቆብ ልምምድ

ያዕቆብ ከመላእክት ጋር የነበረው ልምምድ እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጣቸውን አገልግሎት በአስደናቂ ሁኔታ የሚገልጽ ነው፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ያዕቆብ አታላይ ነበር፡፡ የብኵርና መብቱን ከወንድሙ ሰርቋል፡፡ አባቱ ዓይኑ ማየት በተሳነው ወቅት አባቱን ዋሽቶ አታሎታል፡፡ ሊገድለው ከነበረው ወንድሙ ሸሽቶ አምልጧል፡፡ የአጎቱን የላባን ሁለት ሴት ልጆች ከማግባቱም በላይ አባታቸውና ወንድሞቻቸው እንዳልወደዱት ባየ ጊዜ ቤተሰቡንና መንጋውን በመያዝ ወደ ከነዓን ተመልሷል፡፡

ምንም እንኳ ያዕቆብ ብልጥ፣ አቃጅና በማታለል የተካነ ቢሆንም፣ «በተስፋ ሐረግ» ውስጥ ስለነበር እግዚአብሔር ለእርሱ ይገደው ነበር፡፡ ከእርሱ አሥራ ሁለቱ የእሥራኤል ነገዶች ይወጡ ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ቤቱ እየሄደ ሳለ «የእግዚአብሔር መላእክት ተገናኙት» ብሎ ይናገራል፡፡ በሆነው ያዕቆብ ከመገረሙ የተነሣ «እነዚህ የእግዚአብሔር ሠራዊት ናቸው» ብሏል (ዘፍጥረት 32:2)፡፡ የቦታውንም ስም «መሃናይም» ብሎ ጠራው፡፡ ትርጓሜውም «ሁለት ሰፈሮች» ማለት ነው፡፡ መላእክቱን «የእግዚአብሔር ሠራዊት» ብሎ ጠራቸው፡፡ ታሪኩ ግን በዚሁ አያበቃም፡፡ ወንድሙ ዔሳውን ቀደም ሲል ስላታለለው ይገድለው ወይም በሰላም ይቀበለው እንደሆነ ባለማወቁ ፈራ፡፡ ስለሆነም ያዕቆብ የእግዚአብሔር የመጨረሻ አነስተኛው ምሕረት እንኳን እንደማይገባው ተገንዝቦ ጸለየ፡፡ እግዚአብሔር ከወንድሙ ከዔሳው እጅ እንዲያድነው ጠየቀ፡፡

ያዕቆብ ከዔሳው ጋር ከመገናኘቱ በፊት በነበረው ሌሊት ቤተሰቡንና ባሪያዎቹን አስቀድሞ ከሰደደ በኋላ ብቻውን ነበር፡፡ ድንገት አንድ ሰው መጣና እስከ ንጋት ድረስ ታገለው፡፡

በመጨረሻም የያዕቆብን ጭን ሲነካው «የጭኑ ሹልዳ ወለቀ»:: በዚህ ወቅት ያዕቆብ ሰውዬው የሰማይ ጉብኚ መሆኑን ስለተገነዘበ፣ እስኪባርከው ድረስ ሰውዬውን ላለመልቀቅ ወሰነ:: ለእንግዳው ስሙን በነገረው ጊዜ ሰውዬው፣ «ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል፤ ከእግዚአብሔር ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና» አለው:: ያዕቆብ ሰውዬው ራሱን ይገልጥ ዘንድ በጠየቀው ወቅት ምንም መልስ አላገኘም:: ሰውዬው ግን በዚያው በነበረበት ስፍራ ባረከው:: ያዕቆብ ስፍራውን ጵኒኤል ብሎ ጠራው:: ትርጉሙም «የእግዚአብሔር ፊት» ማለት ሲሆን፣ «እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ፣ ሰውነቴም ድና ቀረች» አለ (ዘፍጥረት 32:24-30)::

በዚህ ጊዜ የሰውን አካል ለብሶ ለያዕቆብ የታገለው ምናልባት ኢየሱስ ሊሆን ይችላል:: ቀደም ባለው ታሪኩ ውስጥ ብዙ መላእክት ያዕቆብን ከብበውት ነበር:: ባሳለፋቸው ሁለት ልምምዶች እግዚአብሔር በያዕቆብ ሕይወት ላይ ያለውን ዓላማ በይበልጥ ገለጸለት:: ልዑል እንደሚሆንም ቃል ገባለት:: ስለሆነም በሚቀጥለው ቀን ዔሳውን ለመገናኘት ደስ እያለው ሄደ:: ሁሉም ነገር ለራሱና ለቤተሰቡ መልካም ሆነለት:: ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ፣ ሆሴዕ ስለዚህ ሁኔታ ሲመሰክር የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር በመልአክ መልክ ተገልጦ ያዕቆብን አገልግሎታል ሲል መስክሯል (ሆሴዕ 12:3-6)::

ምናልባትም ሙሴና አብርሃም በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኙ ሁለት ታላላቅ ገጸ ባሕርያት ሳይሆኑ አይቀሩም:: አስፈላጊ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ መላእክት በእነዚህ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ገብተዋል:: መላእክት አብርሃምን እንዴት እንዳገለገሉት ቀደም ሲል ተመልክተናል:: ቀጥለን የሙሴን የቍጥቋጦ ልምምድ እንመለከታለን::

## ሙሴ ከመልአክ ጋር ሲገናኝ

የዚህን ታሪክ መነሻ መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል:: ሙሴ ከግብፅ ሕዝብ መካከል ቋንቋውን፣ ባህሉንና ሕጎችን በማወቅ ለአርባ

ዓመታት ኖረ:: በግብጽ ምቾት የበዛበት ኑሮ ይኖር የነበረ ሲሆን፣ በማኅበራዊ ደረጃውም ከፍተኛ ሥልጣን ነበረው:: ከዚያ አንድ ግብጻዊ ሰው ከመግደሉ የተነሣ ወደ በረሃ ተሰደደ:: ለአርባ ዓመታት «በብቸኝነት ኑሮ» ውስጥ የበግ ጠባቂነትን ተማረ:: የእግዚአብሔር ቃል ስለዚያ ዘመን ብዙ ባይናገርም፣ ከፈርዖን ቤተ መንግሥት ወደ በግ እርቢነት መተላለፉ ከፍተኛ ለውጥ ነበር:: እረኝነት በኅብረተሰቡ ውስጥ እንደ ትልቅ ሥራና ደረጃ አይቆጠርም ነበር:: ከቀድሞው ሕይወቱ ጋር ሲመዛዘን የተረሳና ብቸኛ ፍጡር ነበር:: እግዚአብሔር ላሰበው አገልግሎት ለመድረስ 40 ዓመታት ፈጅቶበታል:: ስለሆነም የብዙ ሰዎች የሕይወት ዘመን በሚጠናቀቅበት በ80 ዓመት ዕድሜው ላይ ሙሴ ለእግዚአብሔር ጥሪ ብቁ ሰው ሆነ::

አንድ ቀን ለሥራ በተሰማራበት ወቅት ሙሴ ቁጥቋጦው ሲነድ ተመለከተ:: ነገር ግን የእሳት ነበልባል እየታየበት ቁጥቋጦው አለመቃጠሉ ሙሴን አስገረመው:: ከዚህ ባሻገር ደግሞ «የጌታ መልአክ በእሳት ነበልባል ውስጥ ከቁጥቋጦው መካከል ሆኖ ታየው::» ከዚህ በፊት ሙሴ መልአክ አይቶ ስለማያውቅ ይህ ለእርሱ የላቀ ጉብኝት ሳይሆን አይቀርም:: በተጨማሪም ጉጉቱ እየናረ የሄደ ሲሆን፣ እግዚአብሔር ራሱ ከቁጥቋጦው ውስጥ ለሙሴ ተናገረው::

ሙሴ እጅግ ተገረመ:: በተቀደሰ መሬት ላይ እንደ ቆመና ጫማውን እንዲያወልቅ ከተናገረው በኋላ፣ እግዚአብሔርም የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ መሆኑን ይተዋወቀዋል:: በዚህን ጊዜ ሙሴ በመደነቅና በታላቅ ፍርሃት ተዋጠ:: እግዚአብሔርን ማየት ስለ ፈራ ፊቱን ሸፈነ:: ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን መሪ አድርጎ በመጠቀም እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት ነፃ ለማውጣት ያለውን ዕቅድ ገለጸለት:: ከእስራኤላውያን ጋር በሚገናኝበት ወቅት ማን ላከህ ብለው ቢጠይቁኝ ማን ልበላቸው ብሎ በሙሴ በተጠየቀ ጊዜ፣ እግዚአብሔር «ያለና የሚኖር ነው ወደ እናንተ የላከኝ» ብሎ መለሰለት::

ሙሴ እግዚአብሔር እንዲያደርግ ለጠየቀው ነገር ጉጉት

አልነበረውም። ከአገልግሎቱ ለማምለጥ ጠንካራ ናቸው የሚላቸውን ምክንያቶች ማቅረብ ጀመረ። በመጀመሪያ የእስራኤል ልጆች ሊያምኑት እንደማይችሉና አመራሩን እንደማይቀበሉ ተናገረ። በምላሹም እግዚአብሔር በእጁ ምን እንዳለ ጠየቀው። ሙሴም «በትር ነው» አለ። እግዚአብሔርም «በመሬት ላይ ጣለው» አለው። ወዲያውኑም ወደ እባብነት ተለወጠ። ሙሴ ባነሣው ጊዜ ግን ተመልሶ በትር ሆነ። ከዚያም በእግዚአብሔር ትእዛዝ እጁን ወደ ብብቱ አስገብቶ ሲያወጣው ለምጻም ሆኖ አገኘው። ሆኖም ለሁለተኛ ጊዜ አስገብቶ ሲያወጣው ከበሽታው ሁሉ ነፃ ሆኖ አገኘው። እግዚአብሔር በእነዚህ ምልክቶች የሙሴን መለኮታዊ ውክልና ለሕዝቡ እንደሚያሳይ ነገረው።

ከዚያም ሙሴ ሌላ ማመካኛ አመጣ። ተናግሮ ለማሳመን የሚችል አንደበተ ርቱዕ አለመሆኑን ገለጸ። ምናልባትም ይህ ለአርባ ዓመታት ጸጥታ በሰፈነበት በረሃ ውስጥ ከመኖሩ ሳቢያ የተከሰተ ችግር ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር ግን አሮን ድምፅ ይሆንለት ዘንድ እንደሚልክለት ከመግለጹ በስተቀር ይህንን ምክንያቱን አልተቀበለውም። ስለሆነም ሙሴ ነፃ የማውጣት ሥራውን ለማከናወን ከበረሃ ወደ ግብፅ ተጓዘ። ነገር ግን ይህ ክስተት በሚቃጠለው ቍጥቋጦ ከተገለጸለት የጌታ መልአክ ጋር በጥብቅ የተያያዘ በመሆኑ ለጥናታችን አስፈላጊ ነው። እዚህ ላይ የምናየው እግዚአብሔር መላእክትን በመጠቀም (ወይም እንደ መልአክ ሆኖ በመገለጥ) ውሳኔዎቹን ለሰዎች ያስተላለፈ መሆኑን ነው።

የመላእክቱ መገለጥ «ከግብፅ የመውጣት ልምምድ» አንዱ አካል ሆኗል። መጽሐፍ ቅዱስ በዘኍልቍ 20:16 ላይ፣ «ወደ እግዚአብሔርም በጮኽን ጊዜ ድምፃችንን ሰማ። መልአክንም ሰድዶ ከግብፅ አወጣን» ይላል። ኢሳይያስም «በጭንቀታቸው ሁሉ እርሱ ተጨነቀ፣ የፊቱም መልአክ አዳናቸው በፍቅሩና በርኅራኄውም ተቤዣቸው። በቀደመውም ዘመን ሁሉ አንሥቶ ተሸከማቸው» ይላል (63:9)። ከእነዚህ አጋጣሚዎች አንዳንዶቹ የሥላሴ ሁለተኛ አካል የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በመልአክ መልክ የተገለጠባቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ግምት ብቻ ነው። ይህም፣ «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለምም ያው ነው» (ዕብራውያን 13:8) ብሎ

ያወጀውን የጳውሎስን ምስክርነት ሕያው የሚያደርግ ነው።

## የመላእክት ምሥጢርነት

ኢየሱስ ራሱንና ፈቃዱን እየገለጸልን በመንፈሱ ከእኛ ጋር እንደሆነ ሁሉ፣ ከዚህ በፊትም በዘመናት ሁሉ ከሕዝቡ ጋር አብሮ ነበረ። ይህ የሚመራንና የእግዚአብሔርን መገኘት አመልካች መልአክ ለሚቀጥሉትም ዘመናት እንዲሁ ከእኛ ጋር ይሆናል። ባለፉት ዘመናት ለነበሩት «ታማኞቹ»፣ እግዚአብሔር አብ በመላእክቱ በኩል ሕልውናውን ገልጿል። በጌታ መልአክ አማካይነት ራሱን ገልጾ የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስቅላት፣ ሞትና ትንሣኤ ዋጅቶናል። እዚህ ላይ ማንኛ ችንም ሙሉ በሙሉ ልንረዳ የማንችለው ጥልቅ ምሥጢር አለ።

የአይሁድ ምሁራን የጌታን መልአክ «ሜታትሮን፤ የመጽናናት መልአክ» ብለው ይጠሩታል። ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ማጽናናት ካለማቋረጥ የሚመሰክርና እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ያለውን ዕቅድ ለማሳወቅ የሚሠራ ስለሆነ ነው።

እግዚአብሔር ምሉዕ የሆነ ራእይን ማለትም ኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋ ሰጥቶናል። ስለሆነም በዚህ በጸጋ ዘመን ራሱን «በጌታ መልአክ» መልክ መግለጽ አያስፈልገውም። ስለሆነም በአዲስ ኪዳን ዘመንና ዛሬም የሚገለጡ መላእክት «የተፈጠሩ መናፍስት» ናቸው እንጂ በብሉይ ኪዳን ዘመን በተለያዩ ጊዜያት በልዩ የመልአክ አካል የሚገለጠው እግዚአብሔር አይደለም። በብሉይ ኪዳን ዘመን እንደነበረው የእግዚአብሔር ልጅ በአካል መገለጹ አሁን አስፈላጊ አይደለም። በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ልጅ ሥጋ ለብሶ በቤተልሔም መወለዱን ካበሰረው መልካም ዜና ተከትሎ መላእክት የተገኙ መሆኑን አስተውል። በዚያን ወቅት መላእክቱ ያለአግባብ ቦታ ለመያዝ ወይም ለማጣመም ሳይሆን የክርስቶስን ወንጌል ለማጽናትና የእግዚአብሔርን መልእክት ለማስተላለፍ ነበር የተገለጡት።

# መላእክት የሚያገለግሉ መናፍስት ናቸው

እግዚአብሔር በጸጋ ለዳኑት ሰዎች መልእክቱን ለማድረስ መላእክትንና ሰዎችን ይጠቀማል:: «ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ መናፍስት አይደሉምን?» (ዕብራውያን 1:14):: ለሌሎች ካደረግነው የታመነ ምስክርነት የተነሣ መላእክት እኛን በየስማችን ማወቃቸው ምን ዓይነት ከፍተኛ ክብር ይሆንላቸው ይሆን? መላእክት ወንጌልን መስበክ ባይችሉም ንስሐ በሚገቡ ሰዎች አብረውን ሐሴት ያደርጋሉ (ሉቃስ 15:10)::

በዚህ ረገድ በስማርያ ለመንፈሳዊ መነቃቃት እግዚአብሔር የተጠቀመበትን ዲያቆኑን ፊልጶስን አስተውሉ:: መልአክ ተገልጦ በሰጠው መመሪያ መሠረት ወደ በረሃ ከሄደ በኋላ በእግዚአብሔር ቀጠሮ የእውነትን ቃል ለመስበክ የእግዚአብሔር ድምፅ በመሆን ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ተገናኘው (የሐዋርያት ሥራ 8:26)::

መላእክት ዮሐንስንም ጐብኝተውታል:: በፍጥሞ ደሴት ወንዙን እየተመለከተ ከሰማይ በስተቀር ከሌሎች ነገሮች ሁሉ ለምን እንደ ተነጠለ በማሰብ እየገረመው ሳለ፣ የትንቢትን መልእክት የያዘ መልአክ መጣለት:: ይህም መልእክት በዮሐንስ ራእይ ውስጥ የሚገኘውን የመጨረሻ ዘመን ትንቢት ነበር (የዮሐንስ ራእይ 1:1-3)::

በዳንኤል የሕይወት ገጠመኝ ውስጥም መልአክ በተመሳሳይ ሁኔታ አገልግሎታል:: በምዕራፍ አምስት ውስጥ ትልቅ ድግስ በባቢሎን ውስጥ በብልጣሶር እንደ ተዘጋጀ ተገልጿል:: ዝግጅቱ የተደረገው የመንግሥቱን ክብር ለማሳየት ነው ቢባልም፣ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ብልጣሶር የራሱን ታላቅነት ለማሳየት ነበር የወጠነው:: ይህ በመንግሥቱ ውስጥ ለሚገኙ በሺዎች ለሚቆጠሩ የተከበሩ ሰዎች ያዘጋጀው ግብዣ ነበር:: ሆኖም በዚህ ከፍተኛ ዝግጅት ላይ ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ያመጧቸውን ጽዋዎች ስተዋረደ ጉዳይ በማዋል አረከሱት:: በሉ፣ ጠጡም ደግሞም ለእንጨትና ለድንጋይ ለብርና ለወርቅ አማልክት ክብርን ሰጡ:: ቍሳዊው ጣዖት በሥልጣን ላይ ነበር:: ድንገት የሰው ልጅ ጣቶች ተገልጸው በባቢሎን ላይ የመጣውን የእግዚአብሔርን የፍርድ ቃል በግድግዳው ላይ ጻፉ:: «ማኔ፣ ቴቄል ፋሬስ::» -በሚዛን ተመዘንህ

ቀልለህም ተገኘህ፤ መንግሥትህንም ፈጸመው ማለት ነው (ከቍጥር 25-27)። የእግዚአብሔር መልአክ ነበረ ሊመጣ ያለውን ፍርድ ለማወጅ የተላከው። የንጉሡ የብልጣሶር ዘመናት በእግዚአብሔር መቆጠራቸው ብቻ ሳይሆን፣ ፍጻሜውም ተቃርቦ ነበረ።

በኋላም ዳንኤል ለሕዝቡ ጸለየ። ገብርኤል «አስተማረኝም፣ ተናገረኝም እንዲህም አለ፦ ዳንኤል ሆይ፣ ጥበብንና ማስተዋልን እሠጥህ ዘንድ አሁን መጥቻለሁ. . . አሁንም ነገሩን መርምር፣ ራእዩንም አስተውል» (ትንቢተ ዳንኤል 9:22-23)። ዳንኤል ለጸለየው ጸሎት መልስ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር የወደፊቱን የሰውን ዘር «ታሪክ» በተመለከተ አጠቃላይ መግለጫ ሰጠው። በእኔ እምነት ዓለም በዚያን ወቅት እግዚአብሔር ለዳንኤል የሰጠው ራእይ ፍጻሜው ላይ ነች።

በብልጣሶር ዘመን የነበረው ትዕይንት ዛሬ ከምናየውና ከምንሰማው ሁኔታ ጋር በጣም የሚመሳሰል ከመሆኑ የተነሣ፣ ነገሮች በአንድ ዘመን ውስጥ የተከናወኑ ይመስላል። ምናልባትም በዚህ ቀውስ በበዛበት ሰዓት ውስጥ እግዚአብሔር ፍርድን ለማምጣት ሌላ ታሪክ እየጻፈ ይሆናል። ከኃጢአታቸው ንስሐ የማይገቡ ከሆኑ፣ ዘመናቸው እንደ ብልጣሶር እንደሚቆጠርና እንደሚጠናቀቅ በየትኛውም ስፍራ ለሚገኙ ሰዎች እየተናገረ ነው።

ይኼንን የመላእክትን የግል አገልግሎት በተመለከተ እግዚአብሔር መላእክት ዕቅዱን ለሰዎች እንዲያስታውቁ በማድረግ የተጠቀመባቸውን አንዳንድ ሁኔታዎች በማንሣት እናጠናቅቅ።

## መልአኩ ገብርኤል

በአዲስ ኪዳን መጀመሪያ ካህኑ ዘካርያስ ለተስፋው ቃል መሢሕ መንገድ የሚጠርገውን የዮሐንስን ልደት ያወጀውን የጌታን መልአክ የተመለከተው ሲሆን፣ መልእክቱንም ከእርሱ ተቀብሏል። መልአኩ (በዚህ ወቅት የተገለጠው ልዩ መልአካዊ የተስፋ ቃል አገልጋይ የሆነው ገብርኤል ነበር) የዮሐንስ ልደትን በተመለከተ ዙሪያውን የከበበውን ተአምር ያምን ዘንድ ዘካርያስን አበረታታው። ከዚያም በመቀጠል ገብርኤል ስለ ትስብእት፣ ማለትም የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በማኅፀኗ ውስጥ

እንደሚረገዝ ስለሚያስረዳው መለኮታዊ ዕቅድ ለድንግል ማርያም ተገልጾ አወጀላት:: ማርያም ጥያቄዎች የነበሯት ቢሆንም፣ መልአኩ፣ «መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፣ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል:: ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል» ብሎ በመመስከር መለሰላት (ሉቃስ 1:35):: የአገልግሎትና የመገለጥ ልዩ መልአክ የሆነው ገብርኤል ይህንን መልእክት ለማርያም ከማምጣቱም በላይ እርሱ ወይም ሌላ መልአክ ደግሞ ዮሴፍ ማርያምን እንደ ሚስቱ እንዲወስዳት አረጋገጠለት:: «ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ» (ማቴዎስ 1:20):: በተጨማሪም፣ በእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት፣ ኢየሱስ «ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና» ብሎ ለዮሴፍ ነገረው (ማቴዎስ 1:21)::

ጭቆና፣ ተስፋ መቍረጥና ጥንካሬ በተዳከመባቸው ጊዜያት የመላእክት መልእክቶች ክፍለ ዘመናትን በመደልደል ክርስቲያኖች በታማኝነት እንዲያልፉ አድርገዋል:: የእግዚአብሔር የሚያድሱ ባሪያዎችና መለኮታዊ መልእክተኞች የሚንገዳገዱ ቅዱሳንን መንፈስ በማነሣሣት አጽንተዋቸዋል፤ አበረታትተዋቸዋልም:: ተስፋ የተቆረጠባቸውን ብዙ ሁኔታዎችንም ብሩህ ወደ ሆነ ሁኔታ ለውጠዋል:: የሕዝቡን አካላዊ፣ ቍሳዊ፣ ስሜታዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶች ለማሟላት፣ መላእክቱ «ሁሉም መልካም ነው» በሚለው መልእክት አገልግለዋል:: ሰዎች «የእግዚአብሔር መልአክ ወደ እኔ መጥቶ ነበር» ብለው ለመመስከር ይችላሉ::

## ስምንት

# መላእክት ይጠብቁናል፣ ነፃ ያወጡናልም

የእግዚአብሔር ኃያላንን መላእክት ሁልጊዜ አጠገባችን እንደሆኑ እኛንም ለመርዳት ዝግጁ ለመሆናቸው የእግዚአብሔርን ማረጋገጫ ብንቀበል ኖሮ፣ ያስሟቋረጥ የሚዋጉን የክርስቶስ ጠላቶች ብዙ ጊዜ በተሸነፉ ነበር:: የሚያሳዝነው ብዙ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ በተጠቀሰው መሠረት አብዛኛዎቹ ክርስቲያኖች ይህንን እውነት ለመቀበል ያዳግታቸዋል:: በሄድኩባቸው ጉዞዎቼ የተረዳሁት ነገር ቢኖር የበለጠ ወደ ክርስትና የእምነት ድንበር በቀረብሁ ቁጥር በአማኞች ዘንድ በመላእክት ላይ የበለጠ እምነት እንዳለ ተገንዝቤያለሁ:: በመቶዎች የሚቆጠሩ ታሪኮች የሚያስደንቀውን መለኮታዊ ጣልቃ ገብነት በየዓመቱ ይዘግባሉ:: እግዚአብሔር መላእክቱን እንደሚያገለግሉ መናፍስት ይጠቀምባቸዋል::

## መላእክት መለኮታዊ ጠባቂዎች ናቸው

የእግዚአብሔር መላእክት ባሪያዎቹን ብዙ ጊዜ ከሽማቂ ጠላቶች ይጠብቋቸዋል:: 2ኛ ነገሥት 6:14-17 ያለውን ብትመለከት፣ የሶርያው ንጉሥ ነቢዩ ኤልሳዕ በዚያ መሆኑን በማወቁ ሠራዊቱን ወደ ዶታይን በአስቸኳይ ልኳል:: የነቢዩ ረዳት ጠዋት ልብሱን እየለበሰ በነበረበት ወቅት ለኤልሳዕ አካባቢው በሙሉ በጠረኞችና በጦር መሣሪያዎች መሞላቱን በመደነቅ ይገልጽለታል (ቁጥር 16):: ከዚያም ኤልሳዕ እግዚአብሔር የወጣቱን ዓይኖች እንዲከፍትና በዙሪያው ያሉትን ጠባቂዎች የመላእክት ሠራዊት እንዲመለከት ጸለየ:: ይህንን ሲያደርግ ወጣቱ በዙሪያው ሁሉ ከተማውን የከበቡትን የእሳት ሰረገላዎችና ፈረሶችን ለመመልከት ቻለ:: ይህ ምንባብ ለአገልግሎቴ ታላቅ ማረጋገጫዎችና መጽናኛ ከሆኑኝ ክፍሎች አንዱ ነው::

መላእክት በመከራና በአደጋ ወቅት ለእግዚአብሔር ባሪያዎች አገልግሎትን ይሰጣሉ። ሌላ ጉልህ ገለጻ የምናገኘው በሐዋርያት ሥራ 27:23-25 ባለው ክፍል ላይ ነው። ጳውሎስ ወደ ሮም በመጓዝ ላይ እያለ ከሁለት መቶ የበለጡ ተሳፋሪዎች የነበሩት መርከብ ተሰበረ። በዚህ ጊዜ ጳውሎስ በፍርሃት ለተዋጡት የመርከቡ ሠራተኞች፣ «የእርሱ የምሆንና ደግሞ የማመልከው የእግዚአብሔር መልአክ በዚች ሌሊት በአጠገቤ ቆሞ ነበርና፣ እርሱም:- ጳውሎስ ሆይ፣ አትፍራ፤ በቄሣር ፊት ልትቆም ይገባሃል፤ እነሆም፣ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር የሚሄዱትን ሁሉ ሰጥቶሃል አለኝ» ብሎ ተናገራቸው (ከቁጥር 23-24)።

አንዳንድ ሰዎች እያንዳንዱ ክርስቲያን የተመደበለት ወይም የተመደበላት የግል ጠባቂ መልአክ ሊኖራቸው ይችላል ብለው ያምናሉ። ይህ ጥበቃ ከሕፃንነት የሚጀምር ይመስላል። ምክንያቱም ኢየሱስ በማቴዎስ 18:10 ላይ፣ «ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ መላእክቶቻቸው በሰማያት ዘወትር በሰማያት ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ እላችኋለሁና» ብሏል።

## መላእክት ለእኛ ሲሠሩልን

የመላእክት ጠቃሚ ባሕርይ የእኛን ሕይወት ለመቆጣጠር ሥልጣን ስላላቸው ወይም ውብ ስለሆኑ ሳይሆን፣ በእኛ ምትክ ሥራችንን የሚሠሩልን በመሆናቸው ነው። ለእግዚአብሔር ካላቸው የማያልቅ ፍቅር የተነሣ የእግዚአብሔር ፈቃድ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእኛ ውስጥ መፈጸሙን ለማየት ይቀናሉ።

ዳዊት መላእክትን በተመለከተ፣ «በልዑል መጠጊያ የሚኖር ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ውስጥ ያድራል. . . በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና፤ እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡሃል» ብሏል [መዝሙረ ዳዊት (91):1፣ 11፣ 12]።

ባለቤቴ ሩት በቻይና አገር በሻንጋይ የክርስቲያን መጻሕፍት መደብር ውስጥ ስለተፈጸመ እንግዳ ክስተት እንዲህ ትላለች። ጉዳዩን የሰማችው በኪያንግሱ ክፍለ አገር በዲንግኪያንግፑ ሆስፒታል ያገለግሉ ከነበሩት ከአባቷ ከዶክተር ኤል ኔልሰን ቤል

ነበር። ዶ/ር ቤል ለበሽተኞች የሚያድሏቸውን የወንጌል ክፍሎችንና በራሪ ጽሑፎችን (ትራክቶችን) የሚገዙት ከዚህ ሱቅ ነበር።

ሁኔታው የተከሰተው ጃፓኖች የቻይናን የተወሰነ ክፍል ከተቆጣጠሩ በኋላ (እ.ኤ.አ.) በ1942 ነበር። አንድ ቀን ጥዋት በሦስት ሰዓት አካባቢ አምስት የባሕር ኃይል የጦር አባላትን የያዘና ገሚሱ በመጽሐፍ የተሞላ ከባድ መኪና መጽሐፍ መደብሩ ደጃፍ ላይ ቆመ። በዚያን ወቅት ብቻውን የነበረውና ክርስቲያን የሆነው ቻይናዊ የሱቁ ሠራተኛ መጻሕፍቱን ሊወስዱ መምጣቸውን በድንጋጤ ተገነዘበ። በተፈጥሮው ፈሪ ስለነበር፣ ይህ ከዓቅሙ በላይ እንደሚሆንበት ገባው።

የባሕር ኃይል ጦር አባላቱ ከመኪናው ዘልለው በመውረድ ወደ ሱቁ ማምራት ጀመሩ። ሆኖም ከመግባታቸው በፊት አንድ ንጹሕ ልብስ የለበሰ ቻይናዊ ከእነርሱ ቀድሞ ሱቁ ውስጥ ገባ። ሠራተኛው ይህ ሰው በዚያ ስፍራ መጽሐፍ ለመግዛት ከሚመጡት ደምበኞች ሁሉ ፈጽሞ የተለየ እንደሆነ ተገንዝቧል። እነዚያ ወታደሮች ግን ሊታወቅ በማይችል ምክንያት ወደ ሱቁ መግባት ተሳናቸው። በአራቱ ትላልቅ መስኮቶች እየተመለከቱ ወዲህና ወዲያ ይሉ ነበር። እግራቸውን ወደ ውስጥ ሳያስገቡ ከሁለት ሰዓታት በላይ እዚያው አካባቢ ቆሙ። ያ እንግዳ ሰውም ሰዎቹ ምን እንደሚፈልጉ የሱቁን ሠራተኛ ጠየቀው፤ እርሱም ጃፓኖች በከተማው ውስጥ ካሉት መጻሕፍት ቤቶች ብዛት ያላቸውን መጻሕፍት እየነጠቁ መሆናቸውና አሁን ደግሞ የዚህ ሱቅ ተራ መሆኑን ነገረው። ሁለቱም በጋራ ከጸለዩ በኋላ እንግዳው ሰው እያበረታታው ሁለት ሰዓታት አለፉ። በመጨረሻም ወታደሮቹ ከባድ መኪናቸው ላይ ተሳፍረው ሄዱ። ያም እንግዳ ሰው በሱቁ ውስጥ ስላለው ዓይነት ዕቃ ሳይጠይቅ ወይም ምንም ነገር ሳይገዛ ወጥቶ ሄደ።

በኋላ በዚያኑ ዕለት የሱቁ ባለቤት የሆኑት ሚስተር ክርስቶፈር ዊሊስ (የቻይና ስማቸው ሊ ይባል ነበር) ተመልሰው ሲመጡ የሱቁ ሠራተኛ፣ «ሚስተር ሊ፣ በመላእክት ያምናሉን?» ብሎ ጠየቃቸው።

ሚስተር ዊሊስም፣ «አዎ አምናለሁ» አሉት። እርሱም «እኔም

አምናለሁ፣ ሚስተር ሊ» አላቸው:: ዶ/ር ቤል ያ እንግዳ ሰው የእግዚአብሔር ጠባቂ መልአክ ነበርን? እያሉ ዘወትር ያስቡ ነበር::

ኮሪ ቴን ቡም በራቬንስብሩክ የናዚ እስር ቤት ውስጥ ስላሳለፈችው አስገራሚ ትዝታ የሚከተለውን ጽፋለች::

«በአንድ ላይ ሆነን ወደሚያስፈራው ሕንጻ ገባን:: አንድ ጠረጴዛ ላይ ንብረቶቻችንን ሁሉ የሚወስዱ ሴቶች ነበሩ:: ሰው ሁሉ ልብሱን ካወለቀ በኋላ ወደ አንድ ክፍል ይወሰድና የጸጉር ፍተሻ ይካሄዳል::

እኔም አዲስ የመጡትን ሰዎች ንብረት በመተፈሽ ላይ ያለችውን ሴት ወደ ሽንት ቤት ለመሄድ እንደምፈልግ ነገርኋት:: እርሷም ወደ አንድ በር ጠቆመችኝ:: መጠቀሚያው በመታጠቢያው ቤት ወለል ላይ ያለውን ቀዳዳ ነበር የሚያህለው:: ቤትሲ ሁልጊዜ ከእኔ አትለይም ነበር:: ድንገት አንድ አሳብ መጣልኝና፣ «ቶሎ በይና ከሐር የተሠራውን የውስጥ ልብስሽን አውልቂ ብዬ በሹክሹክታ ነገርኳት:: ከእርሷ የወሰድኩትን ከራሴ ጋር አብሬ ጠቀ-ለልኩትና ጥቅልሉን ከትንሿ መጽሐፍ ቅዱሴ ጋር ጥግ ላይ አስቀመጥኩት:: ቦታው በበረሮ የተሞላ ቢሆንም፣ ብዙ አልተጨነቅኩም:: ከፍተኛ ነጻነትና ደስታ ነበር የተሰማኝ:: «ጌታ ጸሎታችንን እየመለሰ ነው:: ልብሶቻችንን በሙሉ መሥዋዕት ማድረግ የለብንም» ብዬ በሹክሹክታ ነገርኳት::

ልብሶቻቸውን ለማውለቅ ተራ ከያዙ ሴቶች ጀርባ ሰልፍ ለመያዝ ተቻኮልን:: ጥቂት ቆይተን ገላችንን ከታጠብንና ሽሚዞቻችንንና የቆሸሹ ቀሚሶቻችንን ከለበስን በኋላ የውስጥ ልብስ ጥቅልሉንና መጽሐፍ ቅዱሴን ከቀሚሴ ሥር ደበቅኩት:: ከዚያም፣ «ጌታ ሆይ፣ ዘበኞቹ እንዳያዩኝ መላእክትህ እንዲከብቡኝ አድርግ:: ዛሬ እንዳይታዩ አድርጋቸው» ብዬ ከጸለይኩ በኋላ ፍጹም ተረጋጋሁ:: ዝም ብዬ ዘበኞቹን አለፍኳቸው:: ሁሉም ሰው ከፊት፣ ከጎንና ከጀርባው ይፈተሽ ነበር:: ምንም ዓይነት አበጥ ያለ ነገር ዘበኞቹ ሳያዩት አያልፉም ነበር:: አንዲት ሴት የሐር ሰደርያ ከቀሚሷ ሥር ደብቃ ተወሰደባት:: እኔን ሲያልፉኝ ከእኔ

ጀርባ የነበረችውን ቤትሲን ግን ፈተሿት።

ነገር ግን ውጪ ስንደርስ ሌላ አደጋ አጋጠመኝ። በሁለቱም በሮች በኩል እያንዳንዱን ሰው ለሁለተኛ ጊዜ የሚፈትሹ ሴቶች ነበሩ። የሚያልፈውን ሰው ሁሉ አትኩረው ቢመለከቱም እኔን ግን መላእክት ስለ ከበቡኝ ሊያዩኝ እንደማይችሉ አውቄ ነበር። ሲያልፉኝ እንኳ ምንም አልተገረምኩም። ነገር ግን «ጌታ ሆይ፣ ጸሎትን የምትሰማ ስለሆንክ ራቬንስብሩክን እንኳ ልጋፈጥ ችያለሁ» የሚል የደስታ ጩኸት ከውስጤ ፈለቀ።

# መለኮታዊ ክትትል

መላእክት በመንገዳችን የሚመለከቱንና የሚጠብቁን ስለሆኑ በክርስቶስ ያለ እያንዳንዱ እውነተኛ አማኝ ሊበረታታና ሊጠናከር ይገባዋል። የእግዚአብሔርን ፍላጐት በማስጠበቅና በሕይወታችን ውስጥ የሚከሰቱትን ሁኔታዎች በበላይነት በመቆጣጠር ተግባራቸውን ያከናውናሉ። ይህንንም የሚያደርጉት ሁልጊዜ ዕቅዶቹን ለመፈጸምና ለእኛ ያለውን ታላቅ ፈቃዱን በመፈጸም ነው። መላእክት ሁሉንም በታዛቢነት የሚመለከቱ ሲሆኑ፣ የምናደርገውን ሁሉ በትኩረት ይከታተላሉ። 1ኛ ቆሮንቶስ 4:9 በቀጥታ ሲተረጐም፣ «ዓለም፣ መላእክትም፣ ሰዎችም ይመለከቱናል» የሚል መልለእክት ያስተላልፋል። እግዚአብሔር መላእክት ይጠብቁን ዘንድ ይልካቸዋል።

የሣራ ደንገጡር የነበረችው አጋር ከአብርሃም ድንኳን ሸሸች። በከፍተኛ ክብር የተሞላ እምነት የነበረው አብርሃም ለባለቤቱ ሽንገላና ነውር እጅ መስጠቱና በዘመኑ የነበረውን ባህል ተቀብሎ ከአጋር ልጅ መውለዱ ግራ የሚያጋባ ነው። ባለቤቱ ሣራ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ልጃቸው ይስሐቅ ሲወለድ አጋርንና ቀደም ብሎ የተወለደውን ልጅ እስማኤልን ለማየት አለመፈለጓም ግራ የሚያጋባ ነገር ነው። ስለሆነም አብርሃም የግል ፍላጎቱን ለማርካት ያደረገው ነገር ወደ ኀዘን ከቶት አጋርን ከቤቱ እንድትወጣ አስገደዳት።

ዳሩ ግን እግዚአብሔር አጋርን ያገለግል ዘንድ መልአኩን ላከ:: «የእግዚአብሔር መልአክም በውኃ ምንጭ አጠገብ በበረሃ አገኛት:: ምንጩም ወደ ሱር በምትወስደው መንገድ አጠገብ ነው» (ዘፍጥረት 16:7):: መልአኩ ካለፈው ጉዳት አእምሮዋን በመመለስ በእግዚአብሔር ላይ እምነቷን ብታደርግ ልታገኝ ስለምትችለው ተስፋ ገለጸላት:: ይህ አምላክ የእስራኤል ብቻ ሳይሆን የዐረቦችም ጭምር ነው:: (ምክንያቱም ዐረቦች ከእስማኤል የዘር ሐረግ የመጡ ናቸው):: የልጇ የእስማኤል ስም ትርጉሙ «እግዚአብሔር ይሰማል» ማለት ሲሆን፣ ስሙም ቀጣይነት ያለው ነው:: እስማኤል እንደ ቀደምት አባቶቹ ከቦታ ቦታ የሚንከራተት ሲሆን፣ እግዚአብሔር የእስማኤል ዘር እንደሚበዛና በዓለም ላይ ፍጻሜው ታላቅ እንደሚሆን ቃል ገብቶአል:: የጌታ መልአክ የአጋርና የእስማኤል ጠባቂ በመሆን ራሱን ገልጦላቸዋል:: አጋር በአክብሮትና በመደነቅ፣ «የሚያየኝን በውኑ እዚህ ደግሞ አየሁትን?» አለች (ዘፍጥረት 16:13):: ይህም፣ «ሁሉን የሚያየውንና እኔን የሚያየኝን አየሁት» ተብሎ ሊተረጐም ይችላል::

መዝሙረ ዳዊት (34):7 መላእክት እንደሚጠብቁንና እንደሚታደጉን የሚያስተምረውን ትምህርት የበለጠ ሲያጠናክር፣ «የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል ያድናቸውማል» ይላል:: ይኼ አሳብ በቻርለስ ዌስሊይ መዝሙር ላይም ተንጸባርቆ እናገኘዋለን::

*መላእክት በምንሄድበት ሁሉ*

*እርምጃዎቻችንን ይጠብቃሉ*

*ጥንቃቄ በተሞላበት ኃላፊነታቸውን ይወጣሉ::*

*ክፋውንም ሁሉ ካጠገባችን ያርቃሉ::*

## ተአምራዊ መታደግ

በጣም ብዙ ክርስቲያኖች ሕይወታቸው ከወሳኝ አደጋዎች መዳኑን የሚያስታውሱባቸው ገጠመኞች ይኖሯቸዋል:: ለምሳሌ፣

ከአውሮፕላን አደጋ፣ ከመኪና ግጭት፣ ከከባድ ፈተና፣ ወዘተ... ምንም እንኳ እነዚህ አደጋዎች መላእክትን ላይመለከቱ ቢችሉም፣ የአደጋው መወገድ የመላእክትን መገኘት ያረጋግጣል:: የሚጠብቁንንና መላእክት በመባል የሚጠሩትን እነዚህን ግሩም ወዳጆች ስለሚጠቀምባቸው፣ የእግዚአብሔርን መልካምነት ዘወትር ልናመሰግን ይገባናል:: የእግዚአብሔር ቃልና የግል ገጠመኞች የሚያረጋግጡልን የሚጠብቁን መላእክት ቢያንስ የተወሰኑ መንገዶቻችንን በትኩረት እንደሚከታተሉና በሕይወታችንም ዙሪያ እያንዣበቡ የሚጠብቁን መሆኑን ነው::

የእግዚአብሔር ቃል መላእክት በምድራዊ አገልግሎታቸው ለእግዚአብሔር ሕዝብ ፍጹም ጥበቃ እንደሚያደርጉ በሚያሳዩ አስገራሚ ማረጋገጫዎች የተሞላ ነው:: ጳውሎስ በክፉው ፊት በጽናት ለመቆም ይችሉ ዘንድ የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ እንዲለብሱ ክርስቲያኖችን መክሯቸዋል (ኤፌሶን 6:10-12):: ውጊያችን ከደምና ከሥጋ ጋር (በዓይን ከሚታዩ ኃይላት ጋር ብቻ) ሳይሆን በሰማይ ካሉት (ከልዕለ ሰብአዊ) ከመንፈሳዊ የክፋት ኃይላት ጋር ጭምር ነው:: የአየር ላይ ገዢ የሆነው ሰይጣን እውነተኛ እምነትን ሳይሆን «ሃይማኖት»ን ነው የሚያስፋፋው:: ሐሰተኛ ነቢያትንም ያበረታታል:: ስለሆነም የብርሃንና የጨለማ ኃይላት በከባድ ውጊያ ውስጥ ናቸው:: የመላእክት ኃይላት የጨለማውን ሥራ የሚዋጉና የሚያሸንፉም ስለሆነ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን:: መላእክት የሚሰጡት አገልግሎት በራስ ወዳድነት ላይ የተመሠረተ አይደለም:: ነገር ግን በሚሰጡት አገልግሎት አማኞች እንዲበረቱና ክብሩ ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሆን ዘንድ ያገለግላሉ:: የመላእክት የጥበቃ ተግባርን የተመለከተ ዓይነተኛ ምሳሌ በሐዋርያት ሥራ 12:5-11 ይገኛል::

ትዕይንቱ ሲከፈት ጴጥሮስ የሞት ቅጣት እየጠበቀ በእስር ቤት ውስጥ ተኝቶ ይገኛል:: ቀደም ሲል የዮሐንስ ወንድም የነበረው ያዕቆብ ተገድሎ ስለነበር ጴጥሮስም የገዳዮችን መጥረቢያ ሊያመልጥ ይችላል ብሎ ለመገመት የሚያስችል ምንም ምክንያት አልነበረም:: ፈራጆቹ ወንጌልንና የእግዚአብሔርን ሥራዎች የተቃወሙትን ሰዎች ለማስደሰት በሚል ነበር እንዲሞት የፈለጉት:: በእርግጥ አማኞች ለያዕቆብም ሳይጸልዩ አልቀሩም::

እግዚአብሔር ግን በሞት ነፃ ሊያወጣው መርጦ ነበር:: አሁን ቤተ ክርስቲያን ለጴጥሮስ ትጸልይ ነበር::

ጴጥሮስ በእንቅልፍ ላይ በነበረበት ወቅት አንድ መልአክ በበሩም ሆነ በብረት መዝጊያዎቹ ሳይታገድ ተገለጠ:: መልአኩ ወደ ውስጠኛው የእስር ቤቱ ክፍል ገብቶ ጴጥሮስን ቀሰቀሰውና ለማምለጥ ራሱን እንዲያዘጋጅ ነገረው:: በእስር ቤቱ ውስጥ ብርሃን ሲበራ የጴጥሮስ ሰንሰለቶች ወደቁና ልብሱን ለብሶ መልአኩን እየተከተለ ወጣ:: መልአኩ እንዳደረገው ጴጥሮስ በተዘጋ በር ውስጥ ለማለፍ ስለማይችል በሩ በተአምራታዊ መንገድ ተከፈተ:: ይህ እግዚአብሔር በመልአኩ በኩል ያካሄደው መታደግ ምን ዓይነት ታላቅ ነው!

## የመላእክት ጣልቃ መግባት

በብሉይና በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙ ብዙ ገጠመኞች የፈለቁት በእስር ላይ የሚገኙ የእግዚአብሔርን ቅዱሳን እግዚአብሔር እንዲታደጋቸው ወይም መላእክት በእርሱ ስም ጣልቃ ገብተው እንዲያድኗቸው ከመለመናቸው ነው:: ዛሬ በጭንቀት ሰንሰለት ምርኮኛ ሆነው የሚመላለሱ ሰዎች ነፃ ለመውጣት ተስፋ እንዳላቸው ሊያምኑ ይችላሉ:: እግዚአብሔር ከሰው ሰው ስለማያዳላ መላእክት በእምነት ወራሾች ለሆኑ ሁሉ አገልግሎትን እንደሚሰጡ ገልጿል::

እኛ የእግዚአብሔር ልጆች የመላእክቱ አገልግሎት ምን ያህል ቅርብ እንደሆነ ብንገነዘብ የኑሮን መቅሠፍቶች ለመጋፈጥ ምን ያህል እርግጠኞች በሆንን ነበር:: ምንም እንኳ እምነታችንን በቀጥታ በመላእክቱ ላይ ማሳደር ባይገባንም፣ እምነታችንን መላእክትን በሚገዛው በእግዚአብሔር ላይ ስንጥል ሰላም ይኖረናል::

ዕብራውያን 11 የብዙ የእምነት ወንዶችንና ሴቶችን ስም ይዘረዝራል:: እግዝአብሔር ከእነዚህ ሰዎች ብዙዎቹን ከበሽታ፣ ከጥፋት፣ ከአደጋና ከሞት ሳይቀር በመታደግ ተአምራትን ሠርቶላቸዋል:: አንድ ሰው ይህንን ምዕራፍ «የእግዚአብሔር የዝና

አዳራሽ» ብሎ ጠርቶታል:: መላእክት እነዚህ ታላላቅ ወንዶችና ሴቶች መንግሥታትን ድል እንዲነሡ፣ ተስፋቸውን እንዲጨብጡ፣ የአንበሶችን አፍ እንዲዘጉ፣ የእሳትን ኃይል እንዲያጠፉ፣ የሰይፍን ስለት እንዲያመልጡና በደከሙ ጊዜ ደግሞ በመላእክት እገዛ ሠራዊቶችን ሙሉ በሙሉ ድል እንዲያደርጉ አስችሏቸዋል::

ሆኖም የታሪኩ ቅኝት በቊጥር 35 ላይ «ሌሎችም መዳንን ሳይቀበሉ የሚበልጠውን ትንሣኤ እንዲያገኙ እስከ ሞት ድረስ ተደበደቡ» በሚሉ ቃላት ይጀምራል:: እነዚህ አሁን የተጠቀሱት ከላይኞቹ ጋር ተመሳሳይ እምነትና ብርታት ነበራቸው:: ይሁንና፣ የከፋ ፌዝና ድብደባን ለመታገሥ ተገድደዋል:: በገመድ መታሰርና እስር ቤት መወርወር ነበረባቸው:: በድንጋይ ተወገሩ፣ በመጋዝ ተሰነጠቁ፣ በሰይፍ ተሰየፉ፣ የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ፤ ብቸኞች፣ ምስኪኖች፣ የተጎዱና የተቸገሩ ሆኑ:: በየጊዜው ኃያላን መላእክቱን በመላክ ይታደጓቸው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ተጣሩ:: የሚታደጋቸው መልአክ ግን አልመጣም:: እግዚአብሔር የሌለ ይመስል ሥቃዩንና መከራውን መቻል ነበረባቸው::

## የእግዚአብሔር አሸናፊዎች

ይህ የሆነው ለምንድን ነው? በማቴዎስ 26:39 ላይ ጌታ የቀራንዮን መስቀል በተጋፈጠ ጊዜ፣ «ቢቻልስ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ» ሲል ከተናገረው ፍንጭ እናያለን:: በኋላ ደግሞ «ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ» ብሎ ተናገረ (ሉቃስ 22:42):: በሚታይ ሁኔታ ነፃ ባላወጣቸው በእነዚህ ታላላቅ ቅዱሳን ሥቃይና ሞት እግዚአብሔር ፈቃዱን የሚፈጽምበት ምሥጢራዊ ዕቅድ ነበረው:: በእምነት የተሠቃዩትና የሞቱትም ይህንኑ ተገንዝበው ነው:: በጸሎታቸው መልስ በዓይን የሚታይ እርዳታ ያልተቀበሉት ሰዎች «በእምነት» ብቻ በመጽናታቸው የበለጠ ሰማያዊ ሽልማት የሚያገኙ መሆኑን የዕብራውያን 11 መጨረሻው ክፍል ይገልጻል:: ከሞቱ በኋላ ግን ዘላለማዊ ነፍሳቸውን ወደ እግዚአብሔር ዙፋን አጅበው በወሰዷቸው መላእክት አገልግሎት ሐሴት አድርገዋል:: የዕብራውያን 11 የመጀመሪያው ክፍል «የእግዚአብሔር የዝና አዳራሽ» ተብሎ ከተጠራ፣ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ

«የእግዚአብሔር የክብር ሜዳሊያ አሸናፊዎች» ተብሎ ሊጠራ ይገባዋል።

በጨለማ ዘመን ውስጥ በማልፍበት በአንድ ወቅት ብጸልይ ብጸልይ ሰማይ እንደ ነሐስ ሆነብኝ። በችግሬና በሽክሜ ውስጥ ብቻዬን ሆኜ እግዚአብሔር የተሰወረብኝ መሰለኝ። ይህ ለነፍሴ የጨለማ ሌሊት ነበረ። ለእናቴ ስለ ሁኔታው ስጽፍላት የመለሰችልኝን መልስ በፍጹም አልዘነጋውም። «ልጄ ሆይ፣ እግዚአብሔር እምነትህን ለመፈተን ብዙ ጊዜ ዘወር ይላል። በጨለማ ውስጥ እንድትተማመንበት ይፈልጋል። ልጄ ሆይ፣ አሁን በዚህ ጭጋግ ውስጥ በእምነት እጅህን ብትዘረጋ በዚያ ውስጥ መኖሩን ታያለህ» አለችኝ። በእንባ ሆኜ ከአልጋዬ ሥር ስንበረከክ የእግዚአብሔርን ልዩ መገኘት ተገነዘብሁ። የመንፈስ ቅዱስ ወይም የቅዱሳን መላእክት መኖር ባይሰማን ወይም ባንገነዘብ እንኳ፣ እግዚአብሔር እንደማይተወንና እንደማይጥለን እርግጠኞች ነን።

# ዘጠኝ

## መላእክት - በፍርድ የእግዚአብሔር ወኪሎች

መጽሐፍ ቅዱስ መላእክት በታሪክ ሁሉ የእግዚአብሔርን ፍርዶች በማስፈጸምና ለእግዚአብሔር የማይታዘዙትን የመንግሥታት የወደፊት ዕድል በመምራት ሲሠሩ መቆየታቸውን ይናገራል:: ለምሳሌ፣ እግዚአብሔር በኃጢአታቸው ምክንያት የእስራኤልን ሕዝብ ለመበተን መላእክትን ተጠቅሞባቸዋል:: በሰዶምና በገሞራ መጨረሻ ላይ ደግሞ በባቢሎንና በነነዌ ላይ ፍርድን ለማምጣት ተጠቅሞባቸዋል:: በተጨማሪም፣ «በመጨረሻው ዘመን» መላእክት የእግዚአብሔርን ፍቅር የተቃወሙትን ሰዎች ፍርድ በተግባር ላይ ያውሉታል::

የዕብራውያን ጸሐፊ መላእክት የእግዚአብሔር ፍርድ አስፈጻሚዎች እንደሆኑ ይናገራል:: «መላእክቱን መናፍስት አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል የሚያደርግ» (ዕብራውያን 1:7):: የእሳት ነበልባል የእግዚአብሔር ፍርዶች እንዴት አሠቃቂ እንደሆኑና የእግዚአብሔርን ውሳኔዎች የሚያስፈጽሙት የመላእክት ኃይል ምን ያህል የሚያቃጥል እንደሆነ የሚገልጽ ነው:: መላእክት ዳኝነትን የሚመሩት የእግዚአብሔርን የጽድቅ መርሆች መሠረት በማድረግ ነው::

ሰዎች በማይገነዘቡት መንገድ፣ ባለፉት ዘመናት እንደ ናዚ ዓይነት ክፉ ሥርዓቶችን ለማጥፋት ያለ ጥርጥር እርዳታ አድርገዋል:: ምክንያቱም እነዚያ መንግሥታት የእግዚአብሔርን ትዕግሥት ያሟጠጡ ነበሩ:: እነዚህ መላእክት ወደፊት ሊመጣ ያለውን አስከፊ ፍርድ ተግባራዊ የሚያደርጉ ይሆናሉ:: ከእነዚህም ፍርዶች አንዳንዶቹን የዮሐንስ ራእይ በሥዕላዊ መልኩ ገልጿቸዋል::

በሰንበት ትምህርት ቤት በገና ዕለት በሥዕላዊ መልኩ

ገልጿቸዋል:: ለልጆች የሚቀርቡትን ድራማዎች በምንመለከትበት ጊዜ ስለ መላእክት የተሳሳተ አስተሳሰብ እንይዛለን:: መላእክት የደኅንነት ወራሾችን ለመርዳት የሚላኩ መናፍስት መሆናቸው እውነት ነው:: ሆኖም በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑት በደኅንነት ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚፈጽሙ ሁሉ፣ በፍርድ ወቅትም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ታላቅ ኃይላቸውን የሚጠቀሙ «ተበቃዮች» ናቸው:: እግዚአብሔር በጎችን ከፍየሎች፣ ስንዴውን ከገለባ እንዲለዩ ሥልጣንን የሰጣቸው ሲሆን፣ በመጨረሻውና ታላቅ በሆነው በፍርድ ዕለት እግዚአብሔር ሕዝቦችን በፊቱ እንዲሰበስቡ በሚያደርግበት ወቅት ከመካከላቸው አንዱ መለከትን በመንፋት የማይቀረውን ፍርድ ያውጃል::

## ስለ ፍርድ የመላእክት ማስጠንቀቂያ

የሰዶምንና የገሞራን ሁኔታ በተመለከተ ፍርዱ ሊታጠፍ የሚችልበት ምንም መንገድ አልነበረም:: ክፋታቸው እጅግ በዝቶ ነበር:: እግዚአብሔር እንዲጠፉ ፈርዶባቸው ነበር:: ሆኖም እግዚአብሔር ፍርድን ከመላኩ በፊት ማስጠንቀቂያ ይሰጣል:: ይህን ጉዳይ በተመለከተ፣ በዓመፃቸው ምክንያት የሰዶምና የገሞራ ጥፋት መቅረቡን ለአብርሃም ለመጠቆም መላእክቱን ተጠቅሟል (ዘፍጥረት 18):: በዚህ ዓመፀኛ ሕዝብ መካከል ይኖሩ የነበሩት የወንድሙ ልጅ ሎጥን፣ ሁለቱንም ከተሞች ይታደጋቸው ዘንድ አብርሃም እግዚአብሔርን መለመን ጀመረ:: አብርሃም ሃምሳ ጻድቅ ሰዎች በሰዶም ውስጥ ቢኖሩ ቍጣውን ይመልስ እንደሆነ እግዚአብሔርን ጠየቀ:: እግዚአብሔርም ሃምሳ ጻድቃን ካሉ ከተማዪቱን እንደማያጠፋ ገለጸለት:: አርባ አምስት ጻድቅ ሰዎች የሚኖሩ ከሆነ፣ ከተማዪቱን እንዲታደግ ጠየቀ:: እግዚአብሔርም ተስማማ:: ደግሞም አብርሃም ስለ ሠላሳና ስለ አሥር ሰዎች ጠየቀ:: እግዚአብሔርም በሰዶም ውስጥ አሥር ጻድቅ ሰዎች የሚገኙ ከሆነ ፍርዱን እንደሚያነሣ ተስማማ:: ሆኖም አሥር ሰዎች እንኳ በዚህች ከተማ ውስጥ አልነበሩም:: ልንገነዘብ የሚገባው እግዚአብሔር አብርሃም የጠየቀውን ጥያቄ ሁሉ የመለሰለት ሲሆን፣

አብርሃም መጠየቁን እስኪተው ድረስ መልስ መስጠቱን እንዳላቆመ ነው።

ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር በእነዚህ ሁለት የዓመፅ ከተሞችና ነዋሪዎቻቸው ሁሉ ላይ የጥፋት ዝናቡን እንዲያዘንቡ የመላእክት የፍርድ አገልጋዮችን አዘዘ። ከሁለቱ ከተሞች ጥፋት ቀደም ብሎ ግን ሁለት ያልታወቁ የሰማይ መልእክተኞች ሎጥና ቤተሰቡ ሊመጣ ካለው ጥፋት እንዲሸሹ ለማስጠንቀቅ ወደ ሰዶም መጡ። የሰዶም ነዋሪዎች ክፋት ከመጠን ያለፈ በመሆኑ መላእክትን አስገድደው ሊደፍሩ ሞከሩ። መላእክቱም የክፋት ባሕርያቸውን ተግባራዊ እንዳያደርጉ ዓይኖቻቸውን አሳወሯቸው። ሲ. ሌስሊ ሚለር "All About Angels" በተሰኘው መጽሐፋቸው፣ «ምንም እንኳ የአብርሃም የወንድም ልጅ የነበረው ሎጥ ከእሳቱ የቅድስና ደረጃ ጋር ሲመዛዘን በእጅጉ አቅጣጫውን የለወጠና ቅድስና በሌለበት ኅብረት በመወዳጀት ለምድራዊ ጥቅም ራሱን የሰጠ ቢሆንም፣ የጌታ መላእክት ግን በራሱ ደካማ ውሳኔ ሊፈጠር የነበረውን ችግር በማስቀረት እርሱን ለመረዳትና ሕይወቱን ለማትረፍ ተገኙ ለት» ብለዋል።

ስለሆነም እጅግ አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ስሙን ለመጥራትና እግዚአብሔርን የሚያስከብር ሕይወት በቅንነት ለመኖር በሚሞክሩ ሰዎች ሕይወት የእግዚአብሔር ምሕረት፣ ጸጋና ፍቅር እንደሚገለጥ ለማየት እንችላለን።

## የአሦርን ሠራዊት ያጠፋው መልአክ

የእግዚአብሔር ቃል በ2ኛ ነገሥት 19 ውስጥ እግዚአብሔር ፍርዱን ለማስፈጸም መላእክትን እንደሚጠቀም በአስደናቂ ሁኔታ ይገልጸዋል። ንጉሡ ሕዝቅያስ ከአሦራውያን የጦር አዛዥ ደብዳቤ ከደረሰው በኋላ የእግዚአብሔርን ምክር በፍጥነት ፈለገ። እግዚአብሔርም አንድም የአሦራውያን ፍላጻ በከተማዋ ላይ እንደማይወረወር ለኢሳይያስ መልስን ሰጠው። ስለ ዳዊት ሲል በዚያ ሁኔታ ውስጥ ኢየሩሳሌምን እንደሚታደጋት ቃል ገባ። በዚያኑ ሌሊት በአስደናቂ ሁኔታ አንድ መልአክ ብቻውን የአሦራውያንን የጦር ሠፈር ሲመታ፣ በሚቀጥለው ጠዋት

185,000 ወታደሮች በጦር ሜዳው ላይ ሞተው ተገኙ (ቍጥር 35)::

## ኢየሩሳሌምን ሊያጠፉ የተቃረበው መልአክ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ መላእክት በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ለፍርድ ሲንቀሳቀሱ የምንመለከትበት ትልቁ ክስተት ዳዊት እሥራኤልን በመቍጠር የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በጣሰ ጊዜ ነው:: እግዚአብሔር ቸነፈርን በእስራኤላውያን መካከል ላከ፣ 70,000 ሰዎችም ሞቱ:: የኢየሩሳሌምንም ከተማ ለማጥፋት አንድ መልአክ ላከ:: ዳዊትም፣ «የእግዚአብሔር መልአክ በምድርና በሰማይ መካከል ቆሞ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ሆኖ ወደ ኢየሩሳሌም ተዘርግቶ አየ» (1ኛ ዜና 21:16):: ዳዊትም ምሕረትን በለመነ ጊዜ፣ መልአኩ በኢያቡሳዊው በኦርና አውድማ ላይ መሠዊያን ይሠራ ዘንድ ነገረው:: እግዚአብሔርም የዳዊትን መሥዋዕት ተቀብሎ ሊያጠፋ የመጣውን መልአክ፣ «እንግዲህ በቃህ እጅህን መልስ አለው» (2ኛ ሳሙኤል 24:16):: የእግዚአብሔር ቃል 70,000 ሰዎችን የገደለው ያው መልአክ መሆኑን ይናገራል (ቍጥር 17):: በእርግጥ መላእክት በፍርድ የእግዚአብሔር ወኪሎች ናቸው::

የአዲስ ኪዳን ታሪክም የበቀል መላእክት ጽድቅ አልባ የሆኑ ሰዎችንና አገራትን ተግባራት የቀጡባቸውን ሁኔታዎች ይዘግባል::

## ሄሮድስ አግሪጳን የመታው መልአክ

ሄሮድስን በተመለከተ ቀደም ሲል ጠቅሰናል:: ልብሰ መንግሥቱን ለብሶ ንግግር ለማድረግ ሕዝቡ ፊት ቀረበ:: ንግግሩን ሲያበቃ ሕዝቡ፣ «የእግዚአብሔር ድምፅ ነው:: የሰውም አይደለም ብለው ጮኹ» (የሐዋርያት ሥራ 12:22):: ሄሮድስም ያሉትን ነገር ከመቃወም ይልቅ በሕዝቡ ላይ ባሳደረው ስሜት ሐሴት አደረገ:: ለዚህ የጣዖት አምላኪነት ተግባር የእግዚአብሔር ምላሽ ፈጣን ነበር:: ለሄሮድስ ደግሞ መጥፊያው ነበር:: «ለእግዚአብሔርም ክብር ስላልሰጠ ያን ጊዜ የጌታ መልአክ መታው፣ በትልም ተበልቶ ሞተ» (ቍጥር 23)::

## የግብፃውያንን በኵሮች የገደለው መልአክ

እስራኤላውያን ከግብፅ ሊወጡ ሲሉ አንድ ሌሊት የሚያጠፋ መልአክ አገሪቱን በሞት ሊጎበኝ ተዘጋጀ (ዘጸአት 12:18-30)። ምን ያህል ጥልቅ ጉጉት በእስራኤላውያን ልብ ውስጥ ተቀርጾ ይሆን? የሚያምኑ አይሁዳውያን መሥዋዕት ከማቅረባቸው በተጨማሪ ደሙን በጉበኑና በመቃኖች ላይ በሥነ ሥርዓት ረጭተዋል። ከዚያም በእግዚአብሔር ጊዜ መሠረት የጨለማና አስፈሪ የሆነው የእኩለ ሌሊት ጊዜ ሲደርስ በግብፅ ላይ ፍርድ መጣ። የሚያጠፋው መልአክ (1ኛ ቆሮንቶስ 10:10፤ ዕብራውያን 11:28) ሞት ተግባሩን እንዲፈጽም የተወው የእግዚአብሔር የፍርድ አገልጋይ ነበር። ለደሙ አክብሮት በነበረውና ቅዱስ አምላክ በሆነው የእግዚአብሔር ፍርድ መሠረት የማያምኑ ግብፃውያንና የእስራኤላውያን ቤተሰብ በኵሮች ሁሉ ሞቱ።

ባለፉት ክፍለ ዘመናት ሁሉ ይህ ልብን የሚከፍል ዘገባ ለአይሁዳውያንና ለክርስቲያኖችም ዋና መልእክት ነበር። «ደሙን ካየሁ አልፋለሁ» ይህ የአይሁድ መምህራንና ክርስቲያን ካህናት ብዙ ሺህ ስብከቶች ያዘጋጁበት ጥቅስ ነው። ግምት ውስጥ የገባው ደሙ በተረጨበት ቤት ውስጥ የነበሩት ሰዎች የሕይወት ጥራት አልነበረም። ነገር ግን ደሙን በመርጨት ያሳዩት ከሥራ የተለየ እምነታቸው ነበር። እግዚአብሔር ያከበረው በእምነት የተረጨውን ደም ብቻ ነበር።

ሁሉን ቻይ የሆነው የእግዚአብሔርን ፍርድ የሚፈጽሙ የእነዚህ ኃያላን መላእክት እንዴት ያስፈራሉ?

## አብርሃምን ያስቆመው መልአክ

በዘፍጥረት 22 እግዚአብሔር የአብርሃምን እምነት እውነተኛነት ለመፈተን ፈልጎ የሚወደውንና «የተስፋ ልጅ» የነበረውን ይስሐቅን ይሠዋለት ዘንድ ጠየቀው። እግዚአብሔርም «አብርሃም ሆይ. . . የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያም ምድር ሂድ፤ እኔም በምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው» አለው (ዘፍጥረት 22: 1-2)።

በዚያ ረዥም ሌሊት አብርሃም ይሄ ታላቅ መሥዋዕት የሚያስከትለውን ሁኔታ በሚያሰላስልበት ወቅት ምን ያህል ልቡ በታላቅ ሥቃይ ተሰብሮና ተጎድቶ ይሆን? የሆነ ሆኖ አብርሃም የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ በመያዝ በእምነት ብቻ እሳት፣ እንጨትና ልጁን ይዞ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ጉዞ ጀመረ:: መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህ የበለጠ የእምነት ድርጊት አልዘገበም::

አብርሃም መሠዊያውን ካዘጋጀ በኋላ በመሠዊያው ላይ የይስሐቅን እጅና እግር በማሰር ቢላውን አውጥቶ የአባቱን ፈቃድ ለመፈጸም ፈቃደኛ መሆኑን ለመግለጽ ፊቱን ወደ ሰማይ አነሣ:: አብርሃም ቢላውን በአየር ላይ አንሥቶ በይስሐቅ ልብ ውስጥ ሊሰካው ሲል፣ «የእግዚአብሔር መልአክም ከሰማይ ጠራና አብርሃም አብርሃም አለው. . . . በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ እንዳችም አታድርግበት፤ አንድ ልጅህን ለእኔ አልከለከልክምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደሆንህ አሁን አውቄያለሁ አለ» ( ዘፍጥረት 22:11-12):: ሁለት ጊዜ ተደጋግሞ መጠቀሱ ሊቀርብ ያለውን መልእክት አስፈላጊነት ያሳያል:: ስሙ መጠራቱን ሲሰማ ታማኙ አብርሃም በፍጥነት መልስ ሰጥቷል፤ እግዚአብሔርም ማሻሻያ ላልታከለበት ታዛዥነቱ ብድራትን ከፈለው:: «አብርሃምም ዓይኑን አነሣ በኋላውም እነሆ አንድ በግ በዱር ውስጥ ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ አየ፤ አብርሃምም ሄደ በጉንም ወሰደው፤ በልጁም ፋንታ መሥዋዕት አድርጎ ሠዋው» (ዘፍጥረት 22:13)::

ብዙ ምሁራን (እኔንም ጨምሮ) የተገለጸው ያ መልአክ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ እንደሆነ ያምናሉ:: ክርስቶስ የመላእክትን ሚና የተላበሰ ሲሆን፣ እግዚአብሔር ደግሞ የምትክ ስርየትን መርህ አሳይቷል:: ይህም እግዚአብሔር ከአብርሃም የልጁን ሞት የጠየቀው መሆኑ ነው:: የሚቃጠል መሥዋዕትን በተመለከተ የተጠየቀውን ጥያቄ መፈጸም ነበረበት:: ደግሞም ተፈጽሟል:: ነገር ግን በይስሐቅ ፋንታ እግዚአብሔር በመልአኩ አማካኝነት የእንስሳን ምትክ ተቀብሏል:: ይኸው መርህ ለእኛም ይሠራል:: እንደ ትክክለኛ ፍርድ ከሆነ መሞት ነበረብን:: ፍርዱ ደግሞ ሊፈጸም ይገባዋል:: ሆኖም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ተተኪው መሥዋዕት ሆነ:: እኛ እንዳንሞት እርሱ ሞተልን:: «በምትካችን» የሚለው ቃል

በክርስቶስ ኢየሱስ ለሚያምኑ ሁሉ በሚያስገርም ሁኔታ ያገለግል ዘንድ ስፍራችንን ወሰደ። በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ በምትካቸው ሞተ።

እግዚአብሔር የሰው መሥዋዕት እንዲቀርብለት እንዴት ይጠይቃል? ሰዎች እንዳይገደሉ እየከለከለ ይስሐቅን ይሠዋለት ዘንድ አብርሃምን ለምን ጠየቀው? (ዘፍጥረት 9:6)። ይህ ከእግዚአብሔር ባሕርይ ጋር የሚጻረር አይደለምን? በሞት የመቅጣትን ፍርድ በተመለከተ ለሚነሡት ለእነዚህ ጥያቄዎች የሮሜ መልእክት መልስ ይሰጠናል። «ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም?» (ሮሜ. 8:32)። እግዚአብሔር ልጁን ይስሐቅን እንዲሠዋ አብርሃምን የጠየቀው ራሱ ልጁን ለሞት አሳልፎ ለመስጠት ፈቃደኛ ስለነበረ ነው። ከአብርሃም የጠየቀው ራሱ በአንድያ ልጁ ላይ ሊፈጸም ከፈቀደው ነገር በላይ አልነበረም።

አብርሃምም ሆነ ይስሐቅ እግዚአብሔር ያቀረበላቸውን ጽዋ መጠጣት አላስፈለጋቸውም። ይስሐቅ አልሞተም፤ አብርሃምም አልሰየፈውም። ሆኖም በጌቴሴማኒ የአትክልት ቦታ ወደነበረው ጽዋ ስንመጣ ሥዕሉ በሚያስገርም ሁኔታ የተለየ ነው። ኢየሱስ ለጥፋተኞች ጥፋት እንደሌለው፣ ለኃጢአተኞች ኃጢአት እንደሌለው ሆኖ መጥቷል። ለዓለም ዓመፅ የእግዚአብሔርን ፍርድ ለመቀበል ፈቃደኛ ሆነ። በቀራንዮ ሞቱም ራሱን ከዓለም ዓመፅ ጋር አመሳሰለ።

ኢየሱስ ወደሚያስፈራ ሥቃይ፣ ፍርድና ሞት የሚወስደውን «ጽዋ» በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ መውሰዱ ምን ትርጉም እንደነበረው መላእክትም ሆኑ ሰዎች ሊረዱት አይችሉም (በማርቆስ 14:36፤ ሉቃስ 22:42)። በአትክልቱ ቦታ ጽዋውን ለመጠጣት ከራሱ ጋር በሚታገልበት ወቅት ማንኛውም አገልጋይ መልአክ ሥቃዩን ሊቀንስለት ወይም ሊታደገው አልቻለም። ይህ የእርሱና የእርሱ ተግባር ብቻ ነበር። በፈቃደኝነት የተቀበለው የፍርድ ጽዋ በአዳኙ ላይ የወደቀ ሲሆን፣ ጻድቅ ሆኖ ሳለ የዓመፀኞችን ጥፋት በራሱ ላይ ተሸከመ። መላእክት በዚያን ሰዓት ሊታደጉት ቢችሉም፣

ክርስቶስ ግን እርዳታቸውን አልጠየቀም:: ይህ የመላእክትን ዕርዳታ ያልፈለገው አዳኝ፣ «እጅግ በጣም ስለምወዳቸው ለሰዎች ኃጢአት እኔ ራሴ እሞታለሁ» ማለቱ ነበር:: በሞቱ ጊዜ ሰዎችና መላእክት ርቀውታል:: እግዚአብሔርም ዓይኖቹ ንጹሐን ስለሆኑና ኃጢአትን ለመመልከት ባለመቻሉ በታላቅ ሥቃይ ላይ ከነበረው ልጁ ላይ ፊቱን መለሰ:: ለዚህ ነው ኢየሱስ «አምላኬ አምላኬ ስለምን ተውኸኝ?» ብሎ በመስቀል ላይ የጮኸው:: ብቻውን ሞተ፣ መላእክት እርሱን ለመታደግ ዝግጁ ቢሆኑም፣ እርሱ ግን ፈቃደኛ አልነበረም::

## መላእክትና ኢየሱስን የማይፈልጉ ሰዎች

የእግዚአብሔር ቃል፣ ሆን ብለው ኢየሱስ ክርስቶስን በሚቃወሙና እግዚአብሔር በእርሱ በኩል ያቀረበውን ደኅንነት በማይቀበሉት ሰዎች መላእክት የእግዚአብሔር መልእክተኞች በመሆን ፍርዱን ተግባራዊ እንደሚያደርጉ በግልጽ ይናገራል:: ሰዎች ሁሉ በተፈጥሮ፣ በምርጫና በተግባር ኃጢአተኞች ቢሆኑም፣ እግዚአብሔር ለዘላለም እንዲለዩ የሚያደርገውን ፍርድ የሚያስከትልባቸው ጌታ ኢየሱስን እንደ አዳኛቸውና ጌታቸው ለመቀበል ፈቃደኞች አለመሆናቸው ነው::

እግዚአብሔር በመጨረሻው ዘመን በጎችን ከፍየሎች፣ ስንዴውን ከእንክርዳድ፣ የዳኑትን ካልዳኑት እንዲለዩ መላእክትን ሾሟቸዋል:: የመላእክትን ድምፅ እንድንሰማ አይደለም የተጠራነው:: ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ከእግዚአብሔር ጋር እንድንታረቅ የሚጠራንን የእግዚአብሔርን ድምፅ ልንሰማና ቅዱስ ቃሉን ልናስተውል ይገባናል:: ይህ ካልሆነ ግን ይቅርታ ያልተደረገለትን የኃጢአት ዋጋ መካፈል ይኖርብናል:: መላእክትም ያንን ቅጣት ያስፈጽማሉ:: «ወደ እቶን እሳትም ይጥሉአቸዋል» (ማቴ. 13:50):: ሁልጊዜ የሚገርመኝ ነገር ቢኖር ዘመናዊው ዓለማችን፣ ክርስቲያኖችም እንኳ የእግዚአብሔርን ድንጋጌዎችና ማስጠንቀቂያዎች እንደ ቀላል ነገር መመልከታቸው ነው::

# መላእክትና ዘላለማዊ ሕይወት

እያንዳንዱ የዓለም ዘር ከሁለት የሕይወት መንገዶች ጋር ይፋጠጣል:: ከእነዚህም አንዱ ወደ ዘላለማዊ ሕይወት፣ ሌላው ደግሞ ወደ ዘላለም ሞት ያደርሳል:: ጌታ ኢየሱስን በማይፈልጉት ላይ መላእክት የእግዚአብሔርን ፍርድ እንዴት ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ተመልክተናል:: መላእክት ወደ እቶን እሳት ይጥሏቸዋል:: ሌላ ፍጹም የተለየ ፍርድ ደግሞ አለ:: ይህ ደግሞ መልካምና አስደናቂ የሆነው የዘላለም ሕይወት ፍርድ ነው:: በዚህም ውስጥ እግዚአብሔር ለመላእክት ኃላፊነትን ይሰጣቸዋል:: እያንዳንዱ አማኝ ለዘላለም ወደሚኖረው እግዚአብሔር በሚገባበት ወቅት ንጉሣዊ አቀባበል ያደርጉለት ዘንድ መላእክትን ወክሏቸዋል:: በክርስቶስ ላይ የታመነን ሁሉ በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ ሐሴት የሚያደርጉትን የመላእክት ሠራዊት እንመለከታለን::

በሉቃስ 16 ውስጥ በሚገኘው በሀብታሙና በአልዓዛር ታሪክ ውስጥ፣ ጌታ ኢየሱስ በእምነት ኖሮ ስለ ሞተ ስለ አንድ ለማኝ ይናገራል:: ይህ ለማኝ ብዙዎቹን የዓለም ቍሳቍሶች ያላገኘ ቢሆንም፣ የዘላለም ሕይወትን ባስገኘለት እምነቱ ግን ሀብታም ነበረ:: በሞተ ጊዜ «መላእክት ተሸክመው ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት::» እዚህ ላይ መላእክት የማይሞት መንፈሱን አጅበው መጽሐፍ ቅዱስ «ሰማይ» ብሎ ወደሚጠራው ስፍራ ሲወስዱት እንመለከታለን:: ይህ አማኝ ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖርበት የክብር ስፍራ ነው::

ሌላው እንደዚህ ዓይነት ውብ ዘገባ የምናገኘው ሰማዕት ከሆነው ከእስጢፋኖስ ሕይወት ነው (የሐዋርያት ሥራ 6:8-7:60):: «በሸንጎም የተቀመጡት ሁሉ ትኵር ብለው ሲመለከቱት እንደ መልአክ ፊት ሆኖ ፊቱን አዩት»:: ከዚያም እስጢፋኖስ ኃይለኛ በሆነው ስብከቱ ያላመኑት እንኳ በመላእክት ሥርዓት ሕግን እንደ ተቀበሉና ዳሩ ግን እንዳልታዘዙት ገልጿል (የሐዋ. 7:53)::ንግግሩን ከጨረሰ በኋላ እስጢፋኖስ የእግዚአብሔርን ክብርና በአባቱ ቀኝ የነበረውን ኢየሱስን ተመለከተ:: ያኔውኑ ጠላቶቹ እስከ ሞት ድረስ ወገሩት:: ወደ ሰማይም ተወሰደ:: መላእክት አልዓዛርን እንዳጀቡት ሁሉ እስጢፋኖስንም ሊያጅቡት እንደሚችሉ ለመገመት እንችላለን:: እኛም በሞት በክርስቶስ ፊት በምንሰበሰብበት ወቅት ያጅቡናል::

የመጀመሪያው የክርስቲያን ሰማዕት የሆነው እስጢፋኖስ ወደ መንግሥተ ሰማይ ሲገባ ታላቅ ክብር የተሞላበት አቀባበል ለማድረግና የሰማዕት አክሊል ለመሸለም የሰማይ ሠራዊት በደስታና በሐሴት እንደ ዘመሩለት ለመገመት እንችላለን::

የእግዚአብሔርን ፍርድ ትፈራለህ? ወይስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቱ ፍርድህን በራሱ ላይ እንዳደረገው ታውቃለህ? ክርስቶስን በምታውቅበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ፍርድ አትፈራም:: ምክንያቱም ደኅንነትህን ሙሉ በሙሉና በፍጹም ስለገዛው ነው:: ልብህን ክፈትለት እንጂ የክርስቶስ ለመሆን ውሳኔህን አታዘግይ:: ከዚያም አንተም ከእርሱ ጋር ኅብረት በማድረግ በሰማያት ለዘላለም የሚገኘውን ደስታ ትካፈላለህ::

# አሥር

# መላእክትና ወንጌሉ

እግዚአብሔር መላእክትን እርሱን በተመለከተ ልዩ መግለጫዎችን እንዲሰጡ የወከላቸው ቢሆንም፣ የወንጌሉን መልእክት የማወጅ ዕድልን ግን አልሰጣቸውም:: ይህ ለምን እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረው ነገር የለም:: ምናልባት በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው ኅብረት ተቋርጦባቸው የማያውቁ እነዚህ መንፈሳውያን ፍጥረታት ደኅንነትን ተገንዝበው ሊሰብኩ ስለማይችሉ ይሆን ይሆናል::

እስቲ «ቅዱስ ቅዱስ እያሉ ነው መላእክት የሚዘምሩት» በሚለው መዝሙር ውስጥ ደራሲው የሚለውን አስተውል::

*ቅዱስ ቅዱስ እያሉ ነው መላእክት የሚዘምሩት*
*የሰማይ ችሎቶች እንዲደውሉ እንደሚያደርጉ አምናለሁ::*
*የመዳንን ታሪክ በምዘምርበት ወቅት*
*ደኅንነት የሚሰጠውን ደስታ ስላልተለማመዱት*
*መላእክት ክንፎቻቸውን ያጥፋሉ::*

በዘመናት ሁሉ የሰው ልብ ሳይለወጥ ቆይቷል:: ምንም ዓይነት የቆዳ ቀለም፣ ባሕላዊ ወይም ጎሳዊ ሥረ መሠረት ቢኖረውም፣ የክርስቶስ ወንጌል ያስፈልገዋል:: ነገር ግን እግዚአብሔር ለወደቁ የሰው ልጆች ወንጌልን እንዲያመጡ የሾማቸው እነማንን ነው? የወደቁት መላእክት ይህንን ማድረግ ቀርቶ ከሠሩት ኃጢአት እንኳን ሊድኑ አይችሉም:: ያልወደቁት መላእክትም እንደዚሁ ወንጌልን ለመስበክ አይችሉም:: ምናልባትም ከንጽሕናቸው የተነሣ ኃጢአት ከሚያመጣው ውጤት ያመለጡና የመጥፋትን ትርጉም የማይረዱ በመሆናቸው ወንጌልን እኛ በምናዳምጠው መንገድ ስለ-ማይሰሙ ሊሆን ይችላል::

ይልቁንስ፣ እግዚአብሔር ወንጌልን ትሰብክ ዘንድ ቤተ

ክርስቲያንን አሂል:: ይህ ታላቅ ተግባር ለአማኞች የተተወ ነው:: እግዚአብሔር ሌላ አማራጭ የለውም:: ለሰው የደኅንነትን ልምምድ ሊናገር የሚችለው ሰው ብቻ ነው::

ነገር ግን እግዚአብሔር መላእክት ለባኪዎችን እንዲያግዙ መድቧቸዋል:: አገልግሎታቸው ተአምራትና አረጋጋጭ ምልክቶች መጠቀምን ያካትታል:: በአሥራ ስምንተኛውና በአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን የነበሩት ሚሲዮናውያን ወንጌልን ለማወጅ በሄዱበት ስፍራ በመላእክት እርዳታ ብዙ አስደናቂ ሁኔታዎችን እንዳለፉ ዘግበዋል:: የቻይና ሚሲዮናውያን ሆነው ካገለገሉት ቤተሰቦች የተወለደችው ባለቤቴ በአባቷና በሌሎች ሚስዮናውያን ባልደረቦቻቸው አገልግሎት ውስጥ መላእክት ጣልቃ የገቡባቸውን ብዙ አጋጣሚዎች ታስታውሳለች::

ያም ሆነ ይህ፣ እኔና እናንተ መላእክት ሊናገሩ የማይችሉትን መልእክት ለሰዎች ለማስተላለፍ ተመርጠናል:: ይህም መልእክት ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ ነው:: አንድ እግዚአብሔር ጥያቄ የተጠየቀበት ታሪክ አለ:: «አንተ በሰጠኸው ትእዛዝ መሠረት ሰዎች ወንጌልን መስበክ የማይችሉበት ሁኔታ ሲፈጠር ሌላ በአእምሮህ የምታስበው ምን የተለየ ዕቅድ አለህ?» ተብሎ ሲጠየቅ፣ «ሌላ ምንም የተለየ ዕቅድ የለኝም» አለ::

የትኛውም መልአክ ወንጌላዊ ሊሆን አይችልም:: ምንም እንኳ መላእክት የተወሰኑ አብያተ ክርስቲያናትን የሚጠብቁ ቢሆኑም፣ ማንም መልአክ ግን የቤተ ክርስቲያን መጋቢ መሆን አይችልም:: የትኛውም መልአክ ሰዎችን በአማካሪነት ሊያገለግል አይችልም:: የትኛውም መልአክ በክርስቶስ ልጅነት ሐሴት የማድረግ ወይም የመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋይ የመሆን ወይም በመንግሥቱ ከክርስቶስ ጋር ወራሽ መሆን አይችልም:: እኔና እናንተ መላእክት እንኳ ሊለማመዱ የማይችሉትን ልዩ የሆነና በሰማይ የመንግሥት ካህናት የመሆን ዕድሉ አለን::

## መልአኩና ዘካርያስ

የመጥምቁ ዮሐንስ ልደት ከወንጌል ጋር በእጅጉ የተያያዘ ነው:: ወላጆቹ ዘካርያስና ኤልሳቤጥ በዕድሜያቸው ያረጁ ነበሩ::

ኤልሳቤጥ ልጅ የመውለድ ዕድሜዋ አልፎ ነበር። እርሷና ባለቤቷ ከአሮን የዘር ሐረግ የመጡ ስለሆኑ ከክህነት ጋር የተያያዙ ነበሩ። ሁለቱም ያለነቀፋ በጌታ ፊት እየተራመዱ ትእዛዛቱንም ይጠብቁ ነበር። የዮሐንስ ወላጆች በተቀደሱ ቤተሰቦች ውስጥ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚሠራ በምሳሌነት ያሳያሉ። ታላላቅ ባሪያዎች ሁሉ ማለት ይቻላል፣ መንፈሳዊ ቤተሰቦች የሚያፈሩትን ደስታ ተቋድሰዋል። የሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን መሥራቾች የነበሩት ጆንና ቻርለስ ዌስሊ ከመንፈሳዊ ቤተሰብ የመጡ ሲሆን፣ እናታቸው ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድረውባቸዋል። ታላቁ የበርማ ሚሲዮናዊ የነበረው አዶኒራም ጁድሰን ከአገልጋይ ቤተሰብ የመጣ ነው። ቀደም ባሉት ዘመናት አሜሪካ መጋቢ፣ ወንጌላዊና የትምህርት ባለሙያ የነበረው ጆናታን ኤድዋርድስ ከመንፈሳዊ ቅድመ-አያቶች ዘር የመጣ ነበር።

መልአኩ ለዘካርያስ በተገለጸ ጊዜ፣ ዕድሜዋ ምንም እንኳ የገፋ ቢሆንም ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅን እንደምትወልድ የነገረው መልካም ዜና፣ ቃላቱ ከወንጌል ጋር የተያያዙ ነበሩ። መልአኩ የዮሐንስ አገልግሎት ምን እንደሚሆን ተነበየ። «ከእስራኤልም ልጆች ብዙዎችን ወደ ጌታ ወደ አምላካቸው ይመልሳል» (ሉቃስ 1:16)። ስለሆነም ማንም ሰው በአማኝ ቤተሰብ ውስጥ የተወለደ፣ አማኝ አያት ቅድመ-አያቶች ያሉትና በምታምን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያደገ ቢሆንም እንኳ መዳን አለመዳኑን ልናውቅ እንደማንችል ያስረዳል። በተጨማሪም፣ ዮሐንስ «የተዘጋጁትን ሕዝብ ለጌታ እንዲያሰናዳ» የተላከ ነበር (ቁጥር 17)።

ከጥቂት ወራት በኋላ የመልአኩን መልእክት ታላቅነትና ዘካርያስም ምን ያህል ለጉዳዩ ትኩረት እንደ ሰጠው ለመመልከት እንችላለን። ዘካርያስም ከመልአኩ ጉብኝት በኋላ ዱዳ ሆነ። ዮሐንስ እስከ ተወለደበት ዕለት ድረስም እንደዚሁ ሆኖ ቆየ። ዮሐንስ በተወለደበት ዕለት አንደበቱ ተፈታ። በመንፈስ ቅዱስም ተሞላ። ኤልሳቤጥ የልጁን መወለድ በምትጠባበቅባቸው በእነዚያ ረዥም ወራት ያሰብ የነበረው መጀመሪያ ባወጣቸው ቃላት ተገለጹ። ይኼውም የመልአኩን ጉብኝትና ለወንጌሉ ትኩረት መስጠትን የሚያንጸባርቅ ነበር። ዘካርያስም፣ «የእስራኤል ጌታ አምላክ ይባረክ፤ ጉብኝቶ ለሕዝበ ቤዛ አድርጓልና። ...በብላቴናው በዳዊት

ቤት የመዳን ቀንድን አስነሥቶልናል» ካለ ከጥቂት ደቂቃ በኋላ፣ «ደግሞም አንተ ሕፃን ሆይ፣ የልዑል ነቢይ ትባላለህ መንገዱን ልትጠርግ በጌታ ፊት ትሄዳለህና፤ እንደዚሁም የኃጢአታቸው ስርየት የሆነውን የመዳን እውቀት ለሕዝቡ ትሰጣለህ:: ይህም ከላይ የመጣ ብርሃን በጐበኘበት በአምላካችን ምሕረትና ርኅራኄ ምክንያት ነው:: ብርሃኑም በጨለማና በሞት ጥላ ተቀምጠው ላሉት ያበራል:: እግሮቻችንንም በሰላም መንገድ ያቀናል» (ሉቃስ 1:76-79)::

ይኼ በእውነት የሚገርም መልእክት ነው:: ይህ ሁሉ እግዚአብሔር ስለ ዮሐንስ ያለውን አሳብ መልአኩ ለዘካርያስ ከገለጸለት የመነጨ ነው:: በተለይ ልንገነዘብ የሚገባን ነገር ቢኖር፣ መልአኩ የመጣው የዮሐንስን መወለድ ለማወጅ ብቻ ሳይሆን፣ ዮሐንስ የመሢሑ መንገድ ጠራጊ በመሆን ሕይወቱን እንደሚያሳልፍ፣ እንዲሁም የመዳንን እውቀትና የኃጢአትን ስርየት ለእስራኤላውያን ወገኖች እንደሚያመጣ ለመግለጽ ጭምር ነው::

## መልአኩና ወንጌሉ በኢየሱስ ልደት ውስጥ

ማርያም ኢየሱስን እንደምትወልድ ያወጀው ተራ መልአክ አልነበረም:: አዋጁን ያወጀው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በስም ከተጠቀሱት ሦስት መላእክት አንዱ የሆነው ገብርኤል ነበር:: ይህ ደግሞ ከወንጌሉ ጋር የተያያዘ ነበር:: ይህ ገብርኤል ስለተናገራቸውም ሆነ ማርያም በእርግዝናዋ ወቅት የልጅዋን መወለድ ስትጠባበቅ ሳለ ስለተናገረቻቸው ቃላት እውነት ነበረ:: መልአኩ ለማርያም ኢየሱስ የልዑል ልጅ እንደሚባል፣ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን እንደሚወርስ፣ በያዕቆብ ቤት ላይ ለዘላለም እንደሚነግሥ፣ ለመንግሥቱም መጨረሻ እንደማይኖረው ነግሯታል:: ይህ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ለማንም ከተሰጠው የተስፋ ቃል በእጅጉ የተለየ ነበረ:: ለአብርሃም፣ ለዳዊት ወይም ለሰሎሞን እንደዚህ ዓይነት ተስፋ አልተገባላቸውም:: ከእነዚህ ተስፋዎች ጋር የተያያዘው የኢየሱስ ስም ብቻ ሲሆን፣ ተስፋዎቹም ከግላዊና ከብሔራዊ ደኅንነት ጋር የተጣመሩ ናቸው::

ማርያም ካረገዘች በኋላ ኤልሳቤጥን ስትጐበኛት በሥነ ጽሑፍ ታሪክ እጅግ ጣፋጭ ከሚባሉት መዝሙሮች አንዱ የሆነውን

ዝማሬ ዘመረች:: መዝሙሩም መልአኩ የነገራትን እንደ ተገነዘበች ያረጋግጣል:: መልአኩ የነገራትንም ደኅንነት የኃጢአት ስርየት በማለት ትገልጸዋለች:: «መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች» (ሉቃስ 1:47):: ይህ ማርያም ራሷ አዳኝ ፈልጋ ያገኘ ችው መሆኑን የሚገልጽ ዜና ነው:: ያ በማኅፀኗ ውስጥ ያደረው ሕፃን አንድ ቀን ለእርሷና ለሰዎች ሁሉ አስታራቂ በመሆን ራሱን መሥዋዕት የሚያደርግ ነበር:: ያ በማኅፀኗ ውስጥ የነበረው ሕፃን በሥጋ በመካከላችን ይኖር ዘንድ ራሱን ዝቅ ያደረገው ኃያሉ እግዚአብሔር ነበረ::

በእርግጥ የእግዚአብሔር «ምሕረት ለሚፈሩት እስከ ትውልድና ትውልድ ይኖራል» ብላ ጮኸለች:: ይህም እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ዓለምን የሚያስታርቅበት ወንጌል እንጂ ሌላ አይደለም:: እንግዲህ ገብርኤል ለማርያም ያመጣላት መልእክት ይኼ ነበር:: መስበክን ራሱ ሊሰብክ ባይችልም፣ ኢየሱስ ክርስቶስና ተከታዮቹ በዘመናት ሁሉ ለሚሰብኩት ወንጌል ምስክርነት ሰጥቷል::

## መልአኩ፣ ወንጌሉና ዮሴፍ

የማርያም ባለቤት የሆነው ዮሴፍ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የነበረ ይመስላል:: እርጉዝ ለሆነች ሴት በሕጋዊ መንገድ ታጭቶ ጋብቻቸው ገና ስላልተፈጸመ የተረገዘው ልጅ አባት እንዳልሆነ ያውቅ ነበር:: ዮሴፍ መንፈስ ቅዱስ በእርሷ ላይ በመምጣቱ እንጂ ከማንም ወንድ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያለማድረጓን ታሪክ ካላመነ በአይሁዳውያን ሕግ መሠረት ማርያም በአመንዝራነት ኃጢአት ትጠየቅ ነበር:: ዮሴፍ ንጹሕ ሰው በመሆኑ በዘመኑ ባህል መሠረት ማርያምን በስውር ሊተዋት ያስብ ነበር:: «እርሱ ግን ይህን ሲያስብ» (ማቴዎስ 1:20) አንድ መልአክ በሕልሙ ተገልጾለት ሥጋ ስለለበሰው አምላክ ታሪክና ስለ ማርያም ሚና ነገረው:: ዮሴፍ መልአኩን አመነው:: ሆኖም መልአኩ ለዮሴፍ የነገረው ማርያም ከማንኛውም ዓይነት የመተላለፍ ኃጢአት ነፃ መሆኗንና ዮሴፍም በዚህ ታላቅ ክስተት ውስጥ ማርያምን ለመንከባከብ በእግዚአብሔር የተመረጠ ዕቃ መሆኑን ብቻ አልነበረም::

መልአኩ በተጨማሪ የወንጌልን እውነት የሚያጐላ ነገርን ለዮሴፍ ነገረው። ምንም እንኳን መልአኩ ለዮሴፍ ሊሰብክለት ባይችልም፣ «እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና» (ማቴዎስ 1:21) ሲል የጉዳዩን ሥር ነክቶታል። እዚህ ላይ ወንጌሉ በሙሉ ውበቱ፣ በቀላል ግልጽነቱና በንጽሕናው ተገልጿል። እንደ መልአኩ ምስክርነት፣ ኃጢአት ይቅር ሊባል ይችላል። ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአትን ይቅር ሊል ይችላል። አዳኙ የሚያስብላቸው ሕዝብ ያሉት ሲሆን፣ ኃጢአታቸው ይቅር እንደሚባልላቸውም ቃል ይገባላቸዋል። ሥጋ ስለለበሰው አምላክ በሚናገረው ታሪክ ውስጥ መልአኩ ስለ ወንጌል እየመሰከረ የመሆኑን እውነት ማጤኑ ተገቢ ነው። ኢየሱስ የመጣው እንዲሁ እንደ አምላክ ብቻ ሳይሆን፣ ሰዎችን ከአባቱ ጋር ለማስታረቅና የዘላለም ሕይወትን ስጦታ ለመስጠት ነው። ይህም የአዳኝነትና የነፃ አውጭነት ሚና መጫወቱን ያሳያል።

## ገብርኤል፣ ወንጌሉና ዳንኤል

ዘካርያስ፣ ኤልሳቤጥ፣ ማርያም፣ ዮሴፍና መጥምቁ ዮሐንስ ከመምጣታቸው ከረዥም ጊዜያት በፊት መልአኩ ገብርኤል ወንጌሉን በሚመለከት ለነቢዩ ዳንኤል መስክሮለት ነበር። ይህንንም ከሰባዎቹ ሳምንታት (ሰባ ሱባዔ) ጋር በተያያዘው ትንቢት ነበር የተናገረው። ዳንኤል የራሱንና የሕዝቡን ኃጢአት እየተናዘዘ ጥልቅ ጸሎት ያደርግ ነበር። እየጸለየ ሳለ ገብርኤል ተገለጠለት። አሁንም ልናስተውል የሚገባን ነገር ቢኖር ገብርኤል ወንጌልን እንዳልሰበከና ዳሩ ግን መልካም ምስክርነት እንደ ሰጠ ነው። እርሱም ሰባ ሳምንታቱ የታቀዱት «ዓመፃን ይጨርስ፣ ኃጢአትንም ይፈጽም፣ በደልንም ያስተሰርይ» ዘንድ ነው ብሎ ተናገረ (ዳንኤል 9:24)። ከዚያም በኢሳይያስ 53 ውስጥ በግሩም ሁኔታ እንደተገለጸው መሢሑ እንደሚወገድ አስቀድሞ ተናገረ።

አይሁዳውያን በአእምሮአቸው የሣሉት መሢሕ በኃይልና በክብር በመምጣት ጠላቶቻቸውን ገልብጦ በድል አድራጊነት በእነርሱ ላይ የሚገዛ እንጂ የሚሠቃይ አልነበረም። ስለሆነም መከራ ስለሚቀበለው መሢሕ የተነገረውን አስተሳሰብ ለመረዳት ተቸግረው ነበር። ገብርኤል ግን ኃጢአት በገዛድ ያለ ነገር በመሆኑ ዋጋ

ሊከፈልበት እንደሚያስፈልግ ለዳንኤል ነገረው። ይህንንም መሚሑ በመወገድ፣ ማለትም ለሰዎች ኃጢአት በመሞት ማከናወን ነበረበት። ከዚያም ከእግዚአብሔር ጋር የሚያለያየን የኃጢአት ኃይል ያበቃና ሰዎች ከእርሱ ጋር ዕርቅን ያደርጋሉ። ምንም እንኳ ገብርኤል መስበክ ባይችልም፣ መተንበይ እንደሚችል እንመለከታለን። በብሉይ ኪዳን የተተነበዩ ትንቢቶች በአዲስ ኪዳን ከተፈጸሙት ነገሮች ጋር ውብ በሆነ ሁኔታ የተያያዙ ናቸው። እግዚአብሔር ወኪሎቹ የሆኑት መላእክት በዘመናት ለጉበኟቸው ሁሉ ወንጌሉን የሚመለከት ምስክርነት እንዲሰጡ ማድረጉ ምንኛ ታላቅ የቸርነት ተግባር ነው።

## መልአኩ፣ ወንጌሉና እረኞቹ

እግዚአብሔር የኢየሱስን ልደት የመጀመሪያ መልእክት ከልዑላንና ነገሥታት ይልቅ ለተራ ሰዎች መግለጹ ምሥጢራዊ አይመስልምን? በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በቅዱስ መልአኩ አማካኝነት በሜዳ ላይ በጎቻቸውን ለሚጠብቁ እረኞች ነበር የተናገረው። ይኼ ዝቅተኛ ሥራ ስለነበረ እረኞች ብዙም የተማሩ አልነበሩም። ሆኖም ማርያም በመንፈሳዊው ዝማሬዋ ውስጥ እውነተኛውን ታሪክ ትናገራለች። «ገዢዎችን ከዙፋናቸው አዋርዷል፤ ትሑታንንም ከፍ አድርጓል፤ የተራቡትን በበጎ ነገር አጥግቦአል፤ ባለጠጎችንም ባዶአቸውን ሰዶአቸዋል» (ሉቃስ 1:52-53)። ይህ ለእኛ ትውልድ እንዴት ያለ ጠቃሚ መልእክት ነው!

ለእረኞቹ የመልአኩ መልእክት ምን ነበረ? በመጀመሪያ እንዳይፈሩ ነገራቸው። ለተገናኟቸው ሰዎች የመላእክቱ መገኘት በማያቋርጥ መልኩ አስፈሪ ነበር። ሆኖም ለፍርድ እስካልመጡ ድረስ መላእክት የሚናገሩት የማረጋገጫን ቃል ነው። ወደ እነርሱ የመጡላቸውን ሰዎች ያረጋጓቸዋል። ይህ የሚያስረዳን ነገር ቢኖር መላእክት በሚገለጡበት ጊዜ ክብር የመስጠት ስሜትን የሚቀሰቅሱና በሰው ልብ ውስጥ ፍርሃትን የመጫር ብርታት ያላቸው መሆኑን ነው። መገለጣቸው ታላቅ ከመሆኑ የተነሣ በጀርባ አጥንታችን ውስጥ ቀዝቃዛ ነገር የወረደ የሚያስመስል ነው። ሆኖም መልአኩ የእረኞቹን ፍርሃት ካረገበ በኋላ ለዘላለም ከወንጌሉ ጋር የሚያያዘውን መልእክት አመጣላቸው፡-

«እነሆ፣ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ:: ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ ተወልዶላችኋልና» (ሉቃስ 2:10-11)::

ብዙ ጠቃሚ የሆኑ ሥነ መለኮታዊ መልእክቶችን ያዘሉ ስለሆኑ፣ በእነዚህ ሁለት ጥቅሶች ላይ በመመሥረት ብዙ ስብከቶችን ልሰብክ እችላለሁ:: አሁንም ልታስተውል የሚገባው መልአኩ ወንጌልን የሚሰብክ አለመሆኑን ነው:: ነገር ግን ስለ ወንጌሉ በመመስከሩ፣ መላእክት ለወንጌሉ ያላቸውን ከፍተኛ ትኩረት ያሳያል::

መልአኩ ምን አለ? በመጀመሪያ፣ ያመጣላቸው ዜና መልካም እንጂ መጥፎ አልነበረም:: እረኞቹ መጥፎውን ዜና፣ ማለትም የሰው ዘር ኃጢአተኛ በመሆኑ ምክንያት የጠፋ መሆኑን ቀደም ሲልም ያውቁታል:: ሆኖም መልአኩ ስለመጥፋታቸው እግዚአብሔር ሊያደርግ ስላለው ነገር ሊነግራቸው ወደ እነርሱ መጣ:: መልካሙም ዜና ለአንድ አገር ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሁሉ መሆኑን ገለጸላቸው:: ኢሳይያስ፣ «እርሱም የምድር ሁሉ አምላክ ይባላል» ብሏል (ኢሳይያስ 54:5):: ዮናስም ለነነዌ ሰዎች ንስሐን እንዲሰብክ በተላከ ጊዜ ከዚሁ ጋር የሚመሳሰል እውነትን ተምሯል:: መልአኩም መልካሙ ዜና ለሰዎች ሁሉ እንደሆነ ለእረኞቹ ነገራቸው::

መልካሙ ዜና አዳኝ መምጣቱ ነበር:: የኮርማና የፍየል ደም ቀጣይነት ባለው መልኩ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ለማድረግ የሚያስችል ባለመሆኑ ወደዚህ ኅብረት የሚመልስ አንድ ሰው ያስፈልግ ነበር:: የአዳኙ ደም ግን ይህንን ለማድረግ ይችል ነበር:: የመልአኩ መልእክት እግዚአብሔር እንደ መጣ፣ መዋጀት መቻሉንና ጌታ ሕዝቡን በማዳን እንደ ጉበኝ የሚያስረዳ ነበረ:: ይህ ለወንጌሉ እንዴት ያለ ታላቅ ምስክርነት ነው! መልእክቱ በብዙ የሰማይ ሠራዊት የታጀበው መልአክ፣ «ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ» እያሉ መዘመር በጀመሩ ጊዜ ነበር:: ከዚህ የበለጠ ጣፋጭ መዝሙር ከየት ሊገኝ ይችላል? ከእነዚህስ ቃላት የበለጠ መንፈሳዊ ዝማሬን የትኛው ደራሲ ሊጽፍ ይችላል?

# መላእክትና ወንጌሉ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ

መላእክት ያላመኑ ሰዎች ወንጌልን እንዲሰሙ፣ ምላሽ እንዲሰጡና እንዲድኑ የሚከታተሉ ለመሆኑ «የናሙና ጥናቶች» ብለን ልንጠራ የምንችለውን ሁለት የሚያስገርሙ ምሳሌዎችን እንመለከታለን:: ይህም መላእክት ለወንጌሉ ግድ እንደሚላቸውና ለተግባራዊነቱ የሚወስዷቸውን እርምጃዎች የሚያሳይ ነው::

የመጀመሪያው ገጠመኝ ከፍተኛ ባለሥልጣን የነበረውና የተከበረው የኢትዮጵያዊው ጉዳይ ነው:: የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት እያነበበ ትንቢተ ኢሳይያስ ላይ ደረሰ:: ሆኖም ነቢዩ ሊል የፈለገውን አሳብ ለመረዳት ባለመቻሉ የእግዚአብሔርን ቃል ሊተረጉምለት የሚችል አንድ ሰው አስፈለገው:: መልአኩ ይህንን ሁኔታ ቢያውቅም፣ ኢትዮጵያዊው የፈለገውን ነገር ለማድረግ አልቻለም ነበር:: ወንጌልን ለመስበክ ባይችልም፣ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ሊረዳ የሚችል ሰው ለመላክ ግን ተችሎት ነበር::

ስለሆነም የእግዚአብሔር ቃል መልአኩ ለፊልጶስ በቀጥታ «ተነሥተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው ምድረ በዳ ወደ ሆነ መንገድ ሂድ» ብሎ እንዳዘዘው ይነግረናል (የሐዋርያት ሥራ 8:26):: ፊልጶስም መልአኩን በመታዘዝ ወደ ሰረገላው ቀረበ:: ከዚያም ለኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የእግዚአብሔርን ቃል ተረጐመለት:: ከዚያም መልአኩ አንሥቶ ከወሰደው በኋላ ኢትዮጵያዊው ሰው ሐሴት እያደረገ መንገዱን ቀጠለ:: መልአኩ ለወንጌሉ ግድ ባይኖረው ኖሮ ለዚህ ለተጠማ ሰው ወንጌልን ይሰብክለት ዘንድ ፊልጶስን ባልላከለት ነበር::

ሁለተኛው አጋጣሚ የጴጥሮስን አገልግሎትና የቆርኔሌዎስን መለወጥ የሚያመለክት ነው:: በዚህ ሁኔታ ነገሮች ተገለባብጠዋል:: መልአኩ ኢትዮጵያዊው መዳንን ያገኝ ዘንድ ለፊልጶስ ምን ማድረግ እንዳለበት ነግሮታል:: በዚህ ሁኔታ ግን ቆርኔሌዎስ ወደ ጴጥሮስ ልኮ መዳንን ያገኝ ዘንድ የወንጌልን ታሪክ ነገረው እንጂ ጴጥሮስ ምን ማድረግ እንዳለበት አልነገረውም:: ቆርኔሌዎስ ወደ ጴጥሮስ መልእክት እንዲልክ ከሚያደርግ ይልቅ መልአኩ ወንጌልን ቢሰብክለት የበለጠ አይቀልም ነበር? እዚህ ላይ ጴጥሮስ

ለመመስከር ፈቃደኛ አልነበረም:: አሕዛብ ይድኑ ዘንድ ወንጌልን ለእነርሱ መስበክ ስሕተት ነው የሚል አስተሳሰብ ነበረው:: ሆኖም ቆርኔሌዎስ የመልአኩን ቃል ታዝዞ ለጴጥሮስ መልእክትን ላከበት:: ከዚያም እግዚአብሔር በሕልም ለጴጥሮስ ተገልጾለት ለአሕዛብ መመስከር ተገቢ እንደ ሆነ አሳመነው:: በመጨረሻ ጴጥሮስ ሄዶ ቆርኔሌዎስ በሚያስገርም ሁኔታ ደኅንነትን አገኘ:: ሆኖም ይህ ሁሉ የተካሄደው ለወንጌሉና ለሮማዊው ወታደር ደኅንነት ከፍተኛ ትኩረት በነበረው በመልአኩ ዕርዳታ አማካኝነት ነው::

አንድ በመጠኑ ለየት ያለ ታሪክ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ይገኛል:: ይኸውም ጳውሎስ ወደ ሮም በሚጓዝበት ወቅት ከደረሰበት የመርከብ አደጋ ጋር የተያያዘ ነው:: መርከቧ እንደምትሰምጥና ሰዎች ሁሉ እንደሚሞቱ ግልጽ በሆነበት ሁኔታ ውስጥ የጌታ መልአክ በሌሊት ለጳውሎስ ተገለጠለት:: መልአኩ በመርከቡ ውስጥ የተሳፈሩት በሙሉ እንደሚድኑ ተናገረ:: ከዚያም የሰዎች መዳን መላእክትን እንደሚያሳስብና ክርስቲያኖች ላልዳኑት ሰዎች የሚሰጡትን ምስክርነት የሚያሳይ ነገር ተናገረ:: «ጳውሎስ ሆይ፣ አትፍራ በቄሣር ፊት ልትቆም ይገባሃል::» (የሐዋ. 27:24):: እዚህም ላይ ተመሳሳይ መርሕ እንመለከታለን:: ጳውሎስ እንጂ መልአኩ ለቄሣር ሊመሰክር አይችልም ነበር:: እግዚአብሔር መለኮታዊ በሆነ ምሪቱ ለዚሁ ጉዳይ ብቻ ወደ ሮም እየላከው ነበር:: ጳውሎስ ቀደም ሲል የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሙሉ በሙሉ ባይረዳ፣ በዚህ ጊዜ በግልጽ ሊገነዘብ ይችል ነበር:: እግዚአብሔር ቄሣር ወንጌልን ይሰማ ዘንድ ፈቃዱ ነበረ:: መልአኩም መልእክቱን በማምጣት ለወንጌሉ የነበረውን የግል ፍላጎት ገለጸ::

## የመልአክ ድምፆች ድምፀት

የወንጌል ዋና አሳብ የተካተተው ሰማያዊ አዋጅ በሆነውና «ዛሬ ተወልዶላችኋልና. . . እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ» በሚለው ቃል ውስጥ ነው:: ዓለምን በወንጌል የማዳረስ ሥራ የሚከናወነው መንፈስ ቅዱስ በሚጠቀምባቸው ወንዶችና ሴቶች ልጆች ነው:: ነገር ግን ወንጌል ሰውን በሚለውጥ መልኩ በየትኛውም ሁኔታና በታ ከተመለከትነው በሆነ መንገድ የመላእክት ተሳትፎ ሊኖር ይችላል:: ይህ ወደ መንግሥተ ሰማያት እስከምንደርስ ድረስ ልንረዳ

የማንችለው ምሥጢር ነው::

«የመልአክ ድምፆች ምን ዓይነት ድምፀት አላቸው? በተናገሩ ጊዜስ ምን አሉ?» ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው:: መላእክት ቁርጥ ያለ ትእዛዝ የሚሰጡ ይመስላል:: ብዙ ጊዜ የመልአክ መልእክተኞች ፍጠን እያሉ የሚያስቸኩሉ ሲሆን፣ ይህም ከእግዚአብሔር ከሚቀበሉት መመሪያ አንጻር መሆኑ ግልጽ ነው:: ዶ/ር ሚለር «ፈጠን በል» የሚለው የአሁኑ ዘመን አገላለጽ መልአክ ከሚሰጡት ትእዛዝ ጋር የበለጠ የሚስማማ መሆኑን ይናገራሉ:: መልአኩ ጴጥሮስን «ፈጥነህ ተነሥ!» ጌዴዎንን «ተነሥና በዚህ በጉልበትህ ሂድ!» ዮሴፍን «ፈጥነህ ሂድ!» እንዲሁም ፊልጶስን «ተነሣና ሂድ» ብሏል::

በተመሳሳይ ሁኔታ የትኛውም የወንጌል አገልግሎት የመፍጠንን አስፈላጊነት ያሳያል:: ይህንን ደቂቃ መልሰን ስለማናገኘው ምንም የምናጠፋው ጊዜ ሊኖር አይገባም:: የመጀመሪያውን ችላ ካልን ልንመሰክር የምንችልበት ሁለተኛ ዕድል ላናገኝ እንችል ይሆናል::

ይህንን ከታይታኒክ መርከብ መስመጥ ጋር በማያያዝ ልናብራራው እንችላለን:: በዘመኑ ታላቅ የተባለችው 46,000 ቶን ክብደት የነበራት ታይታኒክ ልትሰምጥ እንደማትችል ተገምቶ ነበር:: ነገር ግን (እ. አ. አ.) ሚያዝያ 6 ቀን 1992 ሌሊት በውቂያኖስ ውስጥ በሃያ ሁለት የመርከብ ፍጥነት (Knots) እየተጓዘች እያለ ከአንድ የበረዶ ዓለት ጋር ተላተመች:: ከተሳፈሩት ሰዎች ለግማሾች ብቻ የሚሆን የሕይወት አድን ጃኬት የተዘጋጀ በመሆኑ በሰመጠች ጊዜ 1,513 ሰዎች በውኃው ውስጥ ሞተው ቀርተዋል:: ምንም እንኳ ይህ ሁኔታ ከሰባ ዓመታት በፊት የተከሰተ ቢሆንም፣ ዛሬም ቢሆን ይሄን ጉዳይ ሰዎች በትኩረት ይከታተላሉ:: ስለ ታይታኒክ ግዙፍነት በቅርብ ጊዜ የተገኘው ግኝት በዚህ በሚያሳዝን ታሪክ ዙሪያ ፍላጎት እንዲያድርብን አድርጎናል::

እግዚአብሔር ዛሬም ቢሆን ከአሳዛኝ ታሪክ ውስጥ ድልን ሊሰጥ ይችላል::

ጆን ሀርፐር የተባለ መንገደኛ ቺካጎ በሚገኘው የሙዲ ቤተ ክርስቲያን ለመስበክ በጉዞ ላይ ነበር:: ከተፈጠረው ችግር የተነሣ ውቂያኖሱ ውስጥ ላለመስመጥ ሲል አንድ ሣንቃ ወደ ያዘ ወጣት

ልጅ አቅጣጫ ሄደ:: ሀርፐርም፣ «አንተ ወጣት ድነሃል?» ብሎ ጠየቀው:: ሰውዬውም፣ «አይ» አለው:: በዚህን ጊዜ ማዕበል ለያያቸው:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ መነጋገር በሚችሉበት ርቀት ሲለያዩ ሀርፐር፣ መልሶ፣ «ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ፈጥረሃል?» ብሎ ጮኾ ሲጠይቅ፣ ወጣቱ፣ «ገና አልፈጠርኩም» አለው:: ጆን ሀርፐር፣ በማዕበሉ ተወስዶ ብቅ ሳይል ቢቀርም፣ «ድነሃል?» የሚለው ቃል ግን በወጣቱ ጆሮ ላይ መደወሉን ቀጠለ::

ከሁለት ሳምንታት በኋላ በኒው ዮርክ የክርስቲያኖች የሥራ ስብሰባ ላይ አንድ ወጣት ተነሥቶ ታሪኩን ከተናገረ በኋላ፣ «እኔ የጆን ሀርፐር፣ የመጨረሻው ፍሬ ነኝ» ብሎ ተናገረ::

# አሥራ አንድ

# በኢየሱስ ሕይወት የመላእክት አገልግሎት

የኢየሱስ ሕይወት ከመላእክት አገልግሎት ጋር ምን ያህል የተቆራኘ እንደ ሆነ በዝርዝር ለማብራራት ራሱን የቻለ መጽሐፍ ማዘጋጀት ይጠይቃል። ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት ትእዛዙን ተቀብለዋል። ወደ ሰማይ ካረገ በኋላም ለደኅንነታችን ሲል እንደ ታረደ በግ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ያመልኩታል።

ለኢየሱስ መምጣት የሰዎችን ልብ ያዘጋጅ ዘንድ መልአኩ ለዘካርያስ ተገልጦ ባለቤቱ መጥምቁ ዮሐንስን እንደምትወልድ ነገረው (ሉቃስ 1:13)። ከእግዚአብሔር ኃያላን መላእክት አንዱ የሆነው ገብርኤል፣ ማርያም መሢሑን እንደምትወልድ ነገራት። አንድ መልአክና ቍጥር ስፍር የሌላቸው የሰማይ ሠራዊት በሜዳ ወደሚገኙ እረኞች መጥተው የክርስቶስን መምጣት የምሥራች ተናገሩ (ሉቃስ 2:9)። እነዚህ የመላእክት ክስተቶች ከልደቱ በፊት የተከናወኑ ሲሆን፣ ኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎቱን በጀመረበት ወቅት በአገልግሎቱና በሕይወቱ ውስጥ በከፍተኛ ቅርበት ተሳትፈዋል።

ምናልባትም ጌታ ኢየሱስ ከስቅላቱ በፊት በሕይወቱ ዘመን ከተጋፈጣቸው ከፍተኛ ችግር አንዱ በበረሃ በዲያብሎስ መፈተኑ ሳይሆን አይቀርም። አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከጾመ በኋላ ሰይጣን ሊጥለው ሞከረ። ክርስቶስን በደከመ ሰብአዊ ሁኔታ ውስጥ በማግኘ ቱ፣ ሰይጣን ጥቃቱን ጀመረ። ይህ በዔድን ገነት ድል ካደረገ በኋላ እግዚአብሔር ለዓለም ያዘጋጀውን መርሐ ግብር ለማበላሸት የሚችልበት ከፍተኛ አጋጣሚ መስሎ ታየው። የሰውን ዘር ተስፋ ለማጨለም ቆርጦ ተነሣ። የኃጢአተኞችን ደኅንነት ለማገድ ከመመኘቱ የተነሣ የክርስቶስ አካላዊ ድካም ለፈተና በቀላሉ የሚንበረከክ በሚመስልበት ሰዓት ማጥቃት ጀመረ። ሰይጣን ሁልጊዜም ጠንካራ ጥቃቱን የሚሰነዝረው በሚዋጋቸው ሰዎች

ደካማ ጎን በኩል ነው:: የሰዎች ደካማ ጎን የት ሊሆን እንደሚችል ስለሚያውቅ ምቹ በሆነ ሰዓት ለማጥቃት ወደ ኋላ አይልም::

ሰይጣን ሦስት ጊዜ ኢየሱስን ለማሸነፍ ጣረ:: ጌታ ኢየሱስ ለሦስት ጊዜያት የእግዚአብሔርን ቃል በመጥቀስ ሦስቱንም ጊዜያት ሰይጣንን አሸነፈው:: ከዚያም መጽሐፍ ቅዱስ፣ «እስከ ጊዜው (ሰይጣን) ከእርሱ (ከኢየሱስ) ተለየ» (ሉቃስ 4:13) ሲል ያውጃል:: በዚህ ጊዜ ነበር መላእክት ሊረዱት የመጡት:: የመጡት ግን እኛን እንደሚረዱን ሁሉ ሰይጣንን ለመቋቋም ይችል ዘንድ ሊያግዙት ሳይሆን (ይህንን ራሱ አድርጎታል) ጦርነቱን በድል ከተወጣ በኋላ ነበር:: መላእክት ኢየሱስን «አገለገሉት» "diakoneo" የሚለው የግሪኩ ቃል ይህንን የበለጠ ይገልጸዋል:: ዲያቆን እንደሚያገለግል ነበር ያገለገሉት:: «መላእክት ቀርበው ያገለግሉት ነበር» (ማቴ. 4:11):: በዚያች ፈታኝ ሰዓት መልአካዊ መልእክተኞች አግዘውታል፣ አጠንክረውታል፣ ተስፋ እንዳይቆርጥም አድርገውታል:: ከዚያች ሰዓት ጀምሮ «ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ» ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ (ዕብራውያን 4:15) በዘመናት ሁሉ ለክርስቲያን አማኞች እየራራና እየረዳ በፈተናቸው ሰዓት ወደ ድል ይመራቸዋል::

## መልአኩ ከኢየሱስ ጋር በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ

ኢየሱስ ከመሰቀሉ አስቀድሞ በነበረው ሌሊት በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ ነበረ:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ በአስቆሮቱ ይሁዳ አልፎ ከተሰጠ በኋላ ወታደሮች፣ በገዢዎች ፊት ያስቆሙት፣ ይደበድቡትና በመጨረሻ ላይም ይሰቅሉት ነበር:: በመስቀል ላይ ከመሰቀሉ በፊት የደም ጠብታ የሚመስል ላብ ከሰውነቱ እስከሚወርድ ድረስ ከፍተኛ ሥቃይን አሳልፏል:: በዚህን ጊዜ ነበር የሰው ልጅ በሰማይ፣ በምድርም ሆነ በገሃነም ውስጥ ያሉ ሌሎች ፍጥረታት የማያውቁትን ችግር ለመጋፈጥ የውስጥ ጥንካሬ ያስፈለገው:: እንዲያውም የትኛውም ፍጡር ተጋፍጦ በድል ሊያልፍ የማይችለውን ችግር መጋፈጥ ነበረበት:: ለእኛ ሲል ኃጢአት በመሆን የሰዎችን ኃጢአት በራሱ ላይ መሸከም ነበረበት::

ኢየሱስ ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን ከራሱ ጋር ወደ አትክልቱ ስፍራ ወስዷቸው ነበር። እነዚህ ሰዎች ድጋፍና ማበረታቻ ሊሰጡት ሲገባቸው በእንቅልፍ ተሸንፈው ተኙ። በዚህ ጊዜ የሰው ልጅ ብቻውን ነበረ። «አባት ሆይ፣ ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ» ብሎ ጸለየ (ሉቃስ 22:42)። በዚህ ወሳኝ ደቂቃ ነበር መልአኩ መጥቶ «ያበረታው።» ማበረታታት ለሚለው ቃል ያገለገለው የግሪክ "eniskuo" ሲሆን፣ ትርጉሙም የውስጥ ሰውነትን ማጠንከር የሚል ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ሥቃዩን ለመካፈል አዳግቷቸው በተኙበት ወቅት መልአኩ ሊረዳው መጣ።

## መላእክት በመስቀሉ ዙሪያ ሲጠባበቁ

የኃጢአት አስከፊነት በከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰው እግዚአብሔር በክርስቶስ ውስጥ ኃጢአት በሆነበት ወቅት ነው። በዚህ ሁኔታ በእግዚአብሔር ቅን ፍርድ መሠረት ሰው መዋጀት ካለበት ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብ ነበረበት። በዚህ ጊዜ ሰይጣን ዋና ምቱን ለመሞከር በተጠንቀቅ ላይ ነበረ። ክርስቶስን ከመስቀል ላይ ለማውረድ ቢችል፣ ክርስቶስ በሕዝቡ ፊዝ ቢያፍርና ቢናደድ ኖሮ የደኅንነት ጽድቅ አደጋ ላይ በወደቀ ነበር። ደግመው ደጋግመው «የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንክ ከመስቀል ውረድ» ብለው ይጮኹ ነበር (ማቴዎስ 27:40)። መውረድ ምርጫው ቢሆን ኖሮ ሊያደርገው እንደሚችል ያውቅ ነበር። የተመዘዙ ሰይፎችን ከያዙና በዙሪያው ከሚያንዣብቡ ከአሥራ ሁለት ጭፍሮች ከሚበዙ መላእክት እርዳታን ሊያገኝ እንደሚችል ያውቅ ነበር።

ሆኖም ለእኛ ደኅንነት ሲል እዛው ላይ መቆየትን መረጠ። ለሰው ዘር ካለው ፍቅር የተነሣና በእርሱ ሞት ብቻ መዳን እንደሚገኝ በመረዳቱ ምክንያት እርዳታቸውን ለመቀበል ፈቃደኛ አልሆነም እንጂ መላእክቱ ወደ መስቀሉ መጥተው የነገሥታቱን ንጉሥ ባዳኑት ነበር። መላእክት በዚች በተቀደሰችና አስቸጋሪ በሆነችው ደቂቃ ጣልቃ እንዳይገቡ ታዝዘው ነበር። መላእክትም እንኳ የእግዚአብሔርን ልጅ በጎልጎታ ሳለ ሊያገለግሉት አልቻሉም ነበር። ብቻውን በመሞት ለእኔና ለአንተ የተገባውን ሙሉ የሞት ቅጣት

ተቀበለ::

ወደ መስቀሉ በመሄድ የእግዚአብሔርን ልጅ ለመስቀል የዳረገው «ኃጢአት» መሆኑን ካላየን በስተቀር የሰው ልጆች ኃጢአት ምን ያህል ክፉ እንደሆነ ሊሰማን ወይም ኃጢአት ምን ያህል ጥልቀት እንዳለው ለመገንዘብ አንችልም:: የጦርነት ጥፋቶች፣ ራስን የማጥፋት አሳዛኝ ክስተት፣ ድህነት ያጠቃቸው ሰዎች ሥቃይ፣ ከኅብረተሰቡ የተገለሉ ሰዎች ሥቃይና እንቆቅልሽ፣ በአደጋ ሰለባ የሆነው ሰው ደም፣ የአስገድዶ መድፈር ወንጀልና በእኛው ትውልድ የሚካሄዱ ዝርፊያዎች፣ እነዚህ ሁሉ በአንድ ድምፅ የሚናገሩት በዚህ ሰዓት የሰው ዘር ስለ ተወረረበት ዝቅጠት ነው:: ነገር ግን ኢየሱስን ወደ መስቀል ካመጣው ከፍጥረት የኃጢአት ጽዋ ጋር የሚወዳደር ኃጢአት ተፈጽሞ አያውቅም:: በዘመናት ሁሉ ወደ ሰማይ የሚወረወረው ጥያቄ፣ «እርሱ ማን ነው? ለምንስ ሞተ?» የሚል ሲሆን፣ የተመለሰውም መልስ፣ «ይኼ አንዱ ልጄ ነው፣ የሞተውም ለአንተ ኃጢአት ብቻ ሳይሆን ለዓለምም ኃጢአት ጭምር ነው» የሚል ነው:: ለአንተ ኃጢአት ትንሽ ሊመስልህ ይችል ይሆናል፤ ለእግዚአብሔር ግን ትልቅና አስጸያፊ ነገር ነው:: ከእግዚአብሔር ፍቅር ቀጥሎ በዓለም ላይ ትልቁ ነገር ኃጢአት ነው::

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ለመዋጀት ምን ያህል ታላቅ ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ እንደሆነ በአግባቡ ከተረዳን፣ የዚያን ጊዜ የሰው ዘር ምን ያህል አስከፊ ስሕተት እንደ ፈጸመ መገንዘብ እንችላለን:: የሰው ዘር አዳኝ ካላገኘ መጥፋቱ ግልጽ ነበር:: ኃጢአት እግዚአብሔርን የመጨረሻ ውድ የሆነውን ነገር አስከፍሎታል:: ታዲያ መላእክት የእግዚአብሔር ዕቅድ በሥራ ላይ በዋለበት ጊዜ ፊታቸውን ሸፍነው በድንጋጤ ጸጥ ማለታቸው ያስገርማል? የኃጢአትን የሚያስፈራ ብልሹነት ሲመለከቱት ኢየሱስ ይሸከመዋል ብለው ለማመን ምን ያህል አስቸግሯቸው ይሆን? ሆኖም ከጥቂት ጊዜ በኋላ የተሸፈነ ፊታቸውን ገልጠው እንደገና ምስጋና ማቅረብ ጀመሩ:: በዚያን ዕለት በቀራንዮ ላይ ብርሃን በራ:: አስከፊው ጨለማ በደኅንነት ብርሃን ሲቀደድ፣ የእግዚአብሔር ክብር በመስቀሉ ላይ አበራ:: ክፉ የሰይጣን ሠራዊት ከዚህ በኋላ ሰዎችን ሁሉ በጨለማና በሽንፈት ውስጥ ማቆየት አልቻሉም::

## መላእክት በትንሣኤው ወቅት

መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ በሞተ በሦስተኛው ዕለት፣ «እነሆም፣የጌታ መልአክ ከሰማይ ስለ ወረደ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤ ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ ተቀመጠ:: መልኩም እንደ መብረቅ፣ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበረ:: ጠባቆቹም እርሱን ከመፍራት የተነሣ ተናወጡ፤ እንደ ሞቱም ሆኑ» ይላል (ማቴ. 28:2-4)::

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ይህ ድንጋይ ምን ያህል ሊመዝን እንደሚችል ለመገመት ሞክረዋል:: ሆኖም ኢየሱስ ድንጋዩ ቢኖርም ባይኖርም ከመቃብር መውጣቱ አይቀሬ ስለሆነ፣ ግምት መስጠቱ አስፈላጊ አይሆንም:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን የሚጠቅሰው ስለተከናወነው ታላቅ የትንሣኤ ተአምር የሚቀጥሉት ትውልዶች የተወሰነ ነገር እንዲያውቁ ለማድረግ ነው:: ብዙ ጊዜ እነዚያ ጠባቂዎች ከንጋት ጮራ የደመቀው መልአክ ያንን ግዙፍ ቋጥኝ (ምናልባትም በአንድ ጣቱ ብቻ) ሲያንከባልለው ባዩት ጊዜ ምን አስበው ይሆን? እያልሁ እገረማለሁ:: ጠባቂዎቹ በከባድ ሁኔታ የታጠቁ ቢሆኑም በፍርሃት ርደው ነበር::

ማርያምም ወደ መቃብሩ ውስጥ ስትመለከት፣ «የኢየሱስ ሥጋ ተኝቶበት በነበረው አንዱ በራስጌ ሌላውም በእግርጌ ተቀምጠው አየች» (ዮሐንስ 20:11፣12):: ከዚያም ከመቃብሩ አጠገብ ተቀምጠው ከነበሩት መላእክት አንዱ ዓለም ሰምቶ የማያውቀውን ታላቅ መልእክት አወጀ:: «ተነሥቷል እንጂ በዚህ የለም» (ሉቃስ 24:6):: እነዚያ ጥቂት ቃላት የፍጥረትን ታሪክ ለወጡት:: ጨለማና ተስፋ መቍረጥ ሞቶ ተስፋና በጎን ነገር መጠባበቅ በሰዎች ልብ ውስጥ ተወለደ::

## መላእክትና የኢየሱስ ዕርገት

የኢየሱስን የዕርገት ታሪክ የምናገኘው በየሐዋርያት ሥራ 1 ውስጥ ሲሆን፣ ቍጥር 9፣ «ይህንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ፤ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው» ይላል:: ኢየሱስ ወደ ምድር በመጣበት ወቅት በመላእክት ሠራዊት

ታጅቦ ነበር:: «ደመና» የሚለው ቃል እንደገና ወደ እግዚአብሔር አብ ቀኝ አጅበው ለመውሰድ የመጡትን መላእክት የሚያመለክት እንደሆነ እምናለሁ::

የሚጠብቁት ደቀ መዛሙርት አዝነውና ተክዘው ነበር:: ዓይኖቻቸው በዕንባ ተሞልተው ነበር:: ሆኖም እንደገና በሰው የተመሰሉና ነጭ ልብስ የለበሱ ሁለት መላእክት ተገልጠው፣«የገሊላ ሰዎች ሆይ፣ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት፣ እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው» (የሐዋርያት ሥራ 1:11)::

ስለሆነም፣ መላእክት ከሞት የተነሣውን የክብር ጌታ በማጀብ በአባቱ ቀኝ አስቀምጠውታል:: ከዚያም የንጋት ከዋክብት እንኳን የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ለሆነው ክርስቶስ ውዳሴ፣ ክብርና ምስጋናን አቀረቡለት:: በሌላ መልኩ ደግሞ አንዳንድ መላእክት ወደ ኋላ በመቅረት ለክርስቶስ ከመላእክት ሠራዊቱ ጋር እስከሚመለስበት ጊዜ ድረስ ሁልጊዜ አጠገባቸው እንደሚሆኑ፣ በሚመጡት ዘመናት ሁሉ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመርዳት ዝግጁ እንደሆኑ ለደቀ መዛሙርቱ አረጋገጡላቸው::

# አሥራ ሁለት

# መላእክት በትንቢት ውስጥ

መላእክት በወደፊት ሁኔታዎች ውስጥ ጠቃሚ ሚና አላቸው:: የሰው ታሪክ የተጀመረው እግዚአብሔር በዔድን አትክልትን ከተከለ በኋላ ዘላለማዊ ኅብረትን ለማድረግ ይችል ዘንድ ሰውን በፈጠረበት ወቅት ነው:: መላእክት እዚያ ነበሩ:: የሰው ልጆችን ትዕይንት ከመከታተል አቋርጠው አያውቁም:: በሚቀጥሉት ዘመናት እስከ ዘላለምም ድረስ ትዕይንቱን መከታተላቸውን ይቀጥላሉ::

ፍጥረታት በተፈጠሩበት ወቅት በንጋት ከዋክብት ዝማሬ በታጀበው አስደናቂ ትዕይንት ላይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ መላእክት እንደ ተገኙ ሁሉ ትልቁ መሰፍርት የሌላቸው የሰማይ ሠራዊት ለዘመናት ሁሉና ለዘላለም የእግዚአብሔርን ትንቢቶች ከፍጻሜ ለማድረስ ያግዛሉ::

እግዚአብሔር በሚደነግግበት ወቅት ሰይጣን (ሉሲፈር) ሥርዓት አልባ ከሆነችው ዓለም ተወግዶ በምትኩ እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ቅድስናንና እውነተኛ የሆነ መንፈሳዊ መንግሥትን ይመሠርታል:: ያ ሁኔታ በተግባር እስኪታይ ድረስ የሰው ዘር በዓለም ላይ ፍጹም ሰላም ምን እንደሆነ ሊያውቅ አይችልም:: በሮሜ 8 ውስጥ ጳውሎስ ፍጥረት ሁሉ የክርስቶስን የድል ቀን በመቃተትና በጣር እንደሚጠብቅ ይናገራል::

ነቢያት እግዚአብሔር ርግማንን ስለሚያነሣበት ቀን፣ የአንበሳ ደቦልና ጥጃ አብረው ስለሚተኙበትና ሕዝቡም ሰልፍን ስለ-ማይማርበት አስገራሚ ቀን ይናገራሉ (ኢሳይያስ 2:4፤ 11:6):: የመላእክት ሠራዊት ንጉሣዊ ድንጋጌዎቹን ይፈጽማሉ:: ደግሞም እግዚአብሔር በፍጥረት ላይ ያለውን ዓላማ ይቆጣጠራሉ:: ክርስቶስ በታላቅ ኃይል የሚመጣ ሲሆን፣ ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሆናሉ:: በሐዋርያት ሥራ 1:10፣ 11 ላይ እንደተጠቀሰው፣

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ መላእክት ለደቀ መዛሙርቱ የማማከር አገልግሎትን ሰጥተዋል:: ቀደም ብለን እንደተመለከትነው የደብረ ዘይትን ተራራ ከለቀቀ በኋላ መላእክት ተገልጸው፣ «የገሊላ ሰዎች ሆይ፣ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት፣ እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው» (የሐዋ. ሥራ 1:11):: መላእክት ኢየሱስ ክርስቶስ በደመና ውስጥ ተሰውሮ በመሄዱ ምክንያት በኀዘን የተመቱትን ደቀ መዛሙርት አበረታተዋቸዋል:: ከዚህ በኋላ መላእክት የሚያስላስሉት በእግዚአብሔር ትንቢታዊ ዕቅድ መሠረት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተተነበዩትን የወደፊት ክንውኖች ነው::

በየትኛውም ዘመን የነበሩ እውነተኛ አማኞች፣ «ይኼ ለዘመናት የቆየ ግጭት ማብቂያ ይኖረው ይሆን?» ብለው ይጠይቃሉ:: በተመሳሳይ ሁኔታም እያንዳንዱ የታሪክ ዘመን የራሱ ችግሮችና ፍርሃቶች አሉበት:: እያንዳንዱም ትውልድ «የሁኔታዎችን ምንነት ለይቶ ለማወቅ» ይጥራል:: ከጀርባው ደግሞ የማይታይ የዘመናት ትግል አለ:: ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለብዙ የሰው ዘር ችግሮች መፍትሔ ይሰጣል ብለን አስበን ነበር:: በአንዳንድ መንገዶች ለምሳሌ እንደ ፈንጣጣና የልጅነት ልምሻ የመሳሰሉትን በማጥፋት በሽታዎችን እንዳንፈራ አድርጓል:: ነገር ግን ቴክኖሎጂ የሠራናቸው ነገሮች የጥፋት መሣሪያዎች እንዲሆኑም አድርጓል:: ድህነት፣ ረሃብ፣ ስስት፣ ጥላቻ፣ ሽብር፣ ዝሙት፣ ጦርነትና ሞት አሁንም አብረውን አሉ:: ይህም በሉሲፈር ልብ ውስጥ በምሥጢራዊ ሁኔታ ከተጀመረው ጦርነት ጋር አንድ ዓይነት ነው:: ዓለማችንም ራሷን በማጥፋት ጐዳና ላይ ያለች ነው የምትመስለው:: ሆኖም እግዚአብሔር ሌሎች ዕቅዶች አሉት:: በመንገዱ መጨረሻ ላይ ብርሃን አለ:: አንድ ቀን ሰይጣንና ሠራዊቱ ተሸንፈው ወደ ታች ይወርዳሉ:: መጽሐፍ ቅዱስ ጽድቅ በመጨረሻ ድል እንደሚነሣ፣ ፍጹምነት ወደ ምድር እንደሚመጣና በመጨረሻም የእግዚአብሔር መንግሥት ከፍ እንደሚል ይናገራል:: ይህንን ሁሉ ከፍጻሜ በማድረሱ በኩል መላእክት ከፍተኛ ድርሻ ይኖራቸዋል::

አንዲት ትንሽ ልጃገረድ ሰዓቱ 13 ጊዜ ሲደውል በመስማቷ

ትንፋሿ ቍርጥ ቍርጥ እያለ ወደ እናቷ እየሮጠች መጣችና፣ «እማዬ፣ ሰዓቱ ከመቼውም ይልቅ ፈጥኗል» አለች:: በዓለም ውስጥ ያሉ ሁሉ ማለት ይቻላል በዚህ አሳብ ይስማማሉ:: ከመቼውም ይልቅ ረፍዷል:: የሰው ዘር እንደ ዕብደት በሚቆጠር ፍጥነት ወደ አንድ መጨረሻ ወዳለው ነገር የሚሮጥ ይመስላል:: መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ይህንን መጨረሻ የሆነ ነገር የተነበየው ሲሆን፣ እርሱም የአዲስ ዓለም መምጣት ነው:: በዘመናዊ ቴክኖሎጂና ሳይንሳዊ ግኝቶች አማካኝነት የአዲሱን ዓለም ጭላንጭል ብቻ ነው የሚያሳዩን:: የባሕርይ ብልሹነት ባይኖር ኖሮ ሰው ራሱ ያገኘው ነበር:: ሆኖም ሰው በእግዚአብሔር ላይ የሚያምፀው ዓመፅ ነው ሁልጊዜ እንቅፋት የሚሆንበት:: ለሰው ዓመፅ ቅጣቱ ሞት ነው:: ግሩም መሪዎችና ድንቅ አእምሮ ያላቸው ሰዎች በሞት ተገትተዋል:: መጽሐፍ ቅዱስ፣ «ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት. . . . ተመደበባቸው» ብሎ ያስተምረናል (ዕብራውያን 9:27):: ዛሬ እኛ የዓለም ሰዎች እንደ አብርሃም ሊንከን የመሳሰሉትን መሪዎች ብንፈልግም፣ ሞት ግን ይነጥቃቸዋል::

እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ፍጥረት አዲስ ዓይነት ሕይወት በመፍጠር ጊዜን ከዘላለማዊነት ጋር ለማያያዝ መላእክትን ይጠቀምባቸዋል:: የዛሬ ምሁራን እንኳ ጊዜ ስለማይኖርበት ዘመን እየተነጋገሩበት ነው:: ብዙ ሳይንቲስቶች የዘመኑ ሰዓት ማብቂያው ላይ እንደሆነ ይስማማሉ:: ከሥነ ምህዳር፣ ከሕክምና፣ ከሳይንስ፣ ከሥነ ምግባር አኳያ ጊዜው የተሟጠጠ ይመስላል:: በዚች ምድር ላይ በሁሉም አቅጣጫ የሰው ጊዜ እያለቀ የሚሄድ ይመስላል:: ራስን ማጥፋት የሰውን ዘር እየዋጠው ነው::

ሰው ራሱን ያጠፋል? አያጠፋም! እግዚአብሔር ሌላ ዕቅድ አለው:: ከዘመናት በፊት ጀምሮ ሰው ከተሰጠው አጭር ዕድሜ ባሻገር ምን እንዳለ ለማወቅ ሲፈልግ ኖሯል:: ዘመናዊው ሰው የወደፊት ዕድሉን ለማወቅ ወደ አስማት፣ የምሥራቅ ተረታዊ እምነትና፣ መጻፍን ወደሚያነብቡ ሰዎች ፊቱን እያዞረ ነው:: የሚገርመው ነገር ስለ ወደፊቱ በትክክል ወደሚናገረው ብቸኛ መጽሐፍ ቅዱስ ፊታቸውን የሚያዞሩ ጥቂቶች ብቻ ናቸው:: መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሳን መላእክቱ ጋር ተመልሶ እንደሚመጣ ይናገራል:: መምጣቱን በተመለከተ እንደ «ሌባ

በሌሊት» (2ኛ ጴጥሮስ 3:10)፣ የቍጣ ቀን (ሮሜ 2:5)፣ የታላቁ ፍርድ ቀን (ይሁዳ 6) እና ሌሎች ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ብዙ መግለጫዎች ተሰጥተዋል:: የፍጻሜነት ዘመን ከመምጣቱ በፊት የሰው ዘር ተወዳዳሪ በሌላቸው አሠቃቂ ሁኔታዎች ውስጥ ያልፋል:: አምባገነንነት፣ ድህነት፣ በሽታ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ የሞራል ድቀት፣ ጦርነት የሰዎችን ልብ በፍርሃት ያቀልጡታል (ሉቃስ 21:26)::

ሉቃስ 21 ላይ «ጦርንና ሁከትንም . . . ሕዝብ በሕዝብ ላይ፣ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣል፤ ታላቅም የምድር መናወጥና በልዩ ልዩ ስፍራ ቸነፈር፣ ራብም ይሆናል፤ የሚያስፈራም ነገር ከሰማይም ታላቅ ምልክት ይሆናል» (ከቍጥር 9-11) ብሎ ይናገራል::

አማኝ ክርስቲያኖችና የሚያምኑ አይሁዳውያንም ጭምር ይሰደዳሉ:: «ስለ ስሜም ወደ ምኵራብና ወደ ወኅኒ አሳልፈው ይሰጡአችኋል፣ ወደ ነገሥታትና ወደ ገዥዎችም ይወስዱአችኋል፤. . . ወላጆችም ስንኳ ወንድሞችም፣ ዘመዶችም፣ ወዳጆችም አሳልፈው ይሰጡአችኋል፣ ከእናንተም አንዳንዱን ይገድላሉ፤ በሁሉም ስለ ስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ::. . .

«ኢየሩሳሌም ግን በጭፍራ ተከባስታዩ በዚያን ጊዜ ጥፋትዋ እንደ ቀረበ እወቁ::. . . .

«በፀሐይና በጨረቃም በከዋክብትም ምልክት ይሆናል፤ በምድር ላይም አሕዛብ ከባሕሩና ከሞገዱም ድምፅ የተነሣ እያመነቱ ይጨነቃሉ፤ ሰዎችም ከፍርሃትና በዓለም የሚመጣበትን ከመጠበቅ የተነሣ ይደክማሉ፤ የሰማያት ኃይላት ይናወጣሉና» (ከቍጥር 12-26):: በቍጥር 27 ላይ ጌታ ኢየሱስ «በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ በኃይልና በብዙ ክብር በደመና ሲመጣ ያዩታል» ይላል::

በዘመን መጀመሪያ ላይ የመላእክት ኃይላት በሰማይ ጦርነት አውጀው ነበር (ራእይ 12:7-9):: እንደዚሁም ደግሞ ሰይጣን ለመጨረሻ ጊዜ አቋም በሚይዝበት በመጨረሻው ዘመን መላእክት ሌላ ጦርነትን ያውጃሉ:: ጊዜው እየቀረበ ሲሄድ ሰይጣን ሥራዎቹን ያፋፍማል::

ሰይጣንና መላእክቱ እንደገና ሰውን ለማጥፋትና ለመፈተን

በማይመለሱበት ሁኔታ ወደ እሳት ባሕር በሚወረወሩበት ወቅት ለፍጥረት በተለይም ለምድር ከፍተኛ የድል ቀን ይሆናል:: የእግዚአብሔር ቃል ይህ ተግባር ለመላእክት እንደ ተሰጠና ድሉም የእነርሱ መሆኑን ያረጋግጣል (ማቴዎስ 13:41፣42)::

## መላእክት የእግዚአብሔርን ምርጦች ይሰበስባሉ

ከዚህ አሳብ ጋር በተያያዘ ኢየሱስ፣ «የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል» ብሏል (ማቴዎስ 25:31):: በሌላ አነጋገር፣ ኢየሱስ በሚመለስበት ጊዜ በሰማይ ሠራዊት የሚታጀብ ይሆናል:: ቅዱሳን መላእክት ከእርሱ ጋር ይሆናሉ:: በማቴዎስ 13:41-42 እንደተናገረው፣ «የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል፤ ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዓመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ ወደ እቶን እሳትም ይጥሏቸዋል:: በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል::»

ኢየሱስ በተለምዶ የስንዴና የእንክርዳድ ምሳሌ ተብሎ የሚጠራውን አጭር ታሪክ በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ተናግሯል (ማቴዎስ 13:24-30፣36-43):: እስከ መከር ጊዜ ድረስ ሁለቱም አብረው እንዲያድጉ የተፈቀደላቸው ሲሆን፣ በመጨረሻ ግን አጫጆቹ እንክርዳዱን ሰብስበው ያቃጥላሉ:: ስንዴውን ግን በጎተራ ይከቱታል:: ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ብዙ ኃጢአት በዓለም ላይ እንዲሠራ ለምን እንደ ፈቀደና የፍርድ እጁን ለምን እንደማይዘረጋ ያስገርመናል:: እግዚአብሔር ለምን ኃጢአትን እንዲያበቃ አያደርግም? ለዚህ ጥያቄ ኢየሱስ ከተናገረው ከዚህ ክፍል መልስ መስጠት እንችላለን:: ክፉውና መልካሙ ሁለቱም «አብረው ይደጉ» (ቍጥር 30):: ክፋትን ሁሉ ከምድር ገጽ ለማጥፋት ብንሞክር ማን ለፍትሕ ዋስትና ይሰጣል:: እዚህ በንጽሕና የተሞላ ፍትሕ የለም:: ምክንያቱም በፍርድ ወንበር የሚቀመጡት ዳኞች ሳይቀሩ ሁሉም ዓመፀኞች ናቸውና:: ሁላችንም የኃጢአት ጥፋተኞች ነን::

የሰው ልጅ የፍትሕን መመዘኛዎች ለማሟላት የሚችለውን ሁሉ ማድረግ ይኖርበታል:: ይህ ግን ፍጹማዊ ፍትሕን አይመሠርትም:: መላእክት ጥሩውን ከመጥፎ የመለየት አገልግሎት ተሰጥቷቸዋል::

የእግዚአብሔር ፍርድ ንጹሕ ከመሆኑ የተነሣ የተፈረደባቸው እንኳ «አንተ ጻድቅ ነህ» ብለው በጉልበታቸው ተንበርክከው ይመሰክሩለታል:: አንድ ሰው «በምሞትበት ወቅት የምፈልገው ፍርድን ሳይሆን ምሕረትን ነው» ብሏል:: ያ ምሕረት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ተሰጥቷል::

መላእክት ክርስቶስ በሚመለስበት ወቅት እርሱን የማጀብ ብቻ ሳይሆን፣ ከመንግሥቱ ክፉ የሆኑትን ነገሮች ለፍርድ የመሰብሰብ ኃላፊነት ተሰጥቶአቸዋል (ማቴዎስ 13:47-50)::

እግዚአብሔር ሰይጣንና ኃጢአትን ካስወገደ በኋላ ምን ዓይነት ምድር እንደሚሆን መገመቱ ለአእምሮ ይከብዳል:: አእምሮአችን «ክርስቶስ በዙፋን ላይ» የሚለውን አሳብ ለመቀበል ይቸገራል:: በአፍሪካ ከሳሃራ በረሃ በታች የሚገኘው አካባቢ ያብባል ይለመልማልም:: የሰው ልጅ አዳዲስ ምግቦችን ማብቀል ይችላል:: ዛሬ ጥቅም የማይሰጠው መሬት በዓመት አሥራ ሁለት ሰብሎችን ያፈራል::

የሰውን ልጅ ልብ ወደ ምግባረ ብልሹነት የሚገፋፋው ክፋት በዚያን ጊዜ ያከትማል:: በዚያን ወቅት የሰው ሁሉ ጥማት ጽድቅ ይሆናል::

በዚህ አሳዛኝ ዘመን ይህንን ለማመን ከፍተኛ እምነት የሚጠይቅ ቢሆንም፣ ይህ በግልጽ የቀረበ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ነው:: ከዚህ የወደፊት ተስፋ ውጪ ዘመናዊው ሰው ወደ ሐሺሽና ወደ አልኮል መጠጦች ከመመለስ ሌላ ምን ሊያደርግ እንደሚችል አላውቅም::

ዛሬ የመላእክትን አገልግሎት የመቀበል ወይም ያለመቀበል ምርጫ አለን:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል የምንመረጥ ከሆነ የሰማይ መላእክትን ጥበቃና እንክብካቤም መምረጣችን ነው:: በምጽአት ወቅት ግን የመምረጥ ዕድል አይሰጠንም:: ዛሬ ብንዘገይ ጊዜው የሚያበቃ ከመሆኑም በላይ፣ የዘላለም ሕይወት የሚያስገኘውን የደኅንነት ተስፋና የመላእክትን የርኅራኄ አገልግሎት እናጣለን::

## መላእክት በወደፊቱ ዕድላችን

ዶ/ር ሚለር፣ «. . . ለዚህች ቍሳዊ ምድር. . . ለዚህ ለዛለና ላረጀ ዓለም የወደፊቱ ዘመን ምን ይዞ ይጠብቀዋል? . . . ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ የምናገኘው ከኮከብ ቆጠራ ወይም ከጥንቆላ ሳይሆን ከመለኮታዊ የእግዚአብሔር ቃል ነው:: በዘመናት ሂደት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተጻፉት ትንቢቶች እየተፈጸሙ ሲሄዱ ቅዱሳን መላእክት በአፈጻጸሙ ላይ ተካፋዮች እንደሚሆኑ እርግጠኛ መሆን እንችላለን» ብለዋል:: እግዚአብሔር ምድርን ያድሳታል፤ አዲሲቷን ኢየሩሳሌምንም ከሰማይ እንድትወርድ በማዘዝ የተዋጁትን ሰዎች ከመላእክት የበለጠ ደረጃ ይሰጣቸዋል:: ምን ዓይነት ድንቅ ሁኔታ ነው የሚጠብቀን!

ኤልያስ ከእስራኤል የጨለማ ዘመናት በአንደኛው ወቅት በድንገት ብቅ ያለ፣ ታላላቅ ከሚባሉት ነቢያትም አንዱ ነበረ (1ኛ ነገሥት 17):: ኤልያስ ጠንካራና ፀሐይ ያጠወለገው የበረሃ ልጅ ነበረ:: አንዳንድ ጊዜ ደፋር እንደ አንበሳ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ተስፋ በመቍረጥ የተደቆሰ ይሆናል:: በሌላ ጊዜም እውነተኛው አምላክ ማን እንደሆነ እንይ ብሎ ከበኣል ነቢያት ጋር ተወራርዷል (1ኛ ነገሥት 18:19):: የበኣል ነቢያት ከውሸተኛው አምላካቸው ምንም መልስ ሳያገኙ፣ እግዚአብሔር ለኤልያስ በእሳት መለሰለት:: በዚህ ጊዜ ኤልዛቤል የነቢዩን ድል መቀበል አቅቷት ሕይወቱን ለማጥፋት በሰረገላዋ ብዙ ኪሎ ሜትሮች አሳደደችው:: ኤልያስ በጕዞው ዝሎና እጅግ ተርቦ ከክትክታ ዛፍ በታች ተጋደመ:: ለራሱ እጅግ አዝኖ ሲያንቀላፋ መልአክ ዳስሶ አነቃው:: ከዚያም ምግብ በፊቱ ቀረበለትና መልአኩ «ተነሥተህ ብላ» አለው::

«ሲመለከትም፣ እነሆ፣ በራሱ አጠገብ የተጋገረ እንጎቻና በማሰሮ ውኃ አገኘ:: በላም ጠጣም፣ ተመልሶም ተኛ:: የእግዚአብሔር መልአክ ደግሞ ሁለተኛ ጊዜ መጥቶ ዳሰሰውና:- የምትሄድበት መንገድ ሩቅ ነውና ተነሥተህ ብላ አለው:: ተነሥቶም በላ ጠጣም:: በዚያም ምግብ ኃይል እስከ እግዚአብሔር ተራራ እስከ ኮሬብ ድረስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ሄደ» (1ኛ ነገሥት 19:6-8)::

እግዚአብሔር ታማኝ ነቢዩን አልጣለውም:: ሥጋዊ፣ ሥነ ልቦናዊና መንፈሳዊ ፍላጐቱን አሟላለት:: ብዙዎቻችን የኑሮአችንን ጫና ለመቋቋም ተስፋ እንቆርጣለን:: ሆኖም በመንፈስ በተሞላና

በመንፈስ በሚመራ ሕይወት የምንኖር ከሆነ የእግዚአብሔርን ተስፋዎች ለመጨበጥ እንችላለን:: ትንቢታዊ የእግዚአብሔር ቃላት «ተስፋን» ይሰጡናል:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር የወደፊት ዕቅድና ተስፋ ከሚሰጠን ውጭ በመካከለኛ የአስተሳሰብ ደረጃ ላይ ያለ ሰው ምን ሊያደርግ እንደሚችል አላውቅም:: አንድ ሰው እጆቹን በማንቋቋት፣ ራሱን በማጥፋት ወይም ጠንቋዮችን በማመን መልስ ሊያገኝ እንደማይችል ግልጽ ነው:: ስለ ወደፊቱ መልስ ማግኘት የምንችለው ከእግዚአብሔር ቃል ነው:: በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ የተጠቀለለ ነው:: እግዚአብሔር ክርስቶስን የተስፋዎቻችንና የሕልሞቻችን ማዕከል አድርጎታል:: እርሱ በምጽአቱ ጊዜ የሚያጅቡት የእነዚህ የመላእክት ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ ነው::

## የመልአክ ሥልጣን

የአዲስ ኪዳን ጸሐፍት እግዚአብሔር ትንቢቱን ለመፈጸም ለመላእክት ስለሰጠው ሥልጣን ማረጋገጫ ሰጥተዋል:: ሐዋርያው ጴጥሮስ ይህንን እውነት ሲያስረግጥ፣ በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠው ክርስቶስ፣ «መላእክትና ሥልጣናት ኃይላትም ከተገዙለት በኋላ» ወደ ሰማይ እንደሄደ ይናገራል:: ሃያ አራቱ ሽማግሌዎችና መላእክት እየሰገዱ ለበጉ አዲስ ዝማሬን የሚዘምሩበት ጊዜ ይመጣል (የዮሐንስ ራእይ 5:9-10):: ከዚያ በመቀጠል ቅዱሳን መላእክት በዙፋኑ ዙሪያ በመሰብሰብ ስለ በጉ በአንድነት ምስክርነት እየሰጡ በእንደዚህ ዓይነት ቃላት ያሞግሱታል:- «የታረደው በግ ኃይልና ባለጠግነት፣ ጥበብም፣ ብርታትም፣ ክብርም፣ ምስጋናም፣ በረከትም ሊቀበል ይገባዋል» (የዮሐንስ ራእይ 5:12):: መላእክት ከፍተኛ ሥልጣን ያላቸው ቢሆንም፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ የተገደቡ ናቸው:: መላእክት ከእግዚአብሔር መልእክት አያፈነግጡም፤ መልእክቱን በፍጹም አይቀንሱም፤ የእግዚአብሔርንም ዕቅድ በፍጹም አይለውጡም:: በዘመናት ሁሉ ራሳቸውን ሳይሆን እርሱን ብቻ ሲያከብሩ ነው የኖሩት::

መጽሐፍ ቅዱስ አጋንንት ለአለቃቸው ለሰይጣን ይህችን ዓለም ለመቆጣጠር የቆረጡ መሆናቸውን ያስተምረናል:: ኢየሱስ እንኳ

«የዚህ ዓለም ገዥ» ብሎ ይጠራዋል (ዮሐ. 12:31)። እርሱ ዋናው አደራጅና ቀያሽ ነው። ብዙ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክም ሆነ ዛሬ መላእክትና አጋንንት በውጊያ ውስጥ ይሳተፋሉ። በዘመናችን የሚከሰቱት ብዙዎች ሁኔታዎች በዚህ በማይታይ ትግል ውስጥ የተካተቱ ሊሆኑ ይችላሉ።

በመጨረሻው ማን ድልን እንደሚቀዳጅ ግልጽ ነው። ኢየሱስ በየጊዜው መላእክትና እርሱ ድል እንደሚነሡ አረጋግጦልናል። «የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፣ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣሉ» (ማቴዎስ 25:31)። ሐዋርያው ጳውሎስ «ጌታ ኢየሱስ ከሥልጣኑ መላእክት ጋር ከሰማይ በእሳት ነበልባል ሲገለጥ . . .» (2ኛ ተሰሎንቄ 1:7፣8) ብሎ ጽፏል።

ኢየሱስም፣ «በሰው ፊት የሚመሰክርልኝ ሁሉ የሰው ልጅ ደግሞ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ይመሰክርለታል» በማለት አስተምሯል (ሉቃስ 12:8)። ክርስቶስን አውቃለሁ ማለቱ የተሳሳተ በመሆኑ ምክንያት መላእክት እንደማያውቁት ሲገነዘብና ውጤቱም ዘላለማዊ ጥፋት ሲሆን፣ አንድ ሰው የሚደርስበትን ሥቃይ መረዳቱ አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን በዘመናት ሁሉ የነበሩ አማኞች ከነገድ፣ ከዘር፣ ከቋንቋ በሰማይ የፍርድ ዙፋን ፊት የሚቀርቡበት ጊዜ እንዴት ያለ ይሆን? የእግዚአብሔር ቃል ይህንን «የበጉ ሰርግ እራት» ብሎ ይጠራዋል (ራእይ 19:9)። ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ ተብሎ ዘውድ የሚጭንበት ታላቅ ክስተት ነው። ይህ በዘመናት ሁሉ የነበሩ አማኞችና የመላእክት ሠራዊት ጌታ እንደሆነ ተነበርክከው የሚመሰክሩበት ጊዜ ነው።

የዮሐንስ ራእይ ከምዕራፍ 4-19 ድረስ ታይቶ የማይታወቅ ፍርድ በዓለም ላይ የሚመጣ ለመሆኑ ያብራራልናል። መላእክት በእነዚህ ፍርዶች ሁሉ ውስጥ ይሳተፋሉ። ከዚህ አስፈሪ ሁኔታ በኋላ ግን ኢየሱስ መንግሥቱን ለመመሥረት ከመላእክቱ ጋር ይመጣል።

በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል የሚካሄደው ውጊያ ሌሎች ዓለማትና ጋላክሲዎችን ያካትት አያካትት አናውቅም። ነገር ግን ዓለም የግጭቱ ስፍራ መሆኗን እናውቃለን። ይህ ግን ዓለማትን በሙሉ የሚነካ ግዙፍ ውጊያ ነው። በዚህች ዓለም ባለችን አጭር

ጊዜ በዘመናት መካከል በተካሄደው ጦርነት ውስጥ መካፈል አእምሮን የሚያነቃቃ ነገር ነው:: ከሕዋው ውጪ የመጡ ልዕለ ተፈጥሯዊ ፍጥረቶች ለዚህች ዓለም ሲሉ በትግል ውስጥ መሳተፋቸው የሚያስደንቅ ነው::

ይኼ ሁሉ የተጀመረው በመካከለኛው ምሥራቅ በጤግሮስና በኤፍራጥስ ወንዞች አቅራቢያ በዔድን ገነት ውስጥ ነው:: በጥንት ታሪክ የጎላ ስፍራ የነበራቸው እንደ እስራኤል፣ ግብፅ፣ ሶርያ፣ ኢራን፣ ወዘተ... ያሉ አገሮች እንደገና ዛሬም ያንኑ የጎላ ስፍራ መያዛቸው አስፈላጊ ነው:: በዚያች ገነት እግዚአብሔር ትልቅ ተስፋን ሰጥቷል:: «በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ» (ዘፍጥረት 3:15):: ወደ ዘመኑ መጨረሻ ስንቃረብ፣ የእግዚአብሔር ሠራዊት እያየለ ሲሄድ፣ የሰይጣን እየተሰባበረና እየተቀጠቀጠ ነው የሚሄደው:: የመላእክት አለቃ የሆነው ሚካኤል በእግዚአብሔር ትእዛዝ ለመጨረሻው የአርማጌዶን ጦርነት ኃይሉን እያደራጀ ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመጨረሻው ትዕይንት በሰማይ የሚካሄደው ነው::

ከብዙ ዓመታት በፊት የአሜሪካን የምክር ቤት አባላትን ምግብ ቤት እጐበኝ ነበር:: ከብዙ ሰዎች ጋር እየተነጋገርሁ ሳለሁ አንደኛ ው የምክር ቤት አባል ወደ ጠረጴዛው ጠራኝና፣ «ቢሊ፣ ዛሬ በጎ ነገር ይመጣል ብለው ስለሚያስቡና መጥፎ ነገር ይመጣል ብለው ስለማያስቡ ሰዎች ነው የምንወያየው:: አንተ ከየትኛው ወገን ነህ? አለኝ:: እኔም ፈገግ አልሁና፣ «እኔ መልካም ነገር ይመጣል ብለው ከሚያስቡት ወገን ነኝ» ስለው፣ «ለምን?» ብሎ ጠየቀኝ::

እኔም፣ «የመጽሐፍ ቅዱስን የመጨረሻ ገጽ ስላነበብኩ ነው» ብዬ መለስኩለት::

መጽሐፍ ቅዱስ የተዋጁት ሰዎች ከመላእክት የበላይ ስለሚሆኑባት በእግዚአብሔር ስለተሠራች አንዲት ከተማ ይናገራል:: «ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን የሚመጣውን እንደ ብርሌ የሚያንጸባርቀውን የሕይወትን ውኃ ወንዝ አሳየኝ» ይላል (ራእይ 22:1):: እናም «ፊቱንም ያያሉ፤ ስሙም በግምባሮቻቸው ይሆናል:: ከእንግዲህም ወዲህ ሌሊት አይሆንም፤ ጌታ አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና የመብራት ብርሃንና የፀሐይ ብርሃን

አያስፈልጋቸውም፤ ለዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሣሉና» (ከቍጥር 4-5)::

የሚቀጥለው ቍጥር መላእክትን በሚመለከት አስገራሚና የመጨረሻ የሆነውን ቃል ይናገራል:: «እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነቶች ናቸው:: የነቢያትም መናፍስት ጌታ አምላክ በቶሎ ሊሆን የሚገባውን ነገር ለባሪያዎቹ እንዲያሳይ መልአኩን ሰደደ::»

ክርስቲያኖችና ክርስቲያን ያልሆኑ ሁሉ እግዚአብሔር በቍጥር 7 ላይ ስለሚናገረው ነገር ሊያሰላስሉ ይገባል:: ይኸውም «እነሆም በቶሎ እመጣለሁ:: የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ቃል የሚጠብቅ ብፁዕ ነው አለኝ» የሚለውን ነው::

# አሥራ ሦስት

## መላእክትና ሞት

የኢየሱስ አስከሬን ወደ ተጋደመበት ወደ አትክልቱ ስፍራ የመጣው መልአክ ድንጋዩን አንከባልሎ መቃብሩ በንጹሕ አየርና በጥዋት ብርሃን እንዲሞላ አደረገው:: መቃብሩ ሕይወት ያለበትና የሕያው እግዚአብሔር ክብር የተንጸባረቀበት እንጂ ከዚያ ወዲያ ባዶና የቀዘቀዘ ክፍል ወይም የሚደብት ስፍራ አልሆነም:: የሞትን ጥላ የገፈፈው የሰማይ ብርሃን የለውጥ መዘክር እንጂ ከዚያ በኋላ የጨለመ እስር ቤት ሊሆን አልቻለም:: የኢየሱስ ትንሣኤ ለውጦታል::

አንድ ያልታወቀ ገጣሚ መቃብሩን በተመለከተ፣ «አሁን መላእክት ከሰማይ ዜና የሚያመላልሱበት ክፍል ሆኗል» ብሏል:: ኢየሱስ ከሞት መዳፍ በሕይወት በወጣ ጊዜ ዓለም ከእንቅልፏ እንድትነቃ ያደረጋትን የክብር ከፍታና ጥልቀት ርዝመትና ስፋት የሰዎችም ሆኑ የመላእክት ቃላት በአግባቡ ሊገልጹት አይችሉም:: ቻርለስ ዌስሊ በመዝሙሩ እንዲህ ብሏል፣

*የማይሞተው የመሞቱ ጉዳይ በሙሉ ምሥጢር ነው*
*የማይታወቅ ዕቅዱን ማን ሊያስተውለው ይችላል?*
*መጀመሪያ የተፈጠረው መልአክ*
*የመለኮታዊ ፍቅርን ጥልቀት ለመግለጽ በከንቱ ይደክማል*
*ምሕረት እኮ ነው! ምድር ክብርን ትስጥ!*
*የመላእክት አእምሮ ጥያቄን አይጠይቅ ይደክማል::*

ከኢየሱስ በተቃራኒው እኛ ሁላችንንም ሞት ይጠብቀናል:: ሆኖም መልአኩ በክርስቶስ ትንሣኤ ወቅት እንደ ተሳተፈ ሁሉ እንዲሁ እኛንም መላእክት በሞታችን ጊዜ ይረዱናል:: የእኛን ገሃድ ዓለም ከመንፈሳዊ ዓለም የሚለየው አንድ ስስ መጋረጃ ብቻ ነው:: ያንን ስስ መጋረጃ ሞት ብለን እንጠራዋለን:: ሆኖም ክርስቶስ

ሞትን ድል አድርጎ የወደቁ የክፉት መላእክትን የጨለማ ማስፈራሪያ አሸንፏል። ስለዚህ እግዚአብሔር ከዚያ የጨለማ ልምምድ ለአማኞች ሕይወትን ይሰጥ ዘንድ በመላእክት እገዛ ማረጋገጫ ሞትን ይከብባል። እኛ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንወርሳለን።

## ክርስቲያኖች በሞት ጊዜ

ሞት አሁን እስረኛው አድርጎ ከያዘን ክፉ ዓለም ጋር ያስተሳሰረንን ገመድ በመበጠስ መላእክት ወደ ሰማያዊ ርስታችን እንዲያጓጉዙን ያደርጋል። ሞት የእሳት ሰረገላ፣ የንጉሥ ለሆሳስ ድምፅ፣ ብሎም መጨረሻ ወደ ሌለውና የክብር ዓለም ወደሆነው የግብዣ አዳራሽ የሚያደርሰን ነው።

መላእክት አልዓዛርን አብርሃም ወደሚገኝበት ወደ ሰማይ እንደ ወሰዱት ቀደም ብዬ ጠቅሼያለሁ። ስለ ሞት በማስብበት ወቅት ይህ ታሪክ ሁልጊዜ ያጽናናኛል። እግዚአብሔር ወዳለበት ስፍራ መላእክት ይወስዱኛል። እነዚህ ብዙ ጊዜ ሲያገለግሉኝ የነበሩት አገልጋይ መናፍስት በምድር ላይ በሚኖረኝ የመጨረሻ ጦርነት ወቅትም ከእኔ ጋር ይሆናሉ። ሞትና ከባድ ቀውስ የሚከሰትበት ጦርነት ክስተት ነው። ጳውሎስ «የኋለኛው ጠላት» ብሎ ይጠራዋል (1ኛ ቆሮ. 15:26)። የሞት መውጊያ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሠራው ሥራና በትንሣኤው የተወገደ ቢሆንም፣ ይህንን ሸለቆ ማቋረጡ ግን አሁንም ፍርሃትና ምሥጢራዊነትን ይጭራል። ሆኖም ያድኑን ዘንድ መላእክት በዚያ ይሆናሉ። በሞት ጥላ መካከል ስንሄድ «በትርና ምርኩዝ» (መዝ. (23):4) በመሆን የሚያጽናኑን እነዚህ ቅዱሳን መላእክት ይሆኑ?

ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን የፈጠርን ሰዎች እንደ ወንጌላዊ ዲ. ኤል. ሙዲ ልንሆን ይገባናል። ሞት በደጁ እንደሆነ ባወቀ ጊዜ፣ «ሰማይ በፊቴ ተከፍቶ ምድር ወደ ኋላ ቀረች» ብሏል። ሕልምን የሚያልም ይመስል ነበር። በኋላ ግን «አይ፣ ይኼ ሕልም አይደለም። . . . ውብ ነው። እንደ ሰመመን ነው። ይኼ ሞት ከሆነ ጣፋጭ ነገር ነው። እዚህ ሸለቆ የለም፤ እግዚአብሔር እየጠራኝ ስለሆነ መሄድ አለብኝ» አለ።

ለሞት ከተሰጠ በኋላም ሙዲ እግዚአብሔር የሚታየውን

ከማይታየው ከሚለየው ስስ መጋረጃ ባሻገር ያለውን እንዲያይ የፈቀደለት መሆኑን ለመጠቆም ተነሣሣ:: «ትላልቅ በሮችን አልፎ ቤት ውስጥ» ነበረ:: እናም «ለብዙ ጊዜ የሚወዳቸውንና ለጥቂት ጊዜ ያጣቸውን» የሚያውቃቸውን ሰዎች ፊት ተመለከተ:: ከዚያም ቀደም ሲል በነበረው አገልግሎቱ ድምፁን ከፍ አድርጎ ያወጀውን ስብከት አስታወሰ:: «አንድ ቀን ዲ. ኤል. ሙዲ የተባለ የምሥራቅ ኖርዝፊልድ ሰው በሞት ተለይቷል የሚል ጽሑፍ ከጋዜጣ ላይ ልታነቡ ትችላላችሁ:: ይህንን እንዳታምኑ በዚያን ሰዓት አሁን ከሆንኩት ይልቅ የበለጠ ሕያው እሆናለሁ:: ከዚህ አሮጌ ከሆነው የሸክላ ቤት ወጥቼ ወደ ዘላለም ቤቴ እገባለሁ:: የበለጠ ከፍ እላለሁ:: ይኸው ነው:: ሞት ሊነካው የማይችል ሰውነት፤ ኃጢአት ሊበክለው የማይችል የከበረ ሰውነቱን የሚመስል ሰውነት፣ . . . ከሥጋ የተወለደው ይሞታል:: ከመንፈስ የተወለደው ለዘለዓለም ይኖራል::» («The Life of Dwight L. Moody» የድዋይት ኤል. ሙዲ. ሕይወት በደብሊዩ. አር. ሙዲ):: ሙዲ አሁን ቢመሰክርልን ኖሮ የሚያስተናግዱ መላእክት ወደ ጌታ ፊት ይዘውት የቀረቡትን ደስ የሚያሰኝ ገጠመኝ በነገረን ነበር::

"O Little Town of Bethlehem" የተሰኘውን መጽሐፍ የጻፈው ፊሊፕ ብሩክስ በአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ከነበሩት ታላላቅ የመድረክ ተናጋሪዎች በጣም ከተወደዱ ሰባኪዎች አንዱ ነበር:: በቦስተን ትኖር የነበረች አንዲት የአምስት ዓመት ልጃገረድ ከተናገረችው ቃል የበለጠ መታሰቢያ ሊደረግለት አይችልም ነበር:: ተወዳጁ ሚስተር ብሩክስ ዐረፈ ብላ እናቷ ስትነግራት፣ «እማዬ መላእክት ምን ያህል ይደሰቱ ይሆን?» ብላ በመደነቅ መለሰች::

ሰው የተፈጠረው ለመኖር እንጂ ለመሞት ስላልነበረ ሞት ተፈጥሯዊ አይደለም:: ሞት ከሰው ኃጢአትና ዓመፅ የተነሣ የመጣ የእግዚአብሔር ፍርድ ነው:: በክርስቶስ ውስጥ ከሆነው ከእግዚአብሔር ጸጋ ውጪ የሚያስቀቅ ትዕይንት ነው የሚሆነው:: ክርስቶስን ሳያውቁ በመሞት ላይ በነበሩ ሰዎች አልጋ አጠገብ ቆሜ አውቃለሁ:: ሁኔታው አስከፊ ነበረ:: ክርስቶስን አውቀው በመሞት ላይ በነበሩ ሰዎች አልጋ አጠገብም ቆሜ አውቃለሁ:: ይኼ በክብር የተሞላ ገጠመኝ ነበር:: ቻርለስ ስፐርጅን ተዋጅተው በሞት የተለዩ ሰዎች ስለሚጠብቃቸው ክብር ሲናገሩ፣ «አንዳንዶች ሲሞቱ

እንደተመለከትኩት እኔም የምሞት ከሆነ ታላቁን ግብዣ መቀላቀሌ ነው:: እነርሱ እንደ ዘመሩት የምዘምር ከሆነ ሞትን በአቋራጭ ለማምለጥ አልመኝም:: እንዳየኋቸው ዓይነት ሆሣዕናዎችና ሃሌሉያዎች ከዓይኖቼ ውስጥ የሚበሩ ከሆነ መሞት የተባረከ ነገር ነው ማለት ነው::»

ለእውነተኛ አማኝ ሞት ምንም አያስፈራውም:: ሆኖም ያንን የመጨረሻ ጉዟችንን ስናደርግ የእግዚአብሔር ጥበቃ ከእኛ ጋር ሊሆን ይገባል:: በምንሞትበት ጊዜ መንፈሳችን ከሥጋችን ተለይቶ በሕዋው ውስጥ ይጓዛል:: በዚያን ጊዜ ዲያብሎስ የሚያደባ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል:: እርሱ «በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ» (ኤፌሶን 2:2) ነው:: የመረዳት ዓይኖቻችን ቢከፈቱ ምናልባት አየሩ የክርስቶስ ጠላቶች በሆኑ አጋንንት ተሞልቶ እንመለከት ነበር:: ሰይጣን በዳንኤል 10 ላይ የተጠቀሰውን መልአክ የምድር ተልዕኮውን እንዳይወጣ ለሦስት ሳምንታት ከተገዳደረው፣ ክርስቲያን በሞቱ ጊዜ ሊገጥመው የሚችለውን ተቃውሞ መገመት እንችላለን::

ሆኖም ክርስቶስ በቀራንዮ ላይ በሰይጣን መንግሥት ውስጥ መንገዱን ጠርጓል:: ክርስቶስ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ በሰይጣን ግዛት ውስጥ በማለፍ ስፍራውን መቆጣጠር ነበረበት:: ሲመጣ በመላእክት ሠራዊት የታጀበበት አንዱ ምክንያት ለዚህ ነው (ሉቃስ 2:8-14):: ዳግም በሚመጣበት ጊዜም መላእክት ሊያጅቡት የሚገባው ለዚህ ነው (ማቴዎስ 16:27):: እስከዚያ ድረስ ሰይጣን እውነተኛውን አማኝ የሚዋጋበት የመጨረሻ ዕድል ያለው በሞቱ ጊዜ ነው:: ይሁንና፣ እግዚአብሔር በዚያን ወቅት ይጠብቁን ዘንድ መላእክቱን ይልካል::

ኢየሱስ በሉቃስ 16 ላይ ታሪኩን ሲናገር ለማኙን ሰው «መላእክት ወሰዱት» ብሏል:: ማጀብ ብቻ ሳይሆን ተሸክመውታል:: ይህ ለአልዓዛር ምን ዓይነት የሚያስገርም ገጠመኝ ይሆን? እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ በአንድ ባለጠጋ ደጅ ተኝቶ ይለምን የነበረ ሰው በድንገት ራሱን በእግዚአብሔር ኃያላን መላእክት እጅ ውስጥ አገኘው!

በአንድ ወቅት ንግሥት ኤልሳቤጥ ከውጭ አገር ጉዞ ሲመለሱ የነበረውን ትዕይንት ለመመልከት ለንደን ውስጥ ቆሜ ነበር::

በዚህም ጊዜ የባለሥልጣናትን ሰልፈኞች፣ የሙዚቃ ሰልፈኞችን፣ ሰልፈኛ ወታደሮችን፣ የሚውለበለቡ ባንዲራዎችን ተመለከትሁ:: ንግሥቲቷ ወደ አገራቸው መመለሳቸውን ምክንያት በማድረግ እንዲያጅቧቸው የተደረጉትን ውብ ነገሮች ሁሉ ተመለከትሁ:: ሆኖም ከዚህ የሥቃይ ሕይወት ሁሉ ተሰናብቶ፣ መላእክት ከብበውት በክብር ለመቀበል ወደሚጠብቁት ወደ ሰማይ ቤቱ ከሚወስዱት እውነተኛ አማኝ ጋር ሲወዳደር ይህ ምንም ማለት አይደለም::

ክርስቲያን ሞትን እንደ አሳዛኝ ክስተት ሊቆጥር አይገባውም:: ነገር ግን መላእክት እንደሚመለከቱት መመልከት አለበት:: እነርሱ ከዚህ ምድር እስከ ዘለዓለም የሚደረገው ጉዞ በደስታ የሚዘልቅ መሆኑን ይገነዘባሉ:: የሕይወት መንገድ በሞት ሸለቆ ውስጥ ነው፤ መንገዱ ሁሉ ግን በድል የሚዘለቅ ነው:: መላእክት ኢየሱስ ሞትን ድል በመንሣት ሥልጣኑ የፈነጠዙ ሲሆን፣ ይህ ደግሞ ትንሣኤያችንን በማረጋገጥ በሰማይ የሰላም መንገድ እንደ ተከፈተልን ዋስትና ይሰጠናል::

በሞት ወቅት መላእክት ወደ ሰማይ አጅበው እንደሚወስዱን በመቶዎች የሚቆጠሩ ታሪኮች ያስረዳሉ:: ለምሳሌ፣ ሴት አያቴ በሞቱ ጊዜ ክፍሉ በሰማያዊ ብርሃን የሞላ መሰለ:: ሳቅ እየከጀላቸው ከአልጋቸው ላይ ተነሥተው፣ «ኢየሱስን እጁን ወደ እኔ ዘርግቶ አየዋለሁ:: ቤንንና (ከጥቂት ዓመታት በፊት የሞተ ባለቤታቸውን) መላእክትን እመለከታለሁ» አሉና ወደ ኋላቸው ተደፉ፣ በሰውነታቸው ውስጥ የሌሉ ቢሆኑም ከጌታ ጋር ግን ነበሩ::

በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በምማርበት ወቅት አንድ መንፈሳዊት የሆነች ወጣት ሚሲዮናዊት በድንገት ታመመች:: ሐኪሙም በሕይወት ለመኖር ያላት ጊዜ ጥቂት ሰዓታት ብቻ እንደሆነ ተናገረ:: ወጣት ባለቤቷና አንድ ወይም ሁለት የትምህርት ቤቱ ባልደረባዎች እንደ ቆሙ በድንገት፣ «ኢየሱስን አየሁት:: የመላእክትን ዝማሬ እሰማለሁ» በላ በመደነቅ ጮኸች::

በቻይና ሚሲዮናዊ የነበረው ቄስ ኤ. ኤ. ታልቦት በአንድ ወቅት በአንድ በመሞት ላይ በነበረ ቻይናዊ ክርስቲያን አልጋ አጠገብ ነበረ:: በድንገት ክፍሉ በሰማያዊ ሙዚቃ ተሞላ:: ቻይናዊው

ክርስቲያንም በደማቅ ፈገግታ ሆኖ ወደ ላይ ተመልክቶ፣ «ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ ማርጋሬት ጌይንም ከእርሱ ጋር ሆና አያታለሁ» አለ ። ማርጋሬት ጌይ የሚሲዮናዊው የታልቦት ትንሽ ሴት ልጅ ስትሆን ከጥቂት ወራት በፊት በሞት የተለየች ናት።

ሱዛና ዌስሊ፣ «በምሞትበት ወቅት የምስጋና መዝሙር ዘምሩ» ብላ ነበር። በአሁኑ ወቅት በመሞት ላይ ለሚገኙ በሽተኞች ብዙ መድኃኒት ስለሚሰጣቸው እንደዚህ ዓይነት ታሪኮችን አንሰማም። ሆኖም በክርስቶስ ሆኖ ሞትን መጋፈጡ ክብር የተሞላበት ገጠመኝ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እያንዳንዱ አማኝ ክርስቶስ ወደሚገኝበት ሲጓዝ በቅዱሳን መላእክት እንደሚታጀብ ያረጋግጣል።

ብዙ ጊዜ የጌታ መላእክት የመንግሥቱ መልእክተኞች የሚላኩበት ምክንያት በሞታቸው ጊዜ በጌታ የተዋጁትን ለመውሰድ ብቻ ሳይሆን፣ ወዳጆቻቸውን ላጡትና እዚህ ለሚቀሩት ተስፋና ደስታን በመስጠት ለማጽናናትም ጭምር ነው። «በልቅሶ ፋንታ የደስታን ዘይት፤ በኀዘንም መንፈስ ፋንታ የምስጋናን መጐናጸፊያ» እንደሚሰጠን ቃል ገብቶልናል።

ዛሬ ሰዎች እየጨመረ በሚሄደው ተስፋ አስቆራጭ ስሜት እየተወሰዱ ናቸው። ዶማን ሉም "Responding to Suicidal Crisis" በተሰኘው መጽሐፋቸው ሚና ፊልድን በመጥቀስ ብቃት የሌለው ምክርና ሕክምና ስለሚሰጡና፣ «ራሳቸው ሊያልፉበት የማይችሉትን ሥቃይ የማይረባ ነገር ነው የምታወራው በማለት የበሽተኛውን ጀርባ መታ መታ እያደረጉ ለማምለጥ ስለሚጥሩ ሰዎች» ጽፈዋል። ዛሬ በታዋቂ የሕክምና ማዕከሎች ውስጥ የሥነ አእምሮ ባለሙያ ቡድኖች፣ የሥነ ልቦና ባለሙያዎችና ሐኪሞች ሞትን በሚመለከት ሰሚናሮች ላይ እንዲገኙ ይበረታታሉ። ሮበርት ጄ. ሊፍተን ከሄሮሺማ የአቶሚክ ጥፋት የተረፉትን ሰዎች የሚያስገርም አመለካከቶች በማካተት የሕይወትን መቋረጥ በተመለከተ ጽፈው ነበር። «ከሞት ጋር የሚቆይ የሚመስል፣ ጫና የበዛበትና የማያቋርጥ ግጥሚያ ተካሂዶ ነበር። በውጤቱም በሰዎች አቋም ላይ የእምነትና የመተማመን ነገር ወደቀ። ሰዎች ሞትን በተመለከተ ስለማንኛውም ስሜቶች ራሳቸውን ያደነዘዙበት የሥነ አእምሮ ዝገት ነበረ። እናም ለተፈጠረው አሳዛኝ ነገር በኃላፊነት የሚጠይቁ ይመስል በጸጸትና ራሳቸውን በመኮነን ተሞሉ. . . ሞት

ድንገት ይወስደናል በሚል ፍርሃት ተውጠናል፡፡ . . . ሕይወትን ሊጨብጥ የማይችል ባሕርይ ተገንዝበናል» ብለው ነበር፡፡

አንዳንድ ሰዎች ሞትን «ዮርዳኖስን መሻገር» ብለው ሲጠሩት እንሰማለን፡፡ ይህ መንፈሳውያን በሆኑና በጥቂት የክርስቲያን እምነት መዝሙሮች ውስጥ ይገኛል፡፡ አገላለጹ የመጣው እስራኤላውያን የተስፋውን ምድር ለመውረስ ዮርዳኖስን ካቋረጡት የድል ጉዞ ነው፡፡ ዮርዳኖስ ደረቅ መሬት ሆኖላቸው አለፉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም ወደ ሰማያዊው የተስፋ ምድር የዮርዳኖስን የሞት ወንዝ ተሻግረን በሰላም እስክንገባ ድረስ አገልጋይ መላእክት የሚመለከቱን ይሆናል፡፡ ስለሆነም ክርስቲያን ተስፋ እንደሌላቸው ሰዎች ኀዘን አይገባውም (1ኛ ተሰሎንቄ 4:13)፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ መሞቱ እየቀረበ መሆኑን ሲናገር፣ «ይልቁንም ከሥጋ ተለይተን በስደት መኖር በጌታም ዘንድ ማደር ደስ ይለናል» ብሏል (2ኛ ቆሮንቶስ 5:8)፡፡ በክብር የተሞላው አካላዊና መንፈሳዊው መለየት በሚከናወንበት ወቅት፣ መላእክት በፍጹም ደስታ እንደ ተሞላን ወደ አዳኛችን ይሸኙናል፡፡ ይኼ ደግሞ «ዘለዓለማዊ ሕይወት» ነው፡፡

## ሊመጣ ያለው አስገራሚ አቀባበል

ሞት ውብ ሊሆን እንደሚችል አምናለሁ፡፡ በደስታና በጉጉት በመጠባበቅ ላይ እገኛለሁ፡፡ ፊታቸው ድልን እንዳንጸባረቀ ሕይወታቸውን በሰጡት ብዙ ሰዎች አጠገብ ቆሜ አውቃለሁ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በመዝሙረ ዳዊት (116):6 ላይ፣ «የቅዱሳኑ ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው» ማለቱ አስገራሚ አይደለም፡፡ «በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ፤ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፡፡» [መዝ. (23):4]፡፡

ሞትን ስታስቡት በሥጋት ልትዋጡ ትችሉ ይሆናል፡፡ ልታስታውሱት የሚገባው ነገር ቢኖር በአንድ ወቅት ለተወሰነ ደቂቃ እንደምትሠቃዩና በሚቀጥለው ደቂቃ ወደ አዳኛችን የክብር አምሳል በቅፅበት እንደምትለወጡ ነው፡፡ የሰማይ ታላቅነቱ፣ አስደናቂነቱ፣ ውበቱ፣ የአንተ ይሆናል፡፡ ከድካምህ ታርፍ ዘንድ እግዚአብሔር የሚልካቸው መላእክት ወደ ቤትህ ያመጡሃል፡፡

የሥራህም ክብር ይከተልሃል። (የዮሐንስ ራእይ 14:13)።

ሐዋርያው ጳውሎስ፣ «ስለዚህ፣ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፣ ድካማችሁ በጌታ ከንቱ እንዳይሆን አውቃችኋልና የምትደላደሉ፣ የማትነቃነቁም፣ የጌታም ሥራ ሁልጊዜ የሚበዛላችሁ ሁኑ» ማለቱ አስገራሚ አይሆንም (1ኛ ቆሮንቶስ 15:58)።

ሕይወትን ለመጋፈጥ ተዘጋጅተሃል? ሞትን ለመጋፈጥ ተዘጋጅተሃል? ማንም ለእግዚአብሔር ክብር መኖር ያልተማረ ሰው ለመሞት እርግጠኛ ሆኖ የተዘጋጀ ሊሆን አይችልም። ኢየሱስ ለአንተ የሞተልህ ስለሆነ እምነትህን በእርሱ ላይ መጣል ትችላለህ። ከቀውሶች ሁሉ ታላቅ በሆነው በዚያ የመጨረሻ ደቂቃ መላእክቱ በክብርና በሚያስገርም ሁኔታ በእጆቻቸው አቅፈውህ ወደ ሰማይ እንዲያደርሱህ ያደርጋል።

# አሥራ አራት

## የመላእክት ተመልካቾች

ወላጆቻችሁ፣ ባለቤቶቻችሁ፣ ወይም ልጆቻችሁ ብቻ ሳይሆኑ ሰማያዊ ሠራዊትም ዘወትር እንደሚመለከቷችሁ ብታውቁ በምን ዓይነት ሁኔታ ትኖሩ ነበር? መጽሐፍ ቅዱስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 4:9 ላይ መላእክት እንደሚመለከቱን ያስተምራል።

ጳውሎስ እኛ ለእነርሱ «ትዕይንት» [በአማርኛው «መጫወቻ» ተብሎ የተተረጐመው ለተመልካች የሚዘጋጅን ትዕይንት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ይመስላል።] እንደሆንን ይናገራል። ኤ. ኤስ. ጆፒ የመጀመሪያ ክፍለ ዘመን ተመልካቾች ለስፖርት ተብሎ ሰፊና ክብ በሆነ ሜዳ ላይ እንስሳት ሲገደሉና ሰዎች ከእንስሳት ጋር የሞት ሽረት ትግል ሲያካሄዱ ለማየት ይሄዱ ነበር፣ በኋላ ላይ ደግሞ ክርስቲያኖች በአንበሳ ሲበጣጠሱ ቆመው ይመለከቱ ነበር ብሏል። ጳውሎስ «መጫወቻ» የሚለውን ቃል በሚጠቀምበት ወቅት ይህችን ዓለም እንደ አንድ ሰፊ የመዝናኛ ስፍራ መሣሉ ነበር። ክርስቶስን ለመታዘዝ የሚሹ ክርስቲያኖች ሁሉ እነርሱን ለማዋረድ ከተሰጡ የክፉ ኃይላት ጋር ከፍተኛ ግጭት ውስጥ ስለሚገቡ በዚህ ታላቅ ድራማ ውስጥ ይሳተፋሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን «ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም» ይላል (የዮሐንስ ራእይ 12:11)።

በዚህ በትግሉ ስፍራ ብቻ ባልተወሰነው ግጭት ውስጥ ብዙ ጊዜ በደስታ ወደ ሞታቸው የሚጓዙትን ፈጥነው ለማዳንና ነፃ ለማውጣት መላእክት በጕጕት ይጠባበቃሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር መላእክት ነፃ የሚያወጡ ሠራዊቶች በመሆን ፈጥነው እንዳይሄዱ ይከለክላቸዋል። ኢየሱስም ከእግዚአብሔር አብ ጋር የለያየውን የመስቀል ላይ ሞት በቀመሰ ጊዜ እንዲያድኑት አልፈቀደላቸውም። የመላእክት ተመልካቾች በተረጋጋ መንፈስ ሆነው ጣልቃ ለመግባት ቢዘጋጁም፣ ጥቃት እንዲሰነዝሩ ትእዛዝ

አልተሰጣቸውም:: ለምን? ምክንያቱም በእግዚአብሔር ሰዓት በጨካኝ የክፉ ኃይላት ላይ የሚከናወነው የመጨረሻ ድል ገና ስላልመጣ ነው::

ቀደም ብዬ እንደ ጠቀስኩት ዛሬ ብዙ ግራ የሚያጋቡ ጥያቄዎች ያጋጥሙናል:: ለምሳሌ ያህል፣ እግዚአብሔር ክፋትን ለምን ይፈቅዳል? እግዚአብሔር ጣልቃ በመግባት ኃጢአትን ለምን አይቀጣም? እግዚአብሔር ለምን በሽታን ይፈቅዳል? እግዚአብሔር ለምን ጥፋትን ይፈቅዳል? ቢሆንም የእግዚአብሔር ጊዜ ትክክል ነው:: በዓለማችን ውስጥ የሚከናወነውን ነገር ሁሉ የሚመለከቱት የመላእክት ሠራዊት፣ ከእግዚአብሔር ምልክትን ካልተቀበሉ ጻድቃንን ለማጽናናት፣ የተጎዱትን ነፃ ለማውጣት ነጻነት የላቸውም:: አንድ ቀን ግን ያደርገዋል:: ቅዱሳን መላእክት የእግዚአብሔርን ምርጦች ወደ መንግሥቱ እስከሚሰበስቡበት እስከ መከሩ ጊዜ ድረስ ስንዴው ከእንክርዳዱ ጋር፣ ጻድቁ ከኃጢአተኛው ጋር አብረው እንደሚያድጉ ክርስቶስ አስተምሮናል ::

## የመላእክት ትኩረት

የእግዚአብሔር መላእክት የዚህን የዘመን መጨረሻ ድራማ በጥሞና እየተከታተሉት ሲሆን፣ ቤተ ክርስቲያንም በዓለም ዙሪያ ስትመሠረትና ስትስፋፋ ይመለከታሉ:: የዘመንን እንቅስቃሴዎች በጥሞና በሚከታተሉበት ጊዜ የሚያመልጣቸው ነገር የለም:: «ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ አሁን በቤተ ክርስቲያን በኩል በሰማያዊ ስፍራ ውስጥ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት ትታወቅ ዘንድ» (ኤፌሶን 3:10):: ዶ/ር ጆፒ «አሁን» የሚለው ቃል ይህን ሰፊ የቤተ ክርስቲያን ዘመን የሚሸፍን መሆኑን ያሳስበናል:: የመላእክት ሠራዊት የኢየሱስ ክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን መመሥረት የተመለከቱ ሲሆን፣ እግዚአብሔር በእያንዳንዱ ሕይወት ውስጥ ጸጋውን፣ ፍቅሩንና ኃይሉን በመግለጡ ሳቢያ የሚካሄደውን የእያንዳንዱን አማኝ አኗኗር ታዝበዋል:: በዚህ ሰዓት መላእክት የመጀመሪያውን ትኩረት የሚሰጡት በሁሉም ግዛቶች ለሚገነባው የእውነተኛዪቱ ቤተ ክርስቲያን አካል ነው::

ነገር ግን በዚህ ዓለም የትግል ሜዳ ላይ በመኖራችን ምን ያስቡ

ይሆን? በእምነታችን ጸንተን ስንቆምና በጽድቅ ስንመላለስ ያዩን ይሆን? ወይስ በእኛ ጽናት ማጣት ይገረሙ ይሆን? እነዚህ ሁለት አማራጮች በኤፌሶን 3:10 በተጻፈው መሠረት የተረጋገጡ ይመስላል:: ዓላማው «ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ አሁን በቤተ ክርስቲያን በኩል በሰማያዊ ስፍራ ውስጥ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት ትታወቅ ዘንድ» ነው::

አሁን መላእክት አኗኗራችንን እንደሚከታተሉና እንደሚመሰክሩ በእርግጠኛነት ማወቃችን ውሳኔዎች ላይ ከፍተኛ ለውጥ ሊያመጣ ይገባል:: እግዚአብሔር ሁሉንም የሚመለከት ሲሆን፣ መላእክት ደግሞ በጕጕት እየተመለከቱ ናቸው:: «አምፕሊፋይድ ባይብል» የተባለው የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ እትም 1ኛ ቆሮንቶስ 4:9ን ሲያብራራው፣ «እግዚአብሔር ለሰዎችና ለመላእክት የምንታይ የቴአትር መድረክ ትዕይንቶች አድርጐናል» ይላል:: የሚመለከቱ መሆኑ እርግጥ ሲሆን፣ በተጧጧፈው ጦርነት መካከል የማበረታቻ ቃላት ሲናገሩ ብንሰማቸው ምን ያህል አስገራሚ ይሆን ነበር ብዬ አስባለሁ::

## ለጽድቅ የሚሰጡ የማበረታቻ ሽልማቶች

የሰማይና የመላእክት ሠራዊቶች ዋና ትኩረት በክርስቲያኖች እርምጃና ውጊያ ላይ እንደሆነ ስንገነዘብ፣ በዚህ ዓለም በጽድቅ ለመኖር ስለምንከፍለው ዋጋ በጥልቀት እናስባለን:: ጳውሎስ፣ «አንድ እንኳ በአድልዎ ሳታደርግ እነዚህን (ሕጎች) ያለ መዘንበል እንድትጠብቅ በእግዚአብሔርና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በተመረጡትም መላእክት ፊት እመክርሃለሁ» (1ኛ ጢሞቴዎስ 5:21) ብሏል:: ጳውሎስ የተመረጡ መላእክት አማኙን እንዴት እንደሚያገለግልና የክርስትና ሕይወቱን እንዴት እንደሚኖር ሳያቋርጡ እንደሚመለከቱ እንዲያስታውስ ነበረ ጢሞቴዎስን ያነቃቃው:: የጽድቅን ሕይወት ለመኖር ከዚህ እውነት የበለጠ ምን ማበረታቻ ሊቀርብ ይችላል? ለራሴ እንኳ፣ «ተጠንቀቅ መላእክት እየተመለከቱ ናቸው» ማለት ይኖርብኛል::

ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ባለጠግነት ቤተ ክርስቲያን በሁሉም ስፍራ ለጠፉት ሰዎች ስታገለግል መላእክት ታላቅ እርካታ

ይሰማቸዋል። ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ መላእክት ሐሴትን የሚያደርጉ ከሆነ (ሉቃስ 5:10)፣ ይኼ ማለት በሰማያት ሰገነቶች ላይ ሆነው ከሚመለከቱት መካከል የመላእክት ሠራዊት ይገኙበታል ማለት ነው። በዕብራውያን 12:1 ላይ፣ «እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን» ተብለው ከተጠቀሱት ውስጥ እነርሱም ይካተታሉ ማለት ነው። መላእክት እያንዳንዷን ምድራዊ የክርስትና ጉዟችንን ሳያዩት አያልፉም። በጳውሎስ ዘመን የግሪክ ሰዎች እንደ ጮኹት እነርሱ እንዲህ አያደርጉም። ነገር ግን ወንጌሉን አውጀን ወዳጆቻችን በሚድኑበት ወቅት ከእኛ ጋር ሐሴትን ያደርጋሉ።

ዶክተር ቫንስ ሃቭነር "Though I Walk Through the Valley" በተሰኘው መጽሐፋቸው ላይ አነስተኛና ጥቂት አማኞች ለሚገኙ ባት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ሌሊቱ እስኪገፋ ድረስ ስብከታቸውን ያዘጋጁ ስለነበረ አንድ በዕድሜ ስለገፉ ሰባኪ ይናገራሉ። የሰባኪው ባለቤት ጥቂት ሰዎች ብቻ የሚሰሙትን ስብከት ለማቅረብ ይኼን ያህል ለምን እንደሚያመሹ ጠየቀቻቸው። አገልጋዩም ሲመልሱ፣ «የእኔ አዳማጮች ምን ያህል ታላቅ እንደሆኑ ረስተሽዋል፣ የእኔ ፍቅር» ሲሉ ይመልሳሉ። ዶ/ር ሃቭነር ጽሑፋቸውን በመቀጠል ፣ «ሰማይ በዚህ ስፍራ ቢመለከት ምንም የሚናቅ ነገር የለም። የተከበብን መሆናችንንና ማን እንደሚመለከተን ብናስታውስ የበለጠ ሥራን እንሠራለን» ብለዋል።

ሸለቆዎቻችን በጠላቶቻችንና በዕንባ ተሞልተው ይሆናል። ሆኖም ዓይኖቻችንን ወደ ተራራዎቹ አንሥተን እንደ እግዚአብሔር የማይወሰን ጥበብ ወደ ቤታችን በሰላም እንድንገባ እየተጠባበቁን ወዳሉት መላእክትና ወደ እግዚአብሔር ልንመለከት እንችላለን።

# አሥራ አምስት
# መላእክት በዛሬው ኑሮአችን ውስጥ

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የብሪታንያ አየር ኃይል አገሩን ከወረራና ከሽንፈት ታድጓል። አዴላ ሮጀርስ ሴይንት ጆን "Tell No Man" በተሰኘ መጽሐፏ ስለዚያ ለሳምንታት የዘለቀ የአየር ላይ ውጊያ አንዳንድ አስገራሚ ነገሮችን ትገልጻለች። መረጃውን ያገኘችው የአየር ኃይል ዋና አዛዥ ለነበሩት ለተከበሩ ማርሻል ሁግ ዳውዲንግ ክብር ጦርነቱ ካበቃ ከጥቂት ወራት በኋላ ከተዘጋጀ በዓል ላይ ነበር። ንጉሡ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩና ሌሎችም የተከበሩ ሰዎች እዚያው ነበሩ። የአየር ኃይሉ ዋና አዛዥ በንግግራቸው ላይ ጥቂት ተዋጊዎቻቸው እንቅልፍ አጥተው አውሮፕላኖቻቸውን እያበረሩ ስለተዋጉበት ሁኔታ ተረት የሚመስል እውነተኛ ታሪክን በዝርዝር ይናገሩ ነበር። በንግግራቸው ላይም በተልዕኮ ላይ የነበሩ የአየር ኃይል አባላት ተመትተው መጐዳታቸውን ወይም መሞታቸውን ገለጹ። ይሁንና፣ አውሮፕላናቸው በአግባቡ እየበረረ መዋጋቱን እንደ ቀጠለ አስረዱ። አንዳንድ ጊዜ በሌላ አውሮፕላን ላይ የነበሩ ፓይለቶች የአውሮፕላኑን መቆጣጠሪያ የሚቆጣጠር ምስል ይመለከቱ ነበር። ለዚህ ማብራሪያው ምንድን ነው? የአየር ኃይሉ ዋና አዛዥም አብራሪዎቹ የሞቱባቸውን አንዳንድ አውሮፕላኖች መላእክት አብርረዋቸዋል ብለው እንደሚያምኑ ተናገሩ።

በሞቱት አብራሪዎች ምትክ በብሪታኒያ በነበረው ጦርነት መላእክት አውሮፕላኖችን ማብረራቸውን በእርግጠኛነት ልናውቅ አንችልም። ይሁንና፣ ባንችልም መላእክት በትክክል ያደረጓቸውን፣ ሊያደርጉ የሚችሏቸውንና ታሪክ ወደ ፍጻሜው እየቀረበ ሲሄድ የሚያደርጓቸውን አንዳንድ ነገሮች ቀደም ሲል ከእግዚአብሔር ቃል ተመልክተናል። ለእያንዳንዳችን የሚጠቅመን ጥያቄ መላእክት አሁን ባለንበት ሁኔታ እንዴት ሊያግዙን እንደሚችሉ ነው። በክፉ ኃይላት

ላይ ድልን እንድንቀዳጅ እንዴት ይረዱናል? ከእነርሱ ጋር የሚኖረን ቀጣይ ግንኙነት ምንድን ነው?

ከእነርሱ እርዳታ ውጪ በሰይጣን ላይ ድልን ለመቀዳጀት ስለማንችል ያግዙን ዘንድ እግዚአብሔር በእኛ ላይ ኃላፊነትን እንደ ሰጣቸው እናውቃለን:: ሐዋርያው ጳውሎስ፣ «መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፣ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ» ብሎ ይናገራል (ኤፌሶን 6:12):: በመላእክቱ በኩል ከእግዚአብሔር እንዴት እርዳታ እንደምናገኝ እናስብ::

## የዚህ ዘመን አምላክ

ዋናው ጠላታችን የሆነው ሉሲፈር በዚህ ዓለም ላይ ከሚገኙት ኃይለኛና በሚገባ ከተዘጋጁት የጦር መሣሪያዎች አንዱን ይቆጣጠራል:: ኃይላትን፣ ሥልጣናትንና ግዛቶችን ይቆጣጠራል:: እያንዳንዱ አገር፣ ከተማ፣ መንደርና ግለሰብ የክፋውን ኃይል የሚያቃጥል ትንፋሽ ቀምሶታል:: ከክርስቶስ ጋር ለሚያካሄደው ለመጨረሻው ታላቅ ጦርነት (አርማጌዶን) የዓለምን ሕዝቦች በመሰብሰብ ላይ ይገኛል:: ሆኖም ሰይጣን የተሸነፈ ጠላት እንደሆነ ኢየሱስ አረጋግጧል (ዮሐንስ 12:31፤ 16:11):: በ2ኛ ጢሞቴዎስ 1:10 ላይ ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል በኩል ሞትን አጥፍቶ ሕይወትንና ዘላለማዊነትን እንዳመጣ ይናገራል:: ጴጥሮስ፣ ኢየሱስ «መላእክትና ሥልጣናት ኃይላትም ከተገዙለት በኋላ ወደ ሰማይ ሄዶ በእግዚአብሔር ቀኝ አለ» ብሎ ይገልጻል (1ኛ ጴጥሮስ 3:22)::

## የሰይጣን ሽንፈት

ሰይጣን በመርሕ ደረጃ የተሸነፈ ጠላት ቢሆንም፣ እግዚአብሔር እርሱን ከዓለም መድረክ ላይ ገና እንዳላስወገደው እውነት ነው:: ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር እንዲፈርዱበትና ፈጽመው ከዓለም ላይ ይደመስሱት ዘንድ መላእክትን እንደሚጠቀምባቸው

ይናገራል፡፡ በዮሐንስ ራእይ 12 ላይ ስለ ሰይጣን የቀደመ ሽንፈት እናነባለን፡፡ «በሰማይም ሰልፍ ሆነ፤ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ፡፡ ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ አልቻላቸውምም፣ ከዚያም ወዲያ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም፡፡ ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፣ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ፤ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ» (ከቊጥር 7-9)፡፡

በዮሐንስ ራእይ በምዕራፍ 20 ላይ ዮሐንስ ሰይጣን በምድር ላይ በአሁኑ ወቅት ያለው ገዢነት እንዴት ለአጭር ጊዜ እንደሚገታ ይናገራል፡፡ «የጥልቁንም መክፈቻና ታላቁን ሰንሰለት በእጁ የያዘ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፡፡ የቀደመውንም እባብ ዘንዶውን እርሱም ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን ያዘው፤ ሺህ ዓመትም አሰረው፤ ወደ ጥልቅም ጣለው፡፡ አሕዛብንም ወደ ፊት እንዳያስት ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በእርሱ ላይ ዘግቶ ማኅተም አደረገበት. . .»፡፡ ከዚያም በመቀጠል ዮሐንስ ለጥቂት ጊዜ ከተፈታ በኋላ የመጨረሻው ታላቁ ጦርነት እንደሚካሄድና ለዘላለም ይሠቃይ ዘንድ እግዚአብሔር ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ እንደሚጥለው ይናገራል (የዮሐንስ ራእይ 20:10)፡፡

አንዳንድ ሰዎች «ስለ መጨረሻው የሰይጣን ሽንፈት መናገሩ ጥሩ ነው፡፡ ነገር ግን ያ እስከሚሆን ድረስ ዛሬ ከእርሱ ጋር ላለኝ ትግል አይጠቅመኝም» ይላሉ፡፡ ይኼ ግን ታሪኩን ሁሉ አይገልጽም፡፡ በሰይጣን ላይ ድል ልንቀዳጅ የምንችልባቸው የተወሰኑ መመሪዎች በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ተገልጸዋል፡፡

ለምሳሌ «ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት» ተብሎ ተነግሮናል (ኤፌ. 4:27)፡፡ በሌላ አነጋገር በልባችሁ ለሰይጣን ክፍት ቦታ አትተዉለት ማለት ነው፡፡ ሐዋርያው ጴጥሮስ ሲያስተምር፣ «በመጠን ኑሩ ንቁም፤ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና» ብሎ ይናገራል (1ኛ ጴጥሮስ 5:8)፡፡ ከሚጠበቀው በላይ ጠንቃቃ ለመሆን አንችልም፡፡ ነገር ግን ይኼ የእግዚአብሔርን ተዋጊ ኃይላት የመቀላቀልንም አሳብ የሚያካትት ነው፡፡ «በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት» (1ኛ ጴጥሮስ 5:9)፡፡ ያዕቆብም «ዲያብሎስን ተቃወሙት ከእናንተም ይሸሻል» ይላል (ያዕቆብ 4:7)፡፡

ነገር ግን እነዚህ እንድንነቃና ዲያብሎስን እንድንቋቋም የሚያበረታቱን ማጽናኛዎች የታሪኩን የተወሰነ ክፍል ብቻ ነው የሚነግሩን:: በጦርነቱ ውስጥ ብቻችንን አይደለንም:: በራሳችን ብርታት ብቻ ልንተማመን አይገባንም:: ሆኖም በውስጣችን በሚኖረውና በሁኔታዎች ሁሉ ወደ እርሱ ስንቀርብ ሊረዳን ፈቃደኛ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ ላይ ልንደገፍ ይገባል:: በተጨማሪም ከሰይጣንና ከአጋንንቱ ይልቅ በብዙ እጥፍ በሚበልጡት እጅግ ኃያላንና ብርታት በተሞሉ መላእክት ልንተማመን እንችላለን:: ከአንድ ምእተ ዓመት በፊት እንክሪስ ማዘር "Angelographia" በተሰኘ መጽሐፋቸው ውስጥ፣ መልካሞቹም ሆኑ ክፉዎች መላእክት ሰዎች ከሚገነዘቡት በላይ በዚህ ዓለም ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያደርጋሉ:: ሁልጊዜ ነፍሳችንና ሥጋችንን ለመጉዳት ከሚያቅዱ መሠሪ የዓመፅ ኃይላት ይታደጉን ዘንድ ቅዱሳን መላእክት ለእኛ ኃጢአተኛ ለሆንን ፍጥረቶች ስለመመደቡ የእግዚአብሔርን ጸጋ ልናደንቅ ይገባናል» ብለዋል::

ኤልሳዕ እጅግ ብዙ በሆኑ የጠላት ሠራዊት በዶታይን ስለተከበበት ሁኔታ ቀደም ሲል ተመልክተናል::

ነገር ግን እንደ እርሱ ባሪያ መንፈሳዊ ዓይኖቻችን ቢከፈቱ በክፉት ኃይላትና ሥልጣናት የተሞላን ዓለም ብቻ ሳይሆን፣ እኛን ለመጠበቅ የተመዘዙ ሰይፎች የያዙ ኃያላን መላእክትንም ጭምር እናያለን::

በዶታይን በሺዎች የሚቆጠሩ ወታደሮች ከተማዋን ከብበው በኤልሳዕ ላይ ጉዳት ለማድረስ ዐቅደው ነበር:: ያም ቢሆን እርሱ ሰላም ነበረው:: ባሪያው ግን የሚሆነውን ስላላወቀ ዓይኖቹ እንዲከፈቱለት ያስፈልግ ነበር:: የተቸገርን፣ ግራ የተጋባን፣ የምንፈራ፣ የተጨነቅን ክርስቲያኖች በዚህ ደቂቃ እግዚአብሔር ዓይኖቻችንን ሊከፍትልን ያስፈልጋል:: ቫንስ ሃቭነር እንዳሉት፣ «ዋናው ችግራችን ብርሃን ሳይሆን ዓይን ነው:: ብርሃን ለዓይነ ስውር ሰው ምንም አይጠቅመውም:: የዓይኖቻችን በእምነት ካልተነኩ በርእሰ ጉዳዩ ላይ ብዙ መጻሕፍትን ብናነብ መላእክትን አያሳዩንም::»

አጋንንትን በመቍጠር ተጠምደን ቅዱሳን መላእክትን ልንዘነጋ አይገባንም:: በእርግጥ ግዙፍ ከሆነ የጦር መሣሪያ ጋር እየታገልን

ነው:: ሆኖም ጦርነቱ የጌታ ስለሆነና ኃያላን የሆኑ ሰማያዊ ሠራዊት የከበቡን ስለሆነ ጦርነቱን ልንፈራ አይገባንም:: ዙሪያው ሙሉ በሙሉ የተከበበ መሆኑን በተነገረው ጊዜ፣ «መልካም ማንም እንዳያመልጥ ጠብቁ» ብሎ በድፍረት እንደተናገረው ያ የድሮ መሪ፣ እኛም ሰይጣንንና ጭፍሮቹን በድፍረት ለመጋፈጥ እንችላለን:: ሸለቆዎቻችሁ በጠላት የተሞሉ ከሆኑ ዓይኖቻችሁን ወደ ተራራዎች አንሡና በምትካችሁ ሊዋጉ ቀስታቸውን የገተሩትን የእግዚአብሔር ቅዱሳን መላእክት ተመልከቱ::

አብርሃም በዕድሜ የገፋ ባሪያው ለይስሐቅ ከዘመዶቹ ሚስት እንዲፈልግለት በራስ መተማመንና በአጣዳፊ የላከው፣ ከእግዚአብሔር መልአክ የተነሣ ነው:: «መልአኩን በፊትህ ይሰድዳል . . . መንገድህንም ያቀናል» (ዘፍጥ. 24:7፣ 40):: ነቢዩ ኢሳይያስ «በጭንቃቸው ሁሉ እርሱ ተጨነቀ የፊቱም መልአክ አዳናቸው» ይላል (63:9):: እግዚአብሔር በዚያ በብስጭቱ ወቅት ለሙሴ የተስፋ ቃልን ሲሰጠው «መልአኬ በፊትህ ይሄዳልና» አለው (ዘጸአት 23:23):: መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የላካቸውን መላእክት ልንመለከትና ዳሩ ግን ለይተን ላናውቃቸው እንደምንችል ይናገራል:: «እንግዶችን መቀበል አትርሱ በዚህ አንዳንዶቹ ሳያውቁ መላእክትን እንግድነት ተቀብለዋልና» (ዕብራውያን 13:2):: ሰዎች ቢያጤኗቸውም ባያጤኗቸውም መላእክት በሃያኛው ክፍለ ዘመንም በሥራ ላይ ናቸው:: እናስተውላቸዋለን?

በአንድ የቻይና ከተማ አንድ ኀዘን ያደባበት ሌሊት ነበረ:: በመቶዎች የሚቆጠሩ ሴቶችና ሕፃናት የተጠለሉበት የሚሲዮን ግቢ በሽፍቶች ተከበበ:: ቀደም ባለው ሌሊት ደግሞ እኀት ሞንሰን በወባ በሽታ ክፉኛ ታመው ተኝተው ነበር:: በዚህን ወቅት ፈታኙ በጥያቄዎች መነዝነዝ ጀመረ:: «ዘራፊዎች በሚመጡበት ጊዜ ምን ታደርጊያለሽ? ተኩስ በሚከፈትበት ወቅትስ እነዚያ የተማመንሽባቸው ተስፋዎችሽ ምን ሊሆኑ ነው?» አል ብራያንት «1,000 New Illustrations" በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ ውጤቱን ዘግበውታል:: እኀት ሞንሰንም «ጌታ ሆይ፣ የተስፋ ቃሎችህ የተረጋገጡ ናቸው ብዬ እነዚህን ልጆች ለዓመታት ሳስተምር ቆይቻለሁ:: ይኼ ቃልህ የማይፈጸም ከሆነ እንደበቴ ለዘላለም ተዘግቶ ወደ አገሬ ልሂድ» ብለው ጸለዩ::

ሌሊቱን ሁሉ በፍርሃት የተሞሉትን ጥገኞች እንዲጽናኑና ነፃ ያወጣቸው ዘንድ በእግዚአብሔር ላይ እንዲደገፉም አበረታቷቸው። በዙሪያው ሁሉ የሚያስፈሩ ነገሮች ሲካሄዱ የነበረ ቢሆንም፣ የሚሲዮኑ ግቢ ሳይነካ ሽፍቶቹ ሄዱ።

ጠዋት ከሦስት የተለያዩ ቤተሰብ የመጡ የጎረቤት ሰዎች እኅት ሞንሰንን፣ «ሌሊቱን ሁሉ በጣሪያሽ ላይ ሦስቱ ተቀምጠው አንዱ ደግሞ ቆሞ የነበሩት እነዚያ አራት ሰዎች እነማን ናቸው?» ብለው ጠየቋቸው። በጣሪያው ላይ ሰዎች እንዳልነበሩ ሲነግሯቸው ባለማመን፣ «እኛኮ በዓይናችን አይተናቸዋል» አሏቸው። ከዚያም እግዚአብሔር በዚህ በአደገኛ ሰዓት ልጆቹን ለመጠበቅ መላእክቱን እንደ ላከ ነገሯቸው።

ለአማኞች የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች እንደሚሰጧቸውም ተገንዝበናል። በአንድ ወቅት ምግብን እስከ መስጠት እንኳ ደርሰዋል። የበኣል ነቢያትን ድል ካደረገ በኋላ በኤልያስ ሕይወት የተከናወነውን እናውቃለን። ፈርቶ፣ ተዳክሞና ተስፋ ቆርጦ ሳለ «በክትክታውም ዛፍ በታች ተጋደመ፤ እንቅልፍም አንቀላፋ፤ እነሆም መልአክ ዳሰሰውና ተነሥተህ ብላ አለው» (1ኛ ነገሥት 19:5-7)። እግዚአብሔር፣ «ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?» በማለት ቃል ገብቶልናል (ዕብራውያን 1:14)። የመላእክት ዕርዳታ በሺዎች በሚቆጠሩ ዓመታት በፊት አቁመዋል ብለን ልናስብ ይገባል?

በኮሪያ ጦርነት ወቅት የአሜሪካ የጦር ቡድንን በምጐበኝበት ወቅት በአንደኛው ክፍለ ጦር ስለነበሩና በሰሜን በኩል በችግር ውስጥ ስለተጠመዱ የአሜሪካ የባሕር ኃይል አነስተኛ ቡድን ተነገረኝ። የአየር ፀባዩ ከዜሮ በታች 20 ዲግሪ በሚነብብበት ሁኔታ በብርድ ሊሞቱ ጥቂት ቀርቷቸው ነበር። ለስድስት ቀናት ደግሞ የሚበሉት አልነበራቸውም። በሕይወት ለመቆየት ለጠላት እጃቸውን መስጠት ብቻ አማራጭ መስሎ ታያቸው። ከእነርሱ ውስጥ አንዱ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቃል የተወሰኑ ምንባቦች በመጥቀስ ጓዶቹን ለእግዚአብሔር የምስጋና መዝሙርን መዘመር አስተማራቸው። ይኼንን ተከትሎ እየተሰባበረ የሚመጣ ድምፅ ሰምተው ዘወር ሲሉ የዱር ከርከሮ ወደ እነርሱ እየሸመጠጠ ሲመጣ ተመለከቱ። መንገዱን ሊለቁለት ሲዘሉ በድንገት መንገዱ

ላይ ቀጥ ብሎ ቆመ:: እንደኛው ወታደር ለመተኩስ ጠብመንጃውን ሲያነሣ፣ መግለጽ በማይቻል ሁኔታ ከርከሮው ተዘርሮ ወደቀ:: ሊገድሉት ሮጠው ሲሄዱ ሞቶ አገኙት:: በዚያን ሌሊት የሥጋ ግብዣ ሆኖ ጉልበታቸው መታደስ ጀመረ::

በሚቀጥለው ጠዋት ፀሐይ እየወጣች ሳለ ሌላ ድምፅ ሰሙ:: የጠላት ቃኝ የት መሆናቸውን ያወቀ መስሏቸው ሲፈሩ፣ አንድ የደቡብ ኮሪያ ዜግነት ያለው እንግሊዝኛ መናገር የሚችል ሰው ፊት ለፊታቸው አጋጠማቸው:: እርሱም፣ «መውጪያውን አሳያችኋለሁ» አላቸው:: በተራራዎችና በጫካው ውስጥ እየመራቸው መሥመር ላይ በሰላም አደረሳቸው:: ሊያመሰግኑት ዘወር ሲሉ መሰወሩን ተገነዘቡ::

## መላእክት በፍርድ ውስጥ

በዛሬው ኑሮአችን የመላእክትን እርዳታ እንዴት ልናገኝ እንደምንችል የምናጠናውን ጥናት በምንቀጥልበት ወቅት መላእክት ከፍርድ ጋር ስላላቸው ግንኙነት በድጋሚ መመልከት ይኖርብናል::

በኃጢአት ምክንያት እሳትና ዲን በሰዶም ላይ ከመውደቁ በፊት መልአኩ፣ «እኛ ይህን ስፍራ እናጠፋለንና. . . እናጠፋውም ዘንድ እግዚአብሔር ሰድዶናልና» አለ (ዘፍጥረት 19:13)::

በዳንኤል 7:10 ላይ የእግዚአብሔር ቃል፣ «የእሳትም ፈሳሽ ከፊቱ ይፈልቅና ይወጣ ነበር. . . ፍርድም ሆነ፣ መጻሕፍትም ተገለጡ» ይላል:: ከሃያ በማያንሱ ስፍራዎች ላይ እግዚአብሔር ፈቃዱን ለመታዘዝ ባመፁትና ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው ለመቀበል ፈቃደኛ ባልሆኑት ላይ ሁሉ ፍርዶቹን እንዲፈጽሙ መላእክቱን የሚልክ መሆኑን ይናገራል:: ኢየሱስ፣ «የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል፣ ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዓመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ፣ ወደ እቶነ እሳትም ይጥሉአቸዋል፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል» (ማቴዎስ 13:41፣ 42) ብሏል:: ጌታ ኢየሱስም፣ «ነገር ግን እላችኋለሁ፣ በፍርድ ቀን ከእናንተ ይልቅ ለጢሮስና ለሲዶና ይቀልላቸዋል» አለ (ማቴዎስ 11:22):: እንደገናም፣ «እኔ እላችኋለሁ፣ ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል» አለ (ማቴዎስ

12:36)። «ነገር ግን የማይገለጥ የተከደነ፣ የማይታወቅም የተሰወረ ምንም የለም» (ሉቃስ 12:2)።

እግዚአብሔር የሚዘግበው ቃላታችንንና ድርጊቶቻችንን ብቻ ሳይሆን የልቦቻችንን አሳቦችና ምኞቶች ጭምር ነው። አንድ ቀን እኔና አንተ መልስ የምንሰጥበት ጊዜ ይመጣል። በዚያን ጊዜ የመጨረሻ ዕድላችን የሚወሰነው ክርስቶስን በመቀበላችን ወይም ባለመቀበላችን ነው። ጳውሎስ፣ እግዚአብሔር «መከራንም ለምትቀበሉ ከእኛ ጋር ዕረፍትን ብድራት አድርጎ እንዲመልስ በእግዚአብሔር ፊት በእርግጥ ጽድቅ ነውና። እግዚአብሔርን የማያውቁትን፣ ለጌታችንም ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የማይታዘዙትን ይበቀላል» ብሎ ተናግሯል (2ኛ ተሰሎንቄ 1:7-8)።

ፍትሕ የሕይወት መጻሕፍት ሚዛናዊ እንዲሆኑ ይጠይቃል። ይሁንና፣ ካለመጨረሻ ፍርድ ይህ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም። ሕግም ለሚተላለፉ ሰዎች ቅጣትን ካላካተተ ትርጉም አይኖረውም። እንዲሁ ስናስበው እንኳ በዓለማችን ላይ እንደነበሩት እንደ ሂትለርና ኢዲ አሚንን የመሳሰሉ ሰዎች ተጠያቂ የሚሆኑበትን ጊዜ እግዚአብሔር ሊያመጣ ይገባል። ያ ካልሆነ ግን በዓለም ላይ ፍትሕ የለም ማለት ነው።

በሺዎች የሚቆጠሩ ክፉ ሰዎች ክፋት የተሞላበት ሕይወት ከመኖራቸውም በላይ ክፉ ተግባራቸውን በሌሎች ላይ ፈጽመዋል። በዚህ ሕይወት ላጠፉት ጥፋትም ቅጣት የደረሰባቸው አይመስልም። ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ ጠማማ የሆኑ ስፍራዎች እንደሚስተካከሉ ይናገራል (ኢሳይያስ 45:2)። በዚያ ታላቅ የእግዚአብሔር የፍርድ ቀን ሰዎች ምሕረት ቢለምኑም አያገኙም። በዚያን ዕለት እግዚአብሔርን ቢፈልጉ ሊያገኙት አይችሉም። በጣም የዘገየ ይሆናል። መላእክት እንዲያወጧቸው ያለምንም ጥቅም ሊጮኹ ይችላሉ።

## መላእክት በኃጢአተኞች መዳን ሐሴት ያደርጋሉ

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛቸውና ጌታቸው አድርገው ለመቀበል ፈቃደኛ ባልሆኑት ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ ለመፈጸም መላእክት ጠቃሚ ሚና የሚጫወቱ ሲሆን፣ በተመሳሳይ

ሁኔታም ኃጢአተኞች ደኅንነትን በሚያገኙበት ወቅት ሐሴትን እንደሚያደርጉ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል:: ኢየሱስ ብዙ ልብ የሚነኩ ታሪኮችን በሉቃስ 15 ውስጥ ይናገራል:: በመጀመሪያ፣ አንድ ሰው መቶ በጎች ነበሩት:: አንዱ ሲጠፋበት ዘጠና ዘጠኙን በበረሃ ትቶ ሊፈልገው ሄደ:: በጉን ባገኘው ጊዜ በጫንቃው ላይ ተሸክሞ ወደ ቦታው መለሰው:: በቤቱ ወዳጆቹን ሁሉ ሰበሰበና፣ «የጠፋውን በጌን አግኝቼዋለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ» አለ (ቁጥር 6):: ኢየሱስም፣ «እላችኋለሁ፣ እንዲሁ ንስሐ ከሚያስፈላጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል» አለ (ቁጥር 7)::

ሁለተኛው ታሪክ ውድ የሆነ የብር ሣንቲም ስለ ጣለች ሴት ነው:: ቤቷን በጥንቃቄ ጠርጋ ሁሉንም ስፍራ ተመለከተች:: በመጨረሻም ሳንቲሟን ስታገኘው ወዳጆቿንና ጐረቤቶቿን ጠርታ፣ «የጠፋውን ድሪሜን አግኝቼዋለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ» አለቻቸው (ቁጥር 9):: «እላችኋለሁ፣ እንዲሁ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል» (ሉቃስ 15:10)::

በእነዚህ ሁለት ምሳሌዎች ኢየሱስ እየነገረን ያለው በእያንዳንዱ ሰው ላይ የሰማይ መላእክት ዓይኖች እንደሚያዩ አይደለም? በምድር ገጽ ላይ ያለውን የእያንዳንዱን ሰው መንፈሳዊ ሁኔታ ያውቁታል:: እግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን መላእክትም ይወዷችኋል:: ጊዜው ከማለፉ በፊት መዳናችሁን ለማግኘት በንስሐ ወደ ክርስቶስ እንድትመለሱ ለእናንተ ይጓጓሉ:: ፊት ለፊት የተጋረጠውን የገሃነም አስቃቂ አደጋ ያውቁታል:: ፊታችሁን ወደ ሰማይ እንድትመልሱ ይፈልጋሉ:: ሆኖም ውሳኔውን ማድረግ የምንችለው እኔና አንተ ብቻ መሆናችንንም ያውቃሉ::

አንድ ቀን አንድ ሀብታም የሆነ ወጣት ገዢ እየሮጠ መጥቶ በክርስቶስ ፊት ተንበረከከና፣ «ቸር መምህር ሆይ፣ የዘላለም ሕይወትን እወርስ ዘንድ ምን ላድርግ?» ብሎ ጠየቀው (ማርቆስ 10:17):: ጴጥሮስ ታላቅ ስብከቱን በጰንጠቆስጤ በሰበከ ጊዜ ሉቃስ እንደሚለው ሰዎች «ልባቸው ተነካ ጴጥሮስንና . . . ምን እናድርግ? አሉአቸው» (የሐዋ. ሥራ 2:37):: የተከበረው አፍሪካዊው ሰው በሰረገላው እየጋለበ በረሃውን ሲያቋርጥ

ወንጌላዊው ፊልጶስ አነጋግሮታል። በድንገት የተከበረው ሰው ሰረገላውን አቁሞ፣ «እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድር ነው? አለው» (የሐዋ. ሥራ 8:36)። በመንፈቀ ሌሊትም የፊልጵስዩስ ሰው የሆነው የወኅኒ ጠባቂ፣ «ጌቶች ሆይ፣ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?» ብሎ ጳውሎስንና ሲላስን ጠየቃቸው (የሐዋ. ሥራ 16:30)። ዘመናዊው ሰው ይህንን ጥያቄ ዝንተ ዓለም ይጠይቃል። ያረጀ ቢሆንም፣ ሁልጊዜ አዲስ ነው። በድሮው ጊዜ የነበረው አስፈላጊነት ዛሬም ያው ነው።

መላእክት እንዲደሰቱ ለማድረግ ምን ማድረግ ያስፈልግሃል? ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ እንዴት ይቻልሃል? ኃጢአትህን እንዴት መናዘዝ ትችላለህ? ኢየሱስ ነገሮችን ሁሉ እጅግ ቀላል ያደረገው ቢሆንም፣ እኛ ግን አወሳስበነዋል። በማይረሱ ታሪኮች መላእክቶቹን እየገለጸ አጭር በሆነ ዓረፍተ ነገሮች ለሰዎች ተናግሯል። የእግዚአብሔርን መልእክት እጅግ ቀላል በሆነ መንገድ ስላቀረበው ብዙዎች በሰሙት ነገር ተገርመው ነበር። መልእክቱ እጅግ ቀላል ከመሆኑ የተነሣ ጆሮአቸውን ለማመን ተቸገሩ።

በሐዋርያት ሥራ ላይ ፊልጵስዩሳዊው የወኅኒ ጠባቂ ሐዋርያው ጳውሎስን፣ «እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?» ብሎ ሲጠይቅ ጳውሎስ የሰጠው መልስ ቀላል ነበረ፣ «በጌታ በኢየሱስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ» አለው (የሐዋ. ሥራ 16:30፣ 31)። ይኼ ቀላል ከመሆኑ የተነሣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ይሰናከሉበታል። ለመለወጥ የምንችልበት አንዱና ብቸኛው መንገድ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነን እንደ ጌታችንና አዳኛችን ስንቀበለው ብቻ ነው። በመጀመሪያ ኑሮህን ልታስተካክል አይገባም። ከእግዚአብሔር የሚለይህን ሱስ ለመተው መሞከርም የለብህም። ያንን ሁሉ ብዙ ጊዜ ሞክረህ አልተሳካልህም። «ባለህበት ሁኔታ» ና። ዕውሩ ሰው በነበረበት ሁኔታ ነበር የመጣው። ለምጻሙ ሰው በነበረበት ሁኔታ ነበር የመጣው። በመስቀል ላይ የነበረው ሌባ በነበረበት ሁኔታ ነበር የመጣው። በየትኛውም ስፍራ ብትሆን ባለህበት ሁኔታ ወደ ክርስቶስ አሁን ብትመጣ የሰማይ መላእክት ሁሉ ሐሴትን ያደርጋሉ።

በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ከተዘገቡት ታላቅና በጣም ውድ ከሆኑ ቃላት መካከል የተወሰኑትን የተናገረው ሰይጣን ነው።

(እርሱ ግን ለመልካም አስቦ አልነበረም የተናገረው):: ኢዮብን በተመለከተ ከእግዚአብሔር ጋር በሚወያዩበት ወቅት፣ «እርሱንና ቤቱን በዙሪያውም ያሉትን ሁሉ አላጠርህለትምን? የእጁን ሥራ ባርከህለታል፣ ከብቱም በምድር ላይ በዝቷል» (ኢዮብ 1:10):: ሕይወቴን ወደ ኋላ ዘወር ብዬ ስመለከት ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኜና ጌታዬ አድርጌ የተቀበልኩባትን ደቂቃ አስታውሳለሁ:: መላእክት ሐሴትን አድርገዋል! ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከሰይጣንና ከሠራዊቱ ጋር በሺዎች የሚቆጠሩ ጦርነቶችን አካሂጃለሁ:: ፈቃዴን ሳስገዛና ራሴን ፈጽሞ ለክርስቶስ አሳልፌ ስሰጥ፣ ስጸልይና ሳምን እግዚአብሔር «በዙሪያዬ አጥር እንደሚያደርግ» ይኼውም ይጠብቀኝ ዘንድ የመላእክትን አጥር እንደሚያደርግልኝ አውቃለሁ::

የእግዚብሔር ቃል ለመወለድ ጊዜ አለው፣ ለመሞትም ጊዜ አለው ይላል:: የእኔ የመሞቴ ጊዜ በሚመጣበት ወቅት ያጽናናኝ ዘንድ መልአክ ይመጣል:: በዚያ ወሳኝ ሰዓት ደስታና ሰላምን እየሰጠ ወደ እግዚአብሔር ይወስደኛል:: ከዚያም ከጌታ ጋር ለዘለዓለም እኖራለሁ:: ስለ መላእክቱ አገልግሎት እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን!